በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴልን በክፍል ውስጥ ተጠቅሞ ማስተማር ያለው አስተዋጽኦ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለድህረ ምረቃ ት/ቤት
የቀረበ ጥናት (ቴሲስ)

በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተማር ዘዴ ለማስተርስ
ኦፍ አርትስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

የኔሰው ደሴ

ግንቦት 1990 ዓ.ም
አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

በአሮምኛ ቋንቋ አፉቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር ተራክቧዊ የንባንብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴልን በክፍል ውስጥ ተጠቅሞ ማስተማር ያለው አስተዋጽኦ

በ

የኔሰው ደሴ

ቋንቋዎች ጥናት ተቋም

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

ታዲሳ ሃቢሰው (ዶ/ር) — አማካሪ

ገብረወልደሃና አሰጋኝ (ዶ/ር) — ፈታኝ

ሽሬ ኃ/ኢየሱስ (ዶ/ር) — ፈታኝ

የአርዕስት ማውጫ

ገጽ

አርዕስት

ምስጋና i

አጠቃሎ ii

ምዕራፍ አንድ መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት 2

1.3 የጥናቱ ዓላማ 3

1.4 መላምት 4

1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት 4

1.6 የጥናቱ ወሰን 5

1.7 የቃላትና የሃረጎች ግላጼ 7

ምዕራፍ ሁለት የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

2.1 አንብቦ መረዳት ምንድን ነው? 10

2.1.1 ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ ኢአፈ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች አንድን ጽሑፍ አንብቦ ለመረዳት ለምን ይከብዳቸዋል? 11

2.1.2 ቋንቋው ኢአፍመፍቻ የሆናቸው ተማሪዎች አንድ ጽሑፍ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር ይችሉ ዘንድ ምን ዓይነት የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል ተጠቅመን ማስተማር አለብን? 14

2.2 ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞጁል 17

2.2.1 የተለያዩ ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴሎች 18

2.2.2 የተራክቧዊ መካከስ ሞዴል ምንነትና አተገባበር 20

2.2.3 ከተራክቧዊ መካክስ ሞዴል መሠረት አንብቦ
የመረዳትን ክሂል ለማዳበር የክፍል ውስጥ የመማር
ማስተማር ክንውን 23

2.2.3.1 የቡድን ሥራ 26

2.2.3.2 በተራክቧዊ አቀራረብ በክፍል ውስጥ
የመምህሩ ሚና 28

2.2.3.3 በተራክቧዊ አቀራረብ በክፍል ውስጥ
የተማሪው ሚና 29

2.2.4 በተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል
ተጠቅሞ ማስተማር ያሉት አሉታዊ ጎኖች 29

ምዕራፍ ሦስት የአጠናኑ ዘዴ

3.1 የትምህርት ቤትና የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ 32

3.1.1 የትምህርት ቤት አመራረጥ..... 32

3.1.2 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ 32

3.2 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ 33

3.2.1 የማስተማሪያ መሣሪያዎች ዝግጅት 33

3.2.1.1 ለጥብቅ ቡድኑ /Control Group/ከጥንታዊ
የንባብ ክሂል የማስተማሪያ ሞዴል አንፃር
የማስተማሪያ መሣሪያዎች አዘገጃጀት ዘዴ..... 33

3.2.1.2 ለተጠኚ ቡድኑ /Experimental Group/
ከተራክቢዊ መካክስ የንባብ ክሂል
ማስተማሪያ ሞዴል አንፃር የማስተማሪያ
መሣሪያዎች አዘገጃጀት ዘዴ..... 35

3.2.2 የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ክንውን
/Methodology/አቀራረብን በተመለከተ..... 37

3.2.2.1 ለጥብቅ ቡድኑ በውጤት ተኮር ስልት የክፍል
ውስጥ የመማር ማስተማር ክንውን አቀራረብ..... 37

3.2.2.2 ለተጠኚ ቡድኑ በክፍል ውስጥ አንብቦ
የመረዳትን ክሂል ማዳበር ከተራክቢዊ
መካክስ ሞዴል አንጻር በክፍል ውስጥ
የመማር ማስተማር ክንውን አቀራረብ ዘዴ..... 39

3.2.3 የፈተናዎች አዘገጃጀት፣ አስተራራምና የውጤት
አሰጣጥ ዘዴ 42

3.2.3.1 የፈተናዎቹ አሰጣጥ 43

3.2.3.2 የፈተናዎቹ አስተራረምና ውጤት አሰጣጥ ዘዴ 44

3.2.4 የመረጃዎቹ ውጤት አተናተን ዘዴ 44

3.2.5 በአጥኚው የተዘጋጁት የማስተማሪ መሣሪያዎች
/ምንባቦች መልመጃዎች/ እና ፈተናዎች/ቅድመ-
ትምህርትና ድህረ-ትምህርት ፈተናዎች ተገቢነት
/Validity/ እና አስተማማኝ /Reliability..... 44

3.2.5.1 የቅድመ-ትምህርት ፈተና አስተማማኚነት
Reliability..... 46

ምዕራፍ አራት የመረጃው ውጤት ትንትና

4.1 የቅድመ-ፈተና ውጤትና ትንተና 49

4.2 ከቅድመ-ትምህርት ፈተና በኋላ የጥብቅ ቡድኑና የተጠኚ ቡድኑ የክፍል ውስጥ የንባብ ክሂል ትምህርት ልምምድ 52

4.2.1 የጥብቅ ቡድኑ የክፍል ውስጥ ልምምድ 52

4.2.2 የተጠኚ ቡድኑ /Experimental Group/ የክፍል ውስጥ ልምምድ 54

4.2.2.1 በሂደት አንድ /Phase 1/ የመቀስቀስ ደረጃ የተከናወነ የክፍለ ውስጥ ልምምድ 55

4.2.2.2 ሂደት ሁለት /Phase 2/ ምንባቡን በፍጥነት በማንበብ አጠቃላይ ግንዛቤን ማዳበር /Stage of Fluency/ደረጃ የተደረገ ልምምድ 56

4.2.2.3 ሂደት ሶስት /Phase 3/ /Accuracy Stage/ ለትክክለኛ ግንዛቤ ሲባል የተደረገ ልምምድ 57

4.2.2.4 ሂደት አራት /Phase 4: Critical Evaluation Stage የተጻፈውን ጽሁፍ ከራሱ እውቀት በመነሳት በሚገመግምበት ደረጃ የተደረገ ልምምድ 58

4.3 የድህረ-ፈተና ውጤት ትንተና 61

4.4 ፍትነታዊ /Experimental/ ምርምሩ ለመፈተሽ ይዟቸው የተነሳው መላምቶች 64

4.5 የመረጃው ውጤት ማብራሪ /Discussion/..... 65

ምዕራፍ አምስት ማጠቃለያና የመፍትሔ ሐሣቦች

5.1 ማጠቃለያ 68

5.1.1 በቅድመ-ፈተናው የተገኘ ውጤት 69

5.1.2 በድህረ ፈተና የተገኘ ውጤት ማጠቃለያ 70

5.1.3 ፍትነታዊ ምርምሩን ለመፈተሽ በቀረቡ መላምቶች
የቀረበ ማጠቃለያ 70

5.2 መደምደሚያ 72

5.3 የመፍትሔ ሃሣቦች 73

ዋቢ መጻሕፍት 76

ሙዳዬ ቃላት 81

አባሪዎች 82

የአባሪዎች ማውጫ

ር ዕ ስ ገጽ

ሀ የማስተማሪያ
መሣሪያያዎች..... 82

ሀ.1 ለተጠኚ ቡድኑ የተዘጋጁ የማስተማሪያ መማሪያዎች...

ሀ.2 ለጥብቅ ቡድኑ የተዘጋጁ የማስተማሪያ መሣሪያዎች ...

ለ. ፈተናዎች..... 133

ለ.1 ቅድመ-ፈተና.....

ለ.2 ድህረ-ፈተና .....

ሐ.3 ለፖይለት ፕሮጀክት የተካሄደባቸው.....

ሐ. በፖይለት ፕሮጀክት የተገኙ ውጤቶችን የሚያሣይ ስታቲስቲካዊ
መረጃዎች 144

ሐ.1 የግንዛቤ ፈተና ውጤት 144

ሐ.2 የቅድመ-ፈተና አስተማማኝነት ውጤት..... 145

ሐ.3 የድህረ-ፈተና አስተማማኝነት ውጤት..... 146

መ. የፈተናዎች ስታትስቲካዊ መረጃዎች 147

መ.1 የቅድመ-ፈተና ስታቲስቲካዊ ስሌት 147

መ.1 የድህረ-ፈተና ስታቲስቲካዊ ስሌት 148

ሠ. በፍትነታዊ ምርምሩ ሂደት ወቅት ተጠኚ ቡድኑና ጥብቅ ቡድን
በክፍል ውስጥ በመማር ማስተማር ሂደት ወቅት የተከናወነውን
ሁኔታ የሚያሳይ ፎቶግራፍ 149

ሠ.1 የየተጠኚ ቡድኑን የክፍል ውስጥ ልምምድ
የሚያሳይ ፎቶግራፍ 149

ሠ.2 የጥብቅ ቡድኑን የክፍል ውስጥ ልምምድ
የሚያሳይ ፎቶግራፍ 151

ሰ. የግንዛቤ ፈተናዎች 152

የሠንጠረዥ ማውጫ

	ርዕስ	ገጽ
ሠንጠረዥ I	በፓይለት ፕሮጀክት የተገኘውን የግንዛቤ ውጤት የሚያሳይ	45
ሠንጠረዥ II	ለጥብቅ ቡድኑና ለተጠኚ ቡድኑ የቅድመ-ፈተናውን ውጤት የሚያሳይ	49
ሠንጠረዥ III	የጥብቅ ቡድኑንና የተጠኚ ቡድኑን ውጤት ሥርጭት የሚያሳይ ሠንጠረዥ.....	50
ሠንጠረዥ IV	የጥብቅ ቡድኑንና የተጠኚ ቡድኑን ውጤት የሁለቱን ቡድኖች አማካይና የልይይት ዳግም ብዜት ውጤት ግምት ውስጥ በማስገባት በ't' ቴስት ተሰልቶ የተገኘውን ውጤት ቴስት ስታትስቲካዊ ሥሌት የሚያሳይ	51
ሠንጠረዥ V	የጥብቅ ቡድኑንና የተጠኚ ቡድኑን የድህረ-ፈተና ውጤት የሚያሳይ	61
ሠንጠረዥ VI	የጥብቅ ቡድኑንና የተጠኚ ቡድኑን የድህረ-ፈተና ውጤት ስርጭት የሚያሳይ.....	62
ሠንጠረዥ VII	የጥብቅ ቡድኑንና የተጠኚ ቡድኑን ውጤት የሁለቱን አማካይ ውጤትና የልይይት ዳግም ብዜት ግምት ውስጥ በማስገት በ't' ቴስት ቀመር የተሰላውን ስታቲስቲካዊ ስሌት የሚያሳይ	63

ምስጋና

ይህ ጥናት ተጀምሮ እስኪጨረስ ድረስ የሥራ ጊዜያቸውንና የእረፍት ጊዜያቸውን መስዋዕት በማድረግ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ጽሑፉን በጥንቃቄ በማንበብ የማሻሻያ ሃሣብ በመስጠትና በማረም የቅርብ ክትትላቸው ላልተለየኝ አማካሪዬ ለዶ/ር ታደለ አዳሙ ምስጋናዬን ሳቀርብ ላቅ ባለ አክብሮት ነው::

ከቅርብ አማካሪዬ ባላነሰ ሁኔታ ባላቸው የሥራ ፍቅር ሙያዊ እገዛ ላደረጉልኝ ለአቶ አበበ ገብረጻዲቅ፣ የማስተማሪያ መሣሪያዎችን በማዘጋጅበት ጊዜ የቅርብ ክትትል በማድረግ በማረምና በማስተካከል ደከመኝ ሰለቸኝ ለማይሉት ለዶ/ር አረጋ ኃ/ሚካኤል፣ ለዶ/ር ደጀኔ ለታና ለአቶ ይልማ ከበደ ልባዊ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ::

በጥናቱ ሂደት ወቅት ለልምምዱ ተግባራዊነት፣ ተማሪዎችን በመምረጥ፣ ክፍል በመፍቀድ፣ የመማሪያ ክፍለ ጊዜ በመመደብና ተማሪዎች በጥናቱ ተሣታፊ እንዲሆኑ በማበረታታት እስከመጨረሻው ትብብራቸው ላልተለየኝ ለአዳባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምክትል ርዕሰ መምህር ደበላ ዲምባባ ለዩኒት መሪ ለመምህር ምኒልክ ውቤ ለአማርኛ ቋንቋ መምህር ቢክስ ኃይሌ እንዲሁም በጥናቱ ተሣታፊ ለሆኑት ለአዳባ ሁለተኛ ደረጃ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በሙሉ ምሥጋናዬ ይደርሳቸው ዘንድ ምኞቴ ነው::

በጥናቱ ወቅት ምክራቸውን በመለገስ ለተባባሩኝ ለአቶ አበዋ ጥላሁን፣ ለአቶ ብርሃኑ አይቸው ስታትስቲካዊ ስሌቶች በመሥራት ለተባበረኝ ለጓደኛዬ ለአቶ ደመቀ ፀሐይ እንዲሁም ጽሑፉን በኮምፒዩተር በመቅረጽ ለተባበሩኝ ለወ/ሮ ውቢቱ አራጋው ምስጋናዬ የላቀ ነው::

በመጨረሻም በትምህርት ቤት ቆይታዬ የሞራል ማበረታቻና የቁሳቁስ ድጋፍ በማድረግ ለተባበሩኝ ቤተሰቦቼ ምስጋናዬን አቀርባለሁ::

አጠቃሎ

Abstract

ንባብን ለብዙ ተግባራት እናውለዋለን፡፡ ንባብን እውቀትን ለማግኘት፣ አዲስ የተከናወኑ ክስተቶችን ለማወቅም ሆነ ጊዜን ለማሳለፍ እንገለገልበታለን፡፡ ንባብ ካለው ጠቀሜታ አንጻር ክሂሉን በመደበኛ ሁኔታ በትምህርት ቤት ማዳበር ያስፈልጋል፡፡ የዚህ ጥናት ዋና ዓላማም በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎችን በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር ከንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴሎች ውስጥ ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል አስተዋጽኦ ይኖረዋልን? የሚለውን ጥያቄ በፍትነታዊ የምርምር ዘዴ ለመፈተሽ ሲባል አልሞ የተነሳ ነው፡፡

ጥናቱ የተከናወነው በባሌ ዞን በአዳባ ሁለተኛ ደረጃ በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው፡፡ ጥናቱ ከመከናወኑ በፊት በብድግ ብድግ የናሙና አመራረጥ ስልት ሃምሳ ተማሪዎች ተመርጠው በሁለት ቡድኖች ተከፍለዋል፡፡ የመጀመሪያው ጥብቅ ቡድን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ተጠኚ ቡድን ነው፡፡ የሁለቱን ቡድኖች መረጣ ከተከናወነ በኋላ በሁለቱ ቡድኖች መካከል የችሎታ ተመጣጣኝነት መኖሩን ለመለካት ሲባል የቅድመ ፈተና ተሰጥቷቸዋል፡፡ በቅድመ-ፈተናው የተገኘው ውጤት እንደሚያስረዳው የጥብቅ ቡድኑ አማካይ (mean) ውጤት 56.64 ሲሆን የልይይት ዳግም ብዛት ደግሞ 13.564 ነው፡፡ የተጠኚ ቡድኑ አማካይ ውጤት 56.60 ሲሆን የልይይት ዳግም ብዜት ደግሞ 9.916 ነው፡፡ የሁለቱን ቡድኖች አማካይ ውጤትና የልይይት ዳግም ብዜት ግምት ውስጥ በማስገባት በ « t » ቴስት ሲለካ የተገኘው የ« t » calculated 0.01 ነው፡፡ ይህ ውጤት « t » critical 0.05 እና N2+N2-2 degree of Freedom ሲፈለግ የሚገኘው(t-tabulated) ውጤት 2.021 ነው፡፡ ይህ ውጤት ከ t-calculated ጋር ሲነፃፀር በልጦ በመታየቱ በሁለቱ ቡድኖች መካከል የባህሪ ተመጣጣኝነት እንዳለ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ከቅድመ-ፈተና በኋላ ለጥብቅ ቡድኑ በጥንታዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል መሠረት በተዘጋጀ የማስተማሪ መሣሪያና የክፍል ውስጥ ክንውን በተደገፈ ሁኔታ ለተጠኚ ቡድኑ ደግሞ «በተራክቧዊ» የንባብ ክሂል ማስተማሪ ሞዴል እና መሠረት በተዘጋጀ የማስተማሪያ መሣሪያና የክፍል ውስጥ ክንውን በተደገፈ ሁኔታ ለሁለቱ ቡድኖች በተከታታይ ለአምስት ሣምንታት በቀን አንድ ሰዓት ከተማሩ በኋላ የሁለቱም ቡድኖች አንድ ዓይነት የድህረ-ትምህርት ፈተና ተሰጥቷቸዋል፡፡

የድህረ-ፈተናው ውጤት እንደሚያሳየን የጥብቅ ቡድኑ አማካይ ውጤት 53.7826 ቢሆን የልይይት ዳግም ብዜት ደግሞ 11.761 ነው:: የተጠኚ ቡድኑ አማካይ ውጤት 66.7826 ሲሆን የልይይት ዳግም ብዜት ደግሞ 11.029 ነው:: የሁለቱን ቡድኖች የአማካይ ውጤትና የልይይት ዳግም ብዜት ግምት ውስጥ በማስገባት በ « t »ቴስት ሲለካ የሚገኘው የ« t » calculated value 4.09 ነው:: ይህን ውጤት በ0.05 critical value በ N-1 degree of freedom -t-tabulated ሲፈለግ የሚገኘው የt-calculated ውጤት 2.391 ነው:: ይህ ውጤት የ« t » calculated 4.09 ከ t-tabulated 2.391 መብለጡን ሳያል:: ይህም ውጤት በሁለቱ ቡድኖች መካከል ተጠኚ ቡድኑ በተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪ ሞዴል በማማሩ የተሻለ ውጤት እንዳሳየ ያስረዳል::

በመጨረሻም በጥናቱ ሂደት የተሰበሰቡ መረጃዎች ከተተነተኑ በኋላ ያሳዩትን ፍንጭ መሠረት በማድረግ ለወደፊት «ተራክቧዊ» የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል ተጠቅሞ ማስተማር በተለይም አማርኛ ቋንቋ ኢአፍ መፍቻ ቋንቋ ለሆናቸው ተማሪዎች ሊያስገኝ የሚችለውን ጠቀሜታ በማፍትሔ ሃሳቦች ላይ ተጠቁሟል::

ምዕራፍ አንድ

1. መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ የምንመለከተው ስለ ጥናቱ ርዕሰ ነገር ነው። በዚሁ በምዕራፍ መጀመሪያ በዳራው ላይ ስለ ጥናቱ ርዕሰ ነገር አጠቃላይ ንድፈ ሃሳቦችን በማንሳት ከነዚህ ንድፈ-ሃሳቦች አንጻር በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ በመረዳት ክሂል ላይ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ምን ይላሉ? አጥኚው ከነዚህ ምሁራን በመነሳት በርዕሰ-ጉዳዩ ላይ ለማጥናት ያነሳሱት ምክንያቶች ምንድን ናቸው? የጥናቱ ዓላማስ ምንድን ነው? ጥናቱ ተከናውኖ ካለቀ በኋላ ያስገኛል ተብሎ የሚጠበቁት መላምቶች ምንድን ናቸው? ጥናቱ ከየት ተነስቶ የት ድረስ ያለውን አካሎ ያጠናል? በመጨረሻም አጥኚው ለጥናቱ የተጠቀመባቸው የሥራ-ቃላት /working definitions/ ከተገለጹ በኋላ ምዕራፉ ይቋጫል።

1.1 የጥናቱ ዳራ /Background of the Study/

የሰው ልጅ በቋንቋ መግባባት እንደጀመረ ሃሳቡን ለመሰሉ ሰው የሚያስተላልፈው በንግግር ብቻ ነበር፤ ነገር ግን ቀስ በቀስ ተፈጥሮን እየተቆጣጠረና በስልጣኔውም እየገፋ ሲሄድ ሐሰቡን ከንግግር አልፎ በጽሑፍ ማስተላለፍ ጀመረ። በወቅቱ ያከናወናቸውን አዳዲስ ክንዋኔዎች እንዴት እንዳከናወናቸው፤ ለተተኪው ትውልድ ለማስተላለፍና ለማቆየት ከንግግር ይልቅ ጽህፈት እንደዋነኛ መሣሪያ በመሆን ማገልገል ጀመረ። ከተጻፈው ጽሑፍ እውቀትን፤ ሐሳብንና ደስታን ለማግኘት ደግሞ ብቃት ያለው የንባብ ችሎታን ይጠይቃል።

ንባብን ለተለያዩ ተግባራት እንገለገልበታለን። ለምሳሌ በተለያዩ ሣይንቲስቶች የተከናወኑ ጥናቶችን በማንበብ እውቀታችንን እናሰፋበታለን፤ የተለያዩ ድንቅ የፈጠራ ሥራዎችን በማንበብ ደግሞ ደስታችንንም ሆነ ሃዘናችን እየተወጣን ጊዜያችን እናሳልፍበታለን፤ ከዚህም ባሻገር በጋዜጦችና በመጽሔቶች አማካኝነት በዓለም ውስጥ የተከናወኑትን አዳዲስ ክስተቶች እንረዳበታለን። በአጠቃላይ ንባብ ሊሰጠው የሚችለውን ጠቀሜታ በማስመልከት Nuttall /1996፤3/ ሲያጠቃልሉት እንዲህ በማለት ነው። «ታነባለህ ምክንያቱም ከምታነበው ነገር አንድ ነገር ለመውሰድ ትፈልጋለህ፤ ከምታነበው ነገር እውቀትን፤ ሐሳብንና መዝናናትን ትሻለህ፤ የሆነው ሆኖ የምታነበው ከጽሑፉ ውስጥ አንድ የምትፈልገውን ነገር ለመውሰድ ነው።» ይህንን አገላለጽ Brown /1994፤ 285/, Wallace Greelet /1981፤ 5/ እና ሌሎችም ይስማሙበታል።

ንባብ ከሚሰጠው ጠቀሜታ አንጻር ከቋንቋ ክሂሎች ውስጥ እንደ አንድ ዘርፍ ሆኖ በትምህርት ቤት መርሃ-ትምህርት ተነድፎለት መሰጠት ያለበት መሆኑ አያጠራጥርም፤ እንዲያውም ለትምህርት የቀረበው ቋንቋ የሌሎች ትምህርቶች ማስተማሪያ ቋንቋ ከሆነ ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ሁሉ ለንባብ ትምህርት የተለየ ትኩረት መሰጠት እንደሚገባን Carrell, Devine and Eskey /1988፤ 1/ ጠቁመዋል::

የንባብ ክሂል ትምህርት አስፈላጊ መሆኑ ከታመነበት ቀጥለን የምናነሳው ንባብን ለተለያየ ተግባር እንደምንፈልገው ሁሉ የተለያዩ ጽሑፎችን አንብቦ ለመረዳት ክሂሉን ከወዲህ በትምህርት ቤት ለማሳደግ ምን ዓይነት የአነባበብ ስልቶችን ማዳበር አለብን? ወደሚለው ጥያቄ ያመራል::

የንባብን ክሂል በክፍል ውስጥ ማስተማር በተማሪው የፍላጎት መለያየት፤ የችሎታ መለያየት፤ በአካባቢ መለያየት፤ የማስተማሪያ ዘዴዎች መለያየት ወ.ዘ.ተ. ምክንያት ከጊዜ ወደጊዜ አስቸጋሪ እየሆነ መምጣቱን Brown /1994/, Williams /1984/, Nuttall /1996/ እና ሌሎችም ጠቁመዋል::

በአማርኛ ቋንቋም አንብቦ በመረዳት በኩል መሠረታዊ ችግር እንዳለ ተስፋዬ /1986/፤ ማስተዋል /1989/ና ጌታቸው /1986/ በጥናቶቻቸው ላይ ጠቁመዋል:: ለምሳሌ ተስፋዬ /1986/ በአብዛኛው በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ በመረዳት በኩል ያለው ትልቁ ችግር ተማሪው ያነበበውን ነገር ተረድቶ እውነታውን እንደሚፈልገው ዓይነት ተስማሚ መሆኑን አመዛዝኖ መቀበሉ ወይም አለመቀበሉ ቀርቶ ገና ለግንዛቤ የሚያበቃውን ክሂሎት ያላዳበረ እንደሆነ በጽሁፋቸው ላይ ጠቁመዋል:: ማስተዋል /1989/ በተመሳሳይ ሁኔታ በአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለመለካት ባደረገው ጥናት በቋንቋው አፈ-ፈት የሆኑትም ሆነ ያልሆኑት አንብቦ የመረዳት ችግር አለባቸው:: ለዚህም መፍትሔ ይሆን ዘንድ የማስተማሪያ ዘዴው መቀየር አለበት በማለት በጥናታቸው ገጽ /46/ ላይ ጠቁመዋል::

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች /Justifications for the Study/

አማርኛ ቋንቋ በቋንቋነቱ ተማሪው የቀረበለትን ጽሑፍ በአግባቡ እንደሚፈልገው ጉዳይ የራሱን የአነባበብ ስልት ተጠቅሞ ክሂሉን ያዳብር ዘንድ ቋንቋው ኤፍ መፍቻ ለሆናቸውም ሆነ ላልሆናቸው ተማሪዎች ትምህርቱ ይሰጣል፤ ነገር ግን ችግሩ እስካሁን ድረስ እንዳልተቃለለ ቀደም ሲል በምሳሌነት የተጠቀሱት ጥናታዊ ጽሑፎች ይጠቁማሉ::

ከዚህም በተጨማሪ ከአገር ውጭ የተከናወኑ ጥናቶች በተለይም ለትምህርት የቀረበው ቋንቋ ለተማሪው ኢአፍመፍቻ ቋንቋ ከሆነ ባለበት ሥነ-ልሳናዊ ችግርና የቋንቋውን ተናጋሪ ሕብረ-ተሰብ ባህልና ወግ አሚልቶ ባለማወቅ ምክንያት አንድን ጽሑፍ አንብቦ ለመረዳት አስቸጋሪ ሊሆንበት እንደሚችል Carrell, Devine and Eskey /1988፣ 59/ Williams /1984/, Wallace /1992 / እና ሌሎችም ጠቁመዋል:: ከነዚህ ጥናቶች በመነሳት በተለይም አማርኛ ቋንቋ ኢአፍመፍቻ ቋንቋ ከሆናቸው ውስጥ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳትን ክሂል ለማዳበር ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል አስተዋጽኦ ይኖረዋልን? የሚለውን በጥናት ለመፈተሽ ነው:: አጥኚው ተራክቧዊ ሞዴልን የመረጠበት ምክንያት ቀደም ሲል ከነበሩት ፍጹም ጽሑፍ /ውጤት ተኮር/ /Bottom-up/ ከሆነውና ፍጹም ሂደት ተኮር /Top-down/ ከሆኑት የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴሎች አንብቦ የመረዳትን ክሂል ለማዳበር ውጤት ተኮርን /Bottom-up/ እና ጽሑፍ ተኮርን /Top-down/ በማገናኘት በRumelhart /1977/ የተፈለሰፈው ሞዴል የተሻለ መሆኑን ከአገር ውጪ የተከናወኑ ጥናቶች ስለጠቆሙ ነው:: ለምሳሌ Stanovich /1980/, Eskey /1980/ Carrell /1983. a,b/ Weber /1984/, Stoller /1984/, Williams /1996/ Singer, Ruddell and Perfetti /1985/ Uijin /1980/ Waltz & Pollack /1985/ እና ሌሎችም ተራክቧዊ ሞዴል ከሌሎች የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል የተሻለ መሆኑን በየጥናቶቻቸው ጠቁመዋል::

ከነዚህ ጥናቶች በተጨማሪም አጥኚው በባሌ ዞን አዳባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎችን ለሁለት ተከታታይ ዓመታት አማርኛ ቋንቋ ሲያስተምር ተማሪው በንባብ ትምህርት ጊዜ እንኳን የተጻፈውን ለመረዳት ይቅርና ፊደላትን አገጣጥሞ ቃል መሥርቶ ማንበብ የሚቸግረው ተማሪ በማግኘቱ ምንአልባት ይህን ችግር ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ ሊፈታው ይችላል ከሚል በመነሳት ሞዴሉን ለመፈተሽ ሲል ጥናቱን አከናውኗል::

1.3 የጥናቱ ዓላማ /Objectives of the Study/

በጥናቱ ዳራ እንደተጠቆመው ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የተጻፉትን ጽሑፎች አንብቦ የመረዳት ችግር እንዳለባቸው ይታመናል:: በተለይም አማርኛ ቋንቋ ኢአፍ-መፍቻ ቋንቋ የሆናቸው ተማሪዎች ካለባቸው የሥነ-ልሳን ችግርና የቋንውን ቱናጋሪ ሕብረተሰብ ባህል ወግና ልማድ በትክክል ባለማወቃቸው ምክንያት ችግሩ የጎላ ነው:: ስለዚህ ጉዳይ Grabe /in Carrell, Devine and Eskey 1988፣ 57/ ላይ መመልከት ይቻላል:: የዚህ ጥናት ዓላማም አማርኛ ቋንቋ ኢአፍ-መፍቻ ቋንቋ ለሆናቸው ተማሪዎች በተለይም በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎችን በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር

የሚያስችላቸውን የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል መፈለግ ነው:: ከዚህ አጠቃላይ ዓላማ በመነሳት ጥናቱ:-

- በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር «በተራክቧዊ መካክስ» /Interactive Compensatory Model/ በክፍል ውስጥ በሂደት ተጠቅሞ ማስተማር አስተዋጽኦ ይኖረዋልን? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ይሞክራል::

1.4 መላምት /Hypothesis/

– **ዜሮ መላምት / Ho/:-**

በተራክቧዊ መካክስ ሞዴል በተዘጋጀ የማስተማሪያና የክፍል ውስጥ ክንውን በተደገፈ ሁኔታ በክፍል ውስጥ የተማሩትን አንብቦ የመረዳት ክሂል ለመለካት ሲባል ድኅረ ፈተና /post-test/ ከወሰዱ በኋላ የሚያሳዩት የባህሪ ለውጥ አይኖርም::

– **አማራጭ መላምት /Alternative Hypothesis/ H1:-**

በተራክቧዊ መካክስ ሞዴል በተዘጋጀ የማስተማሪያ መሣሪያና የክፍል ውስጥ ክንውን በተደገፈ ሁኔታ በክፍል ውስጥ የተማሩትን አንብቦ የመረዳት ክሂል ለመለካት ሲባል ድህረ ፈተና /post-test/ ከወሰዱ በኋላ የሚያሳዩት የባህሪ ለውጥ ይኖራል::

1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት /Importance of the Study/

ይህ ጥናት አስፈላጊነቱ ለሚከተሉት ምክንያቶች ሲባል ነው::

1.5.1 በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንዳለ የሚነገርለትን በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎችን ችሎታ በአማርኛ ቋንቋ አንብበው የመረዳትን ክሂላቸውን ከፍ ለማድረግ፣

1.5.2 ጥናቱ በዚሁ መሠረታዊ ዓላማ ላይ ለተነሳው ጥያቄ መሠረታዊ መልስ ለማግኘት ያስችላል ተብሎ ስለሚታሰብ፣

1.5.3 ጥናቱ በዓላማው ላይ ለተነሳው ጥያቄ አዎንታዊ ምላሽ የሚያስገኝ ከሆነ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን ለፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ከፍ ለማድረግ ሲባል አዲስ መርሃ-ትምህርት ለሚቀርጹ፣ አዲስ የማስተማሪያ መጽሐፍ ለሚያዘጋጁትና እንዲሁም በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን ለፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳትን ክሂል ከፍ ለማድረግ ጥረት ለሚያደርጉት መምህራን ሁሉ አጋዥ ሊሆን ስለሚችል፣

1.6 የጥናቱ ወሰን /Deliminition of the Study/

ይህ ጥናት ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል ካለው ባህርይ አኳያ አንብቦ የመረዳትን ክሂል በክፍል ውስጥ ከፍ ለማድረግ አስተዋጽኦው አለው በሚለው እንጂ ስለንባብ አጠቃላይ ባህርይ ለመዘርዘር ወይም አንባቢው በሚያነብበት ጊዜ በአእምሮው ውስጥ የሚፈጠረውን የግንዛቤ ሂደት /cognition/ ለመመርመር አይደለም።

1.6.1 ጥናቱ ትኩረት የሚሰጠው ለአጠቃላይ የንባብ ችሎታ ሳይሆን መሠረዊ ለሆኑ አንብቦ የመረዳት ክሂሎች ላይ ነው። ስለ ዝርዝሩ /ምዕራፍ ሦስት/ ገጽ /32-38/ መመልከት ይቻላል።

1.6.2 ጥናቱ የሚከናወነው በጥናቱ የተነሳውን ዓላማ ለመመለስ ሲባል በፍትነታዊ የምርምር ዘዴ ነው።

1.6.3 የንባብ ትምህርት አቀራረቡ በቅድመ ንባብ፣ /pre-reading/ ጥልቅ ንባብ /while-reading/ እና በድኅረ ንባብ ደረጃ /post-reading/ ተወስኖ የቀረበ ነው።

1.6.4 ጥናቱ አንብቦ የመረዳትን ክሂል በክፍል ውስጥ ተግባራዊ የሚያደርገው ተማሪው ከመጽሐፉ፣ ተማሪው ከጓደኛው ፣ ተማሪው ከመምህሩ ጋር መስተጋብራዊ ግንኙነት /Interaction/ ላይ በተመሠረተ ነው።

1.6.5 ጥናቱ የሚመለከተው በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን ለፈቱ ተማሪዎች ብቻ ሲሆን ጥናቱ የተከናወነው በባሌ ዞን አዳባ ወረዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው:: ባሌ ዞን አዳባ ወረዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተመረጠበት ምክንያት፣

1.6.5.1 ቦታው ሌሎች ኦሮምኛ ከሚነገርባቸው ቦታዎች ሁሉ ለአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪው ሕብረተሰብ ርቆ በመገኘቱ የተሻለ መረጃ ያስገኛል ተብሎ በመታሰቡና

1.6.5.2 አጥኚው ለሁለት ዓመታት ያህል በዚሁ ትምህርት ቤት በማስተማሩ ከሌሎች ትምህርት ቤቶች በተሻለ ሁኔታ ለመረጃ አሰባሰቡ ተባባሪዎች ሆነው በመገኘታቸው ነው::

1.6.6 በጥናቱ የታቀፉት ካአዳባ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ውስጥ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ የተመረጡበትም ምክንያት፣

1.6.6.1 ከዘጠነኛና ከአሥረኛ ክፍል ተማሪዎች የተሻለ የትምህርት ደረጃ ስላላቸው፣

1.6.6.2 ለቀጣዩ የትምህርት ዘመን ለሚጠብቃቸው የ12ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መልቀቂያ ፈተና ያግዛቸው ዘንድ ትምህርቱን በንቃት ይከታተሉታል ሲባል በምኞት ናሙና አመራረጥ ስልት ተመርጠዋል::

1.6.7 በጥናቱ የታቀፉት ሁለት ቡድኖች ሲሆኑ አንደኛው ጥብቅ (control) ቡድን ሲሆን ሁለተኛው ተጠኚ (Experimental) ቡድን ነው::

1.6.7.1 ለጥብቅ ቡድኑ ከውጤት ተኮር /Bottom-up/ አኳያ ትምህርቱ ተሰጥቷል::

1.6.7.2 ለተጠኚ ቡድኑ «ከተራክቧዊ» ሞዴል አንጻር ትምህርቱ ተሰጥቷል::

1.6.7.3 ሁለቱም ቡድኖች የተመረጡት በብድግ ብድግ ስልት ነው::

1.6.7.4 በሁለቱም ቡድኖች ሁሉንም ጾታ፣ የተለያየ፣ እድሜ፣ አንድ ዓይነት ቋንቋ ተናጋሪና ተመሳሳይ ችሎታ ያላቸው ብቻ በጥናቱ ተካተዋል::

1.6.8 አጥኚው ካለበት የጊዜ እጥረት አኳያ የመረጃ ማሰባሰቢያው መሣሪያ ቅድመ-ትምህርት እና ድህረ-ትምህርት ፈተና ነው::

1.6.8.1 የቅድመ-ትምህርት ፈተናው ዓላማ ሁለት የተለያዩ ቡድኖችን /Independent samples/ የችሎታ ተጠጣጣኝነት ለመለካት የተከናወነ ነው::

1.6.8.2 የድህረ-ፈተና ትምህርት ዓላማ ሁለቱ ቡድኖች በተለያየ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ስልት ከተማሩ በኋላ ያሳዩትን የባህሪ ለውጥ ለመለካት ነው::

1.7 አጥኚው ለጥናቱ የተጠቀመባቸው የቃላትና የሐረጎች ግላጼ /Operational Definitions/

ንባብ /Reading/:- አንባቢው ከጽሑፉ ውስጥ ከጸሐፊው የሚፈልገውን ሐሳብ ለማግኘት ሲል ስለ ጽሑፉ ርዕሰ-ነገር ቀደም ሲል የሚያውቀውን የቀደምት እውቀት /background knowledge/ እና ሥነ-ልሳናዊ ችሎታውን ወደ ጽሑፉ በማምጣትና ከጽሁፍ ጋር በማገናኘት የተጻፈውን ጽሑፍ ለመረዳት ሲል በሂደት የሚያከናውነው ተግባር ነው::

ተራክቦ /Interactive/:- አንባቢው ከተጻፈው ነገር አንድ ነገር ለማግኘት ሲል ወደ ጽሑፉ ይዞት የመጣውን ሥነ-ልሣናዊ ችሎታና ጽሑፉ ስለተጻፈበት ርዕሰ ነገር በተመለከተ ቀደም ሲል ያለውን እውቀት ከጽሑፉ ሐሳብ ጋር ማገናኘት ወይም ማዋሃድ የሚለውን ይመለከታል::

የክፍል ውስጥ ተራክቦ /Interaction/:- በክፍል ውስጥ በመማር ማስተማር ሂደት ወቅት ተማሪው ከመጽሐፉ፣ ከጓደኛው /በቡድን፣ በጥንድ/ እንዲሁም ከመምህሩ ጋር የሚፈጥረውን መስተጋብራዊ ግንኙነት ይመለከታል::

ተራክቧዊ ሂደት /Interactive process/:- አንባቢው ከጽሑፉ ውስጥ የሚፈልገውን ጉዳይ እንደሚፈልገው ዓይነት ለማግኘት ሲል የራሱን የአነባበብ ስልት ሲቀጠም ለተጻፈው ነገር ትርጉም ለመስጠት /ለመረዳት/ ሲል በአእምሮው ውስጥ የተለያዩ የእውቀት ምንጮች /sources of knowledge/ በጥምረት በሂደት የሚያደርጉትን ጥረት ያመለክታል::

ተራክቧዊ ሞዴል /Interactive Model/:- ተማሪው አንድን ጽሑፍ ሲያነብ የራሱን የአነባበብ ስልት በሂደት ሲጠቀም ለተጻፈው ነገር ትርጉም ለመስጠት ሲል በአእምሮው ውስጥ የተለያዩ አንብቦ የመረዳት የእውቀት ምንጮች በጥምረት በመገናኘት ጥረት እንደሚያደረጉ ሁሉ ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴልም በክፍል ውስጥ ግላዊ ጥረትን በጋራ በመተካት ተማሪው የቀረበለትን ጽሑፍ አንብቦ ለመረዳት ሲል ከመጽሐፉ፣ ከጓደኛውና ከመምህሩ የተለያዩ የአነባበብ ስልቶችን በጋራ በመጠቀም ግለሰቡ ወደፊት ለሚጠብቀው የግል ንባብ በአነስተኛ ጊዜና ጉልበት የሚፈለገውን ጉዳይ እንደሚፈለገው ዓይነት የተለያዩ የአነባበብ ስልቶችን ተጠቅሞ የሚረዳበትን መንገድ ከወዲሁ የሚያመቻች የመማሪያ ስልት ነው::

ተራክቧዊ መካካስ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል /Interactive Compensatory Model/:- አንባቢው በክፍል ውስጥ በግል፣ በቡድን፣ ወይም በጥንድ በመሆን የተለያዩ የአነባበብ ስልቶችን በመጠቀም በሂደት ሲያነብ

በአንዱ የአነባበብ ሂደት ያልተረዳውን በቀጣዩ የአነባበብ ሂደት ሌላ የአነባበብ ስልት በመጠቀም የሚረዳበትን መንገድ ማዳበሪያ ስልት ነው::

አእምሯዊ እውቀት /Background Knowledge/:- ተማሪው ከህብረተሰቡ ጋር አብሮ በመኖር፣ መጻሕፍት በማንበብም ሆነ በትምህርት ቤት ያዳበረው የቀደምት እውቀት /ዳራዊ እውቀትን/ ነው::

ውጤት-ተኮር /Bottom-up/:- በዚህ ጥናት ውጤት ተኮርን የምንጠቀመው በጽሑፍ ላይ ብቻ በመመስረት ከተጻፈው በመነሳት የቋንቋውን ሥነ-ልሳናዊ ይዘት ለመረዳት ሲባል በመምህሩ ገለጻ ላይ በተመሠረተ ሁኔታ የሚሰጠውን ይመለከታል::

ሂደት-ተኮር /Top-down/:- አንባቢው የተጻፈውን ጽሑፍ ለመረዳት ሲል ከተጻፈው ጽሑፍ በመነሳት የራሱን አእምሯዊ እውቀት በመጠቀም በመገመትና በመተንበይ የንባብን ክሂል ትምህርት በሂደት የሚያከናውንበትን ስልት ይመለከታል::

ኢአፍ-መፍቻ ቋንቋ /Non-mother tongue/:- ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ከሚለመድበት የእድገት ደረጃ በኋላ በትምህርት ቤት ወይም ከሌላው ሕብረተሰብ የሚለመደውን ቋንቋ ይመለከታል::

ምዕራፍ ሁለት

የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

በዚህ ምዕራፍ የምንመለከተው ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር አግባብነት ያላቸውን ከተለያዩ የቋንቋ ንድፈ ሃሳቦችና የመማር ንድፈ-ሃሳቦች የተሰነዘሩትን ጽንሰ ሃሳቦች፣ እውቀቶች፣ ልምዶችና አስተያየቶችን ነው:: በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ለመንደርደሪያ ይሆነን ዘንድ ስለአንብቦ መረዳት ምንነት ካነሳን በኋላ በተለይም ለትምህርት የቀረበው ቋንቋ ኢአፍ-መፍቻ ቋንቋ የሆናቸው ተማሪዎች አንድን ጽሑፍ አንብቦ ለመረዳት ለምን ይከብዳቸዋል? የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ እንመለከታለን:: ይህን መሠረታዊ ችግር ለማቃለል ደግሞ የትኛውን የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል እንከተል? ከተመረጠው ሞዴል አንጻርስ የማስተማሪያ መሣሪያዎች በምን ዓይነት የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ክንውን ይቅረቡ? በተመረጠው ሞዴል የመምህሩና የተማሪው ሚናስ ምን መሆን አለበት? የሚሉት ሃሳቦች ከተቃኙ በኋላ ምዕራፉ ይቋጫል::

2.1 አንብቦ መረዳት ምንድን ነው?

በተለያየ ወቅት አንብቦ በመረዳት ላይ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ስለአንብቦ መረዳት የሰጡት ብያኔ ተመሳሳይ ነው:: ከነዚህም ውስጥ Nuttall /1996/ Grelet /1981/ እና ሌሎችም የሚስማሙበትን Carrell, Devine and Eskey /1988፣ 76/ ከሰኪማታ /schemata/ ንድፈ-ሃሳብ ጋር በማያያዝ ሲገልጹት «አንድን ጽሑፍ አንብቦ መረዳት ማለት ለንባብ የቀረበውን ጽሑፍና የአንባቢውን አእምሯዊ እውቀት እንዲሁም ሥነ-ልሳናዊ ችሎታ በሂደት በማገናኘት ለተጻፈው ጽሑፍ ትርጉም መስጠት ማለት ነው::» በማለት ነው:: ይህ ጥናት የሚስማማበትም ይህንን ብያኔ ነው::

እንደ ስኪማታ ንድፈ-ሃሳብ ለንባብ የቀረበው ጽሑፍ ለአንባቢው አቅጣጫ ጠቋሚ እንጂ በራሱ ትርጉም ሰጪ አለመሆኑን ነው:: ለተጻፈው ነገር ትርጉም ለመስጠት አንባቢው የራሱን አእምሯዊ እውቀትና ሥነ-ልሳናዊ ችሎታ በመጠቀም ለተጻፈው ጽሑፍ ትርጉም ለመሸጠት ጥረት ማድረግ አለበት::

2.1.1 አንድን ጽሑፍ አንብቦ ለመረዳት ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ ኢአፈ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች ለምን ይከብዳቸዋል?

ለትምህርት የቀረበው ቋንቋ ኢአፍ መፍቻ ቋንቋ ለሆናቸው ተማሪዎች አንብቦ ለመረዳት ለምን ይከብዳቸዋል ለሚለው Nuttall, /1996/, Carrell, Devine and Eskey /1988፣ 57- 5/, Williams /1984፣4/ እና ሌሎችም የሚስማሙባቸውን አራት ምክንያቶች በአጭሩ እንመለከታለን::

ሀ. ተማሪው ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ ለጽሑፍ የሚያገለግሉትን ወካይ ምልክቶች በተገቢ ሁኔታ ለይቶ ካለማወቅ፣

አንድን ጽሑፍ በተገቢ ሁኔታ አንብቦ ለመረዳት በቅድሚያ የጽሑፉን ምልክት ወካይ የሆኑትን የተለያዩ ምልክቶች /symbols/ ማወቅን ይጠይቃል:: እነዚህን ምልክቶች ከማወቅም አልፎ እንደ ቋንቋው ሥርዓት አቀናጅቶ ትርጉም እንዲሰጡ አድርጎ ቃል መሥርቶ ማንበብ ደግሞ ሌላው ጉዳይ ነው:: የዚህ ዓይነት ችግር በከፍተኛ ሁኔታ የሚንጸባረቀው ለንባብ ትምህርት ጀማሪ ለሆኑት እንጂ ለከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ችግሩ እምብዛም እንዳልሆነ Carrell, Devine and Eskey /1988/ Williams /1984/ ይጠቁማሉ:: ይህ ጥናትም ትኩረቱ ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ስለሆነ ለዚህ ዓይነት ችግር ብዙ ትኩረት የሚሰጠውም አይሆንም::

ለ. ተማሪው ለትምህርት የቀረበውን የቋንቋው ሥርዓት በተሟላ ሁኔታ አለማወቅ

ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ ኢአፈ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች የቋንቋውን ስዋሰዋዊ ሥርዓት በትክክል አሟልተው አያውቁም:: ምክንያቱም ቋንቋውን የለመዱት አፍ-መፍቻ ቋንቋቸው እንደሆኑት በተፈጥሯዊ ሁኔታ ሳይሆን በትምህርት አማካኝነት ነው:: ከዚህም በመነሳት Grabe /in Carrell, Devine and Eskey 1988፣ 58/ ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ አፍ የፈቱ የስድስት ዓመት ልጆችንና በቋንቋው አፍ ያልፈቱ የስድስት ዓመት ልጆችን በአንድ ክፍል ውስጥ አንድ ዓይነት ቋንቋ ማስተማር እንደሌለብን ይመክሩናል:: ከዚህ ጋር በተያያዘ ሁኔታ Williams በቋንቋው አፍ የፈቱ ተማሪዎችና አፍ ያልፈቱ ተማሪዎች አንድ ዓይነት ጽሑፍ እንዲያነቡ ቢሰጣቸው በሁለቱ መካከል ሊከሰት የሚችለውን ልዩነት ምን ሊሆን እንደሚችል ሲያስረዱ እንዲህ በማለት ነው::

ለትምህርት የቀረበው ቋንቋ ኢአፍ-መፍቻ ቋንቋ ለሆናቸው ተማሪዎች አንድን ጽሑፍ አንብቦ ለመረዳት የቋንቋውን ስዋሰዋዊ ሥርዓት ሙሉ በሙሉ ባለማወቃቸው ምክንያት የሚደርስባቸው ችግር ቋንቋው አፍ-መፍቻ ቋንቋ ከሆናቸው ጋር ሲነጻጸር ችግሩ የጎላ ነው:: በእርግጥ ቋንቋው ኢአፍ-መፍቻ ቋንቋ በሆናቸውና ባልሆናቸው መካከል ያለው ትልቅ ልዩነት የመጀመሪያው የቀረበለትን ጽሑፍ የሚያነበው የጽሑፉን ይዘት ወይም መልክት ለመረዳት ሲሆን ሁለተኛው ግን ከመልክቱ በተጨማሪ የቋንቋውን ሥርዓት ለማወቅ ሲልም ይገለገልበታል::
/1984፣ 4/

ከጥቅሱ እንደምንረዳው በተለይም የምናስተምራቸው ተማሪዎች በቋንቋው አፈ-ፈት ካልሆኑ ያለባቸውን ሥነ-ልሳናዊ ችግር ለማቃለል በንባብ ክሂል ትምህርት ጊዜ ለጽሑፉ ትኩረት በመስጠት በጽሑፉ ውስጥ ስለአሉት አዳዲስ ቃላት ዓይነትና ፍች፣ ስለ ዓረፍተነገሮች ዓይነት ከአውድ ጋር በማያያዝ ልናስተምራቸው ይገባል በማለት ጠቁመዋል::

ሐ. ተማሪዎች ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ የጽሑፉን የአጻጻፍ ስልት /Rhetorical Organization/ በትክክል አለማወቅ

ንባብ ማለት በጽሑፉ ውስጥ ያሉትን ቃላት፣ ሐረጎች፣ ዓረፍተ ነገሮችና አንቀጾች በተናጠል ማንበብ ማለት አይደለም:: በእርግጥ አንድ አንባቢ በአንድ ወጥ ጽሑፍ ውስጥ የተካተቱን ቃላት፣ ሐረጎች፣ ዓረፍተ ነገሮችና አንቀጾች በተናጠል ማወቁ ይጠቅመዋል፤ ነገር ግን ይህን ብቻ ማድረጉ ጽሑፉን ለመረዳት በቂ እንዳልሆነ Nuttall /1996፣ 49/ ይነግሩናል:: እንደ Nuttall አባባል ብቃት ያለው የአነባበብ ችሎታ የጽሑፉ አጠቃላይ ዓላማ ምን እንደሆነ፣ ጽሑፉ እንዴት እንደተዋቀረ እና በጽሑፉ ውስጥ ያሉት ዓረፍተ ነገሮች እንዴት እንደተዛመዱ መረዳትን ይጠይቃል:: ቋንቋው ኢአፍ-መፍቻ ቋንቋ ለሆነው ተማሪ በጽሑፉ ውስጥ ያሉትን አያያዥ ቃላት እና ሐረጎችን ለመለየት ባያስቸግረውም ነገር ግን በጽሑፉ ውስጥ ያሉትን ዓረፍተ ነገሮችና አንቀጾች እንዴት እንደተዛመዱ በትክክል መለየትና አገጣጥሞ በሥርዓት መረዳት ሊቸግረው ይችላል::

መ. የቋንቋውን ተናጋሪ ሕብረተሰብ ባህልና ወግ በተሟላ ሁኔታ አለማወቅ

ቋንቋና ሕብረተሰብ የማይነጣጠሉ ነገሮች ናቸው:: ሕብረተሰብ ባለበት ሁሉ ቋንቋ አለ:: ሕብረተሰብና ግለሰብም እንዲሁ የማይነጣጠሉ ነገሮች ናቸው:: ግለሰቡም የሕብረተሰቡ አባል ነው:: አባልነቱም የሚገለጸው በቋንቋ አማካኝነት በሚያደርገው ማህበራዊ ተራክቦ ነው:: ግለሰቡ በሕብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት አግኝቶ ለመኖር ሕብረተሰቡ የሚጠቀምበትን የቋንቋውን ሥርዓት አውቆ ከህብረተሰቡ ጋር መግባባት

አለበት። ይህ ችሎታ ግን የሚመነጨው ግለሰቡ ከሕብረተሰቡ ጋር አለት በአለት በሚያደርገው ግንኙነት /ተራክቦ/ ነው።

ለትምህርት የቀረበው ቋንቋ ኢአፍ-መፍቻ ቋንቋ የሆናቸው ተማሪዎች ከቋንቋው ተናጋሪ ሕብረተሰብ ራቅ ብለው የሚኖሩ ከሆነ ቋንቋውን በተፈጥሯዊ ሁኔታ /informal/ በሆነ መልኩ ለመልመድ እድሉ የላቸውም። ይህም በመሆኑ ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ ሊኖራቸው የሚችለው ሥነ-ልሳናዊ እውቀትና ስለ ቋንቋው ተናጋሪ ሕብረተሰብ ባህል ወግና ልማድ ያላቸው የቀደምት እውቀት /background knowledge/ /ውሱን ሊሆን እንደሚችል በGrabe /in Carrell, Divine and Eskey 1988፣ 57/ ተገልጿል።

ማንኛውም አንባቢ አንድን ጽሑፍ ለተለያዩ ጉዳዮች ሲያነበው ዝም ብሎ የሚያነበው ሳይሆን ወደ ጽሑፉ ይዞት የሚመጣው ነገር አለ። ይህ ይዞት የሚመጣው ነገር ቀደም ሲል ከሌላው ሕብረተሰብ ጋር አብሮ በመኖር በትምህርት ቤት በመደበኛ መልኩ ወይም የተለያዩ መጻሕፍትን በማንበብ ያገኘው ልምድና እውቀት ነው። ይህ ልምድና እውቀት /background knowledge/ በመባል የሚታወቀው እንደሆነ Wallace /1992፣ 33/, Nuttall /1996፣ 7/, Williams /1984፣ 7/ እና ሌሎችም ገልጸዋል።

Wallace /1992፣ 33/, Widdowson /1983/ን እና Cook /1989/ን በመጥቀስ አእምሮአዊ እውቀት አንድን ጽሑፍ አንብቦ ለመረዳት የሚሰጠውን ጠቀሜታ ሲገልጹት እንዲህ በማለት ነው። «አእምሯዊ እውቀት አንድን ጽሁፍ አንብቦ ለመረዳት ከቀረበው ጽሁፍ ውስጥ ቁልፍ የሆኑ ቃላትን፣ ሃረጎችንና ዓረፍተ ነገሮችን መነሻ በማድረግ ተማሪው የተጻፈውን ጽሁፍ እንዲረዳ የሚያስችል ነው።» ከዚህም በተጨማሪ Carrell, Divine and Eskey /1988፣ 104/, Nuttall /1996 ፣7/, Williams /1988፣ 81/ እና ሌሎችም አእምሯዊ እውቀት በእድሜ ደረጃና በአካባቢ፣ ግለሰቡ ከእለት በእለት በአካባቢው በሚያደርገው ተራክቦ ሊወሰን እንደሚችል ጠቁመዋል። ይህም በመሆኑ አንብቦ የመረዳትን ክሂል በክፍል ውስጥ ለማዳበር ይቻል ዘንድ ለማስተማሪያነት የምንመርጠው ጽሑፍና በክፍል ውስጥ አንብቦ የመረዳትን ክሂል ለማስተማር የምንከተለው ዘዴ ተማሪው ካለው እውቀት፣ ልምድ፣ ፍላጎትና አመለካከት እንዲሁም ከሚኖርበት አካባቢ ማህበረሰብ፣ ባህልና ወግ ጋር ተመጣጣኝ መሆን ያለበት መሆኑን ይመክራሉ ይህ ጥናት ይህንን ሃሳብ ይቀበለዋል።

Carrell, /in Carrell, Divine and Eskey 1988፣ 81/ አንብቦ በመረዳትን በኩል ያለውን መሠረታዊ ችግር አስመልክተው የሚጠቁሙት ነገር ቢኖር ተማሪው ለማስተማሪያነት በቀረበው ጽሑፍ በተወሰነ ሁኔታ አእምሯዊ እውቀት ሳይኖረው ቀርቶ ሳይሆን ከሱ ፍላጎት፣ እድሜ፣ አካባቢና ችሎታ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ጽሁፍ ካለመምረጥ

የሚመነጭ እንደሆነ ያስረዳሉ:: ከዚህ ጋር አያይዘው የሚመክሩት ቢኖር የቋንቋ መምህሩ የማስተማሪያ መሣሪያዎችን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት ከተማሪው ችሎታ፣ ልምድና አካባቢ ጋር ተመጣጣኝ መሆን ያለባቸው መሆኑን ማረጋገጥ መቻል እንዳለበት ይመክራሉ:: በዚህ ጉዳይ Nuttall /1996/ Brown /1994/, Wallace /1992/ እና ሌሎችም ይስማማሉ:: ይህ ጥናትም ይህንን አስተያየት ተቀብሎታል::

2.1.2 ቋንቋው ኢ-አፍመፍቻ ቋንቋ ለሆናቸው ተማሪዎች አንብቦ የመረዳትን ክሂል ለማዳበር በክፍል ውስጥ ምን ዓይነት የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴልን ተጠቅመን ማስተማር አለብን?

ቀደም ሲል በምዕራፍ አንድ ለመግለጽ እንደተሞከረው የተጻፈን ጽሑፍ አንብቦ መረዳት ማለት አንባቢው ከተጻፈው ላይ ብቻ በመነሳት ከተጻፈው ነገር ምንም ሳይቀንስ ወይም ሳይጨምር ሙሉ በሙሉ የተጻፈውን መረዳት ማለት እንዳልሆነ Wallace /1992፣ 39/, Grabe /in Carrell, Devine and Eskey 1988፣ 56/ ላይ አስረድተዋል::

አንብቦ የመረዳትን ክሂል ማስተማሪያ ስልት ለማሻሻል እስካሁን ድረስ ተከታታይ ጥናቶች ተከናውነዋል:: በአሁኑ ጊዜ የንባብ ትምህርት አቀራረብ ምን ደረጃ ላይ እንደደረሰ Grabe in /Carrell, Devine and Eskey 1988፣ 56/ ሲገልጹት፣ «ካለፉት አሥር ዓመታት ወዲህ በአፍ መፍቻ ቋንቋም ሆነ በኢ-አፍ መፍቻ ቋንቋ አንብቦ የመረዳትን ክሂል በተመለከተ የተገኙ የምርምር ውጤቶች እንደሚያስረዱት ንባብ ፍጹም ውጤት ተኮር /bottom-up/ እና ሂደት ተኮር /Top-down/ በሆነ ሁኔታ መወሰኑ ቀርቶ ንባብ በጽሑፉ /ውጤት-ተኮር/ እና አእምሯዊ እውቀት /ሂደት-ተኮር/ መካከል በሚደረግ ተራክቧዊ ሂደት የሚከናወን መሆኑ ተረጋግጧል::» በማለት ነው:: ከጥቅሱ እንደምንረዳው ንባብ ማለት በጽሑፉና በአንባቢው እውቀት መካከል የሚካሄድ ተራክቧዊ ሂደት ነው ወደሚል ማጠቃለያ ላይ ያደርሰናል::


አንባቢው አንድን ጽሑፍ እንደሚፈልገው ጉዳይ ለመረዳት ጽሑፉም ሆነ የራሱ አእምሯዊ እውቀቶች ጠቃሚዎች ናቸው:: በተለይም ለትምህርት የቀረበው ቋንቋ ኢአፍ መፍቻ ቋንቋ ለሆናቸው ተማሪዎች ፍጹም ጽሑፍን /bottom/ ወይም አእምሯዊ እውቀትን /top/ ብቻ ተጠቅሞ ከሚማሩ ሁለቱን ውጤት ተኮርን /bottom-up/ እና ሂደት ተኮርን /top-down/ በማገናኘት ቢማሩ የሚሰጣቸው ጠቀሜታ የላቀ እንደሆነ Carrell, Devine and Eskey /1988/, Davis /1995/, Nuttall /1996/ እና ሌሎችም አስረድተዋል:: ይህ ጥናትም የዚህን ዓይነት የንባብ ትምህርት ሂደት የሚቀበለው ነው::

ተማሪው እንዲያነብ በቀረበለት ጽሑፍ በሥነ-ልሳናዊ ችሎታው ደክም ያለ ከሆነ አእምሯዊ እውቀቱን፣ በአንጻሩ ደግሞ ጽሑፉ በቀረበበት ርዕሰ ነገር ያለው አእምሯዊ እውቀት ደካማ ከሆነ ሥነ-ልሳናዊ ችሎታውን እንዲጠቀም በማድረግ በኩል ውጤት-ተኮርን ከሂደት-ተኮር ጋር ማገናኘቱ ጠቃሚ እንደሆነ እነዚህ ምሁራን ይጠቁማሉ። በነዚህ ሁለት ችሎታዎች አማካኝነት የተለያዩ ንዑሳን አንብቦ የመረዳትን ክሂሎችን በጥምረት በሂደት እየተጠቀመ ጽሑፉን እንዲረዳ ለማድረግ ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል እንደተፈለሰፈ Grabe /in Carrell, Devine and Eskey /1988፣ 59/ አስረድተዋል።

«ተራክቦ» የሚለው ቃል የንባብ ሂደትንም ሆነ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴልን ሊወክል እንደሚችል Carrell, Devine and Eskey /1988፣ 65/ ገልጸዋል። «ተራክቦ» ሂደታዊ ነው /process/ የሚባለው አንባቢው እንዲያነብ የቀረበለትን ጽሑፍ እንደሚፈልገው ጉዳይ የራሱን የአነባበብ ስልት በሂደት እየተጠቀመ እስኪገነዘበው ድረስ በአእምሮው ውስጥ የሚያከናውነውን ተግባር የሚያሳይ ነው በማለት ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን አስረድተዋል። ተራክቦ ሞዴል ነው የሚባለው አንድ አንባቢ የቀረበለትን ጽሑፍ በሂደት ለመረዳት የሚያስፈልጉትን ሥልቶችና እነዚህን ስልቶች ደግሞ በሂደት እንዴት እንደሚጠቀምባቸው መንገዱን የሚያሳይ ነው በማለት ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን ገልጸዋል። ተራክቦ ከሞዴል ጋር በተያያዘ ሁኔታ የውጤት ተኮር /bottom-up/ እና የሂደት ተኮርን /top down/ የአነባበብ ስልት በማጣመር እንደ አንድ ሞዴል በመቁጠር ተራክቧዊ ሞዴል በሚል ስያሜ ተገልጿል። ስለዚህ ጉዳይ Grabe in /Carrell, Devine and Eskey 1988፣ 59/ ላይ መመልከት ይቻላል።

ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል የሚያሳየን በጽሑፉና በአንባቢው መካከል የሚያከናወነውን ቅጽበታዊ ግንኙነት ሳይሆን አንባቢው የቀረበለትን ጽሑፍ እስኪረዳው ድረስ የሚያደርገውን ጥረት ሁሉ የሚያሳይ ነው። Grabe /in Carrel, Devine and Eskey 1988፣ 59/ ስለተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል ምንነት ሊያጠቃልሉት። «ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል የሚያሳየን ንባብ ማለት በጽሑፍና በአንባቢው መካከል የሚካሄደውን ተራክቧዊ ግንኙነት ነው የሚለውን ነው።» በማለት ነው። ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል የሚያሳየን ተናጠላዊ የሆነ የተለያዩ አንብቦ የመረዳት ንዑሳን ክሂሎችን ሳይሆን በተለያዩ የአነባበብ ስልቶች አማካኝነት እነዚህ ንዑሳን ክሂሎች ለቀረበው ጽሑፍ ትርጉም ለመስጠት በጥምረት በሂደት የሚያከናውኑትን ተግባር ነው። ስለ ተራክቧዊ የንባብ ክሂል አሠራር ሂደት ከRumelhart /1977/ Carrell, Devine and Eskey /1988፣ 59/ በመውሰድ ያስቀመጡትን ሥዕላዊ መግለጫ ገጽ 16 መመልከት ይቻላል።

ተራክቦአዊ የንባብ ሞዴል



ከ Carrell, Devine and Eskey /1988 ፣ 59/ የተወሰደ

በዚሁ ምዕራፍ ከገጽ 11 - 14 የተጠቀሱት ችግሮች ለማቃለል ውጤት ተኮርንና ሂደት ተኮርን /bottom-up and top down/ በማገናኘት ሊያስገኝ የሚችለውን ጠቀሜታ ግምት ውስጥ በማስገባት ተራክቧዊ ሞዴል /Interactive Model/ መጀመሪያ በ Rumelhart /1977/ እንደተፈለሰፈ ቀጥሎም በ Stanovich /1980/ እና በሌሎችም እየተሻሻለ አሁን ባለበት ደረጃ እንደደረሰ Grabe /in Carrell, Devine and Eskey 1988፣ 60/ አስረድተዋል። ሞዴሉ ፍጹም ጽሑፍን መሠረት አድርጎ የተገነባውን ውጤት ተኮር /bottom-up/ እና ሂደት ተኮር /top-down/የሆነውን አስወግዶ በምትኩ ሁለቱን በማዋሃድ የተገነባ መሆኑን Nuttall /1996/, Davis /1995/ Brown /1994/, Carrell, Devine and Eskey /1988/ በተመሳሳይ ሃሳብ ገልጸዋል።

ይህ ጥናትም ለትምህርት የቀረበው ቋንቋ ኢአፍ መፍቻ ቋንቋ በሆናቸው ተማሪዎች ያለባቸውን ሥነ-ልቦናዊ ችግርና የቋንቋውን ተናጋሪ ሕብረተሰብ ባህልና ወግ በትክክል ባለማወቅ ምክንያት አንድን ጽሑፍ አንብቦ ለመረዳት ያለባቸውን ድክመት ግምት ውስጥ በማስገባት ውጤት ተኮር /bottom-up/ እና ሂደት ተኮር /top-down/ በማዋሃድ «ተራክቧዊ» ሞዴልን /Interactive/ ተከትሏል።

2.2 ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል /Interactive Model/

«ተራክቦ» የሚለው ቃል አንብቦ ከመረዳት ክሂል ጋር በተዛመደ ሁኔታ መከሰቱ የቅርብ ጊዜ ክስተት ነው። በተለይም ቋንቋ ማህበራዊ ነው የሚለው የቋንቋ ፍልስፍና በማህበራዊ ሥነ-ልሳን /Socio-lingustics/ አራማጆች ምክንያት የቋንቋ ትምህርት ፍጹም ቋንቋን ብቻ ከማስተማር ተላቆ ወደ ማህበራዊ አጠቃቀሙ ጭምር እንዲያተኩር መደረጉን Brown /1994/, Richard /1990/, Brumfit /1984/ እና ሌሎችም ጠቁመዋል።

እንደ ማህበራዊ ሥነ-ልሣን አራማጆች የቋንቋ ትምህርት ዓላማ መሆን ያለበት ተግባቦታዊ ችሎታን ማሳደግ ነው። ከዚህ አጠቃላይ ዓላማ በመነሳት የንባብ ክሂልን ለማዳበርም የሚሰጠው ትምህርት አጠቃላይ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር እንጂ የተነጣጠሉ አንብቦ የመረዳት ክሂሎችን ለማዳበር እንዳልሆነ Wallace /1992/ Carrell, Devine and Eskey /1988/ አስረድተዋል።

2.2.1 የተለያዩ ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴሎች

ይህ ጥናት በባህሪው የተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴሎችን ቢከተልም በቴክኒክ ወይም በክፍል ውስጥ በሚከናወነው የንባብ ትምህርት አቀራረብ ቴክኒክ ትኩረት የሰጠው ከዚህ በታች ከተጠቀሱት ሞዴሎች በአንዱ ነው:: ጥናቱ የአሠራር ቴክኒኩን ለምን ወደ አንድ የተለየ ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል ትኩረት እንዳደረገ ምክንያቶችንም እንመለከታለን::

ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴሎች ቁጥራቸው አምስት ሲሆን ዝርዝራቸውን Grabe /in Carrell, Devine and Eskey 1988፤ 60/ ላይ እንደሚከተለው ዘርዝረዋቸዋል::

ሀ. ስትፈተ-ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል /Interactive Activation Model/ በ Rumelhart and McLelland /1981/ የተፈለሰፈ፤

ለ. ተራክቧዊ መካካስ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል /Interractive Compensatory Model/ በ Stanovich /1980/ የተፈለሰፈ፤

ሐ. ተራክቧዊ ግለ-ትግበራ ሂደት የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል /Automatic Processing Model/ በLaBerge and Samuel /1977/ የተፈለሰፈ፤

መ. ተራክቧዊ ጥምር-ምንትዮሽ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል /Bilateral Cooperative Model/ በ Taylor and Taylor's /1977/ ፤

ሠ. ብቃተ-ቃላዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል /Verbal-efficency Model/ በPerfettis /1985, 1986 a,b/ የሚሉ ናቸው::

ከላይ የተዘረዘሩት አምስቱ ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴሎች በአተገባበራቸው /በአሠራር ቴክኒካቸው/ ይለያዩ እንጂ በይዘታቸው ግን ተመሳሳዮች እንደሆኑ Grabe /in carrell, Devine and Eskey 1988፤ 63/ ላይ ተገልጿል:: ሞዴሎቹ ቀደም ሲል በሥራ ላይ የነበረውን ሂደት ተኮር /top-down/ ሞዴልን በማሻሻል በኩል ሁሉም የየራሳቸው አስተዋጽኦ አላቸው:: ሁሉም ሞዴሎች በአሠራር ቴክኒካቸው ተራክቧዊ ሞዴል ሊባሉ የቻሉት፤

ሀ. የንባብ ክሂል ትምህርት በጽሑፍ /bottom-up/ እና በአንባቢው አእምሯዊ እውቀት መካከል በሚደረገው ተራክቧዊ ሂደት የሚከናወን መሆኑን ይቀበሉታል::

ለ. ሁሉም ተራክቧዊ ሞዴሎች አንባቢው የቀረበለትን ጽሑፍ አንብቦ ለመረዳት ጽሑፉ ውስጥ የተካተቱት ሥነ-ልሳናዊ ይዘቶች /form/ ለግንዛቤው እንደ አውድ /context/ ሆነው ሊያገለግሉት የሚችሉ መሆኑን ይቀበሉታል::

ሐ. ሁሉም ሞዴሎች ለጥሩ ግንዛቤ ስፋት ያለው የቃላት ችሎታ አስፈላጊ መሆኑን ይቀበሉታል

መ. ሁሉም ሞዴሎች አንባቢው በንባብ ጊዜ ለግንዛቤው ይረዱት ዘንድ ጽሑፉም ሆነ የራሱ አእምሯዊ እውቀት /background knowledge/ በጣም ጠቃሚ መሆናቸውን ይቀበሉታል:: ይህንን ጉዳይ በተለየ ሁኔታ የሚቀበለው Stanovich /1980/ መሆኑን Grabe /in Carrell, Devine and Eskey 1988፣ 63/ ጠቁመዋል::

ሠ. ሁሉም ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴሎች አንብቦ የመረዳትን ክሂል ለማዳበር የሚዘጋጁ ይዘቶች በቅድመ /pre-reading/፣ ጥልቅ ንባብ /while-reading/ እና ድህረ-ንባብ /post-reading/ ደረጃ መቅረብ ያለባቸው መሆኑን ይቀበሉታል::

Grabe /in Carrell, Devine and Eskey 1988፣ 59/, Davis /1995/, Brown /1994/ እና ሌሎችም የሚስማሙበት ነገር ቢኖር ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴሎች ከላይ በተዘረዘሩት ባካተታቸው የጋራ ባህሪያት ምክንያት ከሌሎች ፍጹም ጽሑፍ ላይ ካተኮረው /bottom-up/ እና ፍጹም ሂደት ላይ ካተኮረው /top-down/ አንብቦ የመረዳትን ክሂል ለማስተማር ተመራጭነት ያለው መሆኑን ጠቁመዋል:: ይህ ጥናትም ከዚህ ማጠቃለያ በመነሳት ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል አንብቦ የመረዳትን ክሂልን ለማዳበር ያለውን አስተዋጽኦ ለመፈተሽ ዓልሞ በመነሳት ጥናቱን አከናውኗል::

አምስቱ የተለያዩት ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴሎች ከላይ የተዘረዘሩትን ባህሪያት ቢያሟሉም የንባብን ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ ጽሑፉን እና አእምሯዊ እውቀቱን በተመጣጠነ ሁኔታ እንደመነሻ በማድረግ ተማሪው እንዲጠቀምበት

በአተገባበር በኩል ለሁለቱም ችሎታዎች እኩል እድል ሰጪ እንዳልሆኑ Carrell Devine and Eskey /1988፣ 63/ አስረድተዋል። አንባቢው በንባብ ሂደት ጊዜ በአንዱ የአነባበብ ስልት ያልተረዳውን በቀጣዩ የአነባበብ ስልት የራሱ ሥነ-ልሣናዊ ወይም አእምሯዊ እውቀት ለሱ የተሻለውን ችሎታ መነሻ በማድረግ ጽሑፉን በሂደት የራሱን የአነባበብ ስልት እየተጠቀመ እንዲረዳ ከሌሎች ሞዴሎች በተሻለ ሁኔታ የሚያስተምርልን የStanovich/ ተራክቢዊ መካክስ ሞዴል /Interactive Compensatory Model/ መሆኑን Carrell, Devine and Eskey /1988፣ 32/ እና Williams /1996፣ 183/ አስረድተዋል። Williams /1996፣ 183/ ስለ ተራክቢዊ መካክስ በማስመልከት ሙሉ የእንግሊዝኛ ጥቅስ የተናገሩት እንዲህ ይላል። "The descrpetive model of reading is widly accepted within applied lingustics is the compensatory model." በማለት ገልጸውታል። ይህ ጥናትም በክፍል ውስጥ የንባብ ክሂል አተገባበር ያለውን የአሠራር ቴክኒክ የተከተለው የStanovich /1980/ ተራክቢዊ መካክስ /Interactive compensatory/ ሞዴልን ነው።

2.2.2 የተራክቢዊ መካክስ ሞዴል ምንነትና አተገባበር /Interactive Compensatory Model/

ተራክቢዊ መካክስ ሞዴል በ1980 በStanovich የተፈለሰፈ ሲሆን ትኩረቱም በክፍል ውስጥ የንባብ ክሂል ትምህርት ጊዜ ተማሪው የተሰጠውን ጽሑፍ አንብቦ ለመረዳት ምን ዓይነት የአነባበብ ስልት ይጠቀም? በሚለው ነው። Stanovich ሞዴሉን እንዲሁ የቀረጹት ሳይሆን በተለያየ ጊዜ ጎበዝ አንባቢያንና ደካማ አንባቢያንን በማነጻጸር እንደሆነ Wallace /1992/, Carrell, Devine and Eskey /1988፣ 32/ ጠቁመዋል። Stanovich ሞዴሉን ሲቀርጹ በአሠራር በኩል የሚከተለውን መንገድ የገለጹት እንዲህ በማለት ነው።

> *ተራክቢዊ መካክስ ሞዴል ፍጹም ጽሑፍን /bottom-up/ ብቻ መሠረት በማድረግ ወይም ፍጹም አእምሯዊ እውቀትን /top-down/ ብቻ መሠረት በማድረግ አንብቦ የመረዳትን ክሂል ለማስተማር ከሚያደርገው ጥረት በተሻለ ሁኔታ አንብቦ የመረዳትን ክሂል ለማዳበር ብቃት አለው። በተራክቢዊ መካክስ ሞዴል አንባቢው የቀረበለትን ጽሁፍ ከራሱ አእምሯዊ እና ሥነ-ልሳናዊ ችሎታ ጋር በሂደት በማገናኘት ጽሁፉን እንደሚፈለገው ሁኔታ የራሱን የአነባበብ ስልት በሂደት ተጠቅሞ እንዲረዳው እንዲገነዘበው ያደርጋል። በተራክቢዊ መካክስ ሞዴል አንባቢው አንድን ጽሑፍ ሲያነብ አንብቦ የመረዳትን ቅደም ተከተላዊ ሂደት ጠብቆ የሚጓዝ ሲሆን አንባቢው በንባብ ሂደት ወቅት በአንዱ የአነባበብ ስልት ያልተረዳውን ሃሣብ በቀጣዩ የአነባበብ ሂደት የተሰየ የአነነባበብ ስልት በመጠቀምና በማካካስ ይረዳዋል።*
>
> */1980፣ 32/*

---

* ስሞች በእንግሊዘኛ የተጻፉ ከሆነ አቆጣጠራቸውም በአሮፖውያን አቆጣጠር ነው። በአማርኛ ቋንቋ የተጻፉ ከሆነ አቆጣጠሩ የኢትዮጵያ አቆጣጠርን የተከተለ ነው።

የStanovich model የውጤት ተኮርን /bottom-up/ እና የሂደት ተኮርን /top-down/ ጠንካራ ጎኖች በመውሰድና በማዋሃድ የተገነባ ከመሆኑም በላይ ጥሩ አንባቢ በንባብ ሂደት ወቅት የሚያከናውነው ተግባር ምንድን ነው? የሚለውን ሁኔታ በማጥናት ጭምር የተቀረጸ ነው::

እንደ Stanovich አባባል ብቃት ያለው አንባቢ አንድን ጽሑፍ አንብቦ ለመረዳት በመተንበይና በመገመት ብቻ ከመወሰን አንባቢው ጽሑፉን በሂደት እያየ በአንዱ የአነባበብ ስልት ያልተረዳውን በቀጣዩ የአነባበብ ስልት የራሱን ሥነ-ልሣናዊ እና አእምሯዊ እውቀት በመጠቀም እያካካሰ ቢያነብ በቀላሉ ክሂሉን ሊያዳብር ይችላል::

ከዚህ በመነሳት የምንመለከተው በተራክቧዊ መካክስ ሞዴል መሠረትነት አንብቦ የመረዳት ክሂልን ለማዳበር የሚዘጋጁት የማስተማሪያ መሣሪያዎች አቀራረብ ምን መምሰል አለባቸው? የሚለውን ነው:: ቀደም ሲል እንዳነሳነው ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል ከሌሎች ሞዴሎች ተመራጪ የሚያደርገው የንባብ ክሂልን ትምህርት ቅድመ ንባብ፣ /pre-reading/ በጥልቅ ንባብ /while-reading/ እና ድህረ-ንባብ /post-reading/ በደረጃ ከፋፍሎ ማቅረብ መቻሉ ነው:: ይህን አከፋፈል Brown /1994/, Grellet /1981/, Wallace /1992/, Carrell, Devine and Eskey /1988/ Williams /1984/ እና ሌሎችም ይቀበሉታል:: ይህ ጥናትም ይህንን አከፋፈል ተቀብሎ ተግባራዊ አድርጓል::

ሀ. ቅድመ-ንባብ /Pre-reading/:- በመጀመሪያ ወይም በትምህርቱ መግቢያ የሚሰጥ ሲሆን ዓላማውም ለሚከተሉት ተግባራት ነው፤

- ተማሪው በቀረበለት ምንባብ ላይ ፍላጎቱን ለመቀስቀስ፣
- ተማሪው ለምን ዓላማ እንደሚያነብ ከወዲሁ ለማዘጋጀትና
- ለማስተማሪያነት በቀረበው ምንባብ በተመለከተ በጽሑፉ ውስጥ አስቸጋሪ ቃላት፣ ሀረጎችና ዓረፍተ ነገሮች ካሉ ከወዲሁ ተማሪውን ለማዘጋጀት እንደሆነ Williams /1984፣ 36/, Brown /1994/, Wallace /1992፣ 86/ እና ሌሎችም ያስረዳሉ::

ለ. ጥልቅ ንባብ /While-reading/:- በዚህ የንባብ ትምህርት ደረጃ ከተማሪው የሚጠበቀው የራሱን ሀሳብ ማመንጨት ሳይሆን ከራሱ ልምድና እውቀት

በመነሳት የጽሁፉን ሥነ-ልሳናዊ ይዘትና /form/ የጽሑፉን መልክት /content/ በጥልቀት ለመረዳት ጥረት የሚያደርግበት ነው:: የዚህ የንባብ ትምህርት ደረጃ /while-reading/ ዓላማ፤

- ጸሐፊው ጽሁፉን ለምን ተግባር እንደጻፈው ተማሪውን እንዲረዳ ለማድረግ፣
- ተማሪው የጽሁፉን አወቃቀር እንዲረዳው ለማድረግ፣
- ተማሪው የጽሁፉን መልክት እንዲገልጸው ለማድረግ ነው::

መምህሩ ይዘቶችን አዘጋጅቶ ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ማንሣት ይችላል::

- የምንባቡ አገልግሎት /function/ ምንድን ነው?
- ምንባቡ በምን ዓይነት የአጻጻፍ ስልት /rehetorical organization/ ስልት ቀረበ?
- አንባቢው ከጽሁፉ የሚፈልገው ሃሳብ ምንድን ነው?
- አንባቢው ከጽሁፉ የሚማረው ቋንቋ ምንድን ነው?

ሐ. ድህረ ንባብ /Post-reading/:- በዚህ ደረጃ አንብቦ የመረዳትን ክሂል የምናስተምርበት ዋና ዋናዎቹ ዓላማዎች፤

- አንባቢው ስለአነበበው ጉዳይ እንዲገለጽ ለማድረግ፣
- አንባቢው ከቀረበው ምንባብ ያገኘውን አዲስ እውቀት ቀደም ሲል ካለው እውቀት ጋር በማያያዝ ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እያዛመደ እንዲገመግመው ለማድረግ ነው::

የቋንቋ መምህሩ የድህረ-ንባብ ይዘቶችን ከማዘጋጀቱ በፊት የሚያነሳቸው ጥያቄዎች የሚከተሉት ዓይነት ናቸው፤

- ተማሪው በጽሁፉ ከተጠቀሰው ይዘት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ እውቀት /background knowledge/ አለው?

- የቀረበው ምንባብ /text/ ተማሪው ተጨማሪ ሀሳብ እንዲያክል የሚያስችል ነው?

- የቀረበው ምንባብ ተማሪው የተቃውሞ ሃሳቡን እንዲያቀርብ የሚያስችል ነው?

2.2.3 በተራክቦአዊ መካከስ ሞዴል መሠረት አንብቦ የመረዳትን ክሂል ለማዳበር የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ክንውን

የዘመኑ የቋንቋ መማር ማስተማር ስልት የሚከተለው ተማሪው የተግባቦታዊ ችሎታውን እንዲሳድግ ነው:: ይህም በመሆኑ ተማሪው ቀደም ሲል የቋንቋን ስዋሰዋዊ ህግጋት ለማወቅ ሲል የቋንቋውን ሥርዓት በመደጋገም ስልት በቃል ማጥናቱ ቀርቶለት ዛሬ በግንዛቤ ላይ በተመሠረተ ሁኔታ ራሱ የሚፈልገውን ብቻ በራሱ የመማር ስልት እያከናወነ የተግባቦታዊ ችሎታውን የሚሳድግበት ደረጃ ላይ እንደተደረሰ Brown /1994/, Richard /1990/ እና ሌሎቹም ያስገነዝባሉ::

Brown /1994/ እንደሚያስረዱት ቀደም ሲል የነበረው የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ ተማሪው የቋንቋ መሰሎችን በመደጋገም በቃሉ እንዲያጠና ከማድረጉም በላይ መምህሩ የሚገልጸውን ብቻ ተማሪው በማዳመጥ እንዳለ እንዲቀበለው በማድረጉ የተማሪውን የተግባቦታዊ ችሎታ ጐትቶታል በማለት ያስረዱናል:: በአንጻሩ የዘመኑ የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ደግሞ ተማሪውን በተግባቦታዊ ችሎታው ከፍ ለማድረግ እንጂ የቋንቋን ሥርዓት አዋቂ ብቻ ለማድረግ እንዳልሆነ እነዚሁ የተጠቀሱት የቋንቋ ምሁራን ይነግሩናል:: ተማሪው ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ የተግባቦታዊ ችሎታውን ለማሳደግ ከመጽሐፉ፤ ከጓደኛው እና ከመምህሩ ጋር በክፍል ውስጥ ተራክቦ ማድረግ እንዳለበት Richard /1990፤ 13/ ላይ ያስረዱናል:: Brown /1994፤ 159/ ስለ ክፍል ውስጥ ተራክቦ ምንነት ሲገልጹ «ተራክቦ ማለት በሁለት ወይም ከሁለት በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል /በቋንቋ አማካኝነት/ ሃሳብን፤ ስሜትንና እውቀትን መለዋወጥ ማለት ነው::» በማለት ነው::

በተለይም በአሁኑ የማህበራዊ ሥነ-ልሳን መርህ ተራክቦ ለተግባቦታዊ ችሎታ ወሳኝነት አለው:: እንዲያውም ተራክቦ ለመግባባት የደም ስር መሆኑን Brown /1994/ ይጠቁማሉ:: የሰው ልጅ ማህበራዊ በመሆኑ ከመሰሉ ጋር ሃሳብ ለመለዋወጥ ይፈልጋል:: በመጀመሪያ መልክት አለው መልክቱን በቋንቋ አማካኝነት ለመሰሉ ሰው ያስተላልፋል መልክት ተቀባዩ ከአውድ ጋር በማያያዝ መልክቱን ትርጉም ይሰጠዋል:: ከዚያም ለተጠየቀው ነገር ምላሽ ይሰጣል:: በዚህ ሁኔታ በሚደረገው የተራክቦ ሂደት ሁለቱ ሰዎች የሚፈልጉትን ጉዳይ በመግባባት ይፈጽማሉ::

ተማሪው ተግባቦታዊ ችሎታውን ለማሳደግ የክፍል ውስጥ ክንውን ምን መሆን እንዳለበት Brown ሲገልጹ እንዲህ በማለት ነው::

> *ከጅምሩ የቋንቋ መማሪያ ክፍል የሃሳብ መለዋወጫ ክፍል መሆን አለበት:: ተማሪው የተለያዩ ጽሑፎችን በማንበብ፣ ከሰዎች ጋር ሃሳብ በመለዋወጥ፣ ወ.ዘ.ተ. ተራክቦ በማድረግ የቋንቋ ችሎታውን ያሳድጋል:: ተማሪው ከጓደኛው ጋር በመጫወት፣ በመወያየት፣ ለአንዳንድ ችግሮች መፍትሄ ለመፈለግ በሚያደርገው የሃሳብ ልውውጥ ሁሉ በሚያደርገው ተራክቦ የቋንቋ ችሎታውን ያዳብራል:: በተራክቦ ጊዜ ተማሪው የሚችለውን ሁሉ በማድረግ ሃሳቡን ስለሚገልጽ የቋንቋ ችሎታው ያድጋል:: ተማሪዎች ከታች ክፍል ጀምሮ ይህንን ስልት እያዳበሩ መምጣት አለባቸው::*
>
> */1994፣ 159/*

ከአገላለጹ እንደምንረዳው ተማሪው በሰው ሠራሽ ክፍል ውስጥ ቋንቋውን በአግባቡ እንዲለምደው ለተማሪው የተለያዩ ክንዋኔዎችን /tasks/ በመስጠት ከመጽሐፉ፣ ከጓደኛው /በጥንድ ወይም በቡድን/ እና ከመምህሩ ጋር ተራክቦ እንዲያደርግ ብናደርገው ተግባቦታዊ ችሎታውን ሊያሳድግ ይችላል::

የመማሪያ ክፍል እንደተፈጥሯዊ አካባቢ በቋንቋ ለመግባባት ውሱን በመሆኑ መምህሩ በተቻለ መጠን በክፍል ውስጥ የሚያቀርባቸው ሥራዎች /ክንዋኔዎች/ /tasks/ ተፈጥሯዊነታቸውን /Authenthic/ ጠብቀው መቅረብ አለባቸው በማለት Brown /1994/, Nuttall /1996/, Grellet /1981/, Carrell, Devine and Eskey /1988/ እና ሌሎችም አስረድተዋል:: የቋንቋን ትምህርት በተራክቧዊ ስልት መሰጠት እንዳለበት Brown /1994፣ 159/ ሲመክሩ «ተራክቦን ለማዳበር እውነተኛው የመማሪያ መንገድ ራሱ ተራክቦ ነው::» በማለት ነው:: ከአገላለጹ እንደምንረዳው ሰዎች ሃሳባቸውን ለመሰላቸው የመግለጽም ሆነ የሰውን ሃሳብ የመቀበልን ችሎታ ለማዳበር ከፈለጉ መጀመሪያ ሃሳብን የመግለጽ ወይም የመቀበልን ክሂሎት ከሌሎች መሰል ክሂሎቶች ጋር በማገናኘትና በመለማመድ ማዳበር አለባቸው::

እንግዲህ ቋንቋን በክፍል ውስጥ ለማስተማር አይነተኛው መንገድ ተራክቦ ነው ካልን የንባብ ክሂል ትምህርትም ከቋንቋ ትምህርት አንዱና ዋነኛው አካል በመሆኑ ተራክቧዊ ሥልት ለማስተማር የምንከተላቸው የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ስልቶች ምንድን ናቸው? የሚለውን ጥያቄ ቀጥለን ለመመለስ እንሞክራለን::

መምህሩ ያዘጋጃቸውን ይዘቶች ራሱ በክፍል ውስጥ ከማቅረብ ተቆጥቦ ከሚያስተምራቸው ተማሪዎች ችሎታ፣ ልምድና ፍላጐት እንዲሁም ከሚኖሩበትና ከሚማሩበት አካባቢ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ይዘቶችን በግል፣ በቡድን ወይም በጥንድ እየተወያዩ ክሂሎታቸውን እንዲያሳድጉ Wallace /1992፣ 80-110/, Brown /1994፣ 142-43/ Williams /1984፣ 246/ እና ሌሎችም የሚስማሙባቸውን የማስተማሪያ መሣሪያዎች ከዚህ በታች በተጠቀሱት ስልቶች መሠረት መዘጋጀት ያለባቸው መሆኑን ይጠቁማሉ:: ይህ ጥናትም እነዚህን ጉዳዮች ግምት ውስጥ በማስገባት የማስተማሪያ መሣሪያዎችን በነዚሁ መሠረትነት አዘጋጅቷቸዋል::

- ርዕስ በመስጠት በBrain Storming ስልት ስለ ርዕሱ የሚያውቁትን ሁሉ ተወያይተው እንዲመልሱ ማድረግ፣

- አንድ ወጥ የሆነ ጽሑፍን የተወሰኑ ክፍት ቦታዎችን በመተው ከራሳቸው ችሎታ በመነሳት ክፍት ቦታውን እየተነበዩ ጥንድ በመሆን እንዲሞሉ cloze test መስጠት፣

- ስለ ጽሑፉ፣ ስለ አንቀጾች ተናጠላዊ መልክት አጠቃላይ ግንዛቤን እንዲያሳድጉ ለማድረግ በገረፍ-ገረፍ ስልት /skimming/ የሚሠሩ ይዘቶችን በቡድን እንዲሠሩ አዘጋጅቶ መስጠት፣

- የአሰሳ /scanning/ የአነባበብ ስልታቸውን እንዲያዳብሩ ከጽሑፉ ውስጥ ስሞችን፣ ቁጥሮችን ዓመተ ምህረቶችን በጥንድ ወይም በግል እንዲፈለጉ ይዘቶችን አዘጋጅቶ መስጠት፣

- ስለ ጽሑፉ ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ጮክ ብለው የሚያነቡበትንና በሎሆሳስ የአነባበብ ስልት አንብበው ጥያቄዎችን እንዲመልሱ መልመጃዎችን አዘጋጅቶ በቡድን፣ በጥንድ ወይም በግል እንዲሠሩ ማድረግ፣

- ተማሪዎች ያገኙትን አዲስ እውቀት ከአካባቢያቸው ጋር እያዛመዱ የደረሱበትን እውነታ እንዲናገሩ በቡድን በውይይት የሚሠሩ ይዘቶችን በመስጠት በጋራ እንዲለማመዱ ብናደርጋቸው እነሱ ይዘቶችን በጋራ በመሥራታቸው ከመቀስቀሳቸውም በላይ ኃላፊነትን ወስደው በመማራቸው በራስ የመተማመን መንፈስንም ሊያዳብሩት ይችላሉ በማለት /Brown 1994፣ 173, Nuttall 1996፣ 173/ እና ሌሎችም አስረድተዋል። ይህ ጥናትም ይህንን ሁኔታ በመከተል በነዚህ ሁኔታ የተለያዩ ይዘቶችን ለተማሪው በማዘጋጀት በቡድን፣ በጥንድ እንዲሁም በግል በክፍል ውስጥ እንዲያከናውን አድርጓል።

ተማሪው በክፍል ውስጥ ከተግባቦታዊ ችሎታ አንጻር አንብቦ የመረዳት ችሎታውን በተራክቧዊ /Interaction/ ስልት ለማዳበር የቡድን ሥራ ወሳኝነት እንዳለው Brown /1994፣ 173/ አስረድተዋል። የቡድን ሥራ ለተራክቧዊ የንባብ ክኂል ትምህርት በክፍል ውስጥ ካለው ጠቀሜታ አንጻር ስለ ቡድን ሥራ ምንነትና አገልግሎት እንዲሁም አሉታዊ ጎኖችን የምንቋቋምበትን መንገድና በቡድን ሥራ ጊዜ የመምህሩና የተማሪው ሚና ምን መሆን እንዳለበት ቀጥለን እንመለከታለን።

2.2.3.1 የቡድን ሥራ

ቡድን ምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ Brown /1994፣ 173/ ሲገልጹ «ቡድን ማለት ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ተማሪዎች አንድ ዓይነት ስልት ተጠቅመው አንድን ዓይነት ተግባር በጋራ እንዲያከናውኑ ሲባል የሚዋቀር ነው።» በማለት ነው።

ቡድን የሚለው ቃል ጥንድ በመሆን ከሚናወነው ጀምሮ ሦስትና ከሦስት በላይ በመሆን በአንድነት የሚከናወነውን ሁሉ ያጠቃልላል። የቡድን ሥራ በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ማድረግ በተራክቧዊ ሥልት ለማስተማር ያለውን ተመራጭነት Brown /1994፣ 173/ እንደሚከተለው ዘርዝረዋቸዋል።

- የቡድን ሥራ በአንድ ክፍል ውስጥ መጠነ ሰፊ የሆነን ተማሪ ለማሳተፍ እድል ሰጪ በመሆኑ፡

- ተማሪው እርስ በርሱ ሃሳብ እንዲለዋወጥ እድል በመስጠቱ፣

- ማንኛውም የቡድን አባል ለመናገር እንዲችል እድል ሰጪ በመሆኑ፣

- የቡድን ሥራ ቀስ በቀስ የተማሪውን የግል ባህሪ ለማወቅ ለመምህሩ እድል ሰጪ በመሆኑ ከጠቀሜታዎቹ ውስጥ ዋናዋናዎቹ እንደሆኑ አስረድተዋል::

የቡድን ሥራ ምንም እንኳ ተመራጪነት እንዲኖረው ጠቃሚ ጎኖች ቢኖሩትም አንዳንድ አሉታዊ ጎኖች ሊኖሩት እንደሚችሉና እነርሱንም በሚከተሉት ዘዴዎች መቋቋም እንደሚቻል ይገመታል:: ለምሣሌ:-

- የቡድን ሥራ በክፍል ውስጥ ለመምህሩ ለቁጥጥር አመቺ አይደለም የሚባለውን አሉታዊ ጎን ለመቋቋም Brown /1994፣ 176/ ሲያስረዱ በክፍል ውስጥ ለሚከናወን ትምህርት ጥብቅ ቁጥጥር አስፈላጊ መሆኑ ባያጠራጥርም፤ የቡድን ሥራ ካለው ጠቀሜታ አንጻር መምህሩ እንደ ኦርኬስትራ መሪ ሆኖ ቡድኑን በጥብቅ በመቆጣጠር የቡድንን ሥራ ተግባራዊ ማድረግ እንደሚቻል ያስረዳሉ::

- ተማሪው በቡድን አማካይነት ሲወያይ በአፍ-መፍቻ ቋንቋ ሊጠቀም ይችላል የሚለውን አሉታዊ ጎን ለማቀነስ የዚህ ዓይነት ችግር ባለበት ክፍል የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪዎችን በአንድ ቡድን በማካተት ችግሩን መቋቋም እንደሚቻል ተጠቁሟል:: /ገጽ 177/

- ተማሪዎች በቡድናቸው አማካይነት ሲወያዩ የሚፈጽሟቸውን ሥህተቶች ለመቆጣጠር አስቸጋሪ ነው ለሚባለው Brown /1994፣ 177/ እንደሚነግሩን በአንድ ወቅት በተደረገ ጥናት ስህተት እንዳይፈጽሙ ቁጥጥር የተደረገባቸው ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ወቅት ስህተት እየፈጸሙ እንዲማሩ ከተደረጉ ተማሪዎች ጋር አንድ ዓይነት ፈተና ወስደው ስህተት ሲፈጽሙ ቁጥጥር የተደረገባቸው ተማሪዎች ስህተት ሲፈጽሙ ቁጥጥር ካልተደረገባቸው ተማሪዎች ያነሰ ውጤት አስመዝግበዋል:: ምንም እንኳ ለቋንቋ ትምህርት ቁጥጥር አስፈላጊ መሆኑ ቢታመንበትም በተራክቧዊ ትምህርት አቀራረብ ግን ተማሪው የፈጸመውን ስህተት ሁሉ ለመቆጣጠር መሞከሩ ተግባቦታዊ ችሎታውን ስለሚገታው መጠነኛ ቁጥጥር ማድረግ ያለብን መሆኑን Brown /1994፣ 177/ ይጠቁማሉ::

- አንዳንድ ተማሪዎች በግል መማርን ሊመርጡ ይችላሉ ለሚባለው በተለይም እድሜያቸው ወደ ጎልማሳነት /adult/ የተጠጉ ተማሪዎች ከቡድን ይልቅ

በግል መማርን ሊፈልጉ ይችላሉ፤ ነገር ግን የቋንቋ ትምህርት መምህሩ ለተማሪው መምከር ያለበት ቋንቋን መማር የቋንቋን ህግጋት ብቻ አውቆ በቋንቋው በአግባቡ ለመገልገል እንደማይቻል ምክር በመስጠት ለመመለስ መምከር ነው::

ከላይ የዘረዘርናቸው ጉዳዮች በቡድን ሥራ እንደ ደካማ ጎን ቢወሰዱም በተጠቀሱት የመፍትሄ ሃሳቦች ችግሮችን ልናስተካክላቸው የምንችል መሆናችንን Brown /1994፤177/ ይነግሩናል:: ከዚህም በተጨማሪ በሂደት ሌሎች ተጨማሪ መፍትሄዎች ሊገኙ እንደሚችሉም እንገምታለን::

2.2.3.2 በተራክቧዊ አቀራረብ በክፍል ውስጥ የመምህሩ ሚና

በተራክቧዊ አቀራረብ በክፍል ውስጥ የመምህሩ ሚና ምን መሆን አለበት? ለሚለው Richard /1990፤ 12/ እንደሚከተለው ዘርዝረዋቸዋል:: መምህሩ፤

- ተማሪዎች በመማር ሂደት የሚያደርጉትን ይቆጣጠራል፤
- ለተማሪው ረዳት ነው፤
- ትክክለኛውን የመማሪያ ሞዴል ተግባራዊ ያደርጋል፤
- ለተማሪው አመራር ሰጪ ነው፤
- የተማሪውን ፍላጎት አሳሽ ነው፤
- ለተማሪዎች አጋዥ የሆኑ የማስተማሪያ መሣሪያዎችን አቅራቢ ነው፤
- ገምጋሚ ነው፤

2.2.3.3 በተራክቧዊ አቀራረብ በክፍል ውስጥ የተማሪው ሚና

የመማር ማስተማሩን ሂደት በክፍል ውስጥ ከተፈለገው ግብ ለማድረስ የተማሪው ሚና ምን መሆን አለበት? ተማሪዎች በትምህርት ፕሮግራሙ ተሳታፊዎች በመሆናቸው በክፍል ውስጥ በመማር ማስተማር ሂደት ወቅት የሚጠበቅባቸው ተግባር ምንድን ነው? ለሚለው Richard /1990፣ 13/ በክፍል ውስጥ የተማሪው ሚና መሆን ያለበትን እንደሚከተለው ዘርዝረዋል::

- በቅድሚያ ለመማር ራሱን ዝግጁ ማድረግ፣
- በክፍል ውስጥ እንዲያከናውን የተሰጠውን ጉዳይ /Task/ ከመጽሐፉ፣ ከጓደኛውና ከመምህሩ ጋር በመተጋገዝ ማከናወን፣
- በውይይት ወቅት ኃላፊነትን በመውሰድ በንቃት መሳተፍ፣

በማለት ገልጸዋል::

2.2.4 በተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል ተጠቅሞ ማስተማር ያሉት አሉታዊ ጎኖች

በተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል ተጠቅሞ አንብቦ የመረዳት ክሂል በክፍል ውስጥ ለማስተማር መሞከር ሊኖሩ የሚችሉትን አሉታዊ ጎኖች Eskey /in Carrell, Devine and Eskey 1988፣ 228/ እንደሚከተለው ጠቁመውናል::

- ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴሎች ሃሣባዊ /ideal/ በመሆናቸው ሙሉ በሙሉ እምነት ሊጣልባቸው የሚችሉ ዓይነት አይደሉም::
- ሁሉም ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴሎች ሲፈለሰፉ በጎበዝ አንባቢና በደካማ አንባቢ መካከል በተደረገው ንጽጽር ሲሆን ፍጹም ጎበዝ ወይም ፍጹም ደካማ የሚለው ነገር ረቂቅ በመሆኑ መቶ በመቶ ይህ ጎበዝ ነው ይህ ደግሞ ደካማ ነው የሚለውን አያሳይም በማለት እነዚህን ደካማ ጎኖች እያሰብን ተግባራዊ ማድረግ እንዳለብን ይመክሩናል::

ስለዚህ ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል ለመጠቀም ኃላፊነቱ የመምህሩ ብቻ ሳይሆን የመርሀ ትምህርት አዘጋጆች፣ የመማሪያ መጽሐፍ አዘጋጆች እንዲሁም

ተማሪውም ኃላፊነት እንዳለበት መታወቅ ያለበት መሆኑን እነዚህ ምሁራን ጨምረው ገልጸዋል። ይህ ጥናትም እነዚህን ደካማ ጎኖች ግምት ውስጥ በማስገባት ሞዴሉን በክፍል ውስጥ በመጠቀም የንባብ ክሂል ትምህርትን ተግባራዊ ለማድረግ ሞክሯል።

እስካሁን በዚህ ምዕራፍ የተመለከትነው ስለ አንብቦ መረዳት ምንነት፣ በተለይም ለትምህርት የቀረበው ቋንቋው ኢአፍ መፍቻ ቋንቋ ለሆኖቸው ተማሪዎች አንድን ጽሑፍ አንብቦ ለመረዳት ያለባቸውን መሠረታዊ ችግሮች፣ እነዚህን መሠረታዊ ችግሮች ለማቃለል የተራክቧዊ የንባብ ብሂል ማስተማሪያ ሞዴል ያለውን አስተዋጽኦ እና ከተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል አንጻር ይዘቶች በምን ሁኔታ በክፍል ውስጥ ይቀርባሉ? የክፍል ውስጥ ክንውኑ ምን መሆን አለበት? የሚሉትን ነው።

ምዕራፍ ሦስት

የአጠናኑ ዘዴ /Methodology/

ይህ ጥናት የተከተለው የአጠናን ዘዴ ፍትነታዊ የምርምር ዘዴ /Experimental Method/ ነው። አጥኚው ጥናቱን ለማከናወን ሁለት ቡድኖች ያሉት ሲሆን አነሱም ጥብቅ ቡድን /Control Group/ እና ተጠኚ ቡድን /Experimental Group/ ናቸው። አጥኚው መረጃውን ለማሰባሰብ የተጠቀመባቸው መሣሪያዎች ቅድመ- እና ድህረ /pre test/ /post-test/ ትምህርት ፈተናዎች ናቸው። ፈተናዎቹ ለሁለቱም ቡድኖች የተሰጡ ሲሆን የቅድመ-ትምህርት ፈተና ዓላማው በጥብቅ ቡድኑ /Control Group/ እና በተጠኚ ቡድኑ /Experimental Group/ መካከል ያለ የችሎታ ተመጣጣኚነት መኖሩን ለመለካት ነው። የድህረ ትምህርት ፈተና ዋና ዓላማው ተጠኚ ቡድኑ በተራክቧዊ መካክስ ሞዴል አንባር በተዘጋጀ የንባብ ክሂል ትምህርት በመማሩ ምክንያት ያመጣው የባሕሪ ለውጥ አለ? የሚለውን ለመለካትና የተገኘውን የባሕሪ ለውጥ በ"t" ቴስት ለክቶ የተገኘውን ውጤት በእስታትስቲካዊ መረጃ ሰብስቦ ውጤቱን አስልቶ ለመድረስ ነው።

አጥኚው ለሁለቱ ቡድኖች የቅድመ ትምህርት ፈተና ከሰጠ በኋላ የሁለቱም ቡድኖች አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር ይችሉ ዘንድ በ1984 ዓ.ም ታትሞ የወጣውን የ11ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ውስጥ የተካተተውን አንብቦ የመረዳትን ክሂል አጠቃላይ ዓላማ መሠረት በማድረግ ከተማሪዎች ችሎታና ፍላጎት ጋር በተመጣጠነ ሁኔታ ተመሣሣይ ይዘቶችን አዘጋጅቶ ለአምስት ተከታታይ ሳምንታት ለጥብቅ ቡድኑ በጥንታዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ /bottom-up/ ለተጠኚ ቡድኑ ደግሞ በዘመናዊ የቋንቋ መማር ንድፈ ሃሣብ በተደገፈው ተራክቧዊ መካክስ ሞዴል /interactive Compensatory Model/ መሠረት ክንውኖችን አዘጋጅቶ ካስተማረ በኋላ ለሁለቱም ቡድኖች አንድ ዓይነት ድህረ-ፈተና /post-test/ ሰጥቷል።

3.1 የትምህርት ቤትና የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

3.1.1 የትምህርት ቤት አመራረጥ

የዚህ ጥናት መነሻ «በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች አማርኛን እንደ ኢአፍ መፍቻ ቋንቋ ሲማሩ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር ተራክቦአዊ መካከስ /Interactive Compensatory Model/ አስተዋጽኦ ይኖረዋልን?» የሚለውን ለመመለስ ነው:: ይህንን ጥናት ለማከናወን የብድግ ብድግ ስልት /simple random sampling/ ተጠቅሞ ጥናቱን ተግባራዊ ለማድረግ አስቸጋሪ ሆኖ በመገኘቱ ጥናቱ የሚካሄድበት ቦታ፣ የትምህርት ቤት አመራረጥና የክፍል መረጣ ምቾት ናሙና convenience sampling Nachmies /1994፣ 175/ መጠቀም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የምቾት ናሙና አመራረጥ ተግባራዊ ሆኗል:: አጥኚው፣ ጥናቱ የሚካሄድበትን ቦታ፣ ትምህርት ቤት እና ክፍል ለምን እንደመረጠው በምዕራፍ አንድ የጥናት ወሰን በሚለው ላይ በዝርዝር ገልጿል::

3.1.2 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

የተማሪዎች መረጣ የተካሄደው በብድግ ብድግ ስልት /simple random sampling/ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ነው:: በዚህ ዘዴ በአዳባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህር ቤት ከሚገኙት የአሥራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ብቻ በጥናቱ እንዲካተቱ ተደርጓል:: አጥኚው በጥናቱ ውስጥ ሁሉንም ጾታ ያካተተ ሲሆን መረጣው በአዳባ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የኦሮምኛ ቋንቋ መምህር አጋዥነት እና የትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪ በሰጠው የተማሪዎች የግል ማኅደር አማካኝነት ተካሂዷል:: አመራረጡ በመጀመሪያ የ11ኛ ክፍል በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በፊደል ተራ ቅደም ተከተል ከተመዘገቡ በኋላ ሶስት፣ ሶስት በመዝለል ከ200 ተማሪዎች ውስጥ 50 ተማሪዎች ተመርጠዋል:: ይህም በፐርሰንት ሲሰላ 25% ይሆናል:: ሃምሣዎች የአጠቃላይ ተጠኚዎች ቁጥር ሲሆን እንደአመራረጣቸው ቅደም ተከተል በስም ተራ ከተመዘገቡ በኋላ በሙሉ ቁጥርና በጎዶሎ ቁጥር እኩል በመክፈል እያንዳንዱ ቡድን 25 አባላት እንዲያካትት በዕጣ ጥብቅ ቡድንና /Control Group/ ተጠኚ /Experimental Group/ ተብለው በመሰየም/ ተከፍለዋል:: —

3.2 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

3.2.1 የማስተማሪያ መሣሪያዎች ዝግጅት

ለተጠኚ ቡድኑም ሆነ ለጥብቅ ቡድኑ አንብቦ የመረዳት ክሂሉን አጠቃላይ ዓላማ በጥናቱ ዘዴ መግቢያ ላይ በተጠቀሰው መርሃ-ትምህርት መሠረት ከቋንቋ ንድፈ ሃሣብና ከሥነ ማስተማር ዘዴ /Pedagogical Principles/ መርሕ አንፃር ከንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴሎች ዓይነትና ባሕሪ ጋር ተስማሚ የሆኑ /ምንባቦች/ ተመርጠው በምንባቦች መሠረት የተለያዩ ይዘቶች ተዘጋጅተዋል::

ለጥብቅ ቡድኑ /Control Group/ የተዘጋጀው የማስተማሪያ መሣሪያ ይዘት /መልመጃዎችና ክንዋኔዎች/ ከቋንቋ ንድፈ-ሃሣብ መዋቅራዊ ሥነ-ልሣን፤ ከማስተማር ንድፈ-ሃሣብ ደግሞ የባሕሪያውያንን መርህ ተከትሎ ከተቀረጸው የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል ጋር /bottom-up approach/ በተጣጣመ ሁኔታ ነው::

ለተጠኚ ቡድኑ /ምንባቦች/ ከተጠኚ ቡድኖች ጋር ተመሣሣይ ሲሆኑ መልመጃዎችና ክንዋኔዎች ግን በተለየ ሁኔታ የማኅበራዊ ሥነ ልሣንን መርህ ተከትለው የተዘጋጁ ናቸው:: ለተጠኚ ቡድኖች ይዘቶችና ክንውኖች የ11ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርትን /1984 ዓ.ም/ መሠረት በማድረግ ምንባቦች ደግሞ Wallace /1992፤ 71/ Nuttall /1996፤ 170/ የሚያስቀምጧቸውን መለኪያዎች ግምት ውስጥ በማስገባት ተመርጠዋል::

3.2.1.1 ለጥብቅ ቡድኑ /Control Group/ ከጥንታዊ የንባብ ክሂል የማስተማሪያ ሞዴል አንፃር የማስተማሪያ መሣሪያዎች አዘገጃጀት ዘዴ

በ1950ዎቹ አካባቢ በቋንቋ ጥናት ላይ በከፍተኛ ሁኔታ ተሰሚነት የነበራቸው መዋቅራዊ ሥነ-ልሣን አራማጅ የሆኑት Fries /1963/ and Lado /1964/ ለንባብ ትምህርት ትኩረት መሰጠት አለበት የሚሉት ለጽሑፉ አጻጻፍ እንጂ አንባቢው ለምን ጉዳይ ያነበዋል? ምን ዓይነት የአነባበብ ስልት ይጠቀም? ከጽሑፉ ውስጥ የሚፈልገው ነገር ምንድን ነው? ለሚለው እንዳልሆነ Carrell, Devine and Eskey /1988፤ 2/ ገልጸዋል:: Lado /1964፤ 135/ ለንባብ ትኩረት መሰጠት አለበት የሚሉት ለተጻፈው ነው:: ይህም በመሆኑ የንባብን ክሂል ለማስተማር ትኩረት መሰጠት ያለብን የሚሉት ተማሪው የተጻፈውን ጽሑፍ በፍጥነት አንብቦ እንዲረዳው ለማድረግ ፊደላትን አቀናጅቶ በፍጥነት እንዲያነብ፤

ማድረግ፣ በከፍተኛ ሁኔታ ለቃላት ትኩረት መስጠት እንዲሁም ለስዋሰው ትኩረት መስጠት አስፈላጊ ነገሮች ናቸው በሚለው ነው::

ጥንታዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል የሚከተለው የተነጣጠሉ ክሂሎችን በማስተማር ላይ የተመሠረተ መሆኑንና ትኩረታቸው ምን እናስተምር? በሚለው እንጂ እንዴት እናስተምር ለሚለው እንዳልሆነ Wallace /1992፣ 54/ ያስረዳሉ::

እንደ Lado /1994/, እና Fries /1963/ አቋም አንብቦ የመረዳት ክሂል የሚዳብረው ተማሪው በፍጥነት ሲያነብ ነው:: ለዚህም ሲባል ትኩረት መስጠት ያለበት ተማሪው በክፍል ውስጥ ጮክ ብሎ እንዲያነብ ማለማመድ፣ ከጽሑፉ ውስጥ ተማሪው ተውላጠ ስሞችን፣ የተለያዩ ሃረጎችን፣ የወከሉትን እንዲፈልግ የሚያደርጉ ይዘቶች ማዘጋጀት፣ አዳዲስ ቃላትን ትርጉማቸውን ከመዝገበ ቃላት እንዲፈልግ፣ በአዳዲስ ቃላት ላይ ዓረፍተ ነገር እንዲሠራ የሚያደርጉ ይዘቶች እንዲዘጋጅ ይመክራሉ:: በአጠቃላይ እንደ Lado /1964/ Fires /1963/ የንባብ ትምህርት ማለት ተማሪው የተጻፈውን ጽሑፍ በፍጥነት አንብቦ መረዳት ነው:: ፈጣን አንባቢ ጽሑፉን በቀላሉ ይረዳዋል:: ፍጥነት ላለው አነባበብ ደግሞ ወሳኙ ተማሪው ድምጾችን አቀናጅቶ በፍጥነት እንዲያነብ በክፍል ውስጥ ተከታታይ የሆነ የቃል ንባብ፣ የቃላት ትምህርትና የስዋሰው ይዘቶችን መስጠት አስፈላጊ መሆኑን እንደሚቀበሉት Eskey and Grabe /in Carrell, Devine and Eskey 1988፣ 230/ ይገልጹልናል::

አጥኚው Lado /1964/, Fries /1963/ Mackey /1965/ Schester /1977/ እና ሌሎችንም መሠረት በማድረግ ለጥብቅ ቡድኑ ይዘቶችን አዘጋጅቷል:: ፍጥነታቸውን እንዲያሻሽሉ በከፍተኛ ሁኔታ ትኩረት የተሰጠው በተራ ጮክ ብለው እንዲያነቡ ነው:: ከዚህም በተጨማሪ ተማሪው በሚያነብበት ጊዜ ፊደላትን አቀናጅቶ ቃላት ከመሠረተ በኋላ ሃረጎችን አዋቅሮና ዓረፈተ ነገር መስርቶ በትክክል ማንበቡን በመቆጣጠር ነው:: ተማሪው በሚያነብበት ጊዜ ስህተት ከፈጸመ አጥኚው የቃሉን ትክክለኛ አነባበብ ይናገራል::

ለጥብቅ ቡድኑ የቀረቡት ምንባቦች ከተጠኚ ቡድኑ ጋር ተመሣሣዮች ሲሆኑ ምንባቦቹን መሠረት በማድረግ የሚመለሱ ጥያቄዎች ከምንባቦቹ በኋላ ተዘጋጅተዋል:: ጥያቄዎች ተማሪው ጽሑፉን በትክክል መረዳቱን ለመገምገም ክፍት ጥያቄዎች /open-ended/ እና የምርጫ ጥያቄዎች /closed ended/ በምንባቡ መሠረት ተማሪው ከምንባቡ ሳይወጣ ትክክለኛው የቋንቋ ሥርዓት ጠብቆ እንዲመልሳቸው የተዘጋጁ ናቸው:: ጥያቄዎች እንዴት እንደሚዘጋጁ Schester /1977/, Macky /1965፣ 134/ እና Lado /1964/ በዝርዝር

ገልጸዋል:: አጥኚው የተጠቀሱትን ምሁራን አዘገጃጀት መሠረት በማድረግ ይዘቶችን አዘጋጅቷል:: ስለ አዘገጃጀቱ አባሪ ሀ2 ያለውን የማስተማሪያ መሣሪያ መመልከት ይቻላል::

3.2.1.2 ለተጠኚ ቡድኑ /Experimental Group/ ከተራክቦአዊ መካከስ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል አንፃር የማስተማሪያ መሣሪያዎች አዘገጃጀት ዘዴ

በዚህ ምዕራፍ ገጽ 33 ላይ እና በተዛማጅ ጽሑፉ ገጽ 23 - 28 እንደተገለጸው በተለይም ከ1970ዎቹ ወዲህ ማኅበራዊ ሥነ-ልሣን /Socio-linguistics/ በቋንቋ ትምህርት ላይ ተጽእኖ እያሳደረ በመምጣቱ ቀደም ሲል የነበረው የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ እየተለወጠ መጣ:: የማኅበራዊ ሥነ-ልሣን አራማጆች የቋንቋ ዓላማ መግባባት ነው ከሚለው አጠቃላይ መርህ በመነሣት የቋንቋ ትምህርትም መሆን ያለበት ከቋንቋው ሥርዓት ባሻገር በመሄድ ተማሪው በክፍል ውስጥ የማህበረሰቡ የሚጠቀምበትን የቋንቋ አጠቃቀም ሥርዓት ጭምር መልመድ አለበት:: በአጠቃላይ የቋንቋ ትምህርት ዓላማ መሆን የአለበት ተማሪው ተግባቦታዊ ችሎታውን ማሳደግ ነው:: በዚህ አጠቃላይ መርህ መነሻነት ቋንቋን በክፍል ውስጥ ከሥርዓቱ ባሻገር አጠቃቀሙን ጭምር ከማኅበራዊ አውድ /social context/ ጋር በማዋሃድ በክፍል ውስጥ ማስተማር ከተጀመረ ብዙ ጊዜያትን አስቆጥሯል::

ከቋንቋ ክሂሎች ውስጥ አንዱ የሆነው የንባብን ክሂል ለማስተማር በተለያየ ጊዜ ከቋንቋ ንድፈ- ሃሣቦችና የመማር ንድፈ-ሃሣቦች ጋር በተያያዘ ሁኔታ አንብቦ የመረዳትን ክሂል ለማዳበር ሲባል የተለያዩ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴሎች ተፈልስፈዋል:: ዝርዝር ጉዳዩን ከተዛማጅ ጽሑፉ ከገጽ 14 - 17 ማግኘት ይቻላል:: ቀደም ሲል በዚህ ጥናት ለጥብቅ ቡድኖች አንብቦ የመረዳትን ክሂል ማስተማሪያነት ተግባራዊ የሆነው ውጤት ተኰር ሞዴል /bottom-up/ ሥነ-መዋቅራዊ ሥነ-ልሣንን መሠረት አድርጎ በመፈልሰፉ ይዘቱ ፍጹም በጽሑፉ ላይ ብቻ እንዲመሠረት መደረጉ ቀደም ሲል በተለያዩ ገጾች ተገልጸዋል::

የቋንቋ ንድፈ-ሃሣብ ከመዋቅራዊ ሥነ-ልሣን ወደ አእምሮአዊ ሥነ-ልሣን /Psycholinguistic/ ሲቀየር የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴልም ፍጹም ጽሑፍን መሠረት አድርጎ የንባብን ክሂል ማስተማር የሚለውን በመተው ከጽሑፍ የተወሰኑ ናሙናዎች አንባቢው በመውሰድ የራሱን አእምሮአዊ እውቀት /background knowledge/ ተጠቅሞ አንብቦ የመረዳት ክሂሉን እንዲያዳብር ሲባል ሂደት ተኮር /process/ የሆነው የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል /top-down/ በGoodman /1967/ እንደተፈለሰፈ ተመልክተናል፤ ነገር ግን ለትምህርት የቀረበው ቋንቋ ለተማሪው ኢአፍ-መፍቻ ቋንቋ ከሆነው ባለበት ሥነ-

ልሣናዊ ችግርና የቋንቋውን ተናጋሪ ሕብረተሰብ ባሕልና ወግ በትክክል ለይቶ አለማወቅ ምክንያት ፍጹም ውጤት-ተኮር ወይም ፍጹም የሆነ ሂደት-ተኮር የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴልን ተከትሎ ለማስተማር መሞከር ችግሩን ለማቃለል ባለመቻሉ ምክንያት ውጤት-ተኮርንና ሂደት-ተኮርን በማቀላቀል ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል እንደተፈለሰፈ ተመልክተናል። ምንም እንኳ ከአምስት የማያንሱ የተለያዩ ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴሎች ቢኖሩም፤ ለተጠኚ ቡድኑ የተዘጋጀው የማስተማሪያ መሣሪያ ከተራክቦአዊ ሞዴሎች ውስጥም Stanovich /1980/ ተራክቦአዊ መካክስ ሞዴልን /Interactive Compensatory Model/ መሠረት አድርጎ የተዘጋጀ ነው። Stanovich የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል ለዚህ ጥናት ለምን እንደተመረጠ ዝርዝር ጉዳዩን ከተዛማጅ ጽሑፉ ከገጽ 20 እስከ 21 መመልከትና መረዳት ይቻላል።

ተራክቦአዊ የንባብ ክሂል ሞዴልም ንባብን በክፍል ውስጥ ለማስተማር ከተማሪው ችሎታ፣ ፍላጐትና አመለካከት እንዲሁም ከሚኖርበት አካባቢ ጋር የተንሰላሰለ ምንባብ በመምረጥ ይዘቶቹ በተለያየ ስልት ተማሪው እንዲያከናውናቸው ሆነው መቅረብ ያለባቸው መሆኑን Wallace /1992፣ 42/ Carrell, Devine and Eskey /1988፣ 96/ Brown /1994/ እና ሌሎችም ያሉትን መመልከት ይቻላል።

ለተጠኚ ቡድኑ የተዘጋጀው የማስተማሪያ መሣሪያ የሚጀምረው ከቅድመ ንባብ ደረጃ ነው። በዚህ ደረጃ ተማሪው ምንባቡን ከማንበቡ በፊት ስለምንባቡ የሚያውቀውን ነገር ሁሉ በቡድን በመወያየት እንዲናገር የተወሰኑ ይዘቶች በክፍት ጥያቄዎች አማካኝነት ቀርበውለታል። በዚህ ደረጃ የተዘጋጁት ይዘቶች ተማሪው ስለ ርዕሱ የሚያውቀውን ሁሉ እንዲናገር /Brainstorming/ አቀራረብ ስልትን መሠረት አድርጎ ተዘጋጅቷል።

ከቅድመ ንባብ ትምህርት በኋላ በንባብ ደረጃ ተማሪው የተለያዩ የአነባበብ ስልቶች በመጠቀም ስለምንባቡ አጠቃላይ ግንዛቤን ለማስጨበጥ ሲባል ይዘቶች ቀርበዋል። በገረፍ ገረፍ ስልት /skimming/ የአነባበብ ስልትን በመጠቀም ስለ አንቀጾች ተናጠላዊ መልዕክት ስለ ምንባቡ አጠቃላይ መልዕክት እንዲናገር የሚያግዙ ይዘቶች እንደ ትንበያ /predicting/፣ በማስተማሪያ መሣሪያነት የቀረበውን ምንባብ የተወሰኑ ቃላትን በመዝለል ባዶ ቦታ በመተው ከራሱ በማመንጨት እንዲሞላ /cloze procedure/ ለማስተማሪያ መሣሪያነት የቀረበውን ምንባብ አንቀጾችን በማዛባት የተዛባውን እንዲስተካክል /rhetorical organization/ ሲባል Nuttall /1996፣ 157-160/, እና ሌሎችንም መሠረት በማድረግ ተዘጋጅቷል።

በዚሁ የንባብ ደረጃ ተማሪው የአሰሳ /scanning/ የንባብ ስልቱን እንዲያዳብር ሲባል ስሞችን፣ ቁጥሮችንና ዓመተምህረቶችን ከጽሑፉ እንዲፈልግ የቃላትን ተመሣሣይና ተቃራኒ እንዲፈልግ፣ ተውላጠ ስሞችን እያለየ እንዲያወጣ ይዘቶች ተዘጋጅተዋል። በቅድመ ንባብ ትምህርት ተማሪው የተለያዩ የአነባበብ ስልቶችን ተጠቅሞ አጠቃላይ ግንዛቤውን ካዳበረ በኋላ ወደ ትክክለኛ ግንዛቤ ደረጃ ለማድረስ ደግሞ ጽሑፉን መሠረት በማድረግ ብቻ የሚመለሱ ይዘቶች ተዘጋጅተውለታል። እነዚህ ይዘቶች ተማሪው ምንባቡን በትክክል መረዳቱን /accuracy/ ለመፈተሽ ሲባል የቀረቡ ይዘቶች ናቸው። ይዘቶቹ በጥያቄ መልክ የቀረቡ ሲሆን ተማሪው ረጋ በማለት በጥልቀት ጽሑፉን ደግሞ ደጋግሞ ካነበበ በኋላ እንዲመልሳቸው የተዘጋጁ ናቸው። በዚህ ደረጃ የተካተቱት ይዘቶች ተማሪው ቀደም ሲል በቅድመ-ንባብ ደረጃ ትርጉማቸውን እንዲናገር ተጠይቆ ያላወቃቸውን ቃላት እንዲያውቃቸው ሲባል አውዳዊ ፍቻቸውን፣ ተውላጠ ስሞች የተኳቸውን ቃላት፣ ሃረጎች፣ እና ዓረፍተ ነገሮችን ከምንባቡ ፈልጎ ተማሪው እንዲያወጣ፣ ፀሐፊው በጽሑፉ ውስጥ አንዳንድ ቃላትን ከመደበኛ ፍቻቸው ባሻገር ሌላ ፍቺ ያስያዛቸውን ቃላት ከአውዳዊ አገባባቸው አንፃር ፍቻቸውን እንዲናገር፣ ደራሲው በጽሑፉ ውስጥ የተጠቀመባቸው የተለያዩ የቋንቋ አጠቃቀሞችን ተማሪው እንዲለይ የሚጠይቁ ናቸው።

በሶስተኛ ደረጃ በማስተማሪያ መሣሪያነት የቀረቡ ይዘቶች በድህረ-ንባብ /post-reading/ ደረጃ የቀረቡ ይዘቶች ናቸው። በዚህ ደረጃ ይዘቶች በጥያቄና መልስ የተዘጋጁ ሲሆን ዓላማቸውም ተማሪው ከምንባቡ ውስጥ ያገኘውን አዲስ እውቀት ቀደም ሲል ካለው እውቀት ጋር በማገናኘት እውነታውን ከአካባቢው እውነታ ጋር በማገናኘት እንዲገመግመው ለማድረግ ነው። ይዘቶቹን መሠረት አድርገው የተዘጋጁት ፀሐፊው በጽሑፉ ውስጥ መልዕክቱን ለማስተላለፍ ሲል የተጠቀመባቸው የተለያዩ የቋንቋ አጠቃቀሞችን፣ የደራሲውን አመለካከት፣ ፍላጎትና ስሜትን የሚጠቁሙ አገላለጾችን ተማሪው ለይቶ በማውጣት በቡድኑ አማካኝነት እንዲወያይባቸው ሲባል የቀረቡ ናቸው።

3.2.2 የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ክንውን /Methodology/ አቀራረብን በተመለከተ

3.2.2.1 ለጥብቅ ቡድኑ በውጤት ተኮር ስልት የክፍል ውስጥ የመማር-ማስተማር ክንውን አቀራረብ

በጥንታዊ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ክንውን አቀራረብ የቋንቋ መሰሎችን መደጋገም /drilling/፣ በቃል ማጥናትና ትምህርቱን መምህሩ ሲገልጽ ተማሪው ፀጥ ብሎ ማዳመጥ ዓይነተኛ የማስተማሪያ ዘዴ እንደሆነ Brown /1994፣

1/, Nuttall /1996፣ 162/, Lado /1964፣ 134/ Reichard and Rodgers /1984፣ 58/ እና ሌሎችም ይነግሩናል::

ከዚህ አንፃር አጥኚው ለጥብቅ ቡድኑ የተከተለው የክፍል ውስጥ ክንውን እንደሚከተለው ነው:: አጥኚው ለጥንታዊ የንባብ ማስተማሪያ ዘዴ በLado /1964፣ 134/ መነሻነት ሲሆን በመጀመሪያ አጥኚው በፍጥነት በግል /በለሆሳስ/ የአነባበብ ስልት እንዲያነቡ አድርጓል:: ይህ ፊደላትን ለመለየት እና በፍጥነት የማንበብ ልምድ እንዲመሠረቱ ለማድረግ ነው:: ከዚህ በመቀጠል ተማሪው ለሌሎች ጓደኞቹ ጮክ ብሎ እንዲያነብ ተደርጓል:: ይህ ደግሞ ተማሪው በሚያነብበት ጊዜ የትኞቹን ፊደላትና ቃላት ለማንበብ እንደተቸገረ ለማወቅ አጥኚውን እንዲረዳው ነው:: ሁለተኛው ተማሪው ፊደላትን አቀናጅቶ፣ በትክክል ቃላትን መስርቶ፣ ሃረጋትን ካዋቀረ በኋላ ዓረፍተነገሮችን አገጣጥሞ ማንበቡን ለመቆጣጠር ነው:: አንዱ ተማሪ ጮክ ብሎ ሲያነብ ከተሳሳተ አጥኚው ጣልቃ እየገባ አስተካክሏል:: ምክንያተቱም Nuttall /1996፣ 167/ እንደሚሉን መምህርን ያማከለ የክፍል ውስጥ ክንውን በመምህሩ ጣልቃገብነት የሚከናወን ስለሆነ ነው:: በተጨማሪም ተማሪው ጮክ ብሎ በሚያነብበት ጊዜ ሌላው በፀጥታ እንዲያዳምጥ ተደርጓል::

በአራተኛ ደረጃ አጥኚው ከምንባቡ ውስጥ አስቸጋሪ ናቸው ያላቸውን ቃላት፣ ሃረጎች እና ዓረፍተ ነገሮች ፈልጎ በማውጣት የቃሉን፣ የሀረጉን፣ እና የዓረፍተነገሩን ዓይነት፣ አወቃቀርና ፍች በተመለከተ ገለጻ አድርጓል:: በዚህ ወቅት የተማሪው ተግባር በፀጥታ ማዳመጥ ነው::

በመጨረሻም በምንባቡ መሠረት የተዘጋጁትን ጥያቄዎች በግል እንዲሠራቸው የክፍል ሥራና የቤት ሥራ ተሰጥቷል:: መምህሩ ተማሪው በተሰጠው ምንባብ መሠረት ሳይጨምር ወይም ሳይቀንስ የቋንቋው ስዋሰዋዊ ሥርዓትን ጠብቆ መሥራቱን በመቆጣጠር ታርሟል:: በመጨረሻም የጥያቄዎችን መልስ ተማሪው እየተነሣ እንዲናገር ተጋብዟል:: ተማሪው የተናገረው መልስ ትንሽ ስህተት ካለበት አጥኚው አስተካክሏል:: አጥኚው የተናገረው መልስ ምንጊዜም እንደ ትክክለኛ መልስ በመውሰድ ተማሪው እርማት እንዲወስድ ተደርጓል::

3.2.2.2 ተጠኚ ቡድኑን በክፍል ውስጥ አንብቦ የመረዳትን ክሂሉን ለማዳበር ከተራክቧዊ መካከስ ሞዴል አንፃር በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ክንውን አቀራረብ ዘዴ

ቀደም ሲል በመግቢያው ላይም ሆነ በተዛማጅ ጽሑፉ እንደተጠቀሰው ንባብ ማለት አንባቢው ከጽሑፉ ውስጥ ያገኘውን ሐሣብና የራሱን የቀደምት አእምሮአዊ እውቀት በሂደት አገናኝቶ ከጽሑፉ የሚፈልገውን ጉዳይ እንደሚፈልገው ሁኔታ ተስማሚውን የአነባበብ ስልት ተጠቅሞ ጽሑፉን በሂደት መረዳት ማለት እንደሆነ አንስተናል። አንባቢው ከተጻፈው ውስጥ የሚፈልገውን ነገር ለማግኘት ሲል የራሱን የአነባበብ ስልት ተጠቅሞ ያነባል።

አጥኚው ለጥናቱ የተከተለው የንባብ ክሂል ትምህርት በአብዛኛው ምሁራን የሚከተሉትን የስልተ-ተኮር ትምህርት ነው። Cellce Murcia /1991፣ 261/ እንደሚሉት በየወቅቱ የሚፈለሰፉት የሁለተኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች አንዱ ከአንዱ የተሻለ አይደለም። ይበልጡን ትኩረት መስጠት ያለብን ለቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች ሣይሆን ተማሪው በክፍል ውስጥ ለሚያከናውናቸው ተግባራት መሆን እንዳለበት አጥብቀው ይመክራሉ። Brown /1984፣ 159/ በተመሣሣይ ሁኔታ ተማሪው ቋንቋን ከማህበራዊ አውድ ጋር በተቆራኘ ሁኔታ በክፍል ውስጥ በተፈጥሯዊ ሁኔታ ተማሪው ከመጽሐፉ፣ ከጓደኛው እና ከመምህሩ ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ወይም ተራክቦ እንደሚያሳድገው ይገልጻሉ። የዚህ ጥናት የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴልም የሚከተለው ቢኖር ተማሪው ከጽሐፉ፣ ከጓደኛው እና ከመምህሩ ጋር የተለያዩ የአነባበብ ስልቶች በመጠቀም በሚያደርገው ተራክቦ ማለትም ሃሣብ በመለዋወጥ ጽሑፉን በቀላሉ ሊረዳው ያስችለዋል የሚለውን ነው። ለጥናት የቀረበው የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል የተሰጠው ስያሜ «ተራክቦ» የሚል ሲሆን የሚያጎለብተውም በክፍል ውስጥ የሚደረገውን የርስ በርስ ተራክቦ ነው። ከBrown /1994/ እንደምንረዳው በንባብ ሂደት ወቅት አንባቢው የራሱን የአነባበብ ስልትን የተጠቀመ ጽሑፉን ለመረዳት ሲያነብ የተለያዩ አእምሮአዊ የእውቀት ምንጮች /sources of knowledge/ በአንባቢው አእምሮ ውስጥ ተራክቦ በማድረግ ጽሑፉን እንዲረዳው እንዳስቻሉት ሁሉ ተማሪው በክፍል ውስጥም ከመጽሐፉ ከጓደኛውና ከመምህሩ የተለያዩ የአነባበብ ስልቶችን እየተጠቀመ በሚያደርግው ተራክቦ አንብቦ የመረዳት ክሂሉን በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲያዳብር ያስችለዋል። በክፍል ውስጥ የሚደረገው የእርስ በርስ ተራክቦ ደግሞ አንባቢውን የተለያዩ የአነባበብ ስልቶችን ለክፍል ውስጥ እንዲያዳብር ያደርገዋል። እነዚህ የአነባበብ ስልቶች ደግሞ ክሂሎችን በማጣመር አንባቢው የቀረበለትን ጽሑፍ በአነስተኛ ጊዜና ጉልበት የሚፈልገውን ነገር ከጽሑፉ እንዲገነዘብ ያስችሉታል።

እንደ Brown /1994፣ 177/ የክፍል ውስጥ ተራክቦ ዓይነተኛው መሣሪያ ቡድን እንደሆነ ገልጸዋል። ከBrown /1994/ Nuttall /1996፣ 162/ በመነሣት አጥኚው ተጠኚ

ቡድኑን በስድስት ንዑሳን ቡድኖች መድቧል። እያንዳንዱን ቡድን 4 አባላት ሲኖሩት ሁሉንም ጾታ ያካተተ ነው። ሁሉም የቡድኑ አባላት በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ስለሆነ አጥኚው የተለየ አመዳደብ አልተጠቀመም። እያንዳንዱ ቡድን አንድ የቡድን መሪ እንዲኖረው ተደርጓል። ለእያንዳንዱ የቡድን አባል የተለያዩ ይዘቶችን እንዲያከናውናቸው ሲባል "Worksheet" በአጥኚው ተዘጋጅቶ ተሰጥቶታል።

በ"Worksheet" የተዘጋጁት ይዘቶች የሚጀምሩት ከቅድመ-ንባብ ደረጃ ነው። ለቅድመ-ንባብ ደረጃ ይዘቶች የተዘጋጁት ጥያቄዎች /open-ended/ ሲሆኑ አጠያየቃቸውም በBrainstorming ስልት ነው። ተማሪው በዚህ ወቅት በቡድኑ አማካኝነት በጥያቄዎች ላይ እየተወያየ የሚያውቀውን ሁሉ ከውይይቱ በኋላ ለአጥኚው ይናገራል። በዚህ ወቅት አጥኚው የማስተካከያ መልስ አይሰጥም፣ በ"Brainstorming" ስልት አቀራረብ መምህሩ ጣልቃ በመግባት ማስተካከል የሌለበት መሆኑን በWallace /1992፣ 92/ ተገልጿል።

ከቅድመ ንባብ ትምህርት በኋላ ተማሪው በቀረበለት ምንባብ ላይ አጠቃላይ ግንዛቤ እንዲኖረው ሲባል ከምንባቡ ስሞችን፣ ቁጥሮችንና ዓመተ ምህረቶችን የቃላትን ተመሣሣይና ተቃራኒ ከምንባብ እየፈለገ እንዲያወጣ ለማድረግ የአሰሳ የአነባበብ ስልት በጥንድና በግል እንዲያከናውንና ስለምንባቡ፣ አጠቃላይ ሃሣብ እንዲኖረው ለማድረግ ደግሞ በገረፍ ገረፍ ስልት እንዲያነብ ተደርጓል። አጥኚው ተማሪው አጠቃላይ ግንዛቤውን ለማስፋት የStenfferን /in Carrell, Devine and Eskey 1988፣ 248/ DRTA* የክፍል ውስጥ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴን ተጠቅሟል። አጥኚው ከዚህም በተጨማሪም Anderson /in Carrell, Devine and Eskey 1988፣ 248/ መሠረት በማድረግ መስመራዊ ሥዕልን /flow chart/ እና ትንበያን በማስተማሪያ ዘዴነት ተጠቅሟል።

አጥኚው ተማሪው አጠቃላይ ግንዛቤውን ካገኘ በኋላ ምንባቡን በትክክል መረዳቱን ለመለካት ጥልቅ የንባብ ትምህርት /while-reading/ ሰጥቷል። በመጀመሪያ ምንባቡ ውስጥ የሚያስቸግሩት ቃላት፣ ሃረጎች፣ እና ዓረፍተ ነገሮች መኖራቸውን ለመለካት ተማሪውን ጮክ ብሎ እንዲያነብ አድርጓል። ጮክ ብሎ የክፍል ውስጥ የንባብ ልምምድ /reading-aloud/ ተማሪው የአነባበብ ፍጥነቱን እንዲያሻሽል ሲባል ተግባራዊ ተደርጓል። በዚህ ወቅት የአጥኚው ተግባር ሌላው ተማሪ በትክክል ማዳመጡን መቆጣጠርና አንባቢው በሚያነብበት ጊዜ የተሳሳተውን ቃል ወይም ሃረግ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ማስፈር ነበር። በአሰፈራቸው ቃላት ላይ ትክክለኛውን አነባበብ ምን እንደሆነ የክፍሉን ተማሪ ጠይቋል። ከክፍሉ ተማሪ ባገኘው መልስ በተጨማሪ የራሱን ማስተካከያ መልስ አጥኚው ሰጥቷል። ምክንያቱም

---

* DRTA = Direct Reassign Thinking Activity

ለትክክለኛ ግንዛቤ ለሚደረግ ንባብ የመምህሩ ተከታታይ የሆነ ጣልቃ ገብነት መኖር እንዳለበት /Nuttall 1996፣ 262/ ይመክራሉ::

በንባብ ደረጃ ጮክ ብሎ ከማንበብ በኋላ የሚከተለው የለሆሣስ የአነባበብ ስልት ሲሆን ዓላማውም ተማሪው የተጻፈውን ነገር በትክክል እንዲረዳ ለማድረግ ነው:: ተማሪው የተሰጠውን ምንባብ ረጋ ብሎ በግል ካነበበ በኋላ ከምንባቡ ውስጥ የተለያዩ ተውላጠ ስሞችን ጥንድ በመሆን በመወያየት ከምንባቡ ውስጥ እየፈለገ በማግኘትና በማውጣት በተሰጠው "Worksheet" ላይ እንዲጽፍ ተጠይቋል:: Williams /1984፣ 39/ ለትክክለኛ ግንዛቤ ሲባል ጽሑፉን መሠረት በማድረግ የሚመለሱ ጥያቄዎች መጀመር ያለባቸው ከአጠቃላይ ምንባቡ በመነሳት ወደ አንቀጾች ከዚያም ወደ ዓረፍተነገሮችና ቃላት መሄድ እንዳለባቸው ይመክራሉ::

ለትክክለኛ ግንዛቤ ሲባል የተዘጋጁት የጥያቄ ዓይነቶች ክፍት /open-ended/ እና ዝግ ጥያቄዎች /close-ended/ ሲሆኑ ክፍት ጥያቄዎችን ተማሪው በመወያየት በጋራ እንዲሠራቸው ተደርጓል:: ነገር ግን የምርጫ ጥያቄዎችን በግሉ እንዲሠራ ከተደረገ በኋላ አጥኚው ተማሪዎች በትክክል መስራታቸውን እየዞረ በማረም አስተካክሏል:: በዚህ መሠረት አጥኚው ለትክክለኛ ግንዛቤ ሲባል በቀረቡ ጥያቄዎች ተማሪው የተሰጠውን ጥያቄ ከምንባቡ ሳይወጣ ከራሱ ሃሣብ በማፍለቅ ከምንባቡ ውስጥ ከተሰጠው ሃሣብ ሳይጨምር ወይም ሳይቀንስ ትክክለኛውን የቋንቋውን ሥርዓት እየተጠቀመ እንዲመልስ አድርጓል::

ተማሪው በድህረ-ንባብ ትምህርት ደረጃ እንዲያከናውን የተጠበቀው ከምንባቡ ውስጥ ያገኘውን አዲስ እውቀት ቀደም ሲል ካለው እውቀት ጋር በማግኘት የጸሐፊውን መልዕክት፣ ስሜት፣ ፍላጎትና አመለካከት እንዲገመግመውና ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እያያያዘ እንዲያመዛዝነውና ትክክለኛው ግንዛቤ ላይ እንዲደርስ ነው:: ይህንን ሁኔታ ለማከናወን የቀረቡ ይዘቶች ተማሪው በውይይት መፍትሔ እንዲፈለግላቸው የሚያደርጉ ጥያቄዎች /problem-solving exercises/ Wallaceን /1992፣ 103-106/, Brownን /1994፣ 183/ Nuttall /1996፣ 199-210/ መነሻ በማድረግ ተማሪዎች በቡድናቸው አማካኝነት ከተወያዩ በኋላ ሐሣባቸውን በንግግር ወይም በጽሑፍ እንዲገልጹ ተጠይቀዋል:: አጥኚው በዚህ ደረጃ ተወያይተው የደረሱበትን ምላሽ ከየቡድናቸው አንድ ተማሪ በቡድኑ ስምምነት በማስነሳት ለክፍል ጓደኞቻቸው በጽሑፍ ወይም በንግግር እንዲገልጹ አድርጓል:: አጥኚው ይህን ያደረገበት ምክንያት የክፍሉ ተማሪ ከአጥኚው ጋር በመረዳዳት ወደ አንድ የማጠቃለያ ሃሣብ ላይ እንዲደርስ ለማድረግ ነው::

በአጠቃላይ ተጠኚው ቡድን በአብዛኛው በክፍል ውስጥ ተራክቦ በማድረግ አንብቦ የመረዳት ክሂሉን እንዲያሣድግ በቅድመ ንባብ ደረጃ ለማስተማሪያነት የቀረበውን ምንባብ ርዕሰ ነገር በማስመልከት እንዲወያይ ለአጠቃላይ ግንዛቤ ለሚደረግ ንባብ ደግሞ የአሰሳ /scanning/ እና የገረፍ ገረፍ የአነባበብ ስልት /skimming/ እየተጠቀሙ በንባብ ደረጃ ደግሞ በመምህሩ ጣልቃ ገብነት የንባብ ፍጥነታቸውን እንዲያሻሽሉና ጽሑፉን በትክክል እንዲገነዘቡ የሚያስችሉ ይዘቶችን በማዘጋጀት በግልና በቡድን እንዲያከናውናቸው እንዲሁም በድህረ-ንባብ ደረጃ ተማሪው የመፍትሔ ሃሣብ በመወያየት እንዲፈልግላቸው ሲባል በቡድን የሚሠሩ /problem solving exercises/ ተዘጋጅተው ጥናቱ ተግባራዊ ሆነዋል::

3.2.3 የፈተናዎች አዘገጃጀት፣ አስተራረምና የውጤት አሰጣጥ ዘዴ

ቅድመ-ፈተናውና ድህረ-ፈተናው እያንዳንዳቸው 45 ጥያቄዎችን ያካተቱ ሲሆን በተመሳሳይ ሁኔታ አራት ክፍሎች አሏቸው:: ስለ አዘገጃጀታቸው አባሪ «ለ» ይመለከቷል:: ፈተናዎቹ አምስት ዓይነት ይዘቶችን አካተዋል:: የመጀመሪያዎቹ አሥር ጥያቄዎች የተለያዩ መደብ አመልካች ተውላጠ ስሞች የወከሉትን ቃል፣ ሀረግ ወይም ዓረፍተ ነገር ተማሪው ከተሰጠው ምንባብ ፈልጎ /infer/ እንዲያወጣና እንዲጽፍ ሲባል የቀረቡ ናቸው:: ዓላማቸውም ተማሪው እነዚህን ተውላጠ ስሞችን ደራሲው ለምን ተግባር እንደተገለገለባቸው ለመለካትና ከዚያም ባሻገር የስዋሰው ችሎታቸውንም ጭምር ለመመዘን ነው::

ክፍል ሁለት የምርጫ ጥያቄዎች ሲሆኑ የመጀመሪዎቹ አሥር ጥያቄዎች ተማሪው ቃላትን ወይም ሀረጎችን ከምንባቡ ውስጥ ካላቸው አገባብ አንጻር የያዙትን ዓውዳዊ ፍች /contextual meaning/ እንዲፈልግና ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ እንዲመርጥ ለማድረግ ነው:: የነዚህ ጥያቄዎች ዓላማ ተማሪው እነዚህን ቃላትና ሀረጎች በምንባቡ ውስጥ ካላቸው አገባብ አንጻር የያዙትን አውዳዊ ፍች ምን ያህል ተረድቷቸዋል? የሚለውን ለመለካት ነው:: በነዚሁ ክፍል ሌሎች አሥር የምርጫ ጥያቄዎች ያሉ ሲሆን በዚህ ደረጃ የቀረቡ ጥያቄዎች ደራሲው በጽሑፉ አማካኝነት ያስተላለፈውን መልክት በትክክል ተማሪው ምን ያህል ተረድቶታል? የሚለውን ለመለካት ሲባል ደራሲው ቃላት፣ ሐረጎች እና ዓረፍተ ነገሮች ከያዙት ቀጥተኛ ፍች ባሻገር ሌላ ትርጉም እንዲይዙ አድርጎ የተጠቀመባቸውን /implied meaning/፣ ደራሲው መልክቱን በቀጥታ ከማስተላለፍ በአባባሎችና በዘይቤዎች አማካኝነት ለማስተላለፍ የተጠቀመባቸውን የተለያዩ አገላለጾች፣ የአንቀጾችን ተናጠላዊ መልክት፣ ምንባቡ የሚያስተላልፈው ዋና መልክት /centeral idea/ ወ.ዘ.ተ. በዚህ ደረጃ የተካተቱ ናቸው::

በክፍል ሦስት የቀረቡ አምስት የማዛመድ ጥያቄዎች ሲሆኑ ዓይነታቸውም ደራሲው በጽሑፉ ውስጥ የተጠቀመባቸውን የተለዩ አገላለጾች ናቸው:: ለምሳሌ ደራሲው ሲናደድ የሚጠቀመው የቋንቋ አጠቃቀምና ሲደሰት የሚጠቀመው የቋንቋ አጠቃቀም የተለያየ ነው:: ለዚህም ሲባል የተለያዩ ሥርዓተ ነጥቦችንና ምልክቶችን የመጠቀም ሁኔታም ይኖራል:: የጥያቄዎቹ ዓላማ ደራሲው በጽሑፉ አማካኝነት መልክቱን ለማስተላለፍ ሲል የተጠቀመባቸውን የተለያዩ የቋንቋ አጠቃቀሞች ምን ያህል ተረድታቸዋል? የሚለውን ለመለካት ነው::

ክፍል አራት አጠቃላይ የግንዛቤ ጥያቄዎች ሲሆኑ ጥያቄዎቹ ከምንባቡ ውስጥ በቀጥታ ለመፈለግ /infer/ የሚመለሱ ጥያቄዎች ናቸው:: በዚህ ደረጃ ተማሪው የተጠየቀው በቃል፣ በሀረግና አልፎ አልፎ ቀላል ዓረፍተ ነገሮች ሲሆኑ ሁሉም ከምንባቡ ውስጥ ብቻ ያለውን እንዲመልስ ሲባል የቀረቡ ናቸው:: ዓላማውም ተማሪው ከጽሑፉ ውስጥ እንደ ጥያቄዎቹ አቀራረብ አጠያየቃቸውን ተረድቶ ከጥያቄዎቹ አንጻር የቋንቋውን ሰዋሰዋዊ ሥርዓት ጠብቆ የመመለስ ችሎታው ምን ያህል ነው? የሚለውን ለመለካት ነው::

3.2.3.1 የፈተናዎቹ አሰጣጥ

ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው ሁለቱም ፈተናዎች በተመሳሳይ ቅርጽና በመጠንም ቢሆን አንድ ሲሆኑ ሁለቱም ፈተናዎች የተሰጡት ከመደበኛው ትምህርት ፕሮግራም ውጭ ነው:: ሁሉም ፈተናዎች ተማሪው ሊረዳቸው በሚችለው መልኩ መመሪያዎች ተጽፈውላቸዋል:: ተማሪው ፈተናውን ከመውሰዱ በፊት ለጥንቃቄ ሲባል ፈተናው ከመስጠቱ አንድ ቀን በፊት ከዚህ በታች በተመለከተው ሁኔታ መግለጫ ተሰጥቶታል:: መግለጫው ለተማሪው ብቻ ሳይሆን ለፈታኙም ጭምር ነው::

- የፈተናው ጥራዝ አራት ክፍሎችና 45 ጥያቄዎች የያዘ መሆኑን ተማሪውም ሆነ ፈታኙ ፈተናውን ከመጀመሩ በፊት ማረጋገጥ ያለበት መሆኑን፣
- ግልጽ ያልሆነ ነገር ካለ ተፈታኞች ፈተኛቸውን መጠየቅ ያለባቸው መሆኑን፣
- ፈተናውን በተረጋጋ መንፈስ እንዲሠሩ የሰዓት ገደብ አለመኖሩን አስቀድሞ ከተገለጸላቸው በኋላ ፈተናዎቹ ተሰጥተዋል::

3.2.3.2 የፈተናዎቹ አስተራረምና ውጤት አሰጣጥ ዘዴ

ሁለቱም ፈተናዎች /Objective Type/ በመሆናቸው በአጥኚው ታርመዋል። ለጥንቃቄ ሲባል በአዳባ ሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ መምህር ቢክስ ኃይሌ ለሁለተኛ ጊዜ የእርማቱ ትክክለኛነት ተረጋግጧል። የሁለቱም ፈተናዎች ውጤት አወሳሰድ ተመሳሳይ ሲሆን የመጀመሪያዎቹ 35 ጥያቄዎች በሁለት ተባዝተው ከ70% ሲያዙ የመጨረሻዎቹ በአጭሩ በጽሑፍ የሚመለሱት ደግሞ ሦስት ማርክ እንዲይዙ ሆነው ከ30% ታርመዋል። በአጠቃላይ ሁለቱም ቡድኖች ከመቶ ያገኙትን የቅድመ-ፈተናውን ውጤት እና ከገጽ 49 የድህረ- ፈተናውን ውጤት ከገጽ 61 መመልከት ይቻላል።

3.2.4 የመረጃዎቹ ውጤት አተናተን ዘዴ

የጥናቱ መረጃ መተንተኛ ዓይነተኛው መንገድ መጠናዊ ዘዴ (quantitative) ነው። አጥኚው መረጃውን ለማሰባሰብ ሲል አንድ ዓይነት ይዘቶችን በተለያዩ አንብቦ የመረዳት የማስተማሪያ ሞዴሎች አቀራረብ ለአምስት ሣምንታት ሊያስተምር ከቆየ በኋላ ለሁለቱ ቡድኖች በተለያየ አቀራረብ ስልት በመማራቸው የተለየ የባህሪ ለውጥ ማምጣታቸውን ለመፈተሽ አንድ ዓይነት የድህረ-ትምህርት ፈተና በሁለቱ ቡድኖች የተገኘውን ውጤት አማካይ (mean) እና የልይይት ዳግም ብዜት (SD) ግምት ውስጥ በማስገባት በ«ቲ» ቴስት ቀመር ተሰልቷል። በቲ-ቴስት ቀመር የተገኘውን አሃዛዊ ውጤት ከተዛማጅ ጽሑፎችና በምርምሩ ወቅት ከታዩት የልምምድ ሂደቶች ጋር በማዛመድ ተነራርቷል።

3.2.5 በአጥኚው የተዘጋጁት የማስተማሪያ መሣሪዎች /ምንባቦች መልመጃዎች/ እና ፈተናዎች /ቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት ፈተናዎች ተገቢነት /Validity/ እና አስተማማኝነት /Reliability/

በአጥኚው የተዘጋጁት የማስተማሪያ መሣሪዎች የይዘት፣ የቅርጽ እና የአቀራረብ ቅደም ተከተል ተገቢነት /validity/ በሚከተለው ሁኔታ ተገምግሟል።

በአጥኚው የተመረጡት ምንባቦች ውሀን አፍልቶ፣ መጠቀም፣ ማህበርና የቡና ቤት ሥፅሎች የሚሉት ሲሆኑ አመራረጣቸውም Wallace /1992፣71/ በሚከተሉት ሁኔታ ባስቀመጣቸው መለኪያዎች ነው።

ሀ. ምንባቡ አዳዲስ ቃላትንና የቋንቋውን ስዋሰዋዊ ሥርዓት የሚያስተምር ከሆነ፣

ለ. ምንባቡ የተለያዩ መሠረታዊ የሆኑ የአነባበብ ስልቶችን የሚያስተምር ከሆነ፣

ሐ. የምንባቡ ይዘት ከተማሪው ፍላጎትና ችሎታ ጋር የሚሄድ ከሆነ፣

መ. ምንባቡ /Authentic/ የሆነ ከሆነ ይህም ማለት ጽሑፉ ለቋንቋ ማስተማሪያ ተብሎ የተመረጠ ሳይሆን ለሌላ ተግባር ተብሎ የተጻፈ ከሆነ፣

ሠ. ምንባቡ በክፍል ውስጥ ለሚደረገው የመማር ማስተማር ሂደት ለተለያዩ ክንዋኔዎች አመቺ ከሆነ፣

ምንባቡ መመረጥ የሚችል መሆኑን ያስረዳሉ፣ Wallace እነዚህን መለኪያዎች ሙሉ በሙሉ ተሳክተው ባይገኙም በከፊል የሚያሟሉ ከሆነ መመረጥ እንደሚችሉ ገልጸዋል። ከዚህ በተጨማሪ Davis /1995፣ 170/ በ Wallace መለኪያዎች የሚስማሙ ሲሆን ሌላ አንድ ተጨማሪ መለኪያ ተነባቢነት /readability/ የሚለውን አክለዋል። በነዚህ መለኪያዎች አማካኝነት ከላይ የተዘረዘሩት ምንባቦች ተመርጠው በሦስት የቋንቋ ማስተማር ሥነ-ዘዴ ላይ ልዩ ሙያ ባላቸው ምሁራን ተገምግመዋል። የምንባቦች የቃላት፣ የሀረጎችና የዓረፍተ ነገሮችን ተነባቢነት በማስመልከት Davis /1995፣ 35/ የግንዛቤ ፈተና /cloze test/ የተሻለ መለኪያ መሆኑን ጠቁመዋል። ከዚህ በመነሳት በፓይለት ፕሮጀክት ጥናቱ ከተከናወነባቸው ተማሪዎች ውጪ በሆነ ሁኔታ አሥር ተማሪዎች በዋናው ጥናት በተካተቱት ተጠኚዎች በተመረጠበት የናሙና አመራረጥ ስልት ተመርጠው የሚከተለውን ውጤት አምጥተዋል።

ሠንጠረዥ I

የምንባቦች ርዕስ	በፓይለት ፕሮጀክት የታቀፉት ቁጥር ጠቅላላ ተማሪ ብዛት	ከሃምሣ በላይ ያገኙ	ፐርሰንት	የተመረጡ ምንባቦች
- ውሃን አፍልቶ መጠቀም	10	9	90	✓
- ማህበር	10	7	70	✓
- የቡና ቤት ሥዕሎች	10	8	80	✓
- ጥንታዊ ጉዞ	10	2	20	X

ከሠንጠረዡ እንደምንረዳው የተመረጡት ምንባቦች ውሃን አፍልቶ፣ መጠቀም፣ ማህበርና የቡና ቤት ሥዕሎች የሚሉ ሲሆኑ ጥንታዊ ጉዞ «X» ምልክት የተቀመጠበት በአብዛኛው ተማሪ ዝቅተኛ ውጤት በማምጣቱ ሳይመረጥ የቀረ ነው። ስለ ዝርዝር ስታትስቲካዊ መረጃው ከአባሪ «ሐ.1» መመልከት ይቻላል።

አጥኚው የ11ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ-ትምህርት /1984/ በውስጡ ያካተታቸውን አጠቃላይ አንብቦ የመረዳት ዓላማና ዝርዝር አንብቦ የመረዳት ዓላማዎችን መነሻ በመድረግ በተመረጡት ምንባቦች «በተራክቧዊ» ሞዴል አንፃር የተለያዩ ይዘቶች በጥያቄ መልክ በአጥኚው ተዘጋጅተው በሦስት ባለሙያዎች ተገምግመዋል። እነዚህ ይዘቶች ከተራክቧዊ ሞዴል አንጻር በክፍል ውስጥ እንዴት መከናወን አለባቸው? የሚለውን ግምት ውስጥ በማስገባት ከተለያዩ የቋንቋ ንድፈ-ሃሳቦችና የቋንቋ መማር ማስተማር ንድፈ-ሃሳቦች በመነሳት የተቀረጹት ክንዋኔዎች በሦስት ባለሙያዎች ተገምግመው አስተያየት ከተሰጣቸው በኋላ ማስተካከያ ተደርጎባቸዋል።

3.2.5.1 የቅድመ-ትምህርትና የድህረ-ትምህርት ፈተና አስተማማኝነት /reliability/

ሀ. የቅድመ-ፈተና አስተማማኝነት /reliability/:- ተጠኚ ተማሪዎች ቅድመ-ፈተናውን ከመውሰዳቸው በፊት ያለውን ረብነት ማለትም ፈተናው ነገም፣ ተነገወዲያም ያለው ፈተና መልሶ ለሌላ ተመሳሳይ ተማሪ ቢሰጥ ውጤቱ ቋሚነት ይኖረዋል? የሚለውን ለመመለስ ከተጠኚዎች ውጪ የሆኑ አሥር ተማሪዎች በዋናው ጥናት በታቀፉት የናሙና አመራረጥ ዘዴ በብድግ ብድግ ሥልት ተመርጠው ፈተናውን ወስደዋል። የተገኘውን ውጤት ስታትስካዊ መረጃ አባሪ «መ2» መመልከት ይቻላል። የተገኘውን ውጤት Nachmias /1992 ፣ 165/ እና Jr. /1970፣ 112/ መነሻ በማድረግ የተገኘውን ውጤት በሙሉ /Even/ እና ጎደሎ /Odd/ በመክፈል /Spiliting half/ ዘዴ በመጠቀም የተገኘው የአስተማማኝነት ውጤት Reliability cofficent **0.85** ነው። ይህም Jr. /1970፣ 112/ የአስተማማኝነት ውጤት በ0.80 እና በ0.95 መካከል ከሆነ ፈተናው አስተማማኝነቱ ተቀባይነት አለው ባሉት መሠረት ፈተናው ተቀባይነት አግኝቶ ለጥብቅ ቡድኑና ለተጠኚ ቡድኑ ተሰጥቷል።

ለ. የድህረ-ፈተና አስተማማኝነት Reliability:- ድህረ-ፈተና /post-test/ በተመሳሳይ ቅርጽና ብዛት ከቅድመ-ፈተናው ጋር የተዘጋጀ ሲሆን ይህ ፈተና በሦስት ባለሙያዎች ከተገመገመ በኋላ ያለውን አስተማማኝነት ለመለካት በቅድመ-ፈተናው የፓይለት ፕሮጀክት የናሙና አመራረጥ ስልት አሥር ተማሪዎች ተመርጠው ያገኙትን ውጤት ከአባሪ «ሐ.3» መመልከት ይቻላል። ይህንን ውጤት ከቅድመ-ፈተናው

በተመሳሳይ ሁኔታ Jr. /1970፣ 112/ መስፈርት መሠረት ተቀባይነት ያለው በመሆኑ ፈተናው ጥብቅ ቡድኑና ተጠኚ ቡድኑ አንድ ዓይነት ይዘትን በተለያየ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ሲማሩ ከቆዩ በኋላ እንዲፈተኑ ተደርጓል::

እስካሁን በዚህ ምዕራፍ ለማየት የተሞከረው ጥናቱ ለዓላማው ተግባራዊነት ምን ዓይነት የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ይከተላል? መረጃውን ለማሰባሰብ የቦታ፣ የትምህርት ቤት፣ የክፍልና የተማሪዎች አመራረጥ ምን ዓይነት የናሙና አመራረጥ ስልት መከተል አለበት? የተመረጡት ናሙናዎችስ በጥብቅ ቡድን እና በተጠኚ ቡድን በምን ዓይነት የናሙና አመራረጥ ስልት መመደብ አለባቸው የሚሉት ሁኔታዎች ተነስተዋል:: ከነዚህ ጥያቄዎች በኋላ ለጥብቅ ቡድኑና ለተጠኚ ቡድኑ ከሚከተሏቸው የተለዩ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴሎች አንጻርና ከተለያዩ የቋንቋ ንድፈ-ሃሳብና የቋንቋ መማር ንድፈ-ሀሳብ በመነሳት የማስተማሪያ መሣሪያዎችና ክንውኖች እንዴት እንደተመረጡ ነው:: በመጨረሻም የተዘጋጁት የማስተማሪያ መሣሪያዎችና ክንውኖች ተገቢነታቸውና /validity/ እና አስተማማኝነታቸው /reliability/ ምን ይመስላል? የሚሉት ጉዳዮች ተወስተዋል:: ከዚህ ምዕራፍ ቀጥለን የምንመለከተው ጥናቱ በተከተለው የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ የተገኙትን ውጤቶች መተንተንና በዓይነት በዓይነታቸው ከፋፍሎ ትርጉም መስጠት ይሆናል::

ምዕራፍ አራት

የመረጃዎች ውጤትና ትንተና

ይህ ምዕራፍ የመረጃው ውጤት የሚተነተንበት ክፍል ነው:: በመጀመሪያ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ያለውን የችሎታ ተመጣጣኚነት ለመለካት ሲባል የተሰጠው የቅድመ ፈተና ውጤት ይተነተናል:: ድህረ-ፈተናውን ከመውሰዳቸው በፊት ጥብቅ ቡድኑ /control group/ እና ተጠኚ ቡድኑ በሙከራው ክንውን ወቅት የተዘጋጀላቸውን የማስተማሪያ መሣሪያ በተዘጋጀላቸው ሞዴል አንፃር የክፍል ውስጥ ልምምድ በምን ሁኔታ እንደተከናወነ ይገለጻል:: ከዚህ በመነሳት የድህረ ፈተናው ዓላማ ከተገለጸ በኋላ በፈተናው የተገኘው ውጤት በ"ቲ" ቴስት ቀመር ተሰልቶ የተገኘው ውጤት ፍትነታዊ ምርምሩ ይዟቸው ከተነሳው ዜሮ /H_0/ መላምትና አማራጭ መላምቱ /H_1/ ጋር በማዛመድ ይብራራል:: በመጨረሻም ከተገኘው መረጃ፣ በክፍል ውስጥ በተደረገው ልምምድ፣ እንዲሁም ከተለያዩ ተዛማጅ ጽሑፎች ጋር በማዛመድ የጥናቱ ውጤት ከተብራራ በኋላ ይህ ምዕራፍ ይቋጫል::

የዚህ ጥናት ዓላማ ከንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴሎች ውስጥ አንዱ የሆነውን ተራክቧዊ /interactive/ ሞዴል በተለይም በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎችን በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ከፍ ለማድረግ አስተዋጽኦ ይኖረዋልን? የሚለውን ጥያቄ በፍትነታዊ /Experimental Method/ የምርምር ዘዴ ለመፈተሽና ውጤት ላይ ለመድረስ ነው:: ይህን መሠረታዊ ጥያቄ ለመመለስ በመጀመሪያ በምኞት የናሙና አመራረጥ ስልት የቦታ፣ የትምህርት ቤትና የክፍል መረጣ ከተከናወነ በኋላ የተጠኚዎችን መረጣ ደግሞ በብድግ ብድግ ስልት /simple random sampling/ በመጠቀም ተጠኚዎች ተመርጠዋል:: መረጣው ከተከናወነ በኋላ ለሁለቱም ቡድኖች የቅድመ-ፈተና ተሰጥቶዋል:: የቅድመ ፈተናውን ወስደው ያላቸው የችሎታ ተመጣጣኚነት በ"ቲ" ቴስት ቀመር ከተለካ በኋላ ለጥብቅ ቡድን በጥንታዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል /bottom-up/ ለተጠኙ ደግሞ በዘመናዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ Interactive ወይም ተራክቧዊ ሞዴል አንፃር በተዘጋጁ የማስተማሪያ መሣሪዎችና ክንውኖች የንባብ ክሂል ትምህርት ልምምድ ተካሂዷል::

4.1 የቅድመ-ፈተና ውጤትና ትንተና

የቅድመ-ፈተናው ዓላማ በሁለቱ የተለያዩ /Independent Samples/ ቡድኖች መካከል የችሎታ ተመጣጣኚነት መኖሩ ለመለካት ሲባል የተሰጠ ነው:: በሠንጠረዥ II እና III እንደተገለጸው ቅድመ ፈተናውን የወሰዱት አባላት ብዛት ሃምሣ ናቸው:: በፈተናው ውጤት መሠረት በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ ልዩነት /significant difference/ መኖሩንና አለመኖሩን ለመለካት Crockerን /1981፣ 66/ እና ሌሎችንም መነሻ በማድረግ የ«ቲ» ቴስት ቀመር በመጠቀም ተከናውኗል:: የቅድመ-ትምህርት ፈተና ስታቲስቲካዊ መረጃዎችንና ስሌቶችን ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ሰንጠረዦች በመመልከት መረዳት ይቻላል::

ሠንጠረዥ II: የቅድመ-ፈተና /Pre-test/ ውጤት ዝርዝር

ተ.ቁ	ጥብቅ ቡድን /Control/	ተጠኚ ቡድን /Experimental/
1	56	70
2	61	46
3	46	48
4	56	52
5	61	48
6	66	53
7	67	41
8	46	61
9	54	53
10	26	78
11	54	61
12	71	56
13	75	56
14	76	59
15	41	48
16	51	61
17	73	55
18	28	48
19	54	43
20	43	53
21	71	63
22	73	54
23	51	71
24	55	79
25	61	58

ሠንጠረዥ III: የቅድመ-ፈተና /Pre-test/ ውጤት አመዳደብ ሥርጭት (Grouped Data)

ጥብቅ ቡድን /Control/			ተጠኚ ቡድን /Experimental/		
Class Interval	Frequency ድግግሞሽ	የድግግሞሽ ድምር Cumulative Frequency	Class Interval	ድግግሞሽ Frequency	የድግግሞሽ ድምር Cumulative Frequency
20-23	0	0	20-23	0	0
24-27	1	1	24-27	1	1
28-35	1	2	28-35	1	2
32-35	0	2	32-35	0	2
36-39	0	2	36-39	0	2
40-43	2	4	40-43	2	4
44-47	2	6	44-47	2	6
48-51	2	7	48-51	2	7
52-55	4	12	52-55	4	12
56-59	2	14	56-59	2	14
60-63	3	17	60-63	3	17
64-67	2	19	64-67	2	19
68-71	2	21	68-71	2	21
72-75	3	24	72-75	3	24
76-79	1	25	76-79	1	25
80-83	0	25	80-83	0	25
84-87	0	25	84-87	0	25
$\overline{X}_1 = 56.64$ $SD_2 = 13.564$			$\overline{X}_2 = 56.60$ $SD_2 = 9.916$		

ሠንጠረዥ IV: የቅድመ-ፈተና ውጤት የ"t" ቴስት ውጤት ትንተና

የፈተናው ዓይነት	ጥብቅ ቡድን /control/			ተጠኚ ቡድን /Experimental/			የt ቴስት ስሌት			
	N_1	$\bar{X}_1$	SD_1	N_2	$\bar{X}_2$	SD_2	t-calaculated	t-tablulated 6.05	CI	Significant
ቅድመ ፈተና /pre-test/									-6.7176,6.7977	t-calculated value ከt-tabulated value ያንሳል
	25	56.64	13.564	25	56.60	9.916	0.01	2.021		No significant

N_1 = ቅድመ-ፈተና የወሰዱ የጥብቅ ቡድኑ አባላት ብዛት

$\bar{X}_1$ = ቅድመ-ፈተና የወሰዱ የጥብቅ ቡድኑ አማካይ ውጤት

SD_1 = ቅድመ-ፈተና የወሰዱ አባላት የልይይት ዳግም ብዜት ውጤት

N_2 = ቅድመ-ፈተና የወሰዱ የተጠኚ አባላት ብዛት

$\bar{X}_2$ = ቅድመ-ፈተና የወሰዱ የተጠኚ ቡድኑ አማካይ ውጤት

SD_2 = ቅድመ-ፈተና የወሰዱ የልይይት ዳግም ብዜት ውጤት

t-calculated = በt ቀመር ተሰልቶ የተገኘው የቅድመ-ፈተና ውጤት

CI (confident Interval) = በ«t» ቀመር ተሰልቶ የተገኘው ዋጋ የሚገኝበት መነሻና መጨረሻ ወሰን

No Significant = በሁለቱ ቡድኖች መካከል ልዩነት የለም

t-tabulated = በ0.05 level of significance እና በN_1+N_2-2 የነፃነት ደረጃ መካከል በ"t" table ሠንጠረዥ ተነቦ የሚገኘው ዋጋ

ከሠንጠረዥ III እና IV መረዳት እንደተቻለው የጥብቅ /Control/ ቡድኑ አማካይ ውጤት 56.64 ሲሆን የልይይት ዳግም ብዜት /SD/ ዳግም 13.564 የተጠኚ ቡድኑ አማካይ ውጤት ዳግም 56.60 ሲሆን የልይይት ዳግም ብዜት 9.919 ነው:: የሁለቱን ቡድኖች አማካይ /mean/ ውጤተና የልይይት ዳግም ብዜት /SD/ ግምት ውስጥ በማስገባት በ«ቲ» ቴስት ቀመር ሲለካ የሚገኘው የ "t" calculated ዋጋ 0.01 ነው:: የ"t" calculated ዋጋን ከ"t" tabulated ዋጋ ጋር ለማነፃፀር ሲባል በ0.05 level of significance እና በN_1+N_2-2 /degree of freedom/ መካከል በt table ሲፈለግ የተገኘው የt-tabulated ዋጋ 2.021 ነው:: የt-calculated ዋጋን ከ"t" tabulated ዋጋ ጋር ሳናነጻጽረው የt-calculated ዋጋ 0.01 ከt-tabulation ዋጋ 2.021 አንሶ እናገኘዋለን:: ከዚህ የምናጠቃልለው ነገር ቢኖር የt-calculated ዋጋ ከ"t" tabulated ዋጋ ካነሰ በሁለቱም ቡድኖች መካከል የችሎታ ልዩነት የለም ወደሚል ማጠቃለያ ያዳርሳል::

ይህ ማለት የተመረጡት ሁለት ቡድኖች በአንድ ዓይነት ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ፣ በአንድ አካባቢ የሚኖሩና የሚማሩ፣ በሁለቱም ቡድኖች በተመጣጣኚ ሁኔታ ሁሉንም ጾታና ተቀራራቢ እድሜ ያላቸው በችሎታም ቢሆን ተመጣጣኚ ናቸው ማለት ነው:: ካሁን በኋላ ለአንድ ዓይነት ቡድኖች /paired samples/ አንድ ዓይነት ይዘት በተለያየ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ተምረው በሁለቱ ቡድኖች መካከል ለውጥ የሚመጣ ከሆነ ለውጡ ለማስተማሪያ ሞዴሎች ተጽእኖ ምክንያት የመጣ ነው ወደሚል ማጠቃላይ ላይ ያደርሳል::

ከዚህ በኋላ የምንመለከተው የድህረ-ፈተናውን ውጤት ከማየታችን በፊት ለግንዛቤያችን እንዲያግዘንና ከትንታኔው ጋርም አብረን ግምት ውስጥ እያስገባን እንድንመለከተው የሁለቱን ቡድኖች የክፍል ውስጥ የንባብ ክሂል ትምህርት ልምምድ ቀጥለን እንመለከታለን::

4.2 ከቅድመ-ትምህርት ፈተና በኋላ የጥብቅ ቡድኑና የተጠኚ ቡድኑ የክፍል ውስጥ የንባብ ክሂል ትምህርት ልምምድ

4.2.1 የጥብቅ ቡድኑ የክፍል ውስጥ ልምምድ

ጥብቅ ቡድኑ በጥንታዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል አንፃር በተዘጋጀ የማስተማሪያ መሣሪያዎችና ክንውኖች በተደገፈ ሁኔታ ልምምዱ ተከናውኗል:: ለጥብቅ ቡድኑ በ1950ዎቹ አካባቢ በነበረው መዋቅራዊ ሥነ-ልሳንና ንድፈ ሃሣብና በሥነ-ባሕሪያውያን ንድፈ-ሃሣብ ተመስርቶ በተፈለሰፈው የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል /bottom-up/ አንፃር በተዘጋጀ የማስተማሪያ መሣሪያና የክፍል ውስጥ ክንውን መሠረት

በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ሆኗል። ስለመሣሪያውና ክንውኑ አቀራረብ በምዕራፍ ሶስት በገጽ 33 እና 37 በሰፊው ተብራርቷል።

በወቅቱ የነበሩት የሥነ-መዋቅራዊያን ሥነ-ልሳን ቋንቋን ማስተማር ማለት የቋንቋውን ሥነ-ድምጽ፣ ሥነ-አገባብና ሥነ-ፍች ሥርዓት ማስተማር ማለት ነው። ስለዚህ ጉዳይ Brown /1994/, Richard and Rodgers /1984/, Nuttall /1996/ እና ሌሎችንም መመልከት ይቻላል። ከዚህ በመነሳት የንባብ ትምህርት ዓላማም ተማሪው የተሰጠውን ጽሑፍ ድምጾችን አቀናጅቶ፣ ቃላት መሥርቶ፣ ሀረጋትንና ዓረፍተነገሮችን አዋቅሮ፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ በፍጥነት አንብቦ የሚረዳበትን ስልት መፈለግ ነው። ለዚህም ሲባል ጮክ ብሎ ማንበብ አንዱና ዋነኛው የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ስልት እንደሆነ Lado /1964/ ይነግሩናል። ከቋንቋ መማር ማስተማር ንድፈ ሃሣብ ደግሞ በወቅቱ የነበረው የባሕሪያውያን ንድፈ-ሃሳብ አመንጪዎች እንደሚሉት የባሕሪ መመስረቻ መንገድ ነገሮችን በመደጋገም በቃል በመያዝ መሞከር ነው። ይህ ሁኔታ ዋንኛ የማስተማሪያ ስልት ተደርጎ የሚወሰድ በመሆኑ በወቅቱ የንባብ ክሂል ትምህርትም የተጻፈውን ጽሑፍ በቃል ማጥናት የተወሰኑ የአገባብ መሰል /patterns/ ሞዴሎችን በመስጠት ተማሪው በዚያ እየተካ እንዲጠቀም በማድረግ በወቅቱ የቋንቋ ማስተማሪያ መንገድ እንደነበር Lado /1964/, Mackey /1965/ Brown /1994/, Richard and Rodgers /1984/ እና ሌሎችም አስረድተዋል። ተማሪው ሲያነብም ሆነ መልመጃዎችን ሲሠራ ከስህተት ለመከላከል መምህሩ በተደጋጋሚ ጣልቃ በመግባት ትምህርቱ ይሰጣል። በአጠቃላይ በመምህሩ ገላጭነት በተማሪው አዳማጭነት ብቻ ትምህርቱ ይሸፈናል። ይህ ጥናትም በተመሣሣይ ሁኔታ በክፍል ውስጥ ለጥብቅ ቡድኑ በአጥኚው ገለጻ ላይ በተመሠረተ ሁኔታ ተማሪው ከጽሑፉ ሳይወጣ ማለትም ከተጻፈው ሳይቀንስ ወይም ሳይጨምር የቋንቋውን ሥርዓትን ሳያፋልስ በንግግር ወየም በጽሑፍ እንዲመልስ አድርጓል። በልምምዱ ወቅት በክፍል ውስጥ የተከናወነውን የመማር ማስተማር ሂደት አተገባበር አባሪ «ሠ-1» የተገለጸውን ፎቶግራፍ በማየት መረዳት ይቻላል።

ተማሪው የቀረበለትን ምንባብ በአጭር ጊዜ ውስጥ አንብቦ እንደረዳው በማድረግ ልምምድ /drilling/ አንዱ መንገድ ሲሆን ተማሪው በተራ በመነሳት ለጓደኞቹ ጮክ ብሎ እንዲያነብና እንዲለማመድ ተደርጓል። ተማሪው ልምምዱን በዚህ ሁኔታ አከናውኖ እንደጨረሰ በአጥኚው ስለ አዳዲስ ቃላት ትርጉም ስለ ጽሑፍ አጠቃላይ መልዕክት፣ በጽሑፍ ውስጥ የተገለጹት አባባሎች፣ ዘይቤዎችን በማስመልከት ማብራሪያ ተደርጎላቸዋል።

በመጨረሻም ተማሪው የንባብ ልምምዱን አከናውኖ እንደጨረሰ በጽሑፍ ውስጥ ያሉትን አዳዲስ ቃላት፣ ሃረጎችና ዓረፍተነገሮችን እንዲሁም ይዘቱን በማስመልከት ከምንባቡ ውስጥ በአግባቡ መረዳቱን ለመለካት ሲባል ከምንባቡ በኋላ የቀረቡትን ይዘቶች በግሉ በንግግርና በጽሑፍ እንዲመልስ ተደርጓል። ተማሪው በዚህ ልምምድ ወቅት የቋንቋውን ሥርዓትና የተጠየቀውን ደግሞ ከጽሑፉ ውጪ እንዳይመልስ በአጥኚው ቁጥጥር እየተደረገ እንዲያስተካክል ተደርጓል። በዚህ ሁኔታ በተከታታይ ለአምስት ሣምንታት ያህል የተዘጋጁት ይዘቶች በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ሆነዋል።

4.2.2 የተጠኚ ቡድኑ /Experimental Group/ የክፍል ውስጥ ልምምድ

ለተጠኚ ቡድኑ የተዘጋጀው የማስተማሪያ መሣሪያና የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ክንውን ከዘመናዊ የቋንቋ ንድፈ ሃሣብና ከዘመናዊ የቋንቋ መማር ንድፈ ሃሣብ ጋር በተንሰላሰለ ሁኔታ በተቀረጸ አዲስ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል አንባር ነው። ልምምዱ በቀን 1 ሰዓት ለአምስት ተከታታይ ሣምንታት ለ25 ሰዓታት ያህል ተሰጥቷል። የጊዜው አመራረጥ ሁኔታ ከትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ጋር በመስማማት በሞቾት ናሙና /convenience sampling/ አመራረጥ ስልት የተመረጠ ነው። ለተጠኚ ቡድኑ የማስተማሪያ መሣሪያዎች እና የክፍል ውስጥ ክንውኖች ከዘመናዊ የቋንቋ ንድፈ ሃሣብና የመማር ንድፈ ሃሣብ እንደተዘጋጁ በምዕራፍ ሶስት ተገልጿል። በልምምዱ ወቅት ተጠኚ ተማሪዎች ያከናውኑትን ተግባር ከአባሪ «ሠ-2» ያለውን ፎቶ ግራፍ በማየት መረዳት ይቻላል።

በ1970ዎቹ አጋማሽ የማሕበራዊ ሥነ-ልሣን አራማጆች የቋንቋ ተግባር ማግባባት ነው። ስለዚህ ቋንቋን ማስተማር ማለት የቋንቋውን ሥርዓት ብቻ ማስተማር ማለት ሣይሆን ከቋንቋው ሥርዓት ባሻገር ያለውን ማኅበረሰቡ የሚጠቀምበትን የቋንቋ ሥርዓት ከማኅበራዊ /social context/ ጋር በማያያዝ ለማስተማር መሞከር ነው። ከዚህም በተጨማሪ የትምህርት አሰጣጡ መሆን ያለበት በተራክቦ /interaction/ ላይ በተመሠረተ ሁኔታ ነው። ከዚህም ባሻገር ትምህርቱ በአንድ ጊዜ ሣይሆን በሂደት ተማሪዎች በራሳቸው ጥረት እንዲረዱት መምህሩ ማድረግ ያለበት መንገዶችን መሻት ነው። የቋንቋ ትምህርቱም ከአካባቢ ጋር በተያያዘ ሁኔታ መሰጠት ያለበት መሆኑን ይመክራሉ። ስለዚህ ጉዳይ በማስመልከት Nunan /1991a/ ያሉትን ከገጽ 179 መመልከት ይቻላል።

ይህ ጥናትም ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል ከአለው ባሕሪ አኳያ የማኅበራዊ ሥነ-ልሳንን መሠረት አድርጎ እንዲጓዝ በማድረግ የተከናወነ ነው። Brown

/1994፣ 159/ «ተራክቦ የሚያድገው በራሱ በተራክቦ ነው»። እንዳሉት ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴልም ተማሪው በሚያነብበት ጊዜ የራሱን የአነባበብ ስልት በሂደት ሲጠቀም ለተጻፈው ነገር ትርጉም ለመስጠት ሲባል በአእምሮው ውስጥ የተለያዩ አንብቦ የመገንዘብ ንኡሳን ክሂሎች በጥምርት ተራክቦ በማድረግ ለተጻፈው ነገር በቀላሉ ትርጉም እንደሚሰጡት ሁሉ ተማሪውም በክፍል ውስጥ ከጽሑፉ፣ ከጓደኛው በጥንድ ወይም በቡድን እንዲሁም ከመምህሩ ጋር ተራክቦ ቢያደርግ ያለውን እውቀት በጋራ እየተጠቀመ፣ እየተወያየ፣ እየተመካከረ፣ እየተጋገዘ በራሱ ጥረት ቢማር ክሂሉን በቀላሉ ያዳብራል ከሚል አጠቃላይ ንድፈ-ሃሣብ በመነሳት ልምምዱ በቡድን፣ በጥንድ፣ አልፎ አልፎ ደግሞ ተማሪው በግሉ ከመጽሐፉ ጋር እየተገናኘ የንባብ ክሂል ትምህርቱን ልምምድ አከናውኗል። በዚህ ወቅት አጥኚው ተማሪው ሲወያይ ረዳት፣ አማካሪ፣ መሪ በመሆን እንዲሁም ከቡድኑ ጋር አብሮ ተሳታፊ በመሆን ልምምዱ ተግባራዊ እንዲሆን ጥረት አድርጓል።

በአጠቃላይ ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል ውጤት ተኮርንና ሂደት ተኮርን በማጣመር ተማሪው ከተጻፈው በመነሳትና የራሱን አእምሯዊ እውቀት በሂደት ቀስ በቀስ በመጠቀም ለተጻፈው ነገር ትርጉም እንዲሰጥ የሚያመቻች ነው። ይህም በመሆኑ ተማሪው የተጻፈውን ነገር ተማሪው በመጠቀሙ ሥነ-ልሣናዊ ችሎታውን እንዲያዳብር አእምሯዊ እውቀቱን በመጠቀሙ ደግሞ በራስ የመማር ስልትን፣ በጋራ በመተጋገዝ መማሩ ደግሞ ተግባቦታዊ ችሎታውን እንዲያዳብር፣ ስለሚያግዘው ለተጠኚ ተማሪው በአራት ደረጃዎች በተከፈለ ሂደት አንብቦ የመረዳት ክሂሉን እንዲያዳብር ሲባል ይዘቶች ተዘጋጅተውለታል። እያንዳንዱ ደረጃ የራሱ የሆነ ዓላማ የአነባበብ ስልትና የክንዋኔ ስልት አለው። ስለይዘቱ አቀራረብና የክንዋኔ ስልት ቀጥለን የምንመለከተው ይሆናል።

4.2.2.1 በሂደት አንድ /Phase 1/ የመቀስቀስ ደረጃ የተከናወነ የክፍል ውስጥ ልምምድ

በዚህ ደረጃ ተማሪው የቀረበለት ትምህርት ምንባቡን በፍጥነት ወይም ረጋ ብሎ በጥልቀት ከማንበቡ በፊት ስለምንባቡ ቀደም ሲል የሚያውቀውን ሁሉ እንዲናገር ለማድረግ በቡድን ተከፋፍለው Carrell, Devine and Eskey /1988፣ 284/ Brown /1994፣ 281/ እና ሌሎችም የሚስማሙበትን /brain storming/ ስልት ተግባራዊ ተደርጓል። በዚህ ደረጃ ተማሪው ሊተወያየበትን ሁሉ እንዲናገር ተጠይቋል። ተማሪው ያለውን መቀበል እንጂ ተቃውሞ አያደርግም ምክንያቱም በዚህ ደረጃ የትምህርት ዓላማ ተማሪውን መቀስቀስ ማሟሟቅና ለዋናው ሥራ ዝግጁ የማድረጊያ ጊዜ ነው። Williams /1984/ እንዳሉት መምህሩ ክፍል ውስጥ እንደገባ ገጽ 10 ያለውን ምንባብ አውጡና በምንባቡ በመሠረት ጥያቄዎቹን ትሠራላችሁ ከማለት ከላይ በተጠቀሰው መንገድ ቢቀርብለት

ተማሪው ትምህርቱን በንቃት እንዲከታተለው ያስችለዋል ለማለት ነው። በዚህ ጥናት የመቀስቀስ ደረጃ በቅድመ ንባብ ደረጃ የተሰጠ ነው።

4.2.2.2 ሂደት ሁለት /Phase 2/ ምንባቡን በፍጥነት በማንበብ አጠቃላይ ግንዛቤን ማዳበር /Stage of Fluency/ ደረጃ የተደረገ ልምምድ

ይህ ደረጃ በዚህ ጥናት የቅድመ-ንባብ አንድ ክፍል ተደርጎ ተወስዷል። በዚህ ደረጃ ተማሪው የሚጠበቅበት ምንባቡን በፍጥነት የገረፍ-ገረፍ ስልት /skimming/ እና የአሰሳ የአነባበብ ስልትን /scanning/ እየተጠቀመ አጠቃላይ ግንዛቤውን ማስፋት ነው።

ከአባሪ ሀ-1 እንደምንመለከተው ተማሪው የገረፍ-ገረፍ የአነባበብ ስልቱን እንዲያዳብር ሲባል በጥንድ፣ በግል እንዲሁም በቡድን እንዲያከናውናቸው ሲባል ጅምር ዓረፍተ ነገሮችን እንዲጨርስ፣ ከምንባቡ የተወሰኑ ቃላት በመዝለል በምንባቡ አውድነት የራሱን ቃል ሊሆን የሚችለውን በመገመት እንዲሞላ፣ የአንቀጾችን ተናጠላዊ መልክት፣ እንዲናገር፣ በአንቀጾች ውስጥ ያሉ መንደርደሪያ ዓረፍተነገሮችን ከዝርዝር ዓረፍተነገሮች እንዲለይና ለማስተማሪያ መሣሪያነት የቀረበውን ምንባብ ቅደም ተከተሉን በማፋለስ የአጻጻፍ ስልቱን በመለየት መልሶ አስተካክሎ እንዲያዋቅር የተወሰኑ ደቂቃዎችን በመስጠት ልምምዱ ተከናውኗል። በገረፍ-ገረፍ የአነባበብ ስልት ተማሪውን ማለማመዱ ዓላማው ተማሪው ስለጽሑፉ አጠቃላይ ግንዛቤን እንዲያሳድግና የተወሰኑ ጽንሰ ሃሣቦችን በአጭር ጊዜ ፈልጎ የማግኘት ስልቱን እንዲያዳብር ሲባል ነው። Nuttall /1996፣ 44/፣ እንዳሉት ብቃት ያለው አንባቢ አንድን ጽሑፍ አንብቦ የሚረዳ ብቻ ሣይሆን የሚፈልገውን ነገር ለመረዳት አነስተኛ ጊዜና ጉልበትን ይጠቀማል። ለዚህም ሲባል ይህ የአነባበብ ስልት ለተጠኚ ተማሪው ተግባራዊ ተደርጓል።

በዚሁ የቅድመ-ንባብ ትምህርት ደረጃ ለአጠቃላይ ግንዛቤ ሲባል ተማሪው የተጻፈውን ጽሑፍ በፍጥነት እያነበበ ስሞችን፣ ቁጥሮችን፣ ዓመተምሕረቶችን፣ ተመሣሣይ ቃላትንና ታቃራኒ ቃላትን ከጽሑፉ እየፈለገ በጽሑፍ ወይም በንግግር እንዲመልስ ሲባል በአሰሳ የአነባበብ /scanning/ ስልት የሚመለሱ ይዘቶች ቀርበውለታል። በዚህ ደረጃ ተማሪው ጽሑፉን ከፈለገው አቅጣጫ ከመጀመሪያ፣ ወይም ከመጨረሻ ወይም ከመካከል የሚፈልገውን ነገር እንዲፈልግና እንዲያገኝ ለማድረግ በአጥኚው መመሪያ ተነግሮታል። ተማሪው በዚህ ወቅት በአብዛኛው መልመጃዎችን በጥንድ እንዲያከናውናቸው ሆነው ተዘጋጅተውለታል። ተማሪው ከጽሑፉ የሚፈልጋቸውን ነገሮች በአጭር ጊዜ ውስጥ ፈልጎ እንዲያገኝ ጊዜ ተወስኖለታል።

በአጠቃላይ በቅድመ-ንባብ ደረጃ ተማሪው ከተጻፈው ነገር አጠቃላይ ግንዛቤን እንዲያዳብር ሲባል ለተጠኚ ቡድኑ ተሰጥቶታል። በዚህ ወቅት የአጥኚው ተግባር በግል፣ በጥንድ ወይም በቡድን ሲለማመድ፣ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ስለ አሠራሩ መመሪያ በመስጠት፣ ከቡድኑ ጋር አብሮ ተሣታፊ በመሆን፣ በመርዳት፣ በማስተባበር ሚና ተጫውቷል። ነገር ግን መምህሩ ይህ መሆን አለበት በሚል ወደ ትክክለኛ መልስ እንዲደርሱ ተጽእኖ አላደረገም።

4.2.2.3 ሂደት ሶስት /Phase 3/ /Accuracy Stage/ ለትክክለኛ ግንዛቤ ሲባል የተደረገ ልምምድ

ይህ የሂደት ደረጃ ተማሪው የተጻፈውን ጽሑፍ ካነበበ በኋላ የጽሑፉን ሥነ-ልሳናዊ ቅርጽና በጽሑፉ የተካተተውን ይዘት /content/ ተማሪው በትክክል እንዲረዳው ሲባል ለማለማመድ የቀረበ የአነባበብ ስልት ደረጃ ነው። በዚህ ደረጃ መምህሩ ተማሪው የተጻፈውን ጽሑፍ ሥነ-ልሣናዊ ቅርጽና ይዘት በትክክል ይረዳ ዘንድ ለጽሑፉ ትኩረት እንዲሰጥበት ተጽእኖ የሚያደርግበት ደረጃ ነው። Williams /1985፣ 38/ Wallace /1992፣ 93/ የሚሉትና ይህ ጥናት የሚደግፈውም በዚህ ደረጃ ተማሪው የሚያነበው ረጋ በማለት፣ በመምረጥና ከጸሐፊው ጋር በጽሑፉ አማካኝነት ሐሣብ በመለዋወጥ ጽሑፉን በትክክል መረዳት አለበት የሚለውን ነው።

በዚህ ደረጃ ተጠኚ ቡድኑ ያለበትን የአነባበብ ችግር ለመፍታት ሲባል ተማሪው ለጓደኞቹ በተራ ቆሞ እንዲያነብ ተደርጓል። በዚህ የአነባበብ ስልት ተማሪው የፈለገውን ጉዳይ እንደሚፈልገው ሁኔታ አንብቦ እንዲረዳው ሲባል ሰፋ ያለ ጊዜ ተሰጥቶታል። ሰፋ ያለ ጊዜ መስጠቱ ተማሪው ጽሑፉን ረጋ በማለት ደግሞ ደጋግሞ የጽሑፉን ሥነ-ልሳናዊ ቅርጽ /form/ እና ይዘት /content/ በትክክል እንዲረዳው ለመርዳት ነው። በዚህ ወቅት የመምህሩ ወይም የአጥኚው ተግባር ተጠኚ ተማሪዎች ሲያነቡ ያልገባቸው ካለ እንዲጠይቁ እየዞረ በማበረታታት እርዳታ አድርጓል።

ተማሪው የተሰጠውን ምንባብ ደግሞ ደጋግሞ ካነበበ በኋላ /inference questions/ ከምንባቡ ፈልጎ በቀጥታ ሊያገኛቸው የሚችሉ ይዘቶችን በቡድንና በጥንድ በመሆን በንግግርና በጽሑፍ እንዲመልስ ተጠይቋል። የጥያቄዎች አዘገጃጀት ከአጠቃላይ ግንዛቤ /direct inference/ ወደ ዝርዝር ግንዛቤ /implied inference/ ማለትም ወደ አንቀጾች፣ ዓረፍተ ዓረፉተ ነገሮችና ቃላት እየቀነሰ እንዲሆን ሆኖ ተዘጋጅቷል። ይህም ማለት ቃላት ዓረፍተ ነገሮች በ/direct inference/ ጊዜ በመጀመሪያ አልቀረቡም ማለት አይደለም። የቃላትንና የሀረጎችን አሠጣጥ ቅደም ተከተል የወሰነው በጽሑፍ ውስጥ በያዙት ፍች ነው። በዚህ

ጥናት ከአጠቃላይ ግንዛቤ የሚለው በቀጥታ ከጽሑፉ እንዳለ የሚመለሱትን ሲሆን ዝርዝር ግንዛቤ የሚለው ደግሞ ቃላት ሃረጎችና ዓረፍተ ነገሮች በጽሑፍ ውስጥ ካላቸው ቀጥተኛ ትርጉም ባሻገር ሌላ ጉዳይን ለመግለጽ ሲል ደራሲው የተጠቀመባቸውን ለማለት ነው። በዚህ ደረጃ ዘይቤዎችም ሆኑ አባባሎች በዚሁ የሚጠቃለሉ ናቸው። የጥያቄው አዘጋጃጀት ሁለት ዓይነት ሲሆን ዝግ /cloze ended/ የምርጫ ጥያቄዎች፣ እውነት ውሸት ዓይነት እና ደረቅ ጥያቄዎች ማን፣ ምን፣ ለምን ዓይነት ናቸው። ሁሉም ጥያቄዎች ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር እንዲሄዱ ሆነው የተዘጋጁ ናቸው። ምክንያቱም ተማሪው ከጅምሩ ሰፋ ያለ አውድን እየተጠቀመ በሂደት የቃላትን፣ የሀረጎችንና፣ ዓረፍተነገሮችን ሥነ-ልሣናዊ ቅርጽና ቀጥተኛ ፍች እንዲሁም ከቀጥተኛ ፍቻቸው ባሻገር የያዙትን ፍች እንዲረዱ ለማድረግ ነው።

በአጠቃላይ በዚህ ደረጃ ተማሪው ያለበትን የሥነ-ልሣን ችግር ለማቃለል ሲባል በጽሑፉ ውስጥ ያሉትን አዳዲስ ቃላት በአውድ በማስገባት ከአውዱ ከጓደኞቹ ጋር በጥንድ ወይም በቡድን በመሆን እየተወያየ እንዲመልስ ተደርጓል። ከዚህም በተጨማሪ ያለበትን የስዋሰው ችግር ለማቃለል ተውላጠ ስሞችን የተኩትን ቃል እየፈለገ የቃሉን ዓይነት የሚገኝበትን ቦታ እንዲረዳ ጥረት ተደርጓል። ከዚህም ባሻገር የጽሑፉን የአጻጻፍ ስልት /rhetorical organization/ እንዲረዳ ሲባል አያያዢ ቃላትንና ሃረጎችን ከጽሑፉ በመፈለግ ደራሲው ለምን ተግባር እንደተጠቀመባቸው እንዲገልጽና ምን ምን ዓይነት ዓረፍተ ነገሮችን እንደያዙ በቡድን ወይም ጥንድ በመሆን እየተወያየ እንዲመልስ ተደርጓል። ተጠኚ ቡድኑ ደራሲው በቀጥታ በጽሑፉ ውስጥ ያስተላለፋቸውን መልዕክቶችና በሥውር በዘይቤዎች አማካኝነት ያስተላለፋቸውን መልክቶች በትክክል እንዲረዳ ሲባል በቡድን፣ በጥንድ፣ እና በግል የሚያከናውናቸው ይዘቶች ቀርበውለት በክፍል ውስጥ አከናውኗል። በዚህ ደረጃ መምህሩ ተማሪዎች በሥነ-ልሳን ደረጃም ሆነ መልክቱን በትክክል ባለመረዳት የፈጸሙትን ሥሕተቶች በቅርብ እየተከታተለ ትክክለኛ ማስተካከያ ምላሽ ሰጥቷል።

4.2.2.4 ሂደት አራት /Phase 4: Critical Evaluation Stage/ የተጻፈውን ጽሑፍ ከራሱ እውቀት በመነሳት በሚገመግምበት ደረጃ የተደረገ ልምምድ


በዚህ ደረጃ ተማሪው ከጽሑፉ ውስጥ ያገኘውን አዲስ ሥነ-ልሣናዊ እውቀትና ከጽሑፉ ይዘት የተገነዘበውን አዲስ የጽንሰ-ሃሣብ እውቀት ቀደም ሲል ካለው ሥነ-ልሣናዊ እውቀትና ጽሑፍ ስለተጻፈበት ርዕሰ ነገር ጋር ካለው እውቀት እንዲሁም ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እያያያዘ የሚገመግምበት ደረጃ እንደሆነ Williams /1984፣ 37/, Wallace /1992፣ 100/, Carrell, Devine and Eskey /1988፣ 238/ እና ሌሎችም ይጠቁማሉ። ይህ ጥናት ከዚህ በመነሳት ለማስተማሪያ መሣሪያነት ከቀረቡት ምንባቦች ደራሲው

ፍላጎቱን፣ አመለካከቱን፣ እምነቱን፣ የሚያመለክቱትን ቃላት፣ ሃረጎች እና ዓረፍተነገሮች ፈልጎ በማውጣት ደራሲው ለምን እንደተጠቀመባቸው፣ ደራሲው በጽሑፉ አማካኝነት የሚያስተላልፈው ጽንሰ-ሃሣብ፣ እውቀትና አስተያየት ተማሪው ከሚኖርበት፣ ከሚማርበት አካባቢ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ያለውን ግንኙነት እየገመገመ እንዲናገር ሲባል /problem solving types/ ዓይነት ጥያቄዎች ቀርበዋል። ጥያቄዎቹ ተማሪው ከራሱ እውቀት ጋር በማያያዝ የመሰለውን ሃሣብ ለቡድኑ አባላት አስተያየት ሲሰጥ ከቆየ በኋላ ቡድኑ የወሰነውን ከቡድኑ አንድ ሰው ቡድኑ የተስማማበትን ሃሣብ ለክፍል ጓደኞቹ እንዲገለጽ ተደርጓል። መምህሩ /አጥኚው/ በዚህ ጊዜ የየቡድኑን አስተያየት ከሰበሰበ በኋላ የክፍሉ ተማሪ እንዲወያይበት መድረክ ፈጥሯል። በመጨረሻም የክፍሉ ተማሪ አስተያየቱን ከሰጠበት በኋላ መምህሩ በተማሪው ላይ ተጨማሪ አስተያየት በመስጠት ለማስተማሪያነት የቀረበው ሙሉ ምዕራፍ በዚህ ደረጃ ተቋጭቷል።


በጥናቱ መረጃ አሰባሰብ ወቅት የክፍሉ ውስጥ የንባብ ትምህርት ልምምድ ሂደትና ክንውን ከዚህ ቀጥሎ በቀረበው ሥዕላዊ መግለጫ መሠረት ተጠቃሏል።

ስዕል I

ስዕል I: ለጥብቅ ቡድኑ የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር አቀራረብና ክንውን የሚያሣይ ሥዕላዊ መግለጫ፣




ስዕል II: ለተጠኚ ቡድኑ የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር አቀራረብን የሚያሣይ ሥዕላዊ መግለጫ፣



P_1 = የመጀመሪያው ደረጃ ተማሪውን ለመቀስቀስ ሲባል የሚቀርብ
P_2 = ስለጽሑፉ አጠቃላይ ግንዛቤን ለማግኘት
P_3 = ጽሑፉን በትክክል ለመገንዘብ ሲባል የንባብ ትምህርት አቀራረብ
P_4 = ተማሪው አዲሱን እውቀት ቀደም ሲል ካለው እውቀት ጋር በማገናኘት ጽሑፉን የሚገመግምበት ደረጃ

ስዕል III: ለተጠኚ ቡድኑ በክፍለ ውስጥ በመማር ማስተማር ሂደት ወቅት የክንውኑን ሂደት የሚያሣይ ሥዕላዊ መግለጫ፣



S = ተማሪ
TE = ማስተማሪያ መሣሪያ
S = ተማሪ ሁለት
S = ተማሪ ሶስት
S = ተማሪ
T = መምህሩ

4.3 የድህረ-ፈተና ውጤት ትንተና

በሠንጠረዥ V፣ VI እና VII እንደተገለጸው ቀደም ሲል የቅድመ-ፈተናውን የወሰዱት ሃምሣ አባላት በጥናቱ የተካተቱ ሲሆን ከሁለቱም ቡድኖች አንድ፣ አንድ ተጠኚ ትምህርት ቤቱን በመልቀቃቸው ከቡድኖች ተቀንሰዋል። እነዚህ አባላት ለአምስት ተከታታይ ሣምንታት የተሰጠውን አንብቦ የመረዳት ክሂል ትምህርት ተከታትለዋል። ስለ ድህረ-ፈተናው መረጃና ስታትስታካዊ ውጤት ቀጥሎ በተመለከቱት ሠንጠረዦች መረዳት ይቻላል።

ሠንጠረዥ V: የድህረ-ፈተና ውጤት ዝርዝር

ተራ ቁጥር	ጥብቅ ቡድን /Control/	ተጠኚ ቡድን /Experimental/
1	54	78
2	71	72
3	57	77
4	45	64
5	48	61
6	56	42
7	58	75
8	43	54
9	57	71
10	48	64
11	60	82
12	54	73
13	77	54
14	65	64
15	40	73
16	43	82
17	61	55
18	30	46
19	52	72
20	45	74
21	66	63
22	56	65
23	67	89
24	41	69

ሠንጠረዥ VI: የሁለት ቡድኖች የድህረ-ፈተና /Post-Test/ ውጤት ስርጭት /Grouped Data/

ጥብቅ ቡድን /Control/			ተጠኚ ቡድን /Experimental/		
Class-Interval	Frequency ድግግሞሽ	የድግግሞሽ ድምር Cumulative Frequency	Class-Interval	ድግግሞሽ Frequency	የድግግሞሽ ድምር Cumulative Frequency
20-23	0	0	20-23	0	0
24-27	0	0	24-27	0	0
28-35	1	1	28-35	0	0
32-35	0	1	32-35	0	0
36-39	0	1	36-39	0	0
40-43	4	5	40-43	1	1
44-47	2	7	44-47	1	2
48-51	2	9	48-51	0	2
52-55	3	12	52-55	3	5
56-59	5	17	56-59	0	5
60-63	2	19	60-63	2	7
64-67	3	22	64-67	4	11
68-71	1	23	68-71	2	13
72-75	0	23	72-75	6	19
76-79	1	24	76-79	2	21
80-83			80-83	3	24
84-87			84-87	0	24
$\overline{X}_2$ = 53.7826 S_{D2} = 11.265			$\overline{X}_2$ = 66.7826 S_{D2} =11.029		

ሠንጠረዥ VI: የድህረ-ፈተናን /Post Test/ የ"t" ቴስት ስሌት ትንታኔን የሚያሣይ ሠንጠረዥ

የፈተናው ዓይነት	ጥብቅ ቡድን /control/			ተጠኚ ቡድን /expermental/			የt ቴስት ውጤት ስሌት					
	N_1	$\bar{X}_1$	SD_1	N_2	$\bar{X}_2$	SD_2	t-calculated	Degree of freedom	t-tabulated	2-tail signified	Confident Interval	Significant
ድህረ ፈተና	24	53.7826	11.265	24	66.7826	11.029	4.09	23	2.391	0.000	19.584-6.416	t-calculated is greater than t-tabulated 4.09 > 2.391 significant

N_1 = ድህረ-ፈተና የወሰዱ የጥብቅ ቡድኑ አባላት ብዛት

$\bar{X}_1$ = ድህረ-ፈተና የወሰዱ የጥብቅ ቡድኑ አማካይ ውጤት

SD_1 = ድህረ-ፈተና የወሰዱ አባላት የውይይት የዳግም ብዜት ውጤት

N_2 = ድህረ-ፈተና የወሰዱ የተጠኚ አባላት ብዛት

$\bar{X}_2$ = ድህረ-ፈተና የወሰዱ የተጠኚ ቡድኑ በፈተናው ያገኙት አማካይ ውጤት

SD_2 = ድህረ-ፈተና የወሰዱ የተጠኚ ቡድኑ የልይይት ዳግም ብዜት ውጤት

t-calculated = በ"t" ቀመር ተሰልቶ የተገኘው ውጤት

በድህረ-ፈተና የተገኘው ውጤት ከሠንጠረዥ /VII/ እንደምንመለከተው የጥብቅ ቡድኑ የድህረ-ፈተና አማካኝ ውጤት 53.7826 ሲሆን የልይይት ዳግም ብዜት /SD/ ደግሞ 11.265 ነው::

የተጠኚ ቡድኑ የድህረ-ፈተና አማካይ ውጤት 66.7826 ሲሆን የልይይት ዳግም ብዜት /SD/ ደግሞ 11.029 ነው:: የሁለቱን አማካይ /mean/ ውጤትና የልይይት ዳግም ብዜት /SD/ ግምት ውስጥ በማስገባት በ"ቲ" ቴስት ቀመር ተለክቷል:: በ"ቲ" ቴስት ቀመር ተሰልቶ የተገኘው የt-calculated value 4.09 ነው:: ይህንን የt-calculated value የt-tabulated value ጋር ለማነፃፀር በ0.05 /level of significance/ እና በN-1 degree of freedom የt-table ሲፈለግ የሚገኘው የt-tabulated ውጤት 2.391 ነው::

ከውጤቱ እንደምንረዳው የt-calculated value ከt-tabulated value ስለበለጠ ወይም 4.09 > 2.391 በሁለቱ ቡድኖች መካከል የባህሪ ልዩነት /significant difference/ እንዳለ ይጠቁማል:: ይህ ልዩነት ከየት መጣ የሚለውን ለመመለስ የጥብቅ ቡድኑን ውጤት ከተጠኚ ቡድኑ ውጤት በመቀነስ ወይም የተጠኚ ቡድኑን ውጤት ከጥብቅ ቡድኑ ውጤት በመቀነስ መለየት ይቻላል:: ይኸውም ከሁለቱ ውጤቶች መካከል ፖዘቲቪ ወይም የበለጠ ውጤት ታሳየው የተሻለ የባህሪ ለውጥ አሳይቷል ማለት ነው:: በዚህ ጥናትም «በተራክቧዊ» የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል የተማረው የተሻለ ወይም ፖዘቲሺ ውጤት አሳይቷል::

4.4 ፍትነታዊ /Experimental/ ምርምሩ ለመፈተሽ ይዟቸው የተነሳው መላምቶች

በተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል መሠረት በተዘጋጁ የማስተማሪያ መሣሪያዎችና ክንውኖች በተደገፈ ሁኔታ የተማሩትን አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለመለካት ድህረ-ፈተና /post-test/ ከወሰዱ በኋላ ምንም ዓይነት የችሎታ ልዩነት አያሳዩም:: ይህ መላምት ዜሮ መላምቱ ነው:: ዜሮ መላምቱን ከምዕራፍ አንድ ገጽ 4 ላይ መመልከት ይቻላል:: ከጥናቱ ውጤት በኋላ እንደተረዳነው የt-calculated value 4.09 ከt-tabulated 2.391 መብለጡን የ"ቲ" ቴስት ስሌት ያሣያል:: ይህ ውጤት በሚያሳየን በሁለቱ ቡድኖች መካከል የባሕሪ ልዩነት /significant difference/ መኖሩን ነው:: ይህ የባሕሪ ልዩነት ዜሮ መላምቱን በአማራጭ /alternative hypothesis/ እንዲተካ አድርጎታል::

አማራጭ መላምቱ H_1 በተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል መሠረት በተዘጋጁ አዲስ አንብቦ የመረዳት ክሂል ማስተማሪያ መሣሪያዎችና የክፍል ውስጥ ክንውኖች በተደገፈ ሁኔታ የተማሩትን ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለመለካት ድህረ-ፈተና ከወሰዱ በኋላ የችሎታ ልዩነት ያሣያሉ:: ይህ መላምት በሁለቱ ቡድኖች መካከል የችሎታ ልዩነት ስለታየ ዜሮ መላምቱን ተክቶታል:: ስለ ውጤቱ ዝርዝር ትንታኔ ከሠንጠረዥ VII መመልከት ይቻላል:: በ"ቲ" ቴስት የታየው ጉልህ ልዩነት በየትኛው የማስተማሪያ ሞዴል የመጣ ነው? የሚለው ቀደም ሲል ተገልጿል:: የባህሪ ለውጡ በተጠኚ ቡድኖች ላይ የታየ ሲሆን ይህም ለውጥ ተማሪዎቹ በተራክቧዊ የንባብ ክሂል የማስተማሪያ ሞዴልና የክፍል ውስጥ ክንውን በመማራቸው ምክንያት የተገኘ እንደሆነ የጥናቱ ውጤት ይጠቁማል::

4.5 የመረጃው ውጤት ማብራሪያ /Discussion/

ከድህረ-ፈተናው ትንታኔ ውጤት ለመረዳት እንደተሞከረው በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ክሂል ክፍ ለማድረግ ተራክቧዊ /interactive/ ሞዴል ተጠቅሞ ማስተማር ውጤቱ የተሻለ መሆኑ ጥናቱ ጠቁሟል:: ቀደም ሲል በተዛማጅ ጽሑፉ ላይ እንደተጠቀሰው ተማሪው በአንዱ የአነባበብ ስልት ያልገባውን በቀጣይ የአነባበብ ስልት የራሱን ሥነ-ልሣናዊ ችሎታና አእምሮአዊ እውቀት በሂደት ተጠቅሞ ካነበበ ጽሑፉን በቀላሉ ሊገነዘበው ይችላል፤ የሚለውን የ Stanovich /1980/ አስተያየት ይህ ጥናትም ሲደግፈው ይታያል::

ቀደም ሲል በተዛማጅ ጽሑፉ በገጽ 11 - 13 ላይ በማንሳት እንደሞከርነው በተለይም ለትምህርት የቀረበው ቋንቋ ለተማሪው ኢአፍ-መፍቻ ቋንቋ ከሆነው በሚማረው ቋንቋ ቢያንስ ቢያንስ ሥነ-ልሣናዊ ችግሮችና የቋንቋውን ተናጋሪ ሕብረተሰብ ባሕልና ወግ በትክክል ለይቶ ያለማወቅ ችግር ሊገጥመው እንደሚችል ተመልክተናል:: ይህ ጥናትም ይህንን ሁኔታ መኖሩን የሚያረጋግጥልን ነገር ቢኖር ተማሪው የቀረበለትን ጽሑፍ በማንበብ ብቻ ጽሑፉን ለመረዳት መሞከሩ በግንዛቤ በኩል የሚያመጣው ለውጥ ዝቅተኛ መሆኑን ነው:: ለዚህም የጥብቅ ቡድኑ /control group/ በውጤት ተኮር ስልት ተማሪው ከጽሑፉ ላይ ብቻ በመነሳት ጽሑፉን እንዲረዳ በመደረጉ የራሱን አእምሯዊ እውቀት በሂደት እየተጠቀመ ጽሑፉን እንዲረዳ ባለመደረጉ ምክንያት እንደ ተጠኚ ቡድኑ የተሻለ ውጤት ላይ ላይደርስ ችሏል::

ቀደም ሲል የነበሩ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴሎች /bottom-up/ አንብቦ የመረዳትን ክሂል ለማዳበር የሚጠቀመው የተከፋፋሉ ንዑሳን ክሂሎችን በማቅረብ በመሆኑ ችግሩ ሣይቃለል የቆየ መሆኑን Carrell, Devine and Eskey /1988/, Brown /1994/, Wallace /1992/, Nuttall /1996/ እና ሌሎችም ጠቁመዋል:: የዚህ ጥናት ውጤትም የሚያስረዳው በተከፋፈሉ ንዑሳን አንብቦ የመረዳት ክሂሎችን ማስተማር ለክሂሉ መዳበር የሚያደርገው አስተዋጽኦ ዝቅተኛ መሆኑን ነው::

አንብቦ በመረዳት ክሂል ላይ በተደጋጋሚ ጥናት ያከናወኑት እንደ Carrell /1980/, Eskey /1978/, Davis /1975/ እና ሌሎችም የሚጠቁሙት ነገር ቢኖር ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል ተማሪው ጽሑፉንና የራሱን አእምሯዊ እውቀት በማገናኘት የተጻፈውን ነገር እንዲረዳ በማስቻሉ ከሌሎች ፍጹም ውጤት ተኮር /bottom-up/ እና ሂደት ተኮር /top down/ ከሆኑት የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴሎች የተሻለ መሆኑን ነው:: ይህ ጥናትም የሚደግፈው ይህንኑ አባባል ነው::

ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል ለተማሪው ከራሱ ፍላጎት፣ አመለካከት፣ ችሎታና አካባቢ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ጽሑፎች በመምረጥና ከማቅረብም ባሻገር ተማሪው በክፍል ውስጥ ከጓደኛው፣ ከመጽሐፉና ከመምሩ ጋር ግንኙነት በመፍጠር እንዲማር እድል ሰጪ ነው:: እነዚህ ሁሉ ባሕሪያት ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል ከሌሎች የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴሎች የተሻለ ባሕሪ እንዲይዝ ያደረገው ይመስላል::

ተዛማጅ ጽሑፎችም ሆነ ይህ ጥናት እንደሚጠቁመው በተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል አንባር የሚያስተምር መምህር የሚጠበቅበት ቢኖር ከተማሪው ፍላጎት፣ ልምድ ችሎታና አካባቢ ጋር ሊሄድ የሚችሉትን ምንባቦች መምረጥ፤ በተመረጡት ምንባቦች መሠረት ደግሞ ተማሪው የራሱን ሥነ-ልሣናዊ ችሎታና የራሱን አእምሯዊ እውቀት በሂደት እየተጠቀመ ጽሑፉን በራሱ የአነባበብ ስልት የሚረዳበትን ስልት ማመቻቸት እንዳለበት ይጠቁማሉ::

በአጭሩ ለትምህርት የቀረበው ቋንቋ አፍ መፍቻ ቋንቋ ለሆናቸው ተማሪዎች አንድን ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል አንድን ጽሑፍ አንብቦ በመረዳት በኩል የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ከዚህ በታች ሊጠቃለል ይችላል::

- የሥነ-ልሣን ችግር ለማስወገድ ሲል ጽሑፍን ለማስተማሪያነት ለመጠቀም በመሞከሩ፣

- ተማሪው ቀደም ሲል ያለበትን አንብቦ የመረዳት ክሂል ለማቃለል ሲባል ከተማሪው ልምድ፣ ፍላጎትና አካባቢ ጋር ሊሄድ የሚችል ጽሑፍ በመምረጥ ጽሑፉን እንደሚፈልገው ጉዳይ የራሱን የአነባበብ ስልት በሂደት እንዲጠቀም የተለያየ ይቶችን አዘጋጅቶ ተማሪው የሚመቸውን ስልት በመጠቀም ከጽሑፉ፣ ከጓደኛው፣ ከመምህሩ ጋር በመገናኘት ክሂሉን የሚያዳብርበት ስልት በማመቻቸቱ፣

- ተማሪው የቋንቋውን ተናጋሪ ሕብረተሰብ ባሕልና ወግ በትክክል ለይቶ ያለማወቅን ችግር ለማቃለል ሲባል ተማሪው ከሚኖርበት ማኅበረሰብ ጋር ተዛማጅ የሆነ ጽሑፍ በመምረጥ እና በማቅረብ ተማሪው ያገኘውን አዲስ እውቀት ከአካባቢው ጋር በማዛመድ እውነታውን እንዲደርስበት እድል ሰጪ በመሆኑ፣

- ቀደም ሲል የነበረው የመምህር መራሽ አሁንም በዚህ ጥናት ላይ በጥብቅ ቡድኑ ተግባራዊ የሆነውን የማስተማር ስልት ወደ ተማሪ መራሽ የአቀራረብ ስልት እንዲተካ በማድረጉ ምክንያት ቀደም ሲል ከነበሩ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴሎች ሁሉ ተሻሽሎ የተገኘበት መልካም ጎኑ እንደሆነ Davis /1995/, Nuttall /1996/, Carrell /in Carrell, Devine and Eskey 1988/, Wallace 1992/ እና ሌሎችም ጠቁመዋል።

ከላይ የተዘረዘሩትን ነገሮች ሁሉ ግምት ውስጥ በማስገባት የተከናወነው ጥናትም ቢሆን የሚጠቁመው ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል እነዚህን መሠረታዊ የሆኑ ችግሮች ግምት ውስጥ አስገብቶ ለማስተማር መሞከሩ ለወደፊትም ቢሆን ሞዴሉ በተግባር ላይ ቢውል ለትምህርት የቀረበው ቋንቋው ኢአፍ መፍቻ ቋንቋ ለሆነው ተማሪ ጥሩ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል ሊሆንለት ይችላል የሚለውን ነው።

ምዕራፍ አምስት

5. ማጠቃለያና የመፍትሔ ሐሣቦች

5.1 ማጠቃለያ

ለዚህ ጥናት መነሻ ሆነው በተለያዩ ጊዜ በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ በመረዳት ክሂል ላይ ጥናት ያደረጉ ምሁራን አማርኛ ቋንቋ አፍ መፍቻ የሆናቸውም ሆነ ያልሆናቸው አንብቦ የመረዳት ክሂላቸው ዝቅተኛ ነው የሚለው ድምዳሜ እንደሆነ ቀደም ሲል በምዕራፍ አንድ ተጠቅሷል። ይህን በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘውን አንብቦ የመረዳት ችግር ለመቀነስ ደግሞ በክፍል ውስጥ የተሻለ አንብቦ የመረዳት ክሂልን ማስተማሪያ ሞዴል ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ የተለያዩ የውጭ ሀገር እና የሀገር ውስጥ ባለሙያዎች ጠቁመዋል።

ንባብ ካለው ጠቀሜታ አንፃር በትምህርት ቤት አንብቦ የመረዳት ክሂልን ለማስተማር በተለያየ ጊዜ የተለያዩ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴሎች እንደተፈለሰፉ በምዕራፍ ሁለት ተገልጿል። ለምሣሌ በ1950ዎቹ አጋማሽ ከቋንቋ ንድፈ ሃሣብ መዋቅራዊ ከቋንቋ ማስተማር ንድፈ-ሃሣብን ደግሞ የሥነ-ባህሪያዊያንን ንድፈ-ሃሣብን መሠረት አድርጎ ውጤት ተኮር የሆነው /bottom-up/ ሞዴል እንደተፈለሰፈ አይተናል። ይህ ሞዴል ቋ"ቋን ማስተማር ማለት ራሱን የቋንቋውን ሥርዓት ማስተማር ማለት ነው ከሚለው ከRobert Lado አቋም በማነሳት የንባብ ክሂል ትምህርትም በክፍል ውስጥ ይሰጥ የነበረው ለተማሪው አንድ የተወሰነ ጽሑፍ በማቅረብ የጽሑፉን የአጻጻፍ ሥርዓት በሚገባ ለይቶ በፍጥነት አንብቦ እንዲረዳ ለማድረግ የቃላትና የስዋሰው ይዘቶችን ብቻ በማቅረብ ትምህርት ይሰጥ እንደነበር ለማየት ሞክረናል።

የቋንቋ ንድፈ-ሃሣብና የመማር ንድፈ-ሃሣብ በተለወጡ ቁጥር የንባብ ክሂል ሞዴልም እንዲሁ ይቀየር እንደነበር ዳሰናል። ለምሣሌ የመዋቅራዊ ሥነ-ልሣን በአእምሯዊ ሥነ-ልሣን ሲተካ ባህሪያዊያን ደግሞ በአእምሯዊያን ሲተካ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴልም ፍጹም ጽሑፍን ብቻ መሠረት አድርጎ ይሸጥ የነበረው በተቃራኒው ከጽሑፉ የተወሰኑ ናሙናዎች ላይ በመነሳት አንባቢው የራሱን አእምሯዊ እውቀት /background knowledge/ በሂደት ተጠቅሞ የሚፈልገውን ብቻ ለሚፈልገው ጉዳይ የራሱን የአነባበብ ስልት እየተጠቀመ ክሂሉን እንዲያዳብር ሲባል ሂደት-ተኮር /top-down/ ሞዴል በGoodman /1967/ እንደተፈለሰፈና ተግባራዊ እንደሆነ ተመልክተናል።

ምንም እንኳ በተለያየ ጊዜ የቋንቋ ንድፈ-ሃሣቦችና የቋንቋ መማር ማስተማር ንድፈ-ሃሣቦች በተለዋወጡ ቁጥር የተለያዩ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴሎች ቢፈለሰፉም እስካሁን ድረስ ችግሩ እንዳልተወገደ በተለያየ ወቅት ጥናት ያደረጉ ምሁራን ጠቁመውናል:: በተለይም ለትምህርት የቀረበው ቋንቋ የተማሪው ኢአፍ-መፍቻ ቋንቋ ከሆነ ያለበትን ሥነ-ልሣናዊ ችግር፣ የቃላትን ፍች የማወቅ ችግርና ተማሪው የቋንቋውን ተናጋሪ ሕብረተሰብ ባሕልና ወግ ለይቶ የማወቅ ችግርን ለማቃለል እነዚህ ሞዴሎች እንዳልቻሉ Carrell, Devine and Eskey /1988/ና Davis /1996/ ጠቁመዋል:: ተማሪው ያለበትን ሥነ-ልሣናዊና ሌሎች ችግሮች ለማቃለል በክፍል ውስጥ ተማሪው ጽሑፉን bottom-up እና ጽሑፉን ደግሞ ከራሱ ልምድና እውቀት በመነሣት ትርጉም እንዲሰጠው ሲባል top-down ሞዴልን በማቀላቀል ተራክቧዊ ሞዴል በRumelheart እንደተፈለሰፈ አንስተናል:: ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል ካለው ጠቀሜታ አንፃር ኦሮምኛ ቋንቋ አፍመፍቻ ቋንቋ ለሆናቸው ነገር ግን አሣሪኛ ቋንቋን ኢአፍ-መፍቻ ቋንቋ ለሆናቸው አንብቦ የመረዳት ክሂልን ለማስተማር አስተዋጽኦ አለው? የሚለው በፍትነታዊ የምርምር ዘዴ ሙከራው ተካሂዶ የተገኘውን ውጤት ቀጥለን እንመለከታለን::

5.1.1 በቅድመ-ፈተናው የተገኘ ውጤት

የቅድመ-ፈተናው ዓላማ ሁለት የተለያዩ ቡድኖችን በተለያዩ አንብቦ የመረዳት ክሂል አቀራረብ ለተወሰነ ጊዜ በክፍል ውስጥ አስተምሮ የተገኘውን ለውጥ ከመመልከታችን በፊት ቀደም ሲል ያላቸውን የችሎታ ተመጣጣኚነት ለመለካት ሲባል የተሰጠ ነው:: ሁለቱ ቡድኖች ጥብቅ እና ተጠኚ ቡድን በብድግ ብድግ የናሙና አመራረጥ ስልት ከተመረጡ በኋላ ጥናቱ ተካሂዶ ውጤቱ እንደሚከተለው ተገኝቷል::

የጥብቅ ቡድኑ በቅድመ ፈተናው ያገኘው አማካኚ ውጤት 56.64 ሲሆን የዳግም ብዜት /SD/ ልይይት ደግሞ 13.564 ነው:: የተጠኚ ቡድኑ ደግሞ የቅድመ-ፈተና አማካኝ ውጤት 56.60 ሲሆን የልይይት ዳግም ብዜት ደግሞ 9.916 ነው:: የሁለቱን ቡድኖች አማካይ ውጤትና የልይይት ዳግም ብዜት ግምት ውስጥ በማስገባት በ«ቲ» ቴስት ቀመር ሲለካ የተገኘው t-calculated value 0.01 ነው:: የt-calculated valueን ከt-tabulated value ጋር ለማነፃፀር N_1+N_2-2 /degree of freedom/ በ0.05 /level of significance/ ሲፈለግ የሚገኘው የt-tabulated ውጤት ዳግም 2.021 ነው:: ይህም የሚያሳየን /0.01<2.021/ የ-t critical ውጤት ከt-tabulated ውጤት ማነሱ ነው:: ይህ ደግሞ በሁለቱ ቡድኖች መካከል የችሎታ ልዩነት የለም ወደሚለው ማጠቃለያ ላይ አድርሷል::

5.1.2 በድህረ-ፈተና የተገኘ ውጤት ማጠቃለያ

የሁለቱም ቡድኖች አባላት አጠቃላይ ችሎታ ተመጣጣኝ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ ለተጠኚ ቡድኑ በተራክቧዊ ሞዴል ለጥብቅ ቡድኑ በጥንታዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል አቀራረብ የተዘጋጀ ይዘት በማቅረብ በመምህሩ ገለጻ ላይ ብቻ ባተኮረ ክንውን ትምህርቱን ተከታትለዋል:: የተጠኚ /Experimental/ ቡድኑ ከተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል አንፃር ተማሪው ጽሑፉንም ሆነ የራሱን አእምሯዊ እውቀት በሂደት እየተጠቀመ ከጥብቅ ቡድኑ ጋር በተመሣሣይ ጊዜ የተሰጠውን አንብቦ የመረዳት ክሂል ትምህርት ተከታትሏል:: የተጠኚ ቡድኑ የክፍል ውስጥ ክንውን ተማሪው የራሱን ችሎታ እንዲያሳድግ ሲባል ከመጽሐፉ ከጓደኛውና ከመምህሩ ጋር ተራክቦ በማድረግ በውይይት ላይ በተመሠረተ ሁኔታ እንዲያከናውነው ጥረት ተደርጓል::

ሁለቱም ቡድኖች በተለያየ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ የተዘጋጀውን ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ ያሳዩትን የባሕሪ ለውጥ ለመመልከት ሲባል የድህረ-ትምህርት ፈተና /post-test/ ተሰጥቷቸዋል:: ሁለቱም ቡድኖች አንድ ዓይነት ፈተና ከወሰዱ በኋላ የሚከተለውን ውጤት አግኝተዋል::

የጥብቅ ቡድኑ ትምህርቱን ተከታትለው ፈተና የወሰዱት አባላት ብዛት 24 ሲሆን ያገኙት አማካይ ውጤት 53.78 ነው:: የልይይት ዳግም ብዜት ውጤት ደግሞ 11.26 ነው:: የተጠኚ ቡድኑ ትምህርቱን ተከታትለው ፈተናውን የወሰዱት 24 ሲሆኑ ያገኙት የድህረ-ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት 66.79 ነው:: የተጠኚ ቡድኑ የልይይት ዳግም ብዜት ደግሞ 11.029 ነው:: የሁለቱን ቡድኖች አማካይ ውጤት እና የልይይት ዳግም ብዜት ግምት ውስጥ በማስገባት በt ቴስት ቀመር ከተለካ በኋላ የt-calculated ውጤት 4.09 ነው:: ይህንን የt-critical value ከt-tabulated ጋር ለማነፃፀር በt-table /N-1/ በ23 /degree of freedom/ በ0.5 /level of significance/ የተገኘው የt-tabulated ውጤት 2.391 ነው:: ይህም ውጤት ሲነፃፀር t-calculated ከt-tabulated በልጦ እናገኘዋለን:: 4.09>2.391 ይህ ውጤት በሁለቱ ቡድኖች መካከል የባህሪ ልዩነት እንዳለ ያስረዳናል::

5.1.3 ፍትነታዊ ምርምሩን ለመፈተሽ በቀረቡ መላምቶች የቀረበ ማጠቃለያ

H₀ /ዜሮ መላምት/: በተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል መሠረት በተዘጋጀ የማስተማሪያ መሣሪያና የክፍል ውስጥ ክንውን በተደገፈ ሁኔታ

በክፍል ውስጥ የተማሩትን አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለመለካት ድህረ-ፈተና ከወሰዱ በኋላ ምንም ዓይነት የችሎታ ልዩነት አያሳዩም::

ይህ መላምት የጥናቱ የመጀመሪያ መላምት ሲሆን ተጠኚዎች በተራክቧዊ የንባብ ክሂል ሞዴል አቀራረብ ስልት በተዘጋጀ የማስተማሪያ መሣሪያና የክፍል ውስጥ ክንውን ሲማሩ ከቆዩ በኋላ ድህረ ፈተናውን ወስደው ያመጡት የt-calculated 4.09 ከt-tabulated 2.391 /4.09>2.391/ በልጦ በመገኘቱ ዜሮ መላምቱ እንዲቀር ተደርጎ በአማራጭ መላምቱ /Alternative Hypothesis /H1// ተተክቷል::

H_1 /አማራጭ መላምት/: በተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል መሠረት በተዘጋጀ አንብቦ የመረዳት ክሂል ማስተማሪያ መሣሪያና የክፍል ውስጥ ክንውን በተደገፈ ሁኔታ የተማሩትን አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለመለካት ድህረ-ፈተና ከተፈተኑ በኋላ የችሎታ ልዩነት ያሣያሉ::

ይህ አማራጭ መላምቱ ሲሆን በዚህ ጥናት t-calculated ከt-tabulated በልጦ በመገኘቱ ተቀባይነት አግኝቷል:: አማራጭ መላምቱ የሚነግረን በሁለቱ ቡድኖች መካከል የባሕሪ ልዩነት እንዳለ ነው:: በዚህ ጥናት የተገኘው አዲስ የባሕሪ ለውጥ ከገጽ 61 እንደምንመለከተው ለውጡ የተጠኚ ቡድኑ ውጤት /Experimented Group/ ከጥብቅ ቡድኑ ውጤት /Control Group/ ጋር ሲነፃፀሩ የተጠኚ ቡድኑ ውጤት ብልጫ አሳይቷል::

ይህም ማለት በዚህ ጥናት ተጠኚ ቡድኑ በተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል አቀራረብ ስልት በክፍል ውስጥ ጽሑፉን ከራሱ አእምሯዊ እውቀት እና ሥነ-ልሣናዊ እውቀት ጋር በማገናኘት በሂደት ከጓደኛው እና ከመምህሩ ጋር በመተጋገዝና በመረዳዳት ጽሑፉን እንደሚፈልገው ጉዳይ የራሱን የአነባበብ ስልት እንዲጠቀም እና እንዲማር በመደረጉ ውጤቱ ፖዘቲቭ ሲሆን ይታያል::

በትምህርት የቀረበው ቋንቋ ኢአፍ-መፍቻ ቋንቋ ለሆኖቸው ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል ከጥንታዊ

የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል ጋር ሲነፃፀር የተሻለ መሆኑን ይህ ጥናት በጥቂቱም ቢሆን ይጠቁማል። ለትምህርት የቀረበው ቋንቋ ኢአፍ-መፍቻ ቋንቋ ለሆነው ተማሪ ያለበትን የሥነ-ልሣናዊ ችግር፣ ብዙ ቃላትን የማወቅን ችግር፣ የቋንቋውን ተናጋሪ ሕብረተሰብ ባሕልና ወግ ያለማወቅን ችግር አቃሎ ተማሪው የተጻፈውን ጽሑፍ በቀላሉ እንዲረዳ በማድረግ በኩል ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል ከጥንታዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል ጋር ሲነፃፀር የተሻለ መሆኑን የዚህ ጥናት ውጤት መነሻ ፍንጭ ጠቁሟል።

5.2 መደምደሚያ

በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን እንደ ኢአፍ-መፍቻ ቋንቋ ሲማሩ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር «በተራክቧዊ» የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል ተጠቅሞ ማስተማር አስተዋጽኦ ይኖረዋል? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ሲባል ጥናቱ ተከናውኗል።

የዚህ ጥናት ውጤት የሚጠቁመው ቢኖር የተገኘው የባሕሪ ለውጥ ዝም ብሎ የተገኘ ሳይሆን በተራክቧዊ ሞዴል ምክንያት የተገኘውን የባህሪ ለውጥ መሆኑን ነው። ተማሪው በሞዴሉ አማካኝነት በክፍል ውስጥ ጽሑፉንም ሆነ የራሱን አእምሯዊ እውቀት በሂደት በመጠቀሙ የባሕሪ ለውጥ ለማምጣት አመቺ ሁኔታ የፈጠረለት ይመስላል። ተማሪው ውጤት ተኮርን ከሂደት ተኮር ጋር በማገናኘት በተራክቧዊ ሥልት በመጠቀሙ የተሻለ ውጤት ላይ እንደደረሰ ይህ ጥናት ፍንጭ ሰጥቷል።

ይህ ጥናት በይዘቱ መጠነኛ ቢሆንም ተማሪው ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ ያለበት ሥነ-ልሳናዊ ችግርና የቋንቋውን ተናጋሪ ሕብረተሰብ ባሕልና ወግ በትክክል አሟልቶ ባለማወቅ ያለበት ችግር ምክንያት የቀረበለትን ጽሑፍ አንብቦ እንዲረዳ ከሌሎች የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴሎች በተሻለ ሁኔታ አንብቦ የመረዳት ክሂል በክፍል ውስጥ ከፍ ለማድረግ ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል የተሻለ መሆኑን መምህሩ እንዲጠቀምበት ይጠቁማል።

ለተማሪው ጽሑፉንና የራሱን አእምሮአዊ እውቀት /background knowledge/ እያገናኘ ከመጽሐፉ፣ ከጓደኛውና ከመምህሩ ጋር እየተጋገዘና እየተረዳዳ የሚማርበትን መንገድ ቢያመቻችለት ተማሪው አንብቦ የመረዳት ክሂሉን ሊያሻሽል እንደሚችል ለተማሪው ለመምህሩም ጠቃሚ ስልት መሆኑን ይህ ጥናት ለመነሻነትም ቢሆን ያመለክታል።

5.3 የመፍትሔ ሐሣቦች

ንባብን ለተለያዩ ጉዳዮች እንጠቀምበታለን። ንባብ ካለው ጠቀሜታ አንፃር ደግሞ ክሂሉን ከወዲሁ በትምህርት ቤት ማዳበር ይጠበቅብናል። ምንም እንኳ የንባብ ክሂል የሚዳብረው ብዙ በማንበብና በመለማመድ ቢሆንም መሠረታዊ የሆኑ አንብቦ የመረዳት ስልቶችን ግን ከወዲሁ በመደበኛ ትምህርት አዳብረን ለወደፊቱ በግላችን ልንገለገልባቸው የምንችላቸው ናቸው። እንግዲህ አንብቦ የመረዳት መንገዶችን ከወዲሁ በትምህርት ቤት ማዳበር አለብን ካልን ደግሞ በትምህርት ቤት የሚሰጠው አንብቦ የመረዳት ክሂል ትምህርት በዘመናዊ የቋንቋ ንድፈ-ሃሣብና የቋንቋ መማር ንድፈ ሃሣብ በተገነባ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴልን ተከትለን ትምህርቱን ተግባራዊ ማድረግ ይገባናል። የዚህ ጥናት ትኩረትም የነበረው ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል አንብቦ የመረዳትን ክሂል ለማዳበር ከሌሎች ሞዴሎች በተሻለ ሁኔታ ያለው አስተዋጽኦ ምን ሊሆን ይችላል? የሚለውን ለመፈተሽ አልሞ የተነሣ ሲሆን ጥናቱ ተከናውኖ የተሻለ ውጤት አሣይቷል። በመሆኑም በዚህ ጥናት መነሻነት ከተራክቧዊ የንባብ ክሂል አንፃር የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መጽሐፍ አንብቦ መረዳትን በተመለከተ ለሚያዘጋጁ፣ አንብቦ የመረዳትን ክሂል ለሚያስተምሩ፣ እንዲሁም ከዚያም አልፎ በሌሎች ቋንቋዎች አንብቦ የመረዳትን ክሂል በተመለከተ የማስተማሪያ መሣሪያ ለሚያዘጋጁና ለሚያስተምሩ ሞዴሉን ከተጠቀሙ፣

ሀ. ሥነ-ልሣንን በማስተማር በኩል

- ለትምህርት የቀረበው ቋንቋ ኢአፍ-መአቻ ቋንቋ ለሆናቸው ተማሪዎች ሞዴሉ ተማሪዎች ያለባቸውን ሥነ-ልሣናዊ ችግር ለመፍታት ሲል ጽሑፉን በክፍል ውስጥ በማቅረብ የድምጾችን አነባበብ፣ የቃላትን አመሰራረት፣ የሀረጎችንና የዓረፍተ ነገሮችን አወቃቀር ከጽሑፉ ለማስተማር በመሞከሩ፣

- የቃላትን ትርጉም ለማስተማር ጽሑፉንና አካባቢን በአውድነት በመጠቀም ተማሪው በግልና በቡድን በመሆን የራሱን አእምሯዊ እውቀት በሂደት እየተጠቀመ እንዲረዳና የራሱን መንገድ በማመቻቸት ለማስተማር በመሞከሩ፣

- ተማሪው ያለበትን ስዋሰዋዊ ችግሮች ለመፍታት ተውላጠ ስሞችን እያያዥ፣ ቃላትን፣ ሃረጎችን፣ የቃላትን ዓይነቶች ከጽሑፉ ውስጥ

ከአገባባቸውና ከአጠቃቀማቸው አንፃር ለመረዳት ጽሑፉን በአውድነት እንዲጠቀም በማስቻሉ፤

ለ. የንባብ ፍጥነትን በማሻሻል ረገድ

- የንባብ ትምህርትን በደረጃ በመክፈል በቅድመ-ንባብ ደረጃ ተማሪው የራሱን አእምሯዊ እውቀት በሂደት እየተጠቀመ በፍጥነት በገረፍ ገረፍ ስልት እና በአሰሳ የአነባበብ ስልት ተማሪው እየተጠቀመ የጽሑፉን አጠቃላይ መልዕክት በአጭሩ የሚረዳበትን ስልት አመቻችቶ ክሂሉን ለማዳበር በመሞከሩ፤

ሐ. የጽሑፉን መልዕክት በትክክል በመረዳት በኩል

- ተማሪው የጽሑፉን የአጻጻፍ ስልት /Rhetorical organization/ እና የጽሑፉን መልዕክት እንዲሁም ጸሐፊው መልዕክቱን ለማስተላለፍ የተጠቀመባቸውን የተለያዩ አገላለጾች ለመረዳት በለሆሣስ የአነባበብ ስልት እየተጠቀመ ጽሑፉን ረጋ ብሎ በማንበብ የሚፈልገውን ጉዳይ በትክክል እንዲረዳ መንገድ በማመቻቸቱ፤

መ. አዲሱን እውቀት ቀደም ሲል ካለው እውቀት ጋር በማያያዝ በኩል

- ሞዴሉ በድህረ-ንባብ ደረጃ ተማሪው ጽሑፉን በሂደት አንብቦ በትክክል ተረድቶ ያገኘውን አዲስ እውቀት ቀደም ሲል ጽሑፉ ከቀረበበት ርዕሰ ነገር ጋር ካለው እውቀት ጋር በማያያዝ በኩል መንገዶችን ያመቻቻል:: ለምሣሌ ተማሪው ከጽሑፉ ውስጥ ያገኘውን አዲስ እውቀት እውነታውን ለመለካት ከራሱ አካባቢ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማያያዝ የአዲሱን እውቀት እውነታነቱን እንዲገመግመውና የተሻለውን እንዲደርስበት ለማስቻል በመሞከሩና

- የፀሐፊውን ስሜትና ፍላጎት እንዲሁም አመለካከቱን የሚገልጹ ቃላትንና አባባሎችን ከጽሑፉ በመፈለግና ተማሪው በቡድን እየተወያየ ፀሐፊው ለምን እንደተጠቀመባቸው የራሱን አስተያየት እንዲሰጥ እድል ሰጪ በመሆኑ፤

ሞዴሉን ብንገለገልበት ጠቀሜታ ሊያስገኝልን ይችላል::

በአጠቃላይ ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል ፀሐፊው በጽሑፉ አማካኝነት ያስተላለፈውን ሐሣብና የአንባቢውን አእምሯዊ እውቀት በጽሑፉ አማካኝነት በሂደት በማገናኘት አንባቢው ጽሑፉን እንደሚፈልገው ጉዳይ የራሱን የአነባበብ ስልት እና የራሱን ችሎታ ተጠቅሞ እንዲረዳ በማድረግ በኩል ድርሻ እንዳለው ይህ ጥናት ጠቁሞናል:: ምንም እንኳ በርግጥ የተጠኚ ተማሪዎች ቁጥር በጥናቱ ከታቀፈው ከጠቅላላው ተማሪ ቁጥር ሲነፃፀር አነስተኛ መሆን፣ ምናልባትም የጥናቱ መሣሪያዎች ፍጹም አስተማማኚ አለመሆንና ከአለ የጊዜ እጥረት አኳያ በሌላ መሣሪያ ባለመደገፉ ሙሉ በሙሉ ትክክለኛ ውጤት አስገኝቷል ተብሎ ባይታሰብም ከዚህ ጥናት ውጤት በመነሳት በተለይም አማርኛ ቋንቋ ኢአፍ-መፍቻ ቋንቋ ለሆኖችው ያለባቸውን ሥነ-ልሣናዊ ችግርና የቋንቋውን ተናጋሪ ማኅበረሰብ ባሕልና ወግ በትክክል ባለማወቅ ምክንያት ጽሑፉን ለመረዳት ያለባቸውን ችግር ተራክቧዊ ሞዴል ሊረዳቸው ስለሚችል አንብቦ የመረዳትን ክሂል በክፍል ውስጥ ለማስተማር በሞዴሉ ላይ ተከታታይ ጥናት ከተከናወነ በኋላ ብንገለገልበት ለተሻለ ውጤት ሊያደርሰን ይችላል::

ዋቢ መጻሕፍት

Bailey, D.K 1987. Methods of Social Research. New York: A Division of Macmillan.

Brown, H.D. 1994. Principles of Language Learning and Teaching. Englewood Cliffs: Prentic Hall Reprints.

_____ 1994. Teaching by Principles: An Interactive Approaches to Language Pedagogy. Englewood Cliffs: Prentic Hall Reprints.

Brumfit, C. 1984. A Communicative Methodology of Language Teaching. Cambridge: Cambridge University Press.

Carrell, P. 1983a. "Three Components of Background Knowledge in Reading Comprehension." Language Learning Journal. Vol. 33/2; pp. 183-228.

_____ 1983b. "Background Knowledge in Second Language Comprehension." Language and Communication. Vol. 2. pp. 25-34.

_____J. Devine, and D. Eskey. 1988. Interactive Approaches to Second Language Learning. Cambridge: Cambridge University Press.

Ceindieore and Cizco. 1967. Statistical Methods. Iowa: Iowa State University.

Cellce Murcia. 1991. Teaching English as a Second or Foreign Language. Boston: Heinle Publisher.

Crocker, A.C. 1981. Statistics for the Teacher. Nefer-nelson: Antony Rowe Ltd., Chippenham, Wilts.

Davis, F. 1995. Introducing Reading. London: Penguin.

David, E. and William, G. 1988. "Interactive Models for Second Language Reading: Perspectives on Instruction." in P. Carrel. J., Devine and D. Eskey /eds./: Interactive Approaches to Second Language Reading. Cambridge: Cambridge University Press. pp. 223-238.

Devine, J. 1988. "A Case Study of Two Readers." In P. Carrell, J. Devine and D. Eskey /eds./: Interactive Approaches to Second Language Reading. Cambridge: Cambridge University Press. pp. 127-238.

Eskey, D.E. 1973. "A Model Program for Teaching Advanced Reading to students of English as a Second Language." Language Learning Journal. /23/ /2/ pp. 169-184.

_____ 1988. "Holding in the Bottom: An Interactive Approach to the Language Problems of Second Language Readers." In P. Carrell, J. Devine, and D. Eskey /eds./: Interactive Approaches to Second Language Reading. Cambridge: Cambridge. University Press.

Fires, C.C 1963. Linguistics and Reading. New York: Hot Rinehart and Winston.

Goodman, K. 1967. "Reading as a Psycholingustic Game." Journal of Reading Specialists. Vol. 6/1 pp. 126-135.

Grabe, W. 1988. "Reassessing the Term Interactive." In P. Carrell, J. Devine, and D. Eskey /eds./: Interactive Approaches to Second Language Reading. Cambridge: Cambridge University Press.

Gebre Medhin, Simon. 1984. "A Comparative Study of Two Second Language Teaching Approaches: The Language Acquisition and Conscious Rule Learning Approaches." A.A.U: M.A Thesis. /Unpublished/.

Grrellet, F. 1981. Developing Reading Skills: A Practical Guide to Reading Comprehension Exercises. Cambridge: Cambridge University Press.

Hailemikayl, Aberra. 1984. "A Communicative Approach Vs Traditional Approach to the Teaching of English Reading Comprehension." A.A.U M.A Thesis /unpublished/.

Jr., Jum, 1970. Introduction to Psychological Measurement New York: McGraw Hill Book.

Lado, R. 1964. Language Teaching: A Scientific Approach. New York: McGrow-Hill.

Mackay 1965. Language Teaching Analysis. London: Green and Co. Ltd. 48 Governor Street.

Nachmias, F.C 1992. Research Methods in Social Sciences. London: Division of Hodder Headline.

Nuttall, C. 1982 Teaching Reading Skills in a Foreign Language. London: Heineman.

_____ 1996. Teaching Reading Skills in a Foreign Language. London: Heineman.

Nunan, D. 1991a. "Communicative Tasks and Teaching Language Curriculum." TESOL QUARTERLY /25/ /2/. pp. 279-296.

Perfetti, C.A 1985. Reading Ability. New York: Oxford.

Richard, J.C., and Rodgers, 1984. Approaches and Methods in Language Teaching. Cambridge: Cambridge University Press.

_____ /1987/. The Context of Language Teaching. Cambridge: Cambridge University Press.

_____ 1990. The Language Teaching Matrix. Cambridge: Cambridge University Press.

Rigg, P. 1988. "The Miscue-ESL Project." In Carrell, P., J. Devine and D.E Eskey /eds./: Interactive Approaches to Second Language Reading. Cambridge: Cambridge University Press. pp. 206-221.

Rumelhart, D.1977. Towards an Interactive Model of Reading: In Attention and Performance. Vol. VI, S. Dorinc /eds./, New York: Academic Press, pp. 573-603.

Savignon, S. 1990. "Communicative Language Teaching: State of the Art." TESOL QUARTERLY. /251/2/. pp. 261-277.

Schesser, O. 1976. Objective Based Reading. Henle Park: Addition Wesley Publishing Company.

Stanovich, K. 1980. "Toward an Interactive. Compensatory Model of Individual Differences in the Development of Reading Fluency." Reading Research Quarterly /16/ pp. 32-71.

_____ 1981b. Attention and Automatic Context Effects. In Lesgold and Perfetti /eds./ pp. 241-267.

_____ 1984. "The Interactive Compensatory Model of Reading: A Confluence of Development, Experimental, and Educational Psychology." Remedial and Special Education /5/: pp. 313-345.

Stern, H.H. 1985. Fundamental Concepts of Language Teaching. Oxford: Oxford University Press.

Stoller, F. 1984. "Implications of the Interactive Model of Reading for Recognition Skills Instruction." Paper Presented at the 18th TESOL conference, Houston March, pp. 7-15.

Ulijn, J. 1980. "Foreign Language Reading Research: Recent Trends and Future Prospects." Journal of Research in Reading /3/ pp. 17-37.

Wallace, C. 1992. Reading: Language Teaching a Scheme for Teacher Education. Oxford: Oxford University Pres.

Waltz, D., and J. Pollak. 1985. "Massively Parallel Parsing: A Strong Interactive Model of Natural Language Interpretation." Cognate Science. pp. 51-74.

Weber, R.H. 1984. "Reading." United States of Annual Review of Applied Linguistics. /4/ pp 111-123.

Williams, E. 1984. Reading in the Language Classroom. London: Macimilan Publisher.

_____ 1996. "Reading in Two Languages at Year Five in Primary School." Applied Injusties. /17/ /2/ PP. 183-207.

መስፍን ሃብተማርያም::1976:: <u>የቡና ቤት ሥዕሎችና ሌሎችም ወጎች</u>:: አዲስ አበባ:: ሴንትራል ማተሚያ ቤት:: ገጽ፣ 12-22::

ማረው ዓለሙ:: 1987:: «በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ክፍል በሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች በግልና በቡድን የመጻፍ በሳል ድርሰቶች ንጽጽራዊ ጥናት::» ለማስተርስ ቴሲስ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ:: አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ:: /ያልታተመ/::

ማስተዋል ውቢቱ:: /1989/:: የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ:: ለማስተርስ ቴሲስ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ::

ማሞ ውድነህ:: 1982:: <u>ማህበርተኞች</u>:: ንግድ ማተሚያ ቤት:: አዲስ አበባ:: ገጽ 6-9::

ስዩም ከበደ:: 1988:: «ድርሰትን በሂደታዊ ዘዴ /Process Approach/ በዘጠነኛ ክፍል ማስተማር ያለው ተግባራዊነት::» ለማስተርስ ቴሲስ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት:: /ያልታተመ/::

በየነ ማሞ:: 1985:: «በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች የቋንቋን ክሂሎት የሚያዳብሩ ናቸው?» ለማስተርስ ቴሲስ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ:: አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ:: ድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት:: /ያልታተመ/::

ተስፋዬ ሸዋዬ:: 1986:: <u>አንብቦ መረዳትና የመጻፍ ችሎታን ማዳበር</u>:: አዲስ አበባ:: ት.መ.ማ.ድ::

_____ :: 1981:: «ሥነ-ልሳንና ቋንቋን ማስተማር::» የማስተማሪያ ጽሑፍ:: አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ:: /የተባዛ/::

ትምህርት ሚኒስቴር:: 1987:: <u>መጽሔተ ትምህርት</u>:: አዲስ አበባ:: በትምህርት ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት ክፍል የሚዘጋጅ:: ቅጽ /1/ /1/:: ገጽ 81::

_____ 1984:: <u>የ11ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ሲለቨስ</u>:: አዲስ አበባ:: ት.መ.ማ.ድ::

ከበደ ደስታ:: 1960:: <u>ነጭ ጥለት በጥቁር</u> ላይ:: አዲስ አበባ:: ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት:: ገጽ፣ 11-12::

ጌታቸው አዱኛ:: 1986:: «ለአሥረኛ ክፍል የተመረጡ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ምንባቦት የብቃት ደረጃ::» ለማስተርስ ቴሲስ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ:: አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ:: /ያልታተመ/::

ግርማቸው ተክለሃዋርያት:: <u>አርአያ</u>:: አዲስ አበባ ብርሃንና ሠላም ማተሚያ ቤት:: ገጽ፣ 55-58::

የውሃ ሃብት ሚኒስቴር::1990:: <u>ውሃና ልማት</u>:: አዲስ አበባ:: በውሃ ሃብት ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነት የሚታተም ቅጽ 1፣ ቁጥር፣ 2:: ገጽ፣ 11-15::

መዳዬ ቃላት (Glossary)

Brain storming	=	ሐሣብን እንደመጣ ማስፈር
Background knowledge	=	አእምሯዊ እውቀት /ደራዊ፣ እውቀት/
Cloze test	=	የግንዛቤ ፈተና
Cognitive psychology		አእምሯዊ ሥነልቦና
Control group	=	ጥብቅ ቡድን
Context	=	አውዳዊ ፍች
Definition	=	ብየኔ /ግላጼ/
Degree of freedom	=	የነፃነት ደረጃ
Drilling	=	ልምምድ
Experimental group	=	ተጠኚ ቡድን
Fluency	=	አንደበተ ርእዑነት
Motivation	=	መቀስቀስ
Pre-reading	=	ቅድመ-ንባብ
Post-reading	=	ድህረ-ንባብ
Reliability	=	አስተማማኚነት
Reliability coefficient	=	የአስተማማኚነት ዋጋ
Scanning	=	የአሰሳ የአነባበብ ስልት
Skimming	=	ገረፍ ገረፍ የአነባበብ ስልት
Significant difference	=	የባሕሪ ልዩነት
Social context	=	ማህበራዊ አውድ
Standard deviation	=	የልይይት ብዜት
T-critical	=	የ«ቲ» ወሳኚ ዋጋ
T-value	=	የ«ቲ» ዋጋ
T-tabulated	=	በ«ቲ» ሠንጠረዥ የሚገኘው ዋጋ
Validity	=	ተገቢነት
While reading	=	ጥልቀት ንባብ

አባሪ «ሀ»

ለተጠኚ ቡድኑና ለጥብቅ ቡድኑ የተዘጋጁ የማስተማሪያ መሣሪያዎች

አባሪ «ሀ-1»

ለተጠኚ /Experimental Groups/ ቡድኑ የተዘጋጀ የማስተማሪያ መሣሪያ

ቅድመ ምንባብ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከራስህ ልምድና እውቀት በመነሳት በቡድንህ አማካይነት ከተወያየህ በኋላ ለክፍል ጓደኞችህ በንግግር ግለጽ /7 ደቂቃ/

   ሀ. ስለ ውሃ አጠቃላይ የምታውቀውን ዘርዝር።

   ለ. አንተ በምትኖርበት አካባቢ ያለው ህብረተሰብ ለመጠጥ የሚሆነውን ውሃ ከየት ያገኛል?

   ሐ. በጥያቄ «ለ» መልስህ ከምንጭ ወይም ከኩሬ ከሆነ ህብረተሰቡ እንዴት እንደሚጠቀም ግለጽ።

   መ. የምንጭ ውሃን በመጠጣት ህብረተሰቡ በቀላሉ ለውሃ ወለድ በሽታዎች ሊጋለጥ እንደሚችል ታውቃለህ፤ ከነዚህ ውሃ ወለድ በሽታዎች በመራቅ ህብረተሰቡ መን ማድረግ አለበት ብለህ ታስባለህ?

   ሠ. ከምንጭ ወይም ከኩሬ የተቀዳን ውሃ እንዳለ መጠቀም ለበሽታ አምጪ ተህዋስያን መጋለጥ ነው፤ ስለዚህ ከነዚህ ተህዋስያን ለማምለጥ አንደኛው መንገድ ውሃን አፍልቶ መጠጣት ነው። ውሃን እንዴት አፍልተንና አቀዝቅዘን መጠጣት እንዳለብን ግለጽ።

2. የሚከተሉትን ቃላት በጥንቃቄ ተመልከተህ ጥንድ በመሆን ከተወያየህ በኋላ የምታውቃቸውን ቃላት በተሰጠው ሳጥን ውስጥ «√» ምልክት አስቀምጥ የማታውቃቸውን ቃላት ደግሞ በተሰጠው ሣጥን «X» ምልክት በመጠቀም አመልክት።

ሀ.	ፍቱን	☐	ረ.	ተህዋስያን	☐
ለ.	ተከበለ	☐	ሰ.	ጣዕም	☐
ሐ.	ማንቆርቆሪያ	☐	ሸ.	ተከድኖ	☐
መ.	ብረት ድስት	☐	ቀ.	ውሃ ወለድ	☐
ሠ.	ገንቦ	☐	በ.	ተቀቅሎ	☐

ምንባብ አንድ

ውሃን አፍልቶ መጠቀም

ውሃን አፍልቶ መጠቀም በውሃ ውስጥ የሚገኙ ማናቸውም በሽታ ለማጥፋት ፍቱን ዘዴ ነው። የሚጣራው ውሃ በመልኩ ንፁህ ወይም ድፍርስ ወይም በከፊለ የተበከለ ወይም በጣም የተከበለ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ ሁሉም ዓይነት ውሃ ለማፍላት የሚገኘው ውጤት ተመሳሳይ ነው።

እንዲጣራ የሚፈለገው ውሃ በማንቆርቆሪያ በብረት ድስት ወይም በገንቦ ማፍላት ይቻላል። ውሃን ማፍላት ማለት ለጥቂት ጊዜ እሳት ላይ ጥዶ ከዚያም አቀዝቅዞ መጠቀም ማለት አይደለም። ለጤና ጠንቅ የሆኑ ተዋስያንን ለማጥፋት መጀመሪያ ውሃው ለጥቂት ደቂቃዎች የፈላል፣ ከዚያም እንዲቀዘቅዝ ይደረግና እንደገና ከ15-20 ደቂቃዎች እየተፍለቀለቀ እንዲፈላ ከተደረገ በኋላ አቀዝቅዞ መጠቀም ነው። ሌላው ሊተኮርበት የሚገባውጉዳይ ውሃው የተፈላበት እቃ ለሌላ አገልግሎት እንዳይውል ማድረግ ነው። ውሃው በዚያው በተፈላበት እቃ ውስጥ እንዲቀዘቅዝና በደንብ ተከድኖ እንዲቆይ ቢደረግ የውሃው ንጽህና እንደተጠበቀ ይቆያል። ይህን ማድረግ ካለተቻለ በፊላ ውሃ ተቀቅሎ በታጠበ ዕቃ ውስጥ ውሃው ከተገለበጠ በኋላ በሚገባ ተከድኖ አገልግሎት ላይ መዋል ይኖርበታል ውሃን ማፍላት በውሃ ውስጥ የሚሟሙ ጋዞችን በተለይም የተቃጠለን አየር ከውሃ ውስጥ ስለሚያወጣው የተፈላ ውሃ ጣዕሙ ይለወጣል። የውሃውን ጣዕም ለማሻሻል ሲባል ከእቃ ወደ እቃ የማገላበጡ

ተግባር ውሃውን እንደገና እንዲበከል የሚያደርገው ስለሆነ ከዚህ ዓይነቱ ድርጊት አቆጠብ ያስፈልጋል። የተከበለ ውሃን ከመጠጣት ጣዕም የሌለው ንጹህ ውሃ መጠጣቱ ይመረጣል።

ተፈለቶ ከቀዘቀዘ የውሃ እቃ ውስጥ ውሃው በሚቀዳበት ጊዜ በጣሳ እየተጠለቀ መሆን የለበትም። የዚህ ዓይነቱ አቀዳድ በተበከለ ጣሳ ምክንያት ውሃው ወዲያውኑ ስለሚከበል ያ የተደከመበት ተግባር ሁሉ ከንቱ ይሆናል።

የውሃው እቃ ውሃን ለማንቆርቆር የሚረዳ ሊዘጋና ሊከፈት የሚችል ጡት ወይም ቀዳዳ ያስፈልገዋል። ከሌለው ግን ውሃውን መቅዳት ሲፈለግ እቃውን ካስጐነበሱ በኋላ በጥንቃቄ ማንቆርቆር ያስፈልጋል።

በአጠቃላይ ውሃን በማፍላትና ንጽህናውን ጠብቆ በመጠቀም ውሃ ወለድ በሽታዎችን መከላከል ይቻላል። ውሃን ከማፍላት ዘዴ ሌላ ኬሚካሎችን በመጠቀም ውሃውን ከጤና ጠንቅ ተህዋስያን ነፃ ማድረግ ይቻላል።

ምንጭ፣ ውሃና ልማት፣ መስከረም 1990 ዓ.ም. ከቁጥር ሁለት ከገጽ 11-15 የተወሰደ።

1. ምንባቡን በፍጥነት ገረፍ ገረፍ በማድረግ ከአነበብህ በኋላ ድምር ዓረፍተ ነገሮችን ጨርሰህ ጽፈህ ለክፍል ጓደኞችህ አንብብላቸው። /10 ደቂቃ/

ሀ. ውሃን ማፍላት ማለት _____

ለ. በውሃ ውስጥ ለጤና ጠንቅ የሆኑ ተህዋስያንን ለማጥፋት ይረዳል _____

ሐ. ውሃን ማፍላት በውሃ ውስጥ የሚሟሙ ጋዞችን በተለይም የተቃጠለን ዓየር ከውሃ ውስጥ ስለሚያወጣው _____

መ. ውሃው በዚያው በተፈላበት እቃ ውስጥ እንዲቀዘቅዝ ቢደረግ_____

ሠ. የተፈላ ውሃን ጣዕም ለማሻሻል ሲባል ከእቃ ወደ እቃ የማገላበጡ ተግባር ውሃውን እንደገና እንዲበከል የሚያደርገው ስለሆነ_____

ረ. የተከበለን ውሃ ከመጠጣት _____

ሰ. የውሃውን እቃ ውሃን ለማንቆርቆር የሚረዳ ሊዘጋና ሊከፈት የሚችል ጡት ወይም ቀዳዳ ያስፈልገዋል ከሌለው ግን _____

ሸ. ውሃን ከማፍላት ዘዴ ሌላ _____

ቀ. በአጠቃላይ ውሃን በማፍላትና ንጽህናውን ጠብቆ በመጠቀም _____

2. ውሃን አፍልቶ መጠቀም የሚለውን ምንባብ በፍጥነት ገረፍ ገረፍ አድርገህ አንብብ፤ በአነበብኸው ላይ ጥንድ በመሆን በመወያየት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃልህ መልስ /15 ደቂቃ/

ሀ. የአንቀጽ አንድ ፍሬ ሀሳብ _____

ለ. የአንቀጽ ሁለት ፍሬ ሀሳብ _____

ሐ. የአንቀጽ ሶስት ፍሬ ሀሳብ _____

መ. የአንቀጽ አራት ፍሬ ሀሳብ _____

ሠ. የአንቀጽ አምስት ፍሬ ሀሳብ _____

ረ. የአንቀጽ ስድስት ፍሬ ሀሳብ _____

ሰ. የአንደኛው አንቀጽ መንደርደሪያ ዓረፍተ ነገር _____

ሸ. ውሃን ለማጣራት ከማፍላት በተጨማሪ ሌላ ዘዴ መኖሩን የሚገልጸው አንቀጽ _____

ቀ. የሁለተኛው አንቀጽ መንደርደሪያ ዓረፍተ ነገር _____

በ. የሶስተኛው አነቀጽ መንደርደሪያ ዓረፍተ ነገር _____

ተ. የአራተኛው አንቀጽ መንደርደሪያ ዓረፍተ ነገር _____

ቸ. የአምስተኛው አንቀጽ መንደርደሪያ ዓረፍተ ነገር _____

ኀ. የስድስተኛው አንቀጽ መንደርደሪያ ዓረፍተ ነገር _____

3. ከዚህ በታች የተሰጠውን ምንባብ በጥንቃቄ ካነበብህ በኋላ ከራስህ ልምድና እውቀት በማነሳት ጥንድ በመሆን እየተወያየህ ተስማሚ የሆነውን ቃል ወይም በተሰጠህ በዶ ቦታ ላይ ጻፍ። /15 ደቂቃ/

ውሃን አፍልቶ መጠቀም በውሃ ውስጥ የሚገኙ _____በሽታ ለማጥፋት ፍቱን ዘዴ ነው። የሚጣራው ውሃ _____ በመልኩ ንጹህ ወይም ድፍርስ ወይም በከፊለ _____ ወይም በጣም የተበከ ሊሆን ይችላል። _____ ሁሉንም ዓይነት ውሃ በማፈላት _____ ውጤት ተመሳሳይ ነው።

እንዲጣራ የሚፈለገው ውሃ በማንቆርቆሪያ፤ በብረት ድስት ወይም በገንቦ_____ ይቻላል። ውሃን ማፍላት ማለት ለጥቂት ጊዜ _____ ላይ ጥዶ ከዚያም አቀዝቅዞ መጠቀም ማለት አይደለም። _____ ጠንቅ የሆነ ተህዋስያንን ለማጥፋት መጀመሪያ ውሃው_____ ደቂቃዎች ይፈላል ከዚያም እንዲቀዘቅዝ ይደረግና እንደገና ከ_____ደቂቃዎች እየተፍለቀለቀ እንዲፈላ ከተደረገ በኋላ አቀዝቅዞ መጠቀም_____ ሌላው ሊተኮርበት የሚገባው ጉዳይ ውሃው የተፈላበት _____ ለሌላ አገልግሎት እንዳይውል ማድረግ ነው። ውሃው _____ በተፈላበት እቃ ውስጥ እንዲቀዘቅዝና በደንብ ተከድኖ _____ እንዲቆይ ቢደረግ የውሃው ንጽህና እንደተጠበቀ ይቆያል። _____ማድረግ ካልተቻለ በፈላ ውሃ ተቀቅሎ በታጠበ _____ ውስጥ ውሃው ከተገለበጠ በኋላ በሚገባ ተከድኖ _____ አገልግሎት ላይ መዋል ይኖርበታል።

ውሃን ማፍላት በውሃ ውስጥ የሚሟሙ ጋዞችን _____ የተቃጠለን አየር ከውሃ ውስጥ ስለሚያወጣቸው የተፈላ _____ጣዕሙ ይለወጣል። የውሃውን ጣዕም ለማሻሻል ሲባል ከ_____ወደ እቃ የማገላበጡ ተግባር ውሃውን እንደገና እንዲበክል_____ ስለሆነ ከዚህ ዓይነቱ ድርጊት መቆጠብ ያስፈልጋል _____ ውሃን ከመጠጣት ጣዕም የሌለው ንጹህ ውሃ መጠጣቱ _____::

ተፈልቶ ከቀዘቀዘው የውሃ እቃ ውስጥ ውሃው በሚቀዳበት _____ ጊዜ በጣሳ እየተጠለቀ መሆን የለበትም የዚህ _____ አቀዳድ በተከበለ ጣሳ ምክንያት ውሃው ወዲያውኑ _____ ያ የተደከመበት ተግባር ሁሉ ከንቱ ይሆናል።

የውሃው እቃ ውሃን ለማንቆርቆር የረዳ ሊዘጋና _____ የሚችል ጡት ወይም ቀዳዳ ያስፈልገዋል። ከሌላው_____ ውሃውን ሲፈለግ እቃውን ካስገነበሱ በኋላ በጥንቃቄ_____ ያስፈለጋል።

በአጠቃላይ ውሃን በማፍላትና ንጽህናውን ጠብቆ በመጠቀም _____ ወለድ በሽታዎችን መከላከል ይቻላል። ውሃን ከማፍላት _____ ሌላ ኬሚካሎችን በመጠቀም ውሃውን ከጤና ጠንቅ ተህዋስያን _____ ማድረግ ይቻላል።

4. «ውሃን አፍልቶ መጠቀም» የሚለውን ምንባብ በአሰላ የአነባበብ ስልት አንብበህ በሚከተሉት ቃላት ጥንድ በመሆን በመወያየት ተቃራኒያቸውን ከምንባቡ እየፈለግህ ለክፍል ጓደኞችህ ተናገር /የተሰጠ ጊዜ 15 ደቂቃ/

ሀ. «ንፁህ» ለሚለው ቃል ተቃራኒ ሊሆን የሚችለው ቃል ከአንቀጽ አንድ ውስጥ _____የሚለው ቃል ነው።

ለ. «በከፊል የተበከለ» የሚለው ሀረግ ተቃራኒ ሊሆን የሚችለው ሀረግ ከአንቀጽ አንድ ውስጥ _____ የሚለው ሀረግ ነው።

ሐ. «ብረት ድስት» ለሚለው ቃል በይዘቱ ተቃራኒ ሊሆነው የሚችለው ከአንቀጽ ሁለት ውስጥ _____የሚለው የእቃ ዓይነት ነው።

መ. «ጣዕም የሌለው የተከበለ ውሃ» ለሚለው ሀረግ ተቃራኒ ሊሆን የችለው ሀረግ በአንቀጽ አራት ውስጥ _____የሚለው ነው።

ሠ. «ሊዘጋ» ለሚለው ሀረግ ተቃራኒ ሊሆን የሚችለው ሀረግ ከአንቀጽ ስድስት ውስጥ _____የሚለው ሀረግ ነው።

5. የቀረበልህን ምንባብ በአሰላ የአነባበብ ስልት ካነበብህ በኋላ በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የጐደለውን ቃል ጥንድ በመሆን ከተወያየህ በኋላ ለክፍል ጓደኞች ተናገር /15 ደቂቃ/

ሀ. ውሃን ለማጣራት በ_____፣ _____እና_____ ማፍላት ይቻላል።

ለ. ውሃ በሚገባ ለመፍላት የሚወስደው ጊዜ _____ነው።

ሐ. የተፈላ ውሃ ጣዕሙ የሚቀንሰው _____ የሚባለው ጋዝ ከውሃው ውስጥ ወጥቶ ሲያልቅ ነው።

መ. ተፈልቶ የቀዘቀዘውን ውሃ በ_____መቅዳት ውሃውን እንደገና እንዲበክል ማድረግ ነው።

ሠ. ውሃን አፍልቶ መጠቀም የሚለው ምንባብ የተወሰደው ከ_____ነው።

6. ከዚህ በታች የተሰጡትን አንቀጾ ቅደም ተከተላቸው ተዛብቷል በተዛቡት አንቀጾች ላይ በቡድን ከተወያየህ በኋላ አንቀጾቹ አንድ የተሟላ ሃሳብ እንዲሰጡ አድርገህ አስተካክለህ ጻፍ:: /10 ደቂቃ/

አንቀጽ 1: እንዲጣራ የሚፈለገው ውሃ በማንቆርቆሪያ በብረት ድስት ወይም በገንቦ ማፍላት ይቻላል:: ውሃን ማፍላት ማለት ለጥቂት ጊዜ እሳት ላይ ጥዶ ከዚያም አቀዝቅዞ መጠቀም ማለት አይደለም:: ለጤና ጠንቅ የሆኑ ተህዋስያንን ለማጥፋት መጀመሪያ ውሃው ለጥቂት ደቂቃዎች ይፈላል፣ ከዚያም እንዲቀዘቅዝ ይደረግና ለ15-20 ደቂቃዎች እየተፍለቀለቀ እንዲፈላ ከተደረገ በኋላ አቀዝቅዞ መጠቀም ነው::

2. ውሃን ማፍላት በውሃ ውስጥ የሚሟሙ ጋዞችን በተለይም የተቃጠለን አየር ከውሃ ውስጥ ስለሚያወጣው የተፈላ ውሃ ጣዕሙ ይለወጣል የውሃውን ጣዕም ለማሻሻል ሲባል ከእቃ ወደ እቃ የማገላበጡ ተግባር ውሃውን እንደገና እንዲበከል የሚያደርገው ስለሆነ ከዚህ ዓይነቱ ድርጊት መቆጠብ ያስፈልጋል:: የተከበለ ውሃን ከመጠጣት ጣዕም የሌለው ንጹህ ውሃ መጠጣቱ ይመረጣል::

3. ውሃን አፍልቶ መጠቀም በውሃ ውስጥ የሚገኙ ማናቸውም በሽታ ለማጥፋት ፍቱን ዘዴ ነው የሚጣራው ውሃ በመልኩ ንጹህ ወይም ድፍርስ በከፊል የተከበለ ወይም በጣም የተበከለ ሲሆን ይችላል:: ይሁን እንጂ ሁሉንም ዓይነት ውሃ በማፍላት የሚገኘው ውጤት ተመሳሳይ ነው::

4. ሌላው ሊተኮርበት የሚገባው ጉዳይ ውሃው የተፈላበት እቃ ለሌላ አገልግሎት እንዳይውል ማድረግ ነው:: ውሃው በዚያው በተፈላበት እቃ ውስጥ እንዲቀዘቅዝና በደንብ ተከድኖ እንዲቆይ ቢደረግ የውሃው ንጽሕና እንደተጠበቀ ይቆያል:: ይህን ማድረግ ካልተቻለ በፈላ ውሃ ተቀቅሎ በታጠበ እቃ ውስጥ ውሃው ከተገላበጠ በኋላ በሚገባ ተከድኖ አገልግሎት ላይ መዋል ይኖርበታል::

5. በአጠቃላይ ውሃን በማፍላትና ንጽህናውን ጠብቆ በመጠቀም ውሃ ወለድ በሽታዎችን መከላከል ይቻላል:: ውሃን ከማፍላት ዘዴ ሌላ ኬሚካሎችን በመጠቀም ውሃውን ከጤና ጠንቅ ተህዋስያን ነፃ ማድረግ ይቻላል::

6. የውሃው እቃ ውሃን ለማንቆርቆር የሚረዳ ሊዘጋና ሊከፈት የሚችል ጡት ወይም ቀዳዳ ያስፈልገዋል:: ከሌለው ግን ውሃውን መቅዳት ሲፈለግ እቃውን ካጐነበሱ በኋላ በጥንቃቄ ማንቆርቆር ያስፈልጋል:: ተፈልቶ ከቀዘቀዘ በውሃ እቃ ውስጥ ውሃውን በሚቀዳበት ጊዜ በጣሳ እየተጠለቀ መሆን የለበትም:: የዚህ ዓይነቱ አቀዳድ በተከበለ ጣሳ ምክንያት ውሃው ወዲያውኑ ስለሚበከል የተደከመበት ተግባር ሁሉ ከንቱ ይሆናል::

7. ውሃን አፍልቶ መጠቀም የሚለውን ምንባብ በድጋሚ በሉሆሳስ የአነባበብ ስልት አንብብ። በአነበብከው መሠረት በቡድንህ አማካኝነት ከተወያየህ በኋላ ከዚህ በታች በሰንጠረዥ ውስጥ የተሰጡትን ዓረፍተ ነገሮች መንደርደሪያ ዓረፍተ ነገር ወይም ዝርዝር ዓረፍተ ነገሮች መሆናቸውን ለይ። ዓረፍተ ነገሩ መንደርደሪያ ከሆነ መንደርደሪያ በሚለው ዓምድ ሥር በ «√» ምልክት አመልክት ዓረፍተ ነገሩ መዘርዝር ከሆነ መዘርዝር በሚለው ዓምድ ሥር በ «X» ምልክት አመልክት /7 ደቂቃ/

	ዓረፍተ ነገር	የዓረፍተ ነገሩ ዓይነት	
		መንደርደሪያ	መዘርዝር
ሀ.	የዚህ ዓይነቱ አቀዳድ በተከበለ ጣላ ምክንያት ውሃው ወዲያውኑ እንዲበከል ያደርገዋል።		
ለ.	እንዲጣራ ከፈለግን ውሃ በማንቆርቆሪያ፣ በብረት ድስት ወይም በገንቦ በእሳት ጥዶ ማፍላት ይቻላል።		
ሐ.	ለጤና ጠንቅ የሆኑ ተህዋስያንን ለማጥፋት በመጀመሪያ ውሃውን ለጥቂት ደቂቃዎች ማፍላት ከዚያም እንዲቀዘቅዝ ማድረግ።		
መ.	ውሃን ከማፍላት ዘዴ ሌላ ኬሚካሎችን በመጠቀም ውሃውን ከጤና ጠንቅ ተህዋስያን ነፃ ማድረግ ይቻላል።		
ሠ.	በአጠቃላይ ውሃን ማፍላት ንጽህናውን ጠብቆ በመጠቀም ውሃ ወለድ በሽታዎችን መከላከል ይቻላል።		

ምንባብ /While Reading/

8. የሚከተሉት ቃላትና ሀረጎች ውሃን አፍልቶ መጠቀም ከሚለው ምንባብ የወጡ ናቸው። ምንባቡን በግል በጥንቃቄ ካነበብህ በኋላ ለቃላቱና ለሀረጋቱ ከአገባባቸው አንፃር ሊይዙት የሚችሉትን ትርጉም ጥንድ በመሆን ተወያይተህ ለክፍል ጓደኞችህ ተናገር።

ሀ. «ፍቱን» /መስመር 1 / _____

ለ. «ተበክለ» /መስመር 2/ _____

ሐ. «ማንቆርቆሪያ» / መስመር 4/ _____

መ. «ብረት ድስት» / መስመር 4/ _____

ሠ. «ገንቦ» /መስመር 4/ _____

ረ. «ተህዋስያን» /መስመር 6/ _____

ሰ. «ጣዕም» / መስመር 16/ _____

ሸ. «ተከድኖ» /መስመር 11/ _____

ቀ. «ውሃ ወለድ» /መስመር 24/ _____

በ. «ተቀቅሎ» /መስመር 11/ _____

2. የሚከተሉትን ቃላት በዓረፍተ ነገሩ ውስጥ ካላቸው አገባብ አንፃር ሊሰጡት በሚችለው ፍቺ ላይ ጥንድ በመሆን ከተወያየህ በኋላ ትርጉማቸውን ለክፍል ጓደኞችህ ተናገር።

ሀ. ንጽህናው ያልተረጋገጠለትን ውሃ ከመጠጣታችን በፊት አፍልተን መጠቀሙ ከማንኛውም በሽታ አምጪ ተህዋስያን ለመከላከል <u>ፍቱን</u> ዘዴ ነው። በዚህ ዓረፍተ ነገር የተሠመረበት ቃል ትርጉም _____ ነው።

ለ. የምንጭ ወይም የኩሬ ውሃ በበሽታ አምጪ ተህዋስያን ሊበከል ስለሚችል በተቻለ መጠን ውሃውን አፍልተን መጠቀም አለብን:: ተህዋስያን የሚለው ቃል ትርጉም _____

ሐ. በዓረፍተ ነገር «ለ» ሊበከል የሚለው ሀረግ ትርጉሙ _____ ነው::

መ. የተፈላ ውሃ በጣዕሙ ካልተፈላ ውሃ ያነሰ ነው:: የተሰመረበት ሀረግ ትርጉሙ_____ ነው::

ሠ. ውሃ ከተፈላ በኋላ ተመልሶ በውሃ ወለድ በሽታዎች እንዳይበከል ውሃው የተፈላበት እቃ በሚገባ ተከድኖ መቀመጥ አለበት «ውሃ ወለድ» የሚለው ቃል ትርጉሙ _____ነው::

ረ. በዓረፍተ ነገር «ሠ» ውስጥ «ተከድኖ« የሚለው ቃል ተርጉሙ _____ ነው::

ሰ. በገጠር አካባቢ ውሃን አፍልተን ለመጠቀም የምንገለገልበት እንደ «ማንቆርቆሪያና ብረት ድስት» ስለማናገኝ የግድ ከሸክላ የተሠራን ገንቦ ለውሃ ማፍያነት መጠቀም አለብን:: «ማንቆርቆሪያ» የሚለው ስያሜ የሚወክለው የእቃ ዓይነት የተሠራበት ጉጥረ ነገር_____ ነው::

ሸ. በዓረፍተ ነገር «ሰ» ውስጥ ብረት ድስት የሚለው ስያሜ የሚወክለው የእቃ ዓይነት የተሠራበት ጉጥረ ነገር _____ ነው::

ቀ. በዓረፍተ ነገር «ሰ» ውስጥ ገንቦ የሚለው ስያሜ የሚወክለው የእቃ ዓይነት የተሠራበት ጉጥረ ነገር_____ነው::

በ. ጥሬ ስጋን ቀቅሎ በመብላት ከኮሶ ትል በሽታ መከላከል ይቻላል:: የተሠመረበት ቃል ትርጉም_____ ነው::

3. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አያያዥ ቃላትና ሀረጋት ውሃን አፍልቶ መጠቀም ከሚለው ምንባብ የወጡ ናቸው በነዚህ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት ደራሲው ምን ዓይነት ዓረፍተ ነገሮችን ለማያያዝ እንደተጠቀመባቸው ጥንድ በመሆን ከተወያየህ በኋላ እያንዳንዱ አያያዥ ቃልና ሀረግ ከአገባቡ አንፃር ያለውን ጥቅም ለክፍል ጓደኞችህ ተናገር::

ሀ. «ይሁን እንጂ» / መስመር 3/ _____

ለ. «ከዚያም» /መስመር 5/ _____

ሐ. «መጀመሪያ» /መስመር 6/ _____

መ. «በተለይ» /መስመር 12/ _____

ሠ. «ስለሆነ» / መስመር 15/ _____

ረ. «እንደገና» /መስመር 7/ _____

4. «ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አያያዥ ቃላትና ሀረጋት ከምንባቡ የወጡ ናቸው:: ከነዚህ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት ላይ ጥንድ በመሆን ከተወያየህ በኋላ በአንቀጹ ውስጥ በተሰጠው ባዶ ቦታ እያስገባህ ጽፈህ ለክፍል ጓደኞችህ አንብብላቸው::

መጀመሪያ	ስለሆነ	እንደገና
ከዚያም	ይሁን እንጂ	ነገር ግን

ከምንጭ ወይም ከኩሬ የተገኘ ውሃ መልኩ ንፁህ ወይም ድፍርስ ሊሆን ይችላል::_____ በውሃ ወለድ አምጭ ተህዋስያን ተሸካሚነታቸው የተለያዩ አይደሉም:: ከምንጭ ወይም ከኩሬ የተቀዳ ውሃ ከመጠጣቱ በፊት_____ ለጥቂት ደቂቃዎች በብረት ድስት ማፍላት _____ እንዲቀዘቅዝ ከተደረገ በኋላ

_____ ከ15-20 ደቂቃ ያህል እየተፍለቀለቀ እንዲፈላ ይደረጋል። ውሃን ማፍላት በውሃ ውስጥ ያሉትን ጋዞች ያሚሚል_____የተቃጠለ አየር ከውሃው ውስጥ ስለሚወጣ የውሃውን ጣዕም ሊቀንስ ይችላል_____ያልተፈላ ውሃ ከመጠጣት ጣዕም የሌለው የተፈላ ውሃ መጠጣቱ ተመራጪነት አለው _____ ሁላችንም በተቻለ መጠን ከምንጭና ከኩሬ የምናገኘውን ውሃ አፍልቶ መጠቀም ይጠበቅብናል።

5. ውሃን አፍልቶ መጠቀም የሚለውን ምንባብ በሉሆሳስ የአነባበብ ስልት ረጋ ብለህ ካነበብህ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቡድንህ አማካይነት በመወያየት በቃል መልስ።

ሀ. ውሃን አፍልቶ መጠቀሙ ጥቅሙ ምንድን ነው?_____

ለ. ውሃን ማፍላት ማለት ምን ማለት ነው? _____

ሐ. የሚጣራው ውሃ መልኩ ንፁህ የሆነውና ያልሆነው ከተፈላ በኋላ በመካከላቸው ልዩነት አለ?» ከሌለስ ለምን ይመስልሃል?»_____

መ. ውሃ ከተፈላ በኋላ እስኪቀዘቅዝ ድረስ ንጽው እንደተጠበቀ ለመቆየት የምንወስደው ርምጃ ምንድን ነው?_____

ሠ. ተፈልቶ የቀዘቀዘ ውሃ ጣዕሙ ለምን ይቀንሳል? _____

ረ. የቀዘቀዘውን ውሃ ለመጠጣት ብንፈለግ እንዴት መጠቀም እንዳለብን ግለጽ?_____

ሰ. የምንጭ ውሃን ከውሃ ወለድ በሽታዎች ለመከላከል ከማፍላት በተጨማሪ የተጠቀሰው ሌላው ዘዴ ምንድን ነው?_____

ሸ. ውሃን በሚገባ ለማፍላት የሚወስደው ጊዜ ስንት ነው?_____

ቀ. የምንባቡን አጠቃላይ መልእክት አጠቃሎ የያዘው ዓረፍተ ነገር የሚገኘው በስንተኛው አንቀጽ ነው? ዓረፍተ ነገሩን ጥቀስ _____

6. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ በመሆን ከተወያየህ በኋላ በምንባቡ መሠረት እውነት ወይም ውሸት በማለት መልስ መልስ ውሸት ከሆነ ምክንያትህን ግለጽ። መልሱ እውነት ከሆነ ያገኘህበትን አንቀጽ ስንተኛው ላይ እንደሆነ ግለጽ።

ሀ. ከምንጭ የተቀዳውን ውሃ መልኩ ንፁህ ከሆነ ማፍላቱ ትርፉ ድካም ነው።

_____

ለ. ከምንጭ የተቀዳ ውሃ መልኩ ንፁህ ይሁንም አይሁን ከተፈላ በኋላ የሚያሳየው ውጤት ተመሳሳይ ነው። _____

ሐ. ከምንጭ የተቀዳን ውሃ አንድ ጊዜ በማፍላት ብቻ ንፁህ ማድረግ ይቻላል።

_____

መ. ለመጠጥ የምንጠቀምባቸውን ውሃ ካፈላን በኋላ ከአንድ እቃ ወደ ሌላ እቃ የምናገላብጠው ከሆነ ውሃው ከመበከል አይድንም። _____

ሠ. የተፈላ ውሃ ጣዕሙ እንዲቀንስ ምክንያት የሚሆነው ከመጠን በላይ እንዲፈላ ሲደረግ ነው። _____

ረ. ውሃን አፍልተን የምንጠቀመው ለጣዕሙና ውሃ ወለድ በሽታዎችን ለመከላከል ሲባል ነው። _____

ሰ. የምንጭ ውሃን ከውሃ ወለድ በሽታዎች ለመከላከል ብቸኛው መንገድ አፍልቶ መጠቀም ነው። _____

ሸ. ከምንባቡ የምንረዳው ውሃን አፍልተን እንዴት ማቀዝቀዝ እንደምንችለው ብቻ ነው::_____

ቀ. እንደ ደራሲው አባባል ከሆነ ተፈልቶ የቀዘቀዘን ውሃ በጣሳ ጠልቆ መጠቀም መሞከር ፈጽሞ የተከለከለ ነው::_____

በ. ተፈልቶ ጣዕም የሌለው ውሃ ከመጠጣት ከምንጭ የተቀዳው ውሃ መልኩ ንፁህ ከሆነ መጠቀሙ ይመረጣል::_____

7. በሚከተሉት ጥያቄዎች በቡድንህ አማካይነት ከተወያየህ በኋላ በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ቁጥር መርጠህ ከፊደሉ በስተግራ በተሰጠህ ባዶ ቦታ ጻፍ::

___ ሀ. ውሃን አፍልቶ መጠቀም ዓላማው _____ ነው::

1. የውሃ ወለድ በሽታዎችን ለማጥፋት
2. የውሃ ወለድ በሽታዎችን ለማጥፋትና ጣዕሙን ለመጨመር
3. የውሃን መልክ ንፁህ ለማድረግ
4. የውሃ ወለድ በሽታዎችን ለማጥፋትና መልኩን ንፁህ ለማድረግ

___ ለ. ውሃን ማፍላት ማለት _____ ማለት ነው

1. ለጥቂት ጊዜ ብቻ እሳት ላይ ጥዶ ማውጣት
2. ከ15-20 ደቂቃ ብቻ ማፍላት
3. ለጥቂት ጊዜ ያህል ውሃን አፍልቶ ከቀዘቀዘ በኋላ እንደገና ከ15-20 ደቂቃ ማፍላት
4. አንድ ጊዜ ብቻ ጥዶ እስኪፍለቀለቅ ማፍላት

___ ሐ. ውሃ ከተፈላ በኋላ ጣዕሙ የሚቀንስበት ምክንያት _____ ነው::

1. ንፁህ ዓየር ከውሃ ውስጥ ወጥቶ ስለሚያልቅ
2. የተለያዩ ጋዞች ወደ ውሃው ውስጥ ስለሚገቡ
3. የተቃጠለውን ዓየር ከውሃ ውስጥ ስለሚውጣ
4. የተቃጠለው ዓየር በውሃው ውስጥ ስለሚበዛ

___ መ. እንደ ደራሲው አባባል ውሃ ከተፈላ በኋላ ከእቃ ወደ እቃ የሚገላበጥ ከሆነ ውሃው_____

1. ጣዕሙ ይቀንሳል
2. ጣዕሙ የበለጠ ይጨምራል
3. እንደገና ይበከላል
4. መልኩ ንፁህ ይሆናል

___ ሠ. እንደ ደራሲው አባባል ውሃ ከተፈላ በኋላ እስከ መጨረሻው ንጽህናውን ጠብቆ እንዲቆይ ለማድረግ የተፈላውን ውሃ ____ነው::

1. በዚያው በተፈላበት እቃ እንዲቀዘቅዝ ማድረግ
2. በተፈላ ውሃ በተቀቀለ ሌላ እቃ ውስጥ መገለበጥ
3. ከእቃ ወደ እቃ በማገላበጥ እንዲቀዘቅዝ ማድረግ
4. በተፈላበት እቃ እንዳይቆይ ማድረግ

___ ረ. ደራሲው ውሃን ከማፍላት ሌላ ይተኮርበት ይገባል የሚለው _____የሚለውን ነው::

1. ውሃው የተፈላበት እቃ ለሌላ አገልግሎት እንዳይውል ማድረግ
2. ውሃው በተፈላበት እቃ እንዳይቀዘቅዝ ማድረግ
3. በተፈላ ውሃ ላይ ሌላ ኬሚካል እንዲጨመር ማድረግ
4. ውሃው በተፈላበት እቃ እንዳይቆይ ማድረግ

___ ሰ. በምንባቡ ውስጥ አራተኛው አንቀጽ ሁለተኛው መስመር <u>የዚህ ዓይነቱ</u> የሚለው ሀረግ የቆመው_____

1. ተፈልቶ የቀዘቀዘው ውሃ በጣሳ ጠለቆ መጠቀም
2. ጣዕም የሌለው ውሃ ከመጠጣት የተበከለ ውሃ መጠጣት
3. የተበከለን ውሃ ከመጠጣት ተፈለቶ የቀዘቀዘን ጣዕም የሌለው ውሃ መጠጣት
4. ተፈልቶ የቀዘቀዘን ውሃ በጣሳ ጠልቆ መጠቀም ተገቢ አይደለም

___ ሸ. ተፈልቶ የቀዘቀዘን ውሃ ለመጠቀም ስንፈልግ ውሃውን ለማንቆርቆር የሚገለግልጡት መሰል ቀዳዳ ወይም ሊከፈትና ሊዘጋ የሚችል ቀዳዳ ከሌለው አማራጩ መንገድ _____ነው::

1. ውሃውን በጣሳ ጠልቆ መጠቀም
2. ውሃውን የተፈላበትን እቃ በጥንቃቄ አስጉንብሶ በጣሳ ቀድቶ መጠቀም
3. በታጠበ ጣሳ ጠልቆ መጠቀም
4. 2 ና 3 መልስ ናቸው

___ ቀ. ደራሲው በአራተኛው አንቀጽ መስመር /24/ «ያ» የሚለውን ቃል የተጠቀመበት_____ለማመልከት ነው::

1. ውሃውን ለማፍላተ የባከነውን ጊዜ
2. ውሃውን ለማፍላት የባከነውን ጋዝ ወይም ማገዶ
3. ውሃውን ለማፍላት የባከነውን ጉልበት
4. ሁሉም መልስ ነው

___ በ. ደራሲው የውሃ ወለድ በሽታን ለማጥፋት ውሃን ከማፍላት ሌላ ተጨማሪ ዘዴ አለ የሚለው _____ የሚለውን ነው::

1. ውሃው መልኩ ንፁህ ከሆነ እንዳለ መጠቀም
2. ማንኛውንም የኬሚካል ዓይነት በውሃው ውስጥ በመጨመር መጠቀም
3. ለውሃ ወለድ በሽታ ማጥፊያ የሚሆን ኬሚካል በውሃው ውስጥ በመጨመር መጠቀም
4. 1 ና 3 መልስ ናቸው

8.. ደራሲው በጽሑፍ ውስጥ የተጠቀመባቸው የተለያዩ አገላለጾች በ«ሀ» ሥር ተዘርዝረዋል። እነዚህን የተጠቀመባቸውን የተለያዩ አገላለጾች ለምን ዓይነት አጠቃቀሞች እንደሆኑ በ «ለ» ሥር ተዘርዝረዋል። በቡድንህ አማካይነት ከተወያየህ በኋላ በ «ሀ» የሚስማማውን ዓይነት አገላለጽ ከ «ለ» ሥር እየመረጥህ አዛምድ።

«ሀ»		«ለ»
___1.	ውሃን ማፍላት በውሃ ውስጥ የሚሟሙ ጋዞችን በተለይም የተቃጠለ አየር ከውሃ ውስጥ ስለሚወጣው የተፈላ ውሃ ጣዕሙ ይቀንሳል።	ሀ. አማራጭን መግለጽ
___2.	በአጠቃላይ ውሃን በማፍላትና ንጽሕናውን ጠብቆ በመጠቀም ውሃ ወለድ በሽታዎችን መከላከል ይቻላል።	ለ. የነገሮችን ሂደታዊ ጉዞ ማሳየት
___3.	ሌላው ሊተኮርበት የሚገባው ጉዳይ ውሃው የተፈላበትን እቃ ለሌላ አገለግሎት እንዳይውል ማድረግ ነው።	ሐ. ተጨማሪ ሀሳብ
___4.	በውሃ ውስጥ ያሉትን ለጤንነት ጠንቅ የሆኑትን ተህዋስያን ለማጥፋት ውሃውን በመጀመሪያ ለጥቂት ደቂቃዎች ማፍላት ከዚያ አቀዝቅዞ እንደገና ከ15-20 ደቂቃ እስኪፍለቀለቅ አፍሉቶ አቀዝቅዞ መጠቀም ነው።	መ. ማጠቃለያ መስጠት
___5.	የተበከለን ውሃ ከመጠጣት ጣዕም የሌለው ውሃን መጠጣቱ ይመረጣል።	ሠ. ሃሳብን ማጠናከር

ድኅረ ንባብ

9. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች የቀረበውን ምንባብ መነሻ በማድረግና የራስህን ልምድ ወይም እውቀት በመጨመር በቡድንህ አማካይነት በጥልቀት ከተወያየህ በኋላ እንደ አጠያየቃቸው ዓይነት መልስ።

ሀ. የተፈላን ውሃ ጣዕሙ እንደሚቀንስ ተረድተሃል። የተበከለን ውሃ ከመጠጣት ደግሞ ጣዕሙ የቀነሰን ውሃ መጠጣቱ የተሻለ እንደሆነ በምንባቡ ተገልጾልሃል። በዚህ አባባል ላይ የአንተስ ውሳኔ ምንድን ነው? አቋምህን ከተወያየህ በኋላ በማስረጃ እየደገፍህ ለክፍል ደኞችህ በቃልህ አስረዳ?

ለ. የሚጣራው ውሃ መልኩ ንፁህ ወይም ድፍርስ፣ በጣም የተበከለ ወይም በጥቂቱ የተበከለ ይሁንም አይሁንም ከተፈላ በኋላ የሚገኘው ውጤት ተመሳሳይ እንደሆነ ተገልጿል። አንተስ በዚህ ላይ ያለህ አቋም ምንድን ነው? ከተወያየህ በኋላ በማስረጃ እየደገፍህ ለክፍል ጓደኞችህ በንግግር አስረዳ።

ሐ. ውሃን አፍለቶ መጠቀም የሚለውን ምንባብ የአጻጻፍ ተጠየቃዊ ቅደም ተከተል ሂደት በመሥመራዊ ሥዕል አሳይ?

መ. ከምንጭ ወይም ከኩሬ የተቀዳን ውሃ እንዴት እንደሚፈላ፣ እንዴት እንደሚቀዘቅዝ በመጨረሻም እንዴት መጠቀም እንዳለብን ከተወያየህ በኋላ አንድ አንቀጽ ጽፈህ ለክፍል ጓደኞችህ አንብብላቸው።

ሠ. ውሃን በጣሳ ጠልቆ መጠጣት ጉዳት እንዳለው ተገልጿል፣ ነገር ግን ውሃው የተፈላበትን ውሃ እቃ ካስጐነበስን በኋላ ቀስ አድርገን አንቆርቁረን ብንጠጣው የተሻለ መሆኑ በምንባቡ ውስጥ ተወስቷል። ለመሆኑ በመጥለቅና በመቅዳት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? የምትደግፈው የቱን ነው? በቡድንህ አማካይነት ከተወያየህ በኋላ የደረስህበትን ማጠቃለያ ለክፍል ጓደኞችህ በንግግር አስረዳ።

ረ. የውሃ ወለድ በሽታዎችን ለመከላከል ከማፍላት በተጨማሪ ውሃን በኬሚካልና በ.ሸዋ በማጣራት መጠቀም ይቻላል። በአካባቢህ ያለው ህብረተሰብ ውሃን በማጣራት ከውሃ ወለድ በሽታዎች ለመከላከል የሚጠቀመው ዘዴ የቱን ነው? አንተስ የምትደግፈው የቱን ነው? በቡድንህ ከተወያየህበት በኋላ ለክፍል ጓደኞችህ በንግግር አስረዳ።

ሰ. በምንባቡ መልእክት ላይ በቡድንህ በጥልቀት ከተወየህ በኋላ በአንድ ነጠላ ዓረፍተ ነገር ጽፈህ ለክፍል ጓደኞችህ አንብብላቸው።

ቅድመ ምንባብ

1. በሚከተሉት ጥያቄዎች ከራስህ ልምድና እውቀት በመነሳት በቡድንህ አማካይነት ከተወያየህ በኋላ ለክፍል ጓደኞችህ በንግግር ግለጽ (7 ደቂቃ)

   ሀ. ስለ ማህበር የምታውቀውን ሁሉ አንድ በአንድ ግለጽ

   ለ. ከሚከተሉት ውስጥ አንተ በምትኖርበት አለ የምትለውን የማህበር ዓይነት በ «√» ምልክት የለም የምትለውን ደግሞ በ «X» ምልክት በተሰጠህ ሳጥን ውስጥ አመልክት

   1. ሃይማኖታዊ ማህበር ☐
   2. አካባቢያዊ ማህበር ☐
   3. ፖለቲካዊ ማህበር ☐
   4. ዓለም አቀፋዊ ማህበር ☐

   ሐ. በጥያቄ «ለ» አለ በማለት የመለስካቸውን መሠረት በማድረግ ከዚህ በታች የተሰጡትን ጥያቄዎች መልስ

   1. በአካባቢህ ያሉትን የሃይማኖታዊ ማህበራት ስም ዝርዝር
   2. በአካባቢህ ያሉትን አለታዊ /የመረዳጃ/ ማህበራትን ስም ዝርዝር
   3. በአካባቢህ ያሉትን ፖለቲካዊ ድርጅቶች /ማህበራትን/ ስም ዝርዝር
   4. በአካባቢህ ያሉትን ዓለም አቀፋዊ ማህበራት ስም ዝርዝር

2. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቃላት ጥንድ በመሆን ከተወያየህ በኋላ የምታውቃቸውን ቃላት «√» ምልክት የማታውቃቸውን ደግሞ በ «X» ምልክት በመጠቀም በተሰጠህ ሳጥን ውስጥ አመልክት::

ሀ.	ሰንበቴ	☐	ሸ.	ዓመተ ምህረት	☐
ለ.	ወበራ	☐	ቀ.	በወዲያኛው ዓለም	☐
ሐ.	ደቦ	☐	በ.	በመንፈሳዊ	☐
መ.	ሰርግ	☐	ተ.	ስያሜ	☐
ሠ.	ቀይ መስቀል	☐	ቸ.	የልደታ በዓል	☐
ረ.	ቀስበቀስ	☐	ኀ.	ዝክረ ቅዱሳን	☐
ሰ.	ፋሽስት	☐	ነ.	ዋልታ	☐

3. በተራ ቁጥር «2» የተዘረዘሩትን የማህበር ዓይነቶች ከራስህ ልመድና እውቀት በመነሳት በጥንድ በመሆን ከተወያየህ በኋላ በሃይማኖታዊ፣ በዕለታዊ /መረዳጃ እና ፖለቲካዊ እና ብሔራዊ/ ዓለም አቀፍ ማህበራት በሚሉት ሥር መድባቸው:: (5 ደቂቃ)

ሀ. በሃይማኖታዊ ማህበር የሚመደቡ

1. _____
2. _____
3. _____

ለ. በአገር አቀፍ ደረጃ በፖለቲካዊ ማህበር የሚመደቡ

1. _____
2. _____
3. _____

ሐ. የመረዳጃ /አለታዊ ማህበራት

1. _____
2. _____
3. _____

መ. ዓለም አቀፋዊ ማህበራት

1. _____
2. _____
3. _____

ምንባብ ሁለት

ማህበር

ስያሜው እንደሚያመለክተው ማህበር ማለት አንድ ሆነ ተባበረ ህብር ሆነ ማለት ነው። በኢትዮጵያም የአያሌ ዘመናት ታሪክና ምክንያት ያለው ነው። የክርስትና እና የእስልምና ሃይማኖቶች ወደ ሀገሪቱ ከገቡ ወዲህ ማህበር ትመሀርት እየተሰጠበትና ግዴታም እየተገባበት መጥቷል። በተለይም በክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ ጠበቅ ያለ እምነት እና አቋም ይዞ ይገኛል።

ለምሳሌ ያህል የጽዋ፣ የሰንበቴ፣ የጽጌ፣ የኳሀናት ማህበራት ዝክረ ቅዱሳን፣ የልደታ በዓል እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉትን ስያሜዎችና ተቋሞች ከሃይማኖት ጋር የተያያዙ ወይም የክርስትና ሃይማኖት ከተሰበከ በኋላ የተመሠረቱ መሆናቸውን ከስያሜያቸውና ከተግባራቸው ላይ እንረዳለን።

በእነዚህ ማህበራት አስተባባሪነት ሕዝቡ እየተሰበሰበ ከእለት ምግቡ እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ ድረስ ለውን ጉዳዩን ሲወያይበትና ሲረዳዳበት እንደኖረ ከዚህ ዓለም ሲለይም በወዲያኛው ዓለም የሚጠበቀውን ምህረትም ሆነ ቅጣት ለመለየት የሚችለበትን መንገድ ሊቀይስበት እንደሚፈልግ በተጨማሪነት እንገነዘባለን።

ማህበር ከሃይማኖታዊ ገጽታው ሌላም ማህበራዊ ወይም ሕዝባዊ ተቋም አለው። የመንደሩ ነዋሪ የጸታና የሃይማኖት ልዩነት ሳያደርግ የሚረዳዳበት ታላቁ ገጽታው አያሌ ዓመታት ያስቆጠረ ነው።

ለምሳሌ በወበራ ወይም በደቦ፣ በሰርግ፣ በሃዘን፣ ሕዝቡ እርስ በርሱ ሲረዳዳና ሲደጋገፍ እንደኖረ ከታሪኩ ላይ መረዳት ይቻላል። ከጥንታዊነት ወደ ዘመናዊነት የተሸጋገረበት ምክንያቶችና ወቅትም እንደዚሁ አያሌ ዓመታት ያስቆጠረ ገጽታ አለው። የምዕራባውያን ሥልጣኔ ወደ ሀገሪቱ መግባት ከጀመረ ወዲህ በማህበር አማካይነት ወይም ዋልታነት ልዩ ልዩ ሥራዎችን ማቋቋም እየተስፋፋ መጥቷል። ገንዘብ አዋጥቶ ሃሳብንና ጉልበትን አስተባብሮ የጋግድ ሥራ ማካሄድና ርዳታ መስጠት የተለመደ ሆኗል።

ማህበር ከመንፈሳዊና የእለት ኑሮ ዋልታም ወጥቶ ወደ ፖለቲካ ምዕራፍም ተሸጋግሯል። ፋሺስት ኢጣሊያ በ1927 ዓ.ም. አገራችንን ለመውረር ግፊትዋን በሰሜንና በምሥራቅ በጀመረችበት ወቅት የኢትዮጵያ ሴቶች በጐ አድራጐትና የሀገር ፍቅር ማህበራት ተመሥርተው ሕዝቡ ለነፃነቱ እና ለሀገሩ ክብርና አንድነት እንዲነሳሳ ገንዘብም እያዋጣ ትጥቅና ስንቅ እንዲያዘጋጅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

ከዚህ ቀጥሎ ማህበር ወደ ብሔራዊ ስሜትና ኃላፊነት ተሸጋግሮ በ1928 ዓ.ም. ጥቁር አንበሳ እና በ1931 የጥንታዊ ጀግኖች ማህበራት ተቋቁመው የተዋጊነቱንና የፖለቲካውን ተጋድሎ ቀጥለው ለድል አድራጊነቱ በቅተዋል።

ማህበር ብሔራዊና ዐለም አቀፋዊ ባህርይ ይዞ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ጉልቶ የታየባቸው ጊዜያትና ምክንያቶች ሰፋ ያለ ምዕራፍ አለው። በመሆኑ ዝርዝር ጉዳን አቆይተን እንደ ቀይ መስቀል የዓለም አቀፍ የሴቶች ክበብ፣ የሞስኮ ኦርቶዶክሳዊ ማህበራትንና የመሳሰሉትን ጠቅሰን ብናልፍ በቂ ይመስላል።

ምንጭ ማሞ ውድነህ፣ ማህበርተኞች ንግድ ማተሚያ ቤት
አዲስ አበባ /1982 6 - 8/

1. ምንባቡን በፍጥነት ገረፍ ገረፍ በማድረግ ካነበብህ በኋላ በምንባቡ መሠረት ጅምር ዓረፍተ ነገሮችን ጨርሰህ ጽፈህ ለክፍል ጓደኞችና አንብብላቸው።

ሀ. ማህበር ማለት _____

ለ. የጽዋ፣ የሰንበቴ፣ ዝክረ ቅዱሳን፣ የጽጌ፣ የልደታ በዓል እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ ስያሜዎችና ተቋሞች ከሃይማኖት ጋር የተያያዙ ወይም የክርስትና ሃይማኖት ከተሰበከ በኋላ የተመሠረቱ _____

ሐ. የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖቶች ወደ ኢትዮጵያ መግባት ከጀመሩ ወዲ የማህበር ትምህርት_____

መ. ማህበር ከሃይማኖታዊ ገጽታው ሌላም_____

ሠ. የምዕራባውያን ሥልጣ ወደ ኢትዮጵያ መግባት ከጀመረ ወዲህ _____

ረ. ማህበር ከመንፈሳዊና ከእለት ኑሮ ዋልታም ወጥቶ_____

ሰ. ፋሺስት ኢጣሊያ በ1927 ዓ.ም. አገራችን ለመውረር ግፊትዋን በሰሜንና በምሥራቅ በጀመረችበት ወቅት _____

ሸ. ከዚህ ቀጥሎ ወደ ብሔራዊ ስሜትና ኃላፊነትም ተሸጋግሮ በ1928 ዓ.ም. _____

ቀ. ማህበር ብሔራዊና ዓለምአቀፋዊ ባህርይ ይዞ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ጉልቶ የታየባቸው ጊዜያትና ምክንያቶች_____

2. ማህበር የሚለውን ምንባብ በፍጥነት ገረፍ ገረፍ አድርገህ አንብብ። በአነበብኸው ላይ ጥንድ በመሆን በመወያየት ማስታወሻ በመያዝ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃልህ ለክፍል ጓደኞችህ ተናገር።

ሀ. የአንቀጽ አንድ ፍሬ ሀሳብ _____

ለ. የአንቀጽ ሶስት ፍሬ ሀሳብ_____

ሐ. የአንቀጽ አራት ፍሬ ሀሳብ _____

መ. የአንቀጽ ስድስት ፍሬ ሀሳብ _____

ሠ. የአንቀጽ ሰባት ፍሬ ሀሳብ _____

ረ. የአንቀጽ ስምንት ፍሬ ሀሳብ_____

ሰ. ስለ ማህበር ምንነት የተገለጸለት አንቀጽ_____

ቀ. ማህበር ከመንፈሳዊና የእለት ኑሮ ውጥቶ ወደ ፖለቲካ ዓለመ መሸጋገሩን የተገለጸበት አንቀጽ _____

በ. ፖለቲካዊ አቋም ያላቸው የማህበር ዓይነቶች በምሳሌነት የተገለፀበት አንቀጽ _____

ተ. ሁለት የተለዩ ሃይማኖቶች መኖራቸውን የተገለፀበት አንቀጽ_____

ቸ. የምንባቡ አጠቃላይ መልእክት _____

ኀ. ምንባቡ ያለው የአንቀጽ ብዛት _____

3. ከዚህ በታች የተሰጠውን ምንባብ በጥንቃቄ ካነበብህ በኋላ ጥንድ በመሆን ከራስህ ልምድና እውቀት በመነሳት እየተወያየህ ከአገባብና ከትርጉም አንፃር- ተስማሚ የሚሆን ቃል ወይም ሀረግ እያስገባህ ጻፍ (20 ደቂቃ)

ስያሜው እንደሚያመለክተው ማህበራት ማለት እንደሆነ ተባበረ ህብር ሆነ_____ ነው። በኢትዮጵያም የአያሌ ዘመናት ታሪክና ምክንያት ያለው ነው። የክርስትና እና _____ ሃይማኖት ወደ ሀገሪቱ ከገቡ ወዲህ የማህበር ትምህርት እየተሰጠበትና ግዴታም እየተገባበት

መጥቷል። _____ በክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ ጠበቅ ያለ እምነት እና አቋም ይዞ_____

ለምሣሌ ያህል የጽዋ፣ የሰንበቴ፣ የጽጌ የካህናትና ማህበራት ዝክረ ቅዱሳን የልደታ _____ እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉት ስያሜዎችና ተቋሞች ከሃይማኖት ጋር የተያያዙ _____ የክርስትና ሃይማኖት ከተሰበከ በኋላ የተመሠረቱ መሆናቸውን ከስያሜዎችና ከተግባራቸው ላይ ____

በእነዚህ ማህበራት አስተባባሪነት ሕዝቡ እየተሰበሰበ ከአለት ምግቡ እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ ድረስ ያለውን ጉዳዩን ሲወያይቡትና ሲረዳዳበት እንደሆረ ከዚህ ዓለም_____ በወዲያኛው ዓለም የሚጠበቀውን ምህረትም ሆነ ቅጣት ለመለየት የሚችልበትን መንገድ_____እንደሚፈለግበት እንገነዘባለን።

ማህበር ከሃይማኖታዊ ገጽታው ሌላም ማህበራዊ ወይም ሕዝባዊ ተቋም አለው።_____ ነዋሪ የጾታና የሃይማኖት ልዩነት ሳያደርግ የሚረዳዳበት ታላቁ ገጽታው አያሌ_____ ያስቆጠረ ነው።

ለምሳሌ በወበራ ወይም በደቦ፣ በሀዘን፣ ሕዝቡ እርስ በርስ ሲረዳዳና _____ እንደኖረ ከታሪኩ ላይ መረዳት ይቻላል። ማህበር ከጥንቃዊነት ወደ ዘመናዊነት የተሸጋገረበት ምክንያትና _____ እንደዚሁ አያሌ ዓመታት ያስቆጠረ ገጽታ አለው። የምዕራባውያን ሥልጣኔ ወደ ሀገሪቱ _____ ከጀመረ ወዲህ በማህበር አማካይነት ወይም ዋልታነት ልዩ ልዩ ሥፍራዎችን _____ እየተስፋፋ መጥቷል። ገንዘብ አዋጥቶ ሃሳብንና ጉልበትን አስተባብሮ የንግድ ሥራ ማካሄድና _____ መስጠት የተለመደ ሆኗል።

ማህበር ከመንፈሳዊ እና ከአለት ኑሮ ዋልታም ውጥቶ ወደ ፖለቲካ ምዕራፍም ተሸጋግሯል።_____ኢጣሊያ በ1927 ዓ.ም. አገራችንን ለመውረር ግፊትዋነ በሰሜንና በምሥራቅ በጀመረችበት _____ የኢትዮጵያ ሴቶች በጐ አድራጐት እና የሀገር ፍቅር ማህበራት ተመሥርተው ሕዝቡ ለነፃነቱ_____ ክብርና አንድነት እንዲነሳሳ ገንዘብም እያዋጣ ትጥቅና ስንቅ እንዲያዘጋጅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ_____ ከዚህ ቀጥሎ ማህበር ወደ ብሔራዊ ስሜትና ኃላፊነትም ተሸጋግሮ በ1928 ዓ.ም. የጥቁር _____ በ1931 ዓ.ም. የጥንታዊ ጀግኖች ማህበራት ተቋቁመው የተዋጊነቱንና የፖለቲካውን ተጋድሎ ቀጥለው_____ድራጊነቱ በቅተዋል።

ማህበር ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ ባህርይ ይዞ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ_____ የታየባቸው ጊዜያትና ምክንያቶች ሰፋ ያለ ምዕራፍ ያለው ለመሆኑ ዝርዝር ጉዳዩን_____ እንደ ቀይ መስቀል እንደ ሠራተኛ፣ የድኩማን፣ ረድዔት የዓለም አቀፍ የሴቶች ክበብ የሞስኮ ኦርቶዶክሳዊ_____ እና የመሳሰሉትን ጠቅሰን ብናልፍ በቂ_____።

ምንጭ፣ ማሞ ውድነህ ማህበርተኞች 1982፣ 6 - 8

1. ማህበር የሚለውን ምንባብ በአሰሳ የአነባብ ስልት ካነበብህ በኋላ በሚከተሉት ቃላት ፍቻቸውን ወይም ተቃራኒያቸውን ከምንባቡ እየፈለግህ ለክፍል ጓደኞችህ እንዳጠያየቃቸው ተናገር (5 ደቂቃ)

ሀ. አንቀጽ አንድ ውስጥ «ማህበር» ለሚለው ቃል ተመሳሳዩ_____ነው።

ለ. አንቀጽ ሶስት ውስጥ «ቅጣት» ለሚለው ቃል ተቃራኒው_____ ነው።

ሐ. አንቀጽ አምስት ውስጥ «ሠርግ» ለሚለው ቃል ተቃራኒው_____ ነው።

መ. አንቀጽ ሶስት ውስጥ «በወዲያኛው ዓለም» ለሚለው ቃል ተቃራኒው_____ ነው።

ሠ. አንቀጽ አምስት ውስጥ «ሲደጋገፍ» ለሚለው ሃረግ ተመሳሳዩ _____ነው።

ረ. አንቀጽ አምስት ውስጥ «ጥንታዊነት» ለሚለው ቃል ተቃራኒው _____ነው።

ሰ. አንቀጽ ስድስት ውስጥ «መንፈሳዊ» ለሚለው ቃል ተመሳሳዩ _____ ነው።

ሸ. አንቀጽ አምስት ውስጥ «ዘመናዊነት» ለሚለው ቃል አንቀጽ አንድ ውስጥ አቻ ቃሉ _____ ነው።

ቀ. አንቀጽ አራት ውስጥ የጾታና የሃይማኖት ልዩነት ሳያደርግ የሚያቅፈው የማህበር ዓይነት _____ ነው።

በ. አንቀጽ ሁለት «እነዚህንና እነዚህን» የሚለው ሀረግ የሚወክለው _____ነው።

ተ. አንቀጽ ሶስት ውስጥ «በእነዚህ» የሚለው ሀረግ የሚወክለው_____ነው።

ቸ. አንቀጽ ሦስት ውስጥ «እርስ በርሱ» የሚለው ሀረግ የሚወክለው _____ ነው።

ኀ. አንቀጽ ሰባት ውስጥ «ከዚህ» የሚለው ሀረግ የሚወክለው _____ነው።

2. ምንባቡን በፍጥነት በአሰሳ የአነባበብ ስልት እያነበብህ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃልህ መልስ (5 ደቂቃ)

ሀ. ጽዋ፣ ሰንበቴ፣ የልደታ በዓላት ምሳሌነታቸው ለ_____የማህበር ዓይነት ነው።

ለ. ወበራ፣ ደቦ፣ ሰርግ ምሳሌነታቸው ለ_____ የማህበር ዓይነት ነው።

ሐ. የኢትዮጵያ በጐ አድራጐት ማህበር ምሳሌነቱ ለ_____የማህበር ዓይነት ነው።

መ. የጥንታዊ ጀግኖች የተቋቋመው በ_____ ዓመተ ምህረት ነው።

ሠ. ጥቁር አንበሳ የተባለው ማህበር የተቋቋመው በ_____ዓመተ ምህረት ነው።

ረ. የሞስኮ ኦርቶዶክሳዊ ማህበናር የቀይ መስቀል ማህበር ምሳሌነታቸው ለ_____ የማህበር ዓይነት ነው።


ሰ. ማህበር ለሚለው ምንባብ ደራሲው _____ነው።

ሸ. ፋሺስት ኢጣሊያ አገራችንን የወረረችው በ_____ዓመተ ምህረት ነው።

ቀ. ማህበር የሚለው ምንባብ የተወሰደው _____ ከሚለው መጽሐፍ ነው።

በ. ምንባቡ የተጻፈው በ_____ዓመተ ምህረት ነው።

3. ስለ ማህበር አጀማመርና እድገት ከምንባቡ በአሰሳ የአነባብ ስልት እየፈለግህ ከዚህ በታች በተሰጠው መስመራዊ ስዕል ሥር ተስማሚውን ቃል ወይም ሀረግ እየፈለግህ በማስታወሻ ከያዝህ በኋላ ለክፍል ጓደኞችህ ተናገር (3 ደቂቃ)



4. ከዚህ በታች የተሰጡት አንቀጾች ቅደም ተከተላቸው ተዛብቷል። በነዚህ በተዛቡ አንቀጾች ላይ በቡድንህ አማካይነት ከተወያየህ በኋላ አንቀጾችን አንድ የተሟላ ሀሳብ እንዲሰጡ አድርገህ በቅደም ተከተላቸው አስተካክለህ ጻፍ (15 ደቂቃ)

1. በእነዚህ ማህበራት አስተባባሪነት ሕዝቡ እየተሰበሰበ ከአለት ምግቡ እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ ድረስ ለውን ጉዳዩን ሲወያይበትና ሲረዳዳበት እንደኖረ ከዚህ ዓለም ሲለይም በወዲያኛው ዓለፍ የሚጠበቀውን ምህረትም ሆነ ቅጣት ለመለየት የሚችልበትን መንገድ ሊቀይስበት እንደሚፈልግ በተጨማሪነት እንገነዘባለን።

2. ማህበር ከሃይማኖታዊ ገጽታው ሌላም ማህበራዊ ወይም ሕዝባዊ ተቋም አለው። የየመንደሩ ነዋሪ የጸታና የሃይማኖት ልዩነት ሳያደርግ የሚረዳዳበት ታላቁ ገጽታው አያሌ ዓመታት ያስቆጠረ ነው።

3. ለምሳሌ በወበራ ወይም በደቦ፣ በሠርግ፣ በሃዘንና ሕዝቡ እርስ በርሱ ሲረዳዳና ሲደጋገፍ እንደኖረ ከታሪኩ ላይ መረዳት ይቻላል። ከጥንታዊነት ወደ ዘመናዊነት የተሸጋገረበት ምክንያት ወቅትም እንደዚሁ አያሌ ዓመታት ያስቆጠረ ገጽታ አለው። የምዕራባዊያን ሥልጣኔ ወደ ሀገሪቱ ማግባት ከጀመረ ወዲህ በማህበር አማካይነት ወይም ዋልታነት ልዩ ልዩ ሥራዎችን ማቋቋም እየተስፋፋ መጥቷል። ገንዘብ አዋጥቶ ሃሳብንና ጉለበትን አስተባብሮ የንግድ ሥራ ማካሄድና ርዳታ መስጠት የተለመደ ሆኗል።

4. ስያሜው እንደሚያመለክተው ማህበር ማለት አንድ ሆነ ተባበረ ህብር ሆነ ማለት ነው። በኢትዮጵያም አያሌ ዘመናት ታሪክና ምክንያት ያለው ነው። የክርስትና እና የእስልምና ሃይማኖቶች ወደ ሀገሪቱ ከገቡ ወዲህ ማህበር ትምህርት እየተሰጠበትና ግዴታም እየተገባበት መጥቷል። በተለይም በክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ ጠበቅ ያለ እምነትና አቋም ይዞ ይገኛል።

5. ማህበር ከመንፈሳዊና ከአለት ኑሮ ዋልታም ውጥቶ ወደ ፖለቲካ ምዕራፍም ተሸጋግሯል። ፋሺስት ኢጣሊያ በ1927 ዓ.ም. አገራችንን ለመውረር ግፊትዋን በሰሜንና በምሥራቅ በጀመረችበት ወቅት የኢትዮጵያ ሴቶች በጐ አድራጐትና የሀገር ፍቅር ማህበራት ተመሥርተው ሕዝቡ ለነፃነቱና ለሀገሩ ክብርና አንድነት እንዲነሳሳ ገንዘብም እያዋጣ ትጥቅና ስንቅ እንዲያዘጋጅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

6. ለምሳሌ ያህል የጽዋ፣ የሰንበቴ፣ የጽጌ፣ የካህናት ማህበራት፣ ዝክረ ቅዱሳን የልደታ በዓል እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉትን ስያሜዎችና ተቋሞች ከሃይማኖት ጋር የተያዙ ወይም የክርስትና ሃይማኖት ከተሰበከ በኋላ የተመሠረቱ መሆናቸውን ከስያሜያቸውና ከተግባራቸው ላይ እንረዳለን።

7. ማህበር ብሔራዊና ዓለማቀፋዊ ባህርይ ይዞ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ጉልቶ የታየባቸው ጊዜትና ምክንያቶች ሰፋ ያለ ምዕራፍ ያለው በመሆኑ ዝርዝር ጉዳዩን አቆይተን እንደ ቀይ መስቀል፣ የዓለም አቀፍ የሴቶች ክበብ፣ የሞክሶ አርቶዶክሳዊ ማህበራትንና የመሳሰሉትን ጠቅሰን ብናልፍ በቂ ይመስላል።

8. ከዚህ ቀጥሎ ማህበር ወደ ብሔራዊ ስሜትና ኃላፊነትም ተሸጋግሮ በ1928 ዓ.ም. ጥቁር አንበሳ፣ በ1931 የጥንታዊ ጀግኖች ማህበራት ተቋቁመው የተዋጊኑቱንና የፖለቲካውን ተጋድሎ ቀጥለው ለድል አድራጊነቱ በቅተዋል።

5. ማህበር የሚለውን ምንባብ በጥንቃቄ ካነበብህ በኋላ የሚከተሉትን ጥቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ በቡድን ተወያይተህ መንደርደሪያ ዓረፍተ ነገሮችንና ዝርዝር ዓረፍተ ነገሮች ለይ። በሠንጠረዡ ውስጥ ያለው ዓረፍተ ነገር መንደርደሪያ ከሆን መንደርደሪያ በሚለው ዓምድ ሥር «√» ምልክት አስቀምጥ ዓረፍተ ነገሩ ዝርዝር ከሆነ ዝርዝር ዓረፍተ ነገር በሚለው አምድ «X» አስቀምጥ (5 ደቂቃ)

ተራ ቁጥር	ዓረፍተ ነገር	የዓረፍተ ነገር ዓይነት	
		መንደርደሪያ	ዝርዝር
1.	ማህበር ከሃይማኖታዊ ገጽታው ሌላም ማህበራዊ ወይም ሕዝባዊ ተቋም አለው። /አንቀጽ ሁለት/		
2.	በእነዚህ ማህበራት አማካይነት ሕዝቡ እየተሰበሰበ ከእለት ምግቡ እስከ ሕይወት ፍጻሜ ድረስ ያለውን ይወያይበታል /አንቀጽ ሶስት/		
3.	ለምሳሌ በወበራ ወይም በደቦ፣ በሠርግ፣ በሃዘን ሕዝቡ እርስ በርሱ ሲረዳዳና ሲደጋገፍ እንደኖረ ከታሪኩ ላይ መረዳት ይቻላል /አንቀጽ አምስት/		
4	ማህበር ከመንፈሳዊና ከእለት ኑሮ ዋልታም ወጥቶ ወደ ፖለቲካ ምዕራፍም ተሸጋግሯል /አንቀጽ ስድስት/		
5.	የየመንደሩ ነዋሪ የጸታና የሃይማኖት ልዩነት ሳያደርግ የሚረዳዳበት ታላቁ ገጽታው አያሌ ዓመታት ያስቆጠረ ነው /አንቀጽ አምስት/		
6.	የክርስትና እና የእስልምና ሃይማኖቶች ወደ ሀገሪቱ ከገቡ ወዲህ ማህበር ትምህርት እየተሰጠበትና ግዴታም እየተገባበት መጥቷል።		

ንባብ (While Reading)

1. የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጎች ማህበር ከሚለው ምንባብ የወጡ ናቸው ምንባቡን በግል በጥንቃቄ ካነበብህ በኋላ ለቃላቱና ለሀረቹ ከአገባባቸው አንፃር ሊይዙት የሚችሉትን ትርጉም ጥንድ በመሆን ተወያይተህ ለክፍል ጓደኞችህ ተናገር።

ሀ. «ማህበር» /መስመር አንድ/ _____

ለ. «ሀብር» /መስመር አንድ/ _____

ሐ. «ጽዋ» /መስመር ስድስት/ _____

መ. «ጽጌ» /መስመር ስድስት/ _____

ሠ. «ዝክረ ቅዱሳን» /መስመር ስድስት/ _____

ረ. «ወዲያኛው ዓለም» /መስመር አሥር/ _____

ሰ. *የልደታ በዓል» /መስመር ስድስት/ _____

ሸ. «ተሰበከ» /መስመር ስምንት/ _____

ቀ. «ወበራ» /መስመር አሥራ ስድስት/ _____

በ. «ደቦ» /መስመር አሥራ ስድስት/ _____

ተ. «ዋልታ» /መስመር ሃያ ሶስት/ _____

ቸ. «መንፈሳዊ» /መስመር ሃያ ሁለት/ _____

ኀ. «ስያሜ» /መስመር ስምንት / _____

ነ. «ምህረት» /መስመር አሥራ አንድ/ _____

2. የሚከተሉትን ቃላት በዓረፍተ ነገሩ ውስጥ ካላቸው አገባብ አንፃር ሊለጡት በሚችለው ፍቺ ላይ ጥንድ በመሆን ከተወያየህ በኋላ ትርጉማቸውን ለክፍል ጓደኞችህ ግለጽ።

ሀ. በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ ከሣምንቱ ቀናት ውስጥ አሁድ <u>የሰንበቴ</u> ማህበር የሚከበርበት ቀን ነው። <u>ሰንበቴ</u> የሚለው ቃል ትርጉም_____ ነው።

ለ. ወይዘሮ ጋዲሌ የመጋቢት አቦን የማህበር <u>ጽዋ</u> ባለተራ በመሆናቸው ከወዲሁ ለድግሱ የሚስፈልገውን ነገር ማዘጋጀት ጀምረዋል። የተሠመረበት ቃል ፍቺ ትርጉም_____ ነው።

ሐ. በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ የቅዱሳንን ስም ለማስታወስ ሲባል በስማቸው ድግስ አዘጋጅቶ ለድሃዎች <u>መዝከር</u> የተለመደ ነው። የተሰመረበት ቃል ፍቺ ትርጉም_____ ነው።

መ. ገበሬው የጤፍ አዝመራውን <u>በወበራ</u> በአጭር ጊዜ ውስጥ አጭዶ ከመረው። የተሠመረበት ቃል ትርጉም_____ ነው።

ሠ. የክርስትና እምነት ተከታዮች <u>በወዲያኛው ዓለም</u> በአምላካቸው ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት ሲሉ በየወሩ የሰንበቴ፣ የልደታ ወዘተ. የመሳሰሉትን ማህበራት በማቋቋም በየወሩ ይዘክራሉ የተሠመረበት ቃል ትርጉም _____ ነው።

3. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የተለያዩ አያያዥ ቃላትና ሃረጎች ከምንባቡ የወጡ ናቸው እነዚህን አያያዥ ቃላትና ሃረጎች ደራሲው በጽሑፍ ውስጥ ምን ዓይነት ሃሳብን ለማስተላለፍ እንደተጠቀመባቸው ጥንድ በመሆን ከተወያየህ በኋላ ለክፍል ጓደኞችህ ግለጽ ተናገር።

ምሳሌ፣ ወዲህ/መስመር ሶስት/ ደራሲው በሚከተለው ሁኔታ በጽሑፍ ውስጥ ተጠቅሞበታል የክርስትና እና የእስልምና ሃይማኖቶች ወደ ሃገሪቱ ከገቡ <u>ወዲህ</u> ማህበር ትምህርት እየተሰጠበትና ግዴታ እየተገባበት መጥቷል። <u>ወዲህ</u> የሚለው ቃል ደራሲው ጊዜን ለማሳየት ሲል የተጠቀመበት ነው።

ሀ. «ምሣሌ» /መስመር ስድስት/ _____

ለ. «ሌላም» /መስመር አሥራ ሶስት/ _____

ሐ. «እንደዚሁ» /መስመር አሥራ ስምንት/ _____

መ. «በተለይም» /መስመር አራት/ _____

ሠ. «በመሆኑ» /መስመር ሰላሣ ሁለት/ _____

ረ. «የመሳሰሉት» /መስመር ሰላሣ ሶስት/ _____

4. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የተለያዩ አያያዥ ሀረጎች ከምንባብ የወጡ ናቸው በእነዚህ ሃረጎች ጥንድ በመሆን ከተወያየህ በኋላ በዓረፍተ ነገሮቹ ውስጥ በተሰጠው ባዶ ቦታ እያስገባህ ጻፍ።

በመሆኑ ለምሣሌ
ከዚህ ቀጥሎ የመሳሰሉት
በተለይም

ሀ. የገና በዓል በተሸያዩ የክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ በከፍተኛ ሁኔታ ይከበራል_____ በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ዘንድ ከፍተኛ ቦታ ይሰጠዋል።

ለ. በአሁኑ የጉብኝታችን ወቅት የጉበኘነው ዋከናን ሲሆን _____ የምንጎበኘው ደግሞ የሶፎሞርን ዋሻ ነው።

ሐ. የክርስትና እምነት ተከታዮች በአምላካቸው ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት ማህበር ያቋቁማሉ፤_____ የሰንበቴ፤ የማርምንና የልደታን ማህበር መጥቀስ ይቻላል።

መ. በሰፈራችን የተለያዩ የመረዳጃ ማህበራት ተቋቁመዋል ለምሳሌ ደቦ፤ ሠርግ፤ እድር _____ ጠቅሶ ማለፍ ይቻላል።

5. ማህበር የሚለውን ምንባብ በፀጥታ አንድ ጊዜ ካነበብህ በኋላ በሚከተሉት ጥያቄዎች በቡድንህ አማካኝነት በመወያየት በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልስ (ሽ)።

ሀ. ማህበር ማለት ምን ማለት ነው? _____

ለ. ማህበር በኢትዮጵያ የተጀመረው መቼ ነው? _____

ሐ. ጽዋ፤ ሰንበቴ፤ ዝክረ ቅዱሳን የሃይማኖት ማህበራት መሆናቸውን የምንረዳው በምንድነው?

_____

መ. የየመንደሩ ነዋሪ የሃይማኖትና የጾታ ልዩነት ሳያደርግ ለመረዳዳት ብሎ የሚቋቋማቸውን የማህበር ዓይነቶች ጥቀስ። _____

ሠ. የዘመናዊ ማህበራት ወደ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲስፋፋ ያስቻለው ምክንያት ምንድን ነው ?

_____

ረ. ፋሺስት ኢጣሊያ አገራችንን በ1927 ዓመተ ምህረት በወረረችበት ወቅት የተለያዩ የፖለቲካ ማህበራት ተመሥርተዋል እነዚህ ማህበራት እነማን ናቸው? ያደረጉት አስተዋጽኦስ ምንድን ነው? _____

ሰ. እንደ ቀይ መስቀል፤ የዓለም አቀፍ የሴቶች ክበብ ማህበራት ምሳሌነታቸው ለየትኛው የማህበር ዓይነት ነው? _____

ሸ. የሃይማኖታዊ ማህበር ጥቅሙ ምንድን ነው ? _____

ቀ. በመንፈሳዊ እና በአለታዊ ኑሮ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው ? _____

6. ማህበር የሚለውን ምንባብ በሉሆሳስ የአነባብ ስልት በግልህ ካነበብህ በኋላ እንደገና በቡድንህ አማካይነት በመወያየት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ እውነት ወይም ውሸት በማለት መልስ። መልሰህ እውነት ከሆነ መረጃውን ያገኘህበትን ምንጭ /የአንቀጹን ቁጥር ጻፍ። መልሰህ ውሸት ከሆነ ምክንያትህ አብራርተህ ጻፍ።/

ሀ. የክርስትና የእስልምና ሃይማኖቶች ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ ወዲህ የማህበር ትምህርት እየተሰጠና ግዴታም እንዲገባበት እየተደረገ መጥቷል።_____

ለ. የጽዋ፤ የሰንበቴ፤ የጽጌ፤ የክህናት ማህበራት እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉት ስያሜዎችና ተቋሞች ከሃይማኖት ጋር ወይም የክርስትና ሃይማኖት ከተሰበከ በኋላ የተመሠረቱ መሆናቸውን ከስያሜያቸውና ከተግባራቸው እንረዳለን። _____

ሐ. ማህበር ከሃይማኖታዊ ገጽታው ሌላም ማህበራዊ ወይም ሕዝባዊ ተቋም አለው። ስለዚህ ጉዳይ የደቦ የሠርግ የሃዘንና የመሳሰሉት የማህበር ዓይነቶች በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል።_____

መ. የምዕራባውያን ሥልጣኔ ወደ ኢትዮጵያ መግባት ከጀመረ ወዲህ በማህበር አማካይነት ወይም ዋልታነት ልዩ ልዩ ሥራዎችን ማቋቋም እየተስፋፋ መጥቷል። _____

ሠ. ማህበር ከጥንታዊነት ወደ ዘመናዊነት ሲሸጋገር አያሌ ዓመት አስቆጥሯል። _____

7. ከዚህ በታች በተሰጡት የምርጫ ጥያቄዎች በቡድንህ አማካይነት ከተወያየህ በኋላ የተስማማህበትን መልስ የያዘውን ፊደል እየመረጥህ ከቁጥሩ በስተግራ በተሰጠው ባዶ ቦታ ፊደሉን ብቻ ጻፍ::

ሀ. የየመንደሩ ነዋሪ የሃይማኖታዊና የጾታ ልዩነት ሳያደርግ የሚያቋቁመው የማህበር ዓይነት_____ ነው::

1. አለታዊ /መረዳጃ/ ማህበር
2. ሃይማኖታዊ ማህበር
3. ፖለቲካዊ ማህበር
4. የሙያ ማህበር

ለ. እንደ ደራሲው አገላለጽ በኢትዮጵያ ውስጥ ሃይማኖታዊ ማህበር ወደ አለታዊ ማህበር የተሸጋገረበት ምክንያት _____ ነው::

1. የአውሮፓ ስልጣኔ ወደ ኢትዮጵያ መግባት
2. የአሜሪካ ሥልጣኔ ወደ ኢትዮጵያ መግባት
3. የምሥራቅ አውሮጳ ሥልጣኔ ወደ ኢትዮጵያ መግባት
4. የምዕራብ አውሮፖ ሥልጣኔ ወደ ኢትዮጵያ መግባት

ሐ. ፋሺስት ኢጣሊያ ሃገራችንን በወረረችበት ወቅት ስንቅና ትጥቅ በማዘጋጀት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉት የፖለቲካ ማህበራት_____ እና _____ ናቸው::

1. የሴቶች በጐ አድራጐትና የጥቁር አንበሳ ማህበራት
2. የሀገር ፍቅርና የሴቶች በጐ አድራጐት ማህበራት
3. የጥንታዊ ጀግኖችና የሴቶች በጐ አድራጐት ማህበራት
4. የጥንታዊ ጀግኖችና የጥቁር አንበሳ ማህበራት

መ. የቀይ መስቀል፣ የሞስኮ ኦርቶዶክሳዊና የድኩማን ማህበራት በይዘታቸው _____ናቸው::

1. አካባቢያዊ
2. አገራዊ /ብሔራዊ/
3. አህጉራዊ
4. ዓለማቀፋዊ

ሠ. በሶስተኛው አንቀጽ የመጀመሪያው መስመር «በእነዚህ» የሚለው ሀረግ የሚወክለው_____ ነው::

1. የክርስትና እና የእስልምና ሃይማኖቶች
2. የጽዋ የሰንበቴ እና የጽጌ ማህበራትን
3. የደቦ የሠርግ የህዘን ማህበራትን
4. የሀገር ፍቅር እና የሴቶች በጐ አድራጐት ማህበራትን

ረ. የጽዋ፣ የሰንበቴ፣ ዝክረ ቅዱሳንና የመሳሰሉትን ማህበራት ከክርስትና ሃይማኖት ከተሰበከ በኋላ መመሥረታቸው የምንረዳው በ_____ነው::

1. በተግባራቸው
2. በስያሜያቸው
3. በአገልግሎታቸው
4. በታሪካዊ አመጣጣቸው

ሲ. «በዚህ ዓለምና በወዲያኛው ዓለም« የሚሉት ሃረጎች _____ ናቸው::

1. በይዘታቸው አንድ የሆኑ
2. በትርጉማቸው አንድ የሆኑ
3. የተለያዩ ዐለማት የሆኑ
4. አንድ ዓይነት ዓለማት የሆኑ

ሸ. የማህበርን ቅደምተከተላዊ አመጣጥ የሚገልጸው ከሚከተሉት ውስጥ _____ ነው::

1. ሃይማኖታዊ፣ እለታዊ፣ ፖለቲካዊ
2. እለታዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሃይማኖታዊ
3. ፖለቲካዊ ሃይማታዊ፣ እለታዊ
4. ሃይማኖታዊ፣ ፖለቲካዊ፣ እለታዊ

ቀ. በምንባቡ የተጻፈበት የአጻጻፍ ስልት _____ ነው::

1. በማወዳደር
2. በምክንያትና ውጤት ተዛምዶ
3. በትረካ
4. በባያኒ

ድህረ ምንባብ

1. ማህበር የሚለውን ምንባብ ደጋግመህ ካነበብህ በኋላ ከራስህ ልምድና እውቀት በመነሳት በሚከተሉት ጥያቄዎች በቡድንህ አማካይነት ተወያይተህ እንደአጠያየቃቸው መልስ።

   ሀ. በአካባቢያሉት የሃይማኖታዊ ማህበራት አስያየማቸውና አተገባበራቸው ቀደም ሲል በምንባብ ከተረዳነው ጋር ተመሳሳይነት አለው? ከሌለውስ ልዩነቱ ምንድን ነው? በንግግር አስረዳ።

   ለ. በአካባቢህ ያሉ ሰዎች በሠርግ፣ በሀዘን ጊዜ ይሰበሰባሉ? ሰዎቹ የሚሰባሰቡ ከሆነ እንዲሰባሰቡ ያደረጋቸው የማህበር ዓይነት ምንድን ነው? የማህበሩ አመሠራረት ዓላማስ ምን ይመስልሃል? በንግግር አስረዳ።

   ሐ. ከአካባቢህ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ስታነፃጽረው ከሃይማኖታዊና ከአለታዊ ማህበር የተሻለ አስተዋጽኦ ያለው የትኛው ነው? ለምን ? _____

   መ. ማህበር ማለት ስያሜው እንደሚያመለክተው ተባበረ ወይም አንድ ሆነ ማለት ነው የዚህ ዓይነት አገላለጽ ምን ዓይነት የአገላለጽ ስልት ይመስልሃል ? _____

   ሠ. ማህበር የሚለውን ምንባብ የአጻጻፍ ስልቱ /አወቃቀሩ/ ምን እንደሚመስል ከተወያየህ በኋላ የደረስህበትን ማጠቃለያ ለክፍል ጓደኞችህ በቃል በንግግር አስረዳ።

ቅድመ ምንባብ

1. የሚከተሉትን ጥቄዎች ከራስህ ልምድና እውቀት በመነሳት በቡድንህ አማከየነት ከተወያየህ በኋላ ለክፍል ጓደኛህ በንግግር ግለጽ /10 ደቂቃ/

   ሀ. ስለ ሥዕል የምታውቀውን ሁሉ ዘርዝር

   ለ. አንዳንድ ጊዜ ሰው የመሰለ አንበሳ ገጥሞህ ታውቃለህ? ወይም ሌላ ሰው ልሆነ እንስሳ ነገር ግን ሰው ሆኖ ተስዕሎ ገጥሞህ ታውቃለህ የዚህ ዓይነት ሥዕል ከገጠመህ በአንተ ግምት ለእነዚህ ዓይነት ሰዓሊዎች ያለህ አስተያየት ምንድን ነው?

   ሐ. አንድ ሴት ስትበላ ምግቡን በእጇ ጠቅለል አድርጋ ወደ አፏመውሰድ ሲገባት ወደ ዓይኗ የምትወስድ ሥዕል ብትመለከት ለዚህ ዓይነት ሥዕል ያለህ አስተያየት ምንድን ነው? ለዚህ ዓይነት ሰዓሊስ የምትሰጠው አስተያየት ምንድን ነው?

   መ. በአብዛኛው የተሳሉት ሥዕሎች ከቆሙለት ጋር የአካላዊ ቅርበት ወይም ተመሳሳይነት የማይታይባቸው ሥዕሎች የሚገኙት የት ነው?

   ሠ. በቡና ቤት ውስጥ የምታያቸው ሥዕሎች ከቆሙለት ነገር ጋር ያላቸው አካላዊ ቅርበት በአንተ ግምት ምን ይመስላል?

2. ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ቃላት ጥንድ በመሆን ከተወያየህ በኋላ የምታውቃቸውን ቃላት በ √ የማታውቃቸውን ቃላት ደግሞ በ X ምልክት በመጠቀም በተሰጠህ ሳጥን አመልክት።

ሀ.	መተቻት	☐	ሲ.	እሽት	☐
ለ.	ጭጋግ	☐	ሸ.	መሸሞንሞን	☐
ሐ.	ልደት	☐	ቀ.	ጌጥ	☐
መ.	አፋፍ	☐	በ.	ጭራ	☐
ሠ.	እምቡጥ	☐	ተ.	ኮማሪ	☐
ረ.	ተስፋ	☐			

ምንባብ

የቡና ቤት ሥዕሎች

1. ሥዕል በጣም እወዳለሁ፤ ሠዓሊዎችንም አደንቃለሁ፤ ለሥዕል ከፍ ያለ ሰሜት አለኝ። ለምን ሠዓሊ አልሆንኩም ብዬ የጠየቅሁት አንድ ወዳጀ «በልጅነትህ ጥሩ የሥዕል አስተማሪዎች ስላላጋጠሙህ ይሆናል።» ብሎኝ ነበር እርግጥ የሥዕል አስተማሪዎቻችን ራሳቸው ሥዕል የማይችሉ ነበሩ።

5. ነበሩ። አፋቸው ላይ የመጣላቸውን ነገር ሳሉ ማለት ይቀናቸው ነበር በተሰይ ሰባተኛ ክፍል ሆኜ በመስኩት ያዩትን ነገር ለምሳሌ ባቡር ሲልፍ ካዩ ባቡር ሳሉ፣ አህያም ካለፈች አህያ ሳሉ የሚሉ አስተማሪ እንደነበሩ ትዝ ይለኛል።

ሥዕል ከማፍቀሬ የተነሳ ትንሽ ልክር ብል ድሮ በአንደኛ

ደረጃ ትምህርት ቤት የተለማመድኩትን ባለአራት እግር ጠረጴዛ ነው ከዚህ ይልቅ የአንድን ሥዕል

10. ውበት መልእክት መገንዘብ በአጠቃላይ አቅሜ በሚፈቅድልኝ መሠረት መተቸት ደስ ይለኛል ከዚህም በመነሳት ስለአንዳንድ የቡና ቤት ሥዕሎች የመሳሰሉትን ነገሮች ለመናገር እሞክራለሁ

ሳስበው በአንዲት የእርሳስ ጨረት ብዙ መናገር ቅርበትን ርቀትንና ጥላና ብርሃንን ክፍታና ዝቅታን ማሳየት ሰማዩን፣ አድማሱን፣ ዝናቡን፣ ጭጋጉን፣ ማሳየት ከሁሉም በላይ ደግሞ እንደ ሃዘን፣ ደስታ፣ ጸጸትና ናፍቆት ያሉትን ረቂቅ ነገሮች ወረቀት ላይ
መፍጠር ምንኛ ደስ ይላል።

በእድሜ ጐዳና ሲያዘግም ኖሮ ወደ ሞት አፋፍ ብቅ የሚል ፀጋ የተሞላበት ሽምግልና፣ እንደ እምቡጥ አበባ የሚፈነዳ በተስፋና በምኞት አዝመራ
ያሸተ ወጣት በረሃብ የተፈታን አካል ስቃይ ካጐደጐደው ዓይንና ከተጨማደደ ፊት ጋር ተባብሮ የሚያሳየው ብሶት የፍቅር ምትሃት የሃዘን ምሬት በአጠቃላይ ተፈጠሮ በሸራ ላይ
የምትሸሞነሞንበት ትልቅ ጥበብ ቢኖር ሥዕል ነው።

ታዲያ ይህችው ተፈጥሮ ተሰጥኦና ችሎታ ባላቸው ሰዓሊያን የምትጌጠውንና በእውነታ የምታሸበርቀውን ያህል ሙያውን በወጉ በማያውቁ ሰዎችም
ትዋረዳለች። ይህንን ለማረጋገጥ የቡና ቤት ሥዕሎችን መመልከቱ ይበቃል። የቡና ቤት ሥዕሎች ስንል የሥዕል ጥበብ የሌላቸውን ተራ በም ተራ የሆኑትን ማለቴ ነው። ለምሳሌ « ምን ልታዘዝ
የምትል እግሯ ክርኗ ሥር ሊሆን ትንሽ የቀረው የመጠጥ ቤት ኮማሪት ወይም ታዲያስ ምን ይምጣ? ከሚል ጽሁፍ ሥር አንዱ አዳምጡኝ እንደሚል አስተማሪ እጁን የዘረጋ የምግብ ቤት አስተናጋጅ ግድግዳ ላይ ተስለው አይታችሁ አታውቁም? ቀንዱ ተጠምዝዞ ጭራው ጋር የደረሰ ዋልያ፣ ጽጌረዳ ሊቀጥፍ የተዘጋጀ እንደ ሰው ጥርስ ችምችም ያለ አንበሳ፣ ማይክሮፎን የሚመስል ቡና ማፍያ መኪና ዝርዝሩ ብዙ ነው።

በአንድ የባህል ምግብ ቤት ያየሁት ሌላ ሥዕል አለ በምን አወቅህ
እንዳትሉኝ እንጂ የተሳሉት ባልና ሚስት ሳይሆኑ አይቀሩም። ጐን ለጐን ተቀምጠዋል። ምግብ ቀርቧል በመሶበወርቅ። አንድ ውሻ ተጋድሟል ዓይኖቹን ጨፍኗል። አንቅልፍ የወሰደው ይመስላል። ምግብ እየሸተተው የሚተኛ ውሳ ታውቃላችሁ? ከምጣኔ ስህተት የተነሳ ውሻው አልጠፋ ቦታ እመሶበወርቁ ሥር ነው። ጭራው እንደ ደህና ነገር ባልየው እግር ላይ
አርፏል። ሴትየዋ እጆቿን ዘርግታለች ወደ ሰዎቹ «በሉ እስቲ እንደ ነገሩም ቢሆን።» ትላለች ማለት ነው፤ ነገር ግን እጅ አዘረጋግዋ መድረክ ላይ ወጥታ ንግግር የምታደርግ አስመስላታል። ባልየው እጁን ይታጠባል፣ የሱ እንኳ ደህና ነው። የምታስታጥበው ልጅ ግን በቅጣት ላይ ነው ለች የሚመስላችሁ። ምክንያቱም ጐንበስ በማለት ፋንታ እንደ መንበርከክ ብላለች።
የቁሱ ከሁሉ የተለየ ነው። ለመብላት የተዘጋጁ አይመስሉም፤ ብቻ ዝም ብለው መስቀልና
ጭራቸውን ለምግብ ቤቱ ደምበኞች ያሳያሉ። የምግብ ቤቱን ባለቤት ማነው ይህን የሳለልዎት ብዬ ጠየቅኳቸው።

« አንድ የተባረከ ልጅ ነወ እንዲህ እንዳንተ ሊመገብ መጥቶ አሉኝ»

« ለመሆኑ ምን ያህል አስከፈለዎት? »

« ዛሬ አታገኘው ምን ያደርግልሃል? »

« እንዲያው ለማወቅ ብዬ ነበር» አልኳቸው።

« ክፍለ ሀገር ከሄደ ዘመን የለውም።»

« የለም ብዬሃለሁ። የለም አዲስ አበባ።»

« ግን ሥዕሉ ጥሩ ነው ወይም እርስዎ ሲያስቡት?»

« ያው ታየዋለህ ምን ትጠይቀኛለህ?»

« ሥለ ሥዕሉ ለዎትን አስተያየት።»

« አንድ አስተያየት የለም የበሉትን በልተው ውልቅ።»

ምንጭ፣ መሥፍን ሀ/ማርያም፣ የቡና ቤት ሥዕሎች፣ ከገጽ 12-22 የተወሰደ።

1. ምንባቡን ገረፍ ገረፍ በማድረግ ካነበብህ በኋላ የሚከተሉትን ጅምር ዓረፍተ ነገሮች ጨርሰህ ጽፈህ ለክፍል ጓደኞችህ አንብብላቸው። /7 ደቂቃ/

ሀ. ሥዕል በጣም እወዳለሁ ሠዓሊያችንም አደንቃለሁ፣ ለሥዕል ከፍ ያለ ስሜት አለኝ።_____

ለ. የሥዕል አስተማሪያችን ራሳቸው ሥዕል የማይችሉ ነበሩ አፋቸው ላይ የመጣላቸውን ነገር ሳሉ ማለት ይቀናቸው ነበር በተለይ _____

ሐ. ሥዕል ከማፍቀሬ የተነሳ ትንሽ ልሞክር ብል ድሮ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተለማመድኩትን ባለአራት አግር ጠረጴዛ ነው ከዚህ ይልቅ _____

መ. ታዲያ ይህችው ተፈጥሮ ተሰጥኦና ችሎታ ባላቸው ሰዓሊያን የምታሸበርቀውን ያህል ሙያውን በወጉ በማያውቁ ሰዎችም ትዋረዳለች ይህን ለማረጋገጥ_____

ሠ. የቡና ቤት ሥዕሎች ስንል _____

ረ. ሴትየዋ እጆቿን ዘርግታለች ወደ ሰዎቹ። በሉ እስቲ እንደነገሩም ቢሆን ትላለች ለማት ነው የምታስታጥበው ልጅ ግን _____

ሰ. የቁሱ ከሁሉም የተለየ ነው። ለመብላት የተዘጋጀ አይመስሉም ብቻ ዝም ብለው _____

2. የቡና ቤት ሥዕሎችን የሚለውን ምንባብ በፍጥነት ገረፍ ገረፍ አድርገህ ካነበብህ በኋላ በቡድንህ አማካኝነት በመወያየት በአነበብኸው መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃልህ መልስ /5 ደቂቃ/

ሀ. የአንደኛው አንቀጽ ፍሬ ሀሳብ _____

ለ. የሁለተኛው አንቀጽ ፍሬ ሃሳብ _____

ሐ. የሰስተኛው አንቀጽ ፍሬ ሀሳብ _____

መ. የአራተኛው አንቀጽ ፍሬ ሀሳብ _____

ሠ. የአምስተኛው አንቀጽ ፍሬ ሀሳብ _____

ረ. የስድስተኛው አንቀጽ ፍሬ ሃሳብ

ሰ. እኔ እያለ የሚተርከው ተራኪ ስለ አንድ ባህል ምግብ ቤት ያየውን ነገር የሚተርከውን ሃሳብ የሚገልፀው አንቀጽ _____ነው።

ሸ. ተራኪው ስለ ሥዕል ያለውን አድናቆት የሚገልጽበት አንቀጽ የሚገኘው በ_____ ነው።

ቀ. ተራኪው ስለ ሥዕል ያለውን አሉታዊ አመለካከት የሚገልጸው አንቀጽ_____ነው።

በ. ተራኪው ስለ ሥዕል ያለውን አሉታዊ አመለካከት የገለጸው አንቀጽ_____ነው።

ተ. በተራኪውና በባለቡናቤቱ መካከል ያለው ምልልስ የተገለጸው አንቀጽ_____ነው

ቸ. ስለ ውሻው፣ ስለቁሱ፣ ስለ ሠራተኛውና የቤቱ ባለቤት የአሳሳል ሁኔታ የተገለጸበት አንቀጽ_____ ነው።

ኀ. በምንባቡ ውስጥ ያለውን አንቀጽ ብዛት _____ ነው።

3. ከዚህ በታች የቀሰጠውን ምንባብ በጥንቃቄ ካነበብህ በኋላ ጥንድ በመሆን ከራስህ ልምድና እውቀት በመነሳት እየተወያየህ ተስማሚ የሆነውን ቃል ወይም ሀረግ በተሰጠህ ባዶ ቦታ እያስገባህ ጻፍ።

ሥዕል በጣም እወዳለሁ። ሠዓሊዎችንም አደንቃለሁ። ለሥዕል_____ ያለ ስሜት እያለኝ ለምን ሠዓሊ አልሆንኩም _____የጠየቅሁት አንድ ወዳጄ በልጅነትህ ጥሩ የሥዕል_____ ስላላጋጠመህ ይሆናል ብሎኝ ነበር እርግጥ የሥዕል_____ ራሳችን ሥዕል የማይችሉ ነበሩ። አፋቸው

ላይ_____ ነገር ሳሉ ማለት ይቀናቸው ነበር በተለይ _____ ክፍል ሆኜ በመስኮት ያዩትን ነገር ለመሳል_____ ሲያልፍ ካዩ ባቡር ሳሉ አህያ ሲልፍ _____ አህያ ሳሉ የሚሉ አስተማሪ እንደነበሩ ትዝ_____

ሥዕል ከማፍቀሬ የተነሳ ትንሽ ልሞክር ብል_____ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተለማመድኩትን ባለአራት እግር _____ነው።

ከዚህ ይልቅ የአንድን ሥዕል ውበት _____ መገንዘብ ባጠቃላይ አቅሜ በሚፈቅድልኝ መሠረት መተቸት_____ ይለኛል። ከዚህ በመነሳት ስለአንዳንድ የቡና ቤት ሥዕሎች _____የመሳሰሉትን ነገሮች ለመናገር እከራለሁ።

ሳስበው በአንዲት የእርሳስ ጭረት ብዙ መናገር _____ ርቀትን ጥላንና ብርሃንን፣ ከፍታና ዝቅታን፣ ማሳየት _____አድማሱን፣ ዝናቡን፣ ጭጋጉን ማሳየት ከሁሉም በላይ ደግሞ እንደ _____እንደ ደስታ፣ ጸጸት፣ ናፍቆት፣ ያሉትን ረቂቅ ነገሮች _____ ላይ መፍጠር ምንኛ ደስ ይላል።

በአድሜ ጉዳና ሲያዘግም ኖሮ ወደ ሞት አፋፍ_____ የሚል ፀጋ የተሞላበት ሽምግልና፣ እንደ እምቡጥ አበባ _____በተስፋና በምኞት አዝመራ ያሸተ ወጣት በረሃብ _____ አካል ስቃይ ከተጎዳው ዓይንና ከተጨማደደ ፊት_____ተባብሮ የሚያሳየው ብሶት፣ የፍቅር ምትሃት፣ የሐዘን_____በአጠቃላይ ተፈጥሮ በሸራ ላይ የምትሸሞነሞንበት ትልቅ_____ቢኖር ስዕል ነው።

ታዲያ ይህችው ተፈጠሮ፣ ተሰጥኦና ችሎታ ባላቸው_____የምትሰጠውንና በእውነታ የምታሸበርቀውን ያህል ሙያውን በወጉ_____ሰዎችም ትዋረዳለች ይህን ለማረጋገጥ የቡና ቤት ሥዕሎችን _____ይበቃል። የቡና ቤት ሥዕሎችን ስንል የሥዕል ጥበብ የሌላቸውን_____ በጣም ተራ የሆኑትን ማለቴ ነው። ለምሳሌ ምን_____ የምትል እግሯ ክርኗ ሥር ሊሆን ትንሽ _____ የመጠጥ ቤት ኮማሪት ወይም ታዲያስ ምን _____ከሚል ጽሁፍ ሥር አንዴ አዳምጡኝ እንደሚል _____ እጁን የዘረጋ የምግብ ቤት አስተናጋጅ ግድግዳ ላይ_____ አይታችሁ አታውቁም ቀንዱ ተጠምዝዞ ጭራው ጋር የደረሰ_____ጽጌረዳ ሊቀጥፍ የተዘጋጀ አንድ ሰው ጥርስ_____ ያለ አንበሳ፣ ማይክሮፎን የሚመስል ቡና መፍያ _____ ዝርዝሩ ብዙ ነው።

በአንድ የባህል ምግብ ቤት ያየሁት ሌላ ሥዕል_____። በምን አወቅህ እንዳትሉኝ እንጂ የተሳሉት ባልና_____ሳይሆኑ አይቀሩም። ጉን ለጉን ተቀምጠዋል።_____ቀርቧል። በመሶበወርቅ አንድ ውሻ ተጋድሟል።_____ ጨፍኗል፣ እንቅልፍ የወሰደው ይመስላል ምግብ አየሸተተው_____ውሻ አይታችሁ ታውቃላችሁ? ከምጣኔ ስህተት የተነሳ ውው_____ ቦታ እመሶበወርቁ ሥር ነው። ጭራው እንደደህና ነገር_____እግር ላይ አርፏል። ሴትየዋ እጆቿን ዘርግታለች_____በሉ እስቲ እንደነገሩም ቢሆን ትላለች ለማለት_____ ነገር ግን እጅ አዘረጋግዋ መድረክ ላይ ሆና_____ ንግግር የምታደርግ_____ባልየው እጁን ይታጠባል፣ የሱ እንኳን ደህና_____የምታስታጥበው ልጅ ግን በቅጣት ላይ ያለች_____ ምክንያቱም ጉንበስ በማለት ፈንታ እንደመንበርከክ ብላለች_____ ከሁሉም የተለየ ነው ለመብላት የተዘጋጀ አይመስሉም። _____ ዝም ብለው መስቀልና ጭራቸውን ለምግብ ቤቱ ደምበኞች_____የምግብ ባለቤት ማነው ይህን ሥዕል የሳለልዎት _____ ጠየቅኳቸው።

« አንድ የተባረከ ልጅ ነው እንዲሁ እንዳንተ_____ መጥቶ አሉኝ»

« ለመሆኑ ምን ያህል አስከፈለዎት»

« ዛሬ አታገኘው_____ያደርግልሃል? ክፍለ ሀገር ከሄደ ዘመን የለውም።»

« እንዲያው _____ብዬ ነበር አልኳቸው»

« የለም ብዬሃለሁ እንግዲህ _____»

« ግን ሥዕሉ ጥሩ ነው ወይ? እርስዎ ሲያስቡት ?

« _____ ታየዋለህ ምን ትጠይቀኛለህ»

« ስለ ሥዕሉ ያለዎት አስተያየት::»

« አንድ አስተያየት የለም የበሉትን በልተው_____»

4. የቡና ቤት ሥዕሎች ከሚለው ምንባብ በአሰላ የአነባበብ ስልት እየፈለግህ ከዚህ በታች ለተሰጡት ቃላት እንደ አጠያየቃቸው የቃሉን ተመሳሳይ ፍቺ ወይም ተቃራኒ ለክፍል ጓደኞችህ ተናገር:: /5 ደቂቃ/

ሀ. «ቅርበት» ለሚለው ቃል ተቃራኒ ሊሆን የሚችለው ቃል ከአንቀጽ ሶስት ውስጥ_____የሚለውን ቃል ነው::

ለ. «ጌጥ» ለሚለው ቃል ከአንቀጽ አምስት ውስጥ ተመሳሳይ ሊሆን የሚችለው ቃል_____ የሚለው ቃል ነው::

ሐ. «ጸጸት» ለሚለው ቃል ተቃራኒ ሊሆን የሚችለው ቃል ከአንቀጽ ሶስት ውስጥ_____ የሚለው ነው::

መ. «ተስፋ» ለሚለው ቃል ከአንቀጽ አራት ውስጥ ተመሳሳይ ሊሆን የሚችለው ቃል_____ የሚለው ነው::

ሠ. «ደስታ» ለሚለው ቃል ከአንቀጽ ሶስት ውስጥ ተመሳሳይ ሊሆን የሚችለው ቃል_____የሚለው ቃል ነው::

5. «የቡና ቤት ሥዕሎች» ከሚለው ምንባብ በአሰላ የአነባብ ስልት እየፈለገህ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃልህ መልስ:: /10 ደቂቃ/

ሀ. አንቀጽ /ሶስት/ ውስጥ እንደተገለጸው ቅርበትንና ርቀትን፣ ጥላና ብርሃንን፣ ከፍታና ዝቅታን ማሳየት ሰማዩን፣ አድማሱን፣ ጭጋጉን ማሳየት የሚችለው በ_____ አማካኝነት ነው::

ለ. በአንቀጽ /አንድ/ ውስጥ እንደተገለጸው በመስኮት ያዩትን ነገር ሁሉ ሳሉ ማለት የሚቀናቸው_____ ናቸው::

ሐ. አንቀጽ /አምስት/ ውስጥ እንደተገለጸው የሥዕል ጥበብ የተዋረደ መሆኑን ለማሳየት ቢሳል ለምሳሌነት የተጠቀሰው_____ሥል ነው::

መ. አንቀጽ /ስድስት/ ውስጥ እንደተገለጸው መድረክ ላይ ወጥታ ንግግር የምታደርግ ትመስላለች የተባለችው _____ ናት::

ሠ. አንቀጽ /ስድስት/ ውስጥ እንደተገለጸው እመሶበወርቁ ሥር ተጋድሞ የተሳለው _____ ነው::

ረ. አንቀጽ /ስድስት/ ውስጥ እንደተገለጸው ከሁሉም በተሻለ ሁኔታ የተሳለው _____ ነው::

ሰ. አንቀጽ /ስድስት/ ውስጥ እንደተገለጸው ከሁሉም በተለየ ሁኔታ ምጣኔውን ሳይጠብቅ የተሳለው የ_____አሳሳል ነው::

6. ከዚህ በታች የተሰጡት አንቀጾች ቅደም ተከተላቸው ተዛብቷል በነዚህ በተዛቡ አንቀጾች ላይ በቡድንህ አማካይነት ከተወያየህ በኋላ አንቀጾች አንድ የተሟላ ሃሳብ እንዲሰጡ አድርገህ በቅደም ተከተላቸው አስተካክለህ ጻፍ:: /15 ደቂቃ/

1. ታዲያ ይህችው ተፈጥሮ ተሰጥኦና ችሎታ ባላቸው ሠዓሊያን የምትጌጠውንና በእውነታ የምታሸበርቀውን ያህል ሙያው በሆኑ በማያውቁ ሰዎችም ትዋረዳለች ይህን ለማረጋገጥ የቡና ቤት ሥዕሎችን መመልከቱ ይበቃል:: የቡና ቤት ሥዕሎች ስንል

የሥዕል ጥበብ የሌላቸውን ተራ በጣም ተራ የሆኑትን ማለቴ ነው። ለምሳሌ ምን ልታዘዝ? የምትል እግሯ ክርኗ ሥር ሊሆን ትንሽ የቀረው የመጠጥ ቤት ኮማሪት ወይም ታዲያስ ምን ይምጣ? ከሚል ጽሁፍ ሥር አንዱ አዳምጡኝ እንደሚል አስተማሪ እጁን የዘረጋ የምግብ ቤት አስተናጋጅ ግድግዳ ላይ ተስለው አይታችሁ አታውቁም? ቀንዱ ተጠምዝዞ ጭራው ጋር የደረሰ ዋልያ፣ ጽጌረዳ ሊቀጥፍ የተዘጋጀ እንደ ሰው ጥርስ ችምችም ያለ አንበሳ፣ ማይክሮፎን የሚመስል ቡና ማፍያ መኪና ዝርዝሩ ብዙ ነው።

2. በአንድ የባህል ምግብ ቤት ያየሁት ሌላ ሥዕል አለ። በምን አወቅህ አንዳትሉኝ እንጂ የተሳሉት ባልና ሚስት ሳይሆኑ አይቀሩም ጉን ለጉን ተቀምጠዋል። ምግብ በርቧል፣ በመሶበወርቁ። አንድ ውሻ ተጋድሟል፣ ዓይናቹን ጨፍኗል። እንቅልፍ የወሰደው ይመስላል ምግብ እየሸተተው የሚተኛ ውሻ ታውቃላችሁ? ከምጣኔ ስህተት የተነሳ ውሻው አልጠፋ ቦታ እመሶበወርቁ ሥር ነው ጭራው እንደ ደህና ነገር ባልየው እግር ላይ አርፏል። ሴትየዋ እጀጀን ዘርግታለች ወደ ሰዎቹ በሉ እስቲ «እንደ ነገሩም ቢሆን» ትላለች ለማት ነው ነገር ግን እጅ አዘረጋግዋ መድረክ ላይ ወጥታ ንግግር የምታደርግ አስመስሏታል። ባልየው እጁን ይታጠባል። የሱ እንኳን ደህና ነው። የምታስታጥበው ልጅ ግን በቅጣት ላይ ነው ያለች የሚመስላችሁ። ምክንያቱም ጉንበስ በማለት ፋንታ እንደመንበርከክ ብላለች። የቁሱ ከሁሉም የተለየ ነው። ለመብላት የተዘጋጁ አይመስሉም። ብቻ ዝም ብለው መስቀልና ጭራቸውን ለምግብ ቤቱ ደምበኞች ያሳያሉ። የምግብ ቤቱን ባለቤት ማነው ይህንን ሥዕል የሣለለዎት? ብዬ ጠየቅኳቸው።

« አንድ የተባረከ ልጅ ነው እንዲህ አንዳንተ ሊመገብ መጥቶ አሉኝ»

« ለመሆኑ ምን ያህል አስከፈለዎት? »

« ዛሬ አታገኘው ምን ያደርግልሃል? »

« እንዲያው ለማወቅ ብዬ ነበር» አልኳቸው።

« ክፍለ ሀገር ከሄደ ዘመን የለውም።»

« የለም ብዬሃለሁ። የለም አዲስ አበባ።»

« ግን ሥዕሉ ጥሩ ነው ወይ እርስዎ ሲያስቡት?»

« ያው ታየዋለህ ምን ትጠይቀኛለህ?»

« ሥለ ሥዕሉ ያለዎት አስተያየት።»

« አንድ አስተያየት የለም የበሉትን በልተው ውልቅ።»

3. በአድሜ ጉዳና ሲያዘግም ኖሮ ወደሞት አፋፍ ብቅ የሚል ፀጋ የተሞላበት ሽምግልና እንደ እምቡጥ አበባ የሚፈነዳ በተስፋና በምኞት አዝመራ ያሸተ ወጣት በረሃብ የተፈታን አካል ስቃይ ከጐድጓዳው ዓይንና ከተጨማደደ ፊት ጋር ተባብሮ የሚያሳየው ብሶት፣ የፍቅር ምትሃት፣ የሃዘን ምሬት፣ በአጠቃላይ ተፈጥሮ በሸራ ላይ የምትሸምነመንበት ትልቅ ጥበብ ቢኖር ሥዕል ነው።

4. ሥዕል በጣም አወዳለሁ ሠዓሊዎችንም አደንቃለሁ ለሥዕል ከፍ ለ ስሜት አለኝ። ለምን ሠዓሊ አልሆንኩም? ብዬ የጠየቅሁች አንድ ወዳጀ «በልጅነትህ ጥሩ የሥዕል አስተማሪዎች ስላላጋጠመህ ይሆናል።» ብሎኝ ነበር እርግጥ የሥዕል አስተማሪዎቻችን ራሳቸው ሥዕል የማይችሉ ነበሩ። አፋቸው ላይ የመጣላቸውን ነገር ሳሉ ማለት ይቀናቸው ነበር። በተለይ ሰባተኛ ክፍል ሆኜ በመስኮት ያዩትን ነገር ለምሳሌ ባቡር ሲያልፍ ካየ ባቡር ሳሉ አህያም ካለፈች አህያ ሳሉ የሚሉ አስተማሪ እንደነበሩ ትዝ ይለኛል።

5. ሳስበው በአንዲት የእርሳስ ጭረት ብዙ መናገር ቅርበትን ርቀትን ጥላና ብርሃንን ከፍታና ዝቅታን ማሳየት ሰማዩን፣ አድማሱን፣ ዝናቡን፣ ጭጋጉን፣ ማሳየት ከሁሉም በላይ

ደግሞ እንደ ሃዘን፣ ደስታ፣ ናፍቆት ያሉትን ረቂቅ ነገሮች ወረቀት ላይ መፍጠር ምንኛ ደስ ይላል።

6. ሥዕል ከማፍቀሬ የተነሳ ትንሽ ልምክር ብል ድሮ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተለማመድኩትን ባለ አራት እግር ጠረጴዛ ነው። ከዚህ ይልቅ የአንድን ሥዕል ውበት መልእክት መገንዘብ በአጠቃላይ አቅሜ በሚፈቅድልኝ መሠረት መተቸት ደስ ይለኛል። ከዚህም በመነሳት ስለ አንዳንድ የቡና ቤት ሥዕሎች የመሳሰሉትን ነገሮች ለመናገር እሞክራለሁ።

7. የቡና ቤት ሥዕሎች የሚለውን ምንባብ በድጋሚ በሎሆሳስ የአነባብ ስልት አንብብ። በአነበብሽው መሠረት በቡድንህ አማካኝነት ከተወያየህ በኋላ የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች መንደርደሪ ዓረፍተ ነገሮችና ዝርዝር ዓረፍተ ነገሮች መሆናቸውን ለይ። ዓረፍተ ነገሩ መንደርደሪያ ከሆነ መንደርደሪያ በሚለው ዓምድ ሥር « ✓ » ምልክት አመልክት ዓረፍተ ነገሩ መዘርዝራዊ ከሆነ መዘርዝር በሚለው ዓምድ ሥር « X » ምልክት አመልክት። /5/ ደቂቃ

ተ.ቁ	ዓረፍተ ነገር	የዓረፍተነገሩ	
		መንደርደሪያ	ዝርዝር
ሀ.	ከዚህ ይልቅ የአንድን ሥዕል ውበት መልእክት መገንዘብ በአጠቃላይ አቅ በማፈቅድልኝ መሠረት መተቸት ደስ ይለኛል።		
ለ.	ሥዕል ከማፍቀሬ የተነሳ ትንሽ ልምክር ብል ድሮ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተለማመድኩትን ባለአራት እግር ጠረጴዛ ነው።		
ሐ.	ከዚህም በመነሳት ስለአንዳንድ የቡና ቤት ሥዕሎች የመሳሰሉትን ነገሮች ለመናገር እሞክራለሁ።		
መ.	ሥዕል በጣም እወዳለሁ ሠዓሊዎችንም በጣም አደንቃለሁ።		
ሠ.	በአጠቃላይ ተፈጥሮ በሸራ ላይ የምትሽሞነሞንበት ትልቅ ጥበብ ቢኖር ስዕል ነው።		
ረ.	ይህን ለማረጋገጥ የቡና ቤት ሥዕሎችን መመለከት ያሻል።		
ሰ.	በአንድ የባህል ምግብ ቤ ሌላ ሥዕል አለ።		
ሸ.	አፋቸው ላይ የመጣላቸውን ነገር ሳሉ ማለት ይቀናቸው ነበር።		
ቀ.	ታዲ ይህችው ተፈጥሮ ተሰጥኦና ችሎታ ባላቸው ሰዓሊያን የምትጌጠውንና በእውነታ የምታሸበርቀውን ያህል ሙያውን በወጉ በማያውቁ ሰዎችም ትዋረዳለች።		

ንባብ (While Reading)

1. የሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት የቡና ቤት ሥዕሎች ከሚለው ምንባብ የወጡ ናቸው ። ምንባቡን በግል በጥንቃቄ ካነበብህ በኋላ ለቃላቱና ለሀረጎቹ ከአነባበባቸው አንፃር ሊይዙት የሚችሉትን ትርጉም ጥንድ በመሆን በመወያየት ለክፍል ጓደኞችህ ተናገር።

ሀ. «አፋፍ» /መስመር 18/ _____

ለ. «ጸጸት» /መስመር 16/ _____

ሐ. «መተቸት» /መስመር 11/ _____

መ. «መሽሞንሞን» /መስመር 22/ _____

ሠ. «ኮማሪ» /መስመር 27/ _____

ረ. «እምቡጥ» /መስመር 19/ _____

ሰ. «እሽት» /መስመር 20/ _____

ሸ. «ውበት» /መስመር 11/ _____

ቀ. «ተስፋ» /መስመር 19/ _____

በ. «ጭጋግ» /መስመር 16 _____

ተ. «ተሰጥኦ» /መስመር 23/ _____

ቸ. «ማሸብረቅ» /መስመር 24/ _____

ኀ. «መሶበወርቅ /መስመር 36/ _____

ነ. «ምጣኔ» /መስመር 38/ _____

ኘ. «ደምበኛ» /መስመር 46/ _____

አ. «ጌጥ» /መስመር 23/ _____

2. የሚከተለውን አንቀጽ ረጋ ብለህ ካነበብህ በኋላ በአንቀጹ መሠረት በቀረቡት የምርጫ ጥያቄዎች ላይ በቡድን ተወያይተህ ትክክለኛውን መልስ በያዘው ሆሄ ላይ አስምርበት።

አንቀጽ

<u>በእድሜ ጐዳና</u> ሲዘግም ኖሮ <u>ወደ ሞት አፋፍ</u> ብቅ የሚል <u>ፀጋ</u> የተላበት ሽምግልና እንደ እምቡጥ አበባ የሚፈነዳ በተስፋና በምኞት አዝመራ <u>ያሸተ ወጣት</u> በረሃብ የተፈተነ አካል ስቃይ ከገደጉደው ዓይንና ከተጨማደደ <u>ፊት ጋር</u> ተባብሮ የሚያሳየው ብሶት <u>ፍቅር ምትሃት የሃዘን</u> ምሬት በአጠቃላይ ተፈጥሮ በሸራ ላይ የምትሸሞነሞንበት ትልቅ ጥበብ ቢኖር ስዕል ነው።

ሀ. <u>በእድሜ ጐዳና</u> በሚለው ሀረግ ጐዳና የሚለው ቃል የያዘው ትርጉም _____ የሚል ነው።

1. የሕይወት ውጣ ውረድ
2. የጉዞን አቅጣጫ
3. በሕይወት እያሉ ከቦታ ቦታ የሚደረገውን እንቅስቃሴ

ለ. <u>ወደሞት አፋፍ</u> በሚለው ሀረግ «አፋፍ» የሚለው ቃል የቆመለት ፍች _____ ለሚለው ነው።

1. ተራራው የመጨረሻ ጫፍ
2. ከዓለም ምድረ ገጽ ጨርሶ መጥፋት
3. የሕይወት የመጨረሻው ፍጻሜ ላይ መድረስ

ሐ. <u>ያሸተ ወጣት</u> በሚለው ሀረግ «ያሸተ» የሚለው ቃል የቆመለት ፍች_____ለሚለው ነው።

1. የተለያዩ ፍላጐቶችን ለማሟላት የሚፈልግ
2. ፍላጐቱን እውን ለማድረግ የተዘጋጀ
3. ሁሉ ነገር የሀልም እንጀራ የሆነበት

መ. <u>ከተጨማደደ ፊት</u> ሲል _____ ማለቱ ነው።

1. ከተኩሳተረ ፊት
2. ከተጐሳቆለ ፊት
3. ከማይፈታ ፊት

ሠ. ብሶት፣ ፍቅር፣ ምትሃትና ሀዘን_____ናቸው።

1. ስሜቶች ናቸው
2. ረቂቅ ነገሮች ናቸው
3. ሁሉም መልስ ነው

3. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አያያዥ ቃላትና ሀረጋት ከምንባቡ የወጡ ናቸው። እነዚህን አያያዥ ቃላትና ሀረጋት ደራሲው በምንባቡ ውስጥ ለምን እንደተጠቀመባቸው ጥንድ በመሆን ከተወያየህ በኋላ ጥቅማቸውን ከአገባባቸው አንፃር ለክፍል ጓደኞችህ ተናገር።

ሀ. «ከሁሉም በላይ» /መስመር 16/ _____።

ለ. «ከዚህ ይልቅ» /መስመር 11/ _____።

ሐ. «ነገር ግን» /መስመር 41/ _____።

መ. «ከዚህም በመነሳት» /መስመር 12/ _____።

ሠ. «ምክንያቱም» /መስመር 44/ _____።

4. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አያያዥ ቃላትና ሀረጋት ከምንባቡ የወጡ ናቸው። አያያዥ ቃላትና ሀረጋት ጥንድ በመሆን ከተወያየህ በኋላ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በተሰጠው ባዶ ቦታ በተገቢ ቦታቸው እያስገባህ ጽፈህ ለክፍል ጓደኞችህ አንብብላቸው።

ከሁሉም በላይ	ነገር ግን	ከዚህ በመነሳት
ከዚህ ይልቅ	በተለይ	ምክንያቱም

ሀ. ሥዕል ለመሳል ፍላጐቱ የለኝም_____አጫጭር ልቦለዶችን ቀልዶችን መጻፍ ደስ ይለኛል።

ለ. በዚህች ዓለም ላይ እኔን_____ የሚያስደስተኝ ነገር ቢኖር ሁሉም ሰው ደስተኛ ሆኖ ማየትን ነው።

ሐ. ሥዕል ለመሳል ያለኝ ችሎታ በጣም ዝቅተኛ ነው_____የተሳሉትን ሥዕሎች መልእክት መገንዘብና አስተያየት መስጠት ደስ ይሰኛል።

መ. በአብዛኛው የዱር እንስሳት አራሳቸውን ከጠላት ለመከላከል ሲሉ መተናኮላቸው አይቀርም_____ ለዚህ ዓይነት ተግባር እንበሳና ነብር በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው።

ሠ. ቀደም ሲል ከሰባተኛ ክፍል ጀምሮ ከተለያዩ መጽሔቶችና ጋዜጦች አንዳንድ ወጋዊ ጽሑፎችንና ቀልዶችን አነባለሁ።_____ዛሬ የተለያዩ አጫጭር ልቦለዶችንና በተለያዩ መጽሔቶችና ጋዜጦች ለማቅረብ በቅቻለሁ።

ረ. መዲና ከቤተመጻሕፍት ውስጥ ገብታ ረዘም ላለ ጊዜ ለማንበብ ልምዱ የላትም_____ቀደም ሲል ጀምሮ ለንባብ የምትሰጠው ጊዜ አነስተኛ በመሆኑ ነው።

5. ከዚህ በታች የቀረቡት ጥያቄዎች ከምንባቡ የወጡ ናቸው ጥያቄዎችን በቡድንህ አማካኝነት ከተወያየህባቸው በኋላ የተስማማህበትን መልስ ለክፍል ጓደኞችህ ጽፈህ አንብብላቸው /ጥቄዎችን ከመመለስህ በፊት ምንባቡን በሉሰስ በርጋታ አንብብ።

ሀ. በምንባቡ ውስጥ «እኔ» የሚለው ተራኪ ሠዓሊ ለመሆን ያለቻለበት ምክንያት ምንድን ነው? _____

ለ. በምንባቡ ውስጥ እኔ የሚለው ተራኪ ሠዓሊ ለመሆን ፍላጐት እንዳለው ተገልጿል። ነገር ግን ተራኪው ምንም እንኳን ሠዓሊ የመሆን ፍላጐት ቢኖረውም ሊስል ቢፈልግ ምን የሚመስል ይመስልሃል? ለምን የመስልሃል?_____

ሐ. በምንባቡ ውስጥ እኔ የሚለው ተራኪ ከአገላለጹ እንደምንረዳው ችሎታው ምንድን ነው ብለህ ታስባለህ? _____

መ. እንደ ምንባቡ አባባል ከሆነ ተፈጥሮ በእውነታ የምትሄጠውና የምታሸበርቀው በምን ይመስልሃል? _____

ሠ. የሥዕል ሙ የተከበረውን ያህል እንደተዋረደ በደራሲው ተገልጿል የሥዕል ሙያ የተዋረደ መሆኑን ለመግለጽ ለአብነት የጠቀሰውን የሥዕል ዓይነት ዘርዝር። _____

ረ. አንድ ሰው በሰዓሊነት ሙያ ለመሰማራት የሚያስፈለገው ምንድን ነው? _____

ሰ. እኔ የሚለው ተራኪ በአንድ የባህል ምግብ ቤት ገብቶ ያየውን የሥዕል ዓይነት ዘርዝር?

_____

ሸ. ተራኪው የምግብ ቤቱን ባለቤት ስለምግብ ቤታችን ባለው ሥዕል አስተያየታቸውን እንዲሰጡት ጠይቆ የተሰጠው ቁርጠኛ ምላሽ ምንድን ነው? _____

ቀ. እኔ የሚለው ተራኪ ስለ ሥዕል ሙ ለውን ከፍተኛ አድናቆቱን የገለጸባቸው አንቀጾች ምሳሌ እየሰጠህ ዘርዝር። _____

በ. የምንባቡን መልእክት በአጭሩ ግለጽ። _____

6. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት አድርገው የወጡ ናቸው ጥያቄዎቹን ከመመለስህ በፊት ምንባቡን በሉሰስ የአነባብ ስልት ረጋ ብለህ በማንበብ በጥያቄዎቹ ላይ በቡድንህ አማካኝነት ከተወያየህ በኋላ እውነት ወይም ሀሰት በማለት በጽሑፍ መልስ መልሰህ እውነት ከሆነ እውነትነቱን ያገኘህበትን ምንጭ ገጽ አንቀጽ ወይም መስመር ጥቀስ መልስህ ውሸት ከሆነ ምክንያትህን በአጭሩ ግለጽ።

ሀ. በታሪኩ ውስጥ እኔ እያለ የሚተርከው ተራኪ ለስዕል ያለው ፍላጐት ከፍተኛ ነው

_____

ለ. እኔ የሚለው ተራኪ ስዕል ከመሳል ይልቅ ሥዕልን መተቸት ይወዳል። _____

ሐ. በምንባቡ እንደተገለጸው የሥዕልን ሙያ የተዋረደ መሆኑን ለመግለጽ ለዓብነት የቀረቡት የቲያትር ቤት ሥዕሎች ናቸው። _____

መ. በምንባቡ ውስጥ እንደተገለጸው የሥዕልን ሙያ ከሁሉም በፊላይ ሊያስደንቀው የሚችል ረቂቅ ነገሮችን ለመግለጽ በመቻሉ ነው። _____

ሠ. በምንባቡ መሠረት ሁሉም የቡና ቤት ሥዕሎች በግድየለሽነት የተሳሉ በመሆናቸው ከተራነት ያስመድባቸዋል። _____

7. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የምርጫ ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ የወጡ ናቸው። ለጥያቄዎች ምላሽ ከመስጠትህ በፊት ምንባቡን ረጋ ብለህ በግል በፀጥታ አንብበው በአነባብኽው መሠረት በቡድንህ አማካይነት ከተወያየህ በኋላ ለጥያቄው ተስማሚ የሚሆነውን መልስ የያዘውን እየመረጥህ ክበብ።

ሀ. በምንባቡ ውስጥ «እኔ» በማለት ስለሚተርከው ተራኪ እውነት የሆነው የትኛው ነው?

1. ተራኪው የአንድን ሥዕል ውበት መገንዘብና መተቸት ይችላል
2. ተራኪው ሰዓሊ ለመሆን ያለው ፍላጐት በጣም ዝቅተኛ ነው።
3. ተራኪው ለስዕል ያለው አድናቆት ዝቅተኛ ነው።
4. ተራኪው ከፍተኛ የሆነ የሥዕል ችሎታ አለው።

ለ. ደራሲው የሥዕልን ሙያ ሥዕልን በማያውቁ ሰዎች የተዋረደች መሆኗን ለማስረዳት ሲሉ ለምሳሌነት የጠቀሰው_____ ነው።

1. የቲያትር ቤት ሥዕሎች
2. የጠጅ ቤት ሥዕሎች
3. የቡና ቤት ሥዕሎች
4. የመኖሪያ ቤት ሥዕሎች

ሐ. ደራሲው ተራ በጣም ተራ የሚላቸው የሥዕል ዓይነቶች _____ናቸው

1. የተለያየ ቀለማት የሌላቸውን ሥዕሎች
2. የምጣኔ ጉድለት የሚታይባቸውን ሥዕሎች
3. የሥዕል ጥበብን ያልተከተሉ ስዕሎች
4. 2 ና 3 መስል ናቸው::

መ. ለጉደጉደ ዓይንና ለተጨማደደ ፊት መንስዔው_____ነው::

1. ጉስቁልና 2. ርሃብ 3. እርጅና 4. ሁሉም

ሠ. ቅርበትና ርቀት፣ ጥላና ብርሃን፣ ከፍተና ዝቅታ /አንቀጽ ሶስት/ የሚሉት ጥንድ ቃላት ተምሳሌነታቸው_____ ነው::

1. ለረቂቅ ነገሮች 2. ተሰጥኦና ችሎታ
3. ስሜትና ብዕር ብቻውን 4. ተሰጥኦ ብቻ

ረ. በምንባቡ መሠረት ሰዓሊ ለመሆን የሚያስፈለጉ ሁለት መሠረታዊ ነገሮች ____ ና _____ ናቸው::

1. ብዕርና ወረቀት 2. ተሰጥኦና ችሎታ
3. ስሜትና ብዕር ብቻውን 4. ተሰጥኦ ብቻ

ሰ. በምንባቡ ውስጥ እኔ የሚለው ተራኪ ስለ ቡና ቤት ስዕሎች አስተያየት ለመስጠት የተነሳሳበት ምክንያት_____ ነው::

1. ሠዓሊ በመሆኑ
2. ሠዓሊ ከመሆኑም በላይ በተሳሉት ስዕሎች ላይ አስተያየት ለመስጠት ችሎታ ያለው በመሆኑ
3. ችሎታው ከሰዓሊነት ይልቅ ወደ ተቺነት ስለሚያደላ
4. ለስዕል ስሜት በሌላቸው ሰዎች

ቀ. «በልጅነትህ ጥሩ የሥዕል አስተማሪዎች ስላላጋጠሙ ይሆናል የሚለው አባባል _____ ነው::

1. የደራሲው 2. የተራኪው
3. የተራኪ ወዳጅ 4. የተራኪው ወንድም

በ. እንደተራኪው አባባል የስዕልን ሙያ ከሁሉም በላይ ተደናቂ የሚያደርገው ከሚከተሉት ውስጥ_____የመሳሰሉትን ለይቶ በማመለከቱ ነው::

1. ከፍታን፣ ዝቅታን፣ ብርሃንንና ጨለማን
2. አድማስን፣ ሰማይን፣ ጭጋግንና ዝናብን
3. ደስታን፣ ጸጸትን፣ ፍቅርንና ናፍቆትን
4. ሁሉም መልስ ነው

4. የቡና ቤት ሥዕሎች የሚለውን ምንባብ ረጋ ብለህ በሉሳስ የአነባብ ስልት ካነበብህ በኋላ በቡድንህ አማካይነት በመወያየት በ«ሀ» ሥር ለተዘረዘሩት የአንቀጾች ተናጠላዊ መልእክት ለየትኛው የአንቀጽ ዓይነት እንደሆነ ከ«ለ» ስር ከተዘረዘሩት አንቀጾች እየመረጥህ አዛምድ

«ሀ«	«ለ»
____ 1. ችሎታዬ በተሳሉ ስዕሎች አስተያየት መስጠት እንጂ ሥዕል መሣል አይደለም።	ሀ. አንቀጽ አንድ
____ 2. የስዕልን ሙያ በማያውቁ ሰዎች የተከበረው የስዕል ሙያ ተዋርዷል።	ለ. አንቀጽ ሁለት
____ 3. ምንም እንኳ የሥዕል ፍላጎት ቢኖረኝም በወቅቱ ደህና የሥዕል አስተማሪ ባለማግኘቴ ምኞቴ ሳይሳካልኝ ቀርቷል።	ሐ. አንቀጽ ሶስት
____ 4. የተፈጥሮ ረቂቅ ምስጢር የሚገለጸው በስዕል አማካኝነት ነው።	መ. አንቀጽ አራት
____ 5. የተፈጥሮን ውስብስብ ባሕሪ በስዕል አማካኚነት ለመረዳት መሞከር በጣም ያስደስታል።	ሠ. አንቀጽ አምስት ረ. አንቀጽ ስድስት

7. ደራሲው መልእክቱን ለማስተላለፍ በምንባቡ ውስጥ የተጠቀመባቸው የተለዩ አገላለጾች በሀ ስር ተዘርዝረዋል። ደራሲው የተጠቀመባቸውን የተለያዩ አገላለጾች በምን ዓይነት አጠቃቀሞች እንደሆነ በለ ሥር ተዘርዝረዋል በቡድንህ አማካይነት ከተወያየህ በኋላ በሀ ሥር ላሉት ዓረፍተ ነገሮች የሚስማማቸውን አገላለጽ ከለ ሥር እየመረጥህ አዛምድ።

ሀ	ለ
1. የምግብ ቤቱን ባለቤት ማነው ይህን ስዕል የሣለልዎት? ብዬ ጠየቅኋቸው።	ሀ. መረጃ ለመሰብሰብ መጠየቅ
2. «አንድ የተባረከ ልጅ ነው እንዲሁ እንዳንተ ሊመገብ መጥቶ» አሉኝ።	ለ. አለመስማማት
3. ለመሆኑ ምን ያህል አስከፈለዎት?	ሐ. ሃሳብ ለማግኘት መጠየቅ
4. «ዛሬ አታገኘው ምን ያደርግልሃል? ክፍለ ሀገር ከሄደ ዘመን የለውም»	መ. ተጨማሪ ማብራሪያ
5. «እንዲያው ለማወቅ ብዬ ነበር» አልኳቸው	ሠ. መስማማትን መጠየቅ
6. «ግን ሥዕሉ ጥሩ ነው ወይ እርስዎ ሲያስቡት»	ረ. ትክክለኛ ምንጩን ለማግኘት መጠየቅ
7. «ሥለ ሥዕሉ ያለዎት አስተያየት»	ሰ. ለተጠየቁት ሃሳብን ግለጽ
8. «አንድ አስተያየት የለም የበሉትን በልተው ውልቅ»	ሸ. ማስተባበያ ሃሳብ መሰንዘር

ድህረ ምንባብ

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች የቀረበውን ምንባብ መነሻ በማድረግና የራስህን ልምድ ወይም እውቀት በመጨመር በጥልቀት ከተወያየህ በኋላ የደረስህበትን ማጠቃለያ እንደ አጠያየቃቸው መልስ።

1. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዓረፍተ ነገሮች በጥንቃቄ ካነበብህ በኋላ ትክክለኛውን ሥርዓተ ነጥብና ምልክት ተጠቅመህ እንደገና አስተካክለህ ጻፍ።
   ሀ. «ማነው ይህን ስዕል የሣለልዎት»? አለ ጠያቂው
   ለ. «ጠያቂው ይህን ሥዕል የሣለልዎት ማን ነው»? አለ
   ሐ. ጠያቂው «ይህን ሥዕል የሣለልዎት ማን ነው»? አለ
   መ. ይህል የሣለልዎት ማነው? ብዬ ጠየቅኳቸው
2. ሥዕል ይነበባል ይህን ሃሳብ በመደገፍ ወይም በመቃወም ከተወያየህ በኋላ የደረስህበትን ማጠቃለያ በአንድ አንቀጽ ጽፈህ ለክፍል ጓደኞችህ አንብብላቸው።
3. ጥላና ብርሃን ከፍታና ዝቅታ ሰማይ አድማስ ጭጋግ የሚሉት ከህዘን ደስታ ጸጸት ናፍቶች ከሚሉት ጋር ያላቸው አንድነትና ልዩነት ከተወያየህ በንግግር ግለጽ
4. በአንተ አካባቢ ባሉት ቡና ቤቶች የተሳሉት ሥዕሎች ከቆሙለት ነገር ያላቸው አካላዊ መመሳሰል እንዴት ነው? የአንተን አካባቢ የቡና ቤት ሥል ከምንባቡ በቀረበው ሃሳብ ጋር ስታነጻጽረው ያለውን እውነታ ከተወያየህ በኋላ በኋላ አብራራ
5. በምንባቡ ውስጥ እኔ እለ ስለ ሥዕል የሚተርከው ተራኪ ሥዕል ከመሳል ይልቅ መተቸት ደስ ይለዋል ለምን? አንተስ ?

ምንባብ አንድ

ውሃን አፍልቶ መጠቀም

1. ውሃን አፍልቶ መጠቀም በውሃ ውስጥ የሚገኙ ማናቸውም በሽታ ለማጥፋት ፍቱን ዘዴ ነው። የሚጣራው ውሃ በመልኩ ንፁህ ወይም ድፍርስ ወይም በከፊለ የተበከለ ወይም በጣም የተከበለ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ ሁሉም ዓይነት ውሃ ለማፍላት የሚገኘው ውጤት ተመሳሳይ ነው።

እንዲጣራ የሚፈለገው ውሃ በማንቆርቆሪያ በብረት ድስት ወይም በገንቦ ማፍላት ይቻላል።

5. ውሃን ማፍላት ማለት ለጥቂት ጊዜ እሳት ላይ ጥዶ ከዚያም አቀዝቅዞ መጠቀም ማለት አይደለም። ለጤና ጠንቅ የሆኑ ተዋስያንን ለማጥፋት መጀመሪያ ውሃው ለጥቂት ደቂቃዎች የፈላል፣ ከዚያም እንዲቀዘቅዝ ይደረግና እንደገና ከ15-20 ደቂቃዎች እየተፍለቀለቀ እንዲፈላ ከተደረገ በኋላ አቀዝቅዞ መጠቀም ነው። ሌላው ሊተኮርበት የሚገባውጉዳይ ውሃው የተፈላበት እቃ ለሌላ አገልግሎት እንዳይውል ማድረግ ነው። ውሃው በዚያው በተፈላበት እቃ ውስጥ እንዲቀዘቅዝና በደንብ ተከድኖ

10. እንዲቆይ ቢደረግ የውሃው ንጽህና እንደተጠበቀ ይቆያል። ይህን ማድረግ ካለተቻለ በፊላ ውሃ ተቀቅሎ በታጠበ ዕቃ ውስጥ ውሃው ከተገለበጠ በኋላ በሚገባ ተከድኖ አገልግሎት ላይ መዋል ይኖርበታል ውሃን ማፍላት በውሃ ውስጥ የሚሟሙ ጋዞችን በተለይም የተቃጠለን አየር ከውሃ ውስጥ ስለሚያወጣው የተፈላ ውሃ ጣዕሙ ይለወጣል። የውሃውን ጣዕም ለማሻሻል ሲባል ከእቃ ወደ እቃ የማገላበጡ

15. ተግባር ውሃውን እንደገና እንዲበከል የሚያደርገው ስለሆነ ከዚህ ዓይነቱ ድርጊት አቆጠብ ያስፈልጋል። የተከበለ ውሃን ከመጠጣት ጣዕም የሌለው ንጹህ ውሃ መጠጣቱ ይመረጣል።

ተፈለቶ ከቀዘቀዘ የውሃ እቃ ውስጥ ውሃው በሚቀዳበት ጊዜ በጣሳ እየተጠለቀ መሆን የለበትም። የዚህ ዓይነቱ አቀዳድ በተበከለ ጣሳ ምክንያት ውሃው ወዲያውኑ ስለሚከበል ያ

20. የተደከመበት ተግባር ሁሉ ከንቱ ይሆናል።

የውሃው እቃ ውሃን ለማንቆርቆር የሚረዳ ሊዘጋና ሊከፈት የሚችል ጡት ወይም ቀዳዳ ያስፈልገዋል። ከሌለው ግን ውሃውን መቅዳት ሲፈለግ እቃውን ካስጐነበሱ በኋላ በጥንቃቄ ማንቆርቆር ያስፈልጋል።

በአጠቃላይ ውሃን በማፍላትና ንጽህናውን ጠብቆ በመጠቀም ውሃ ወለድ በሽታዎችን

25. መከላከል ይቻላል። ውሃን ከማፍላት ዘዴ ሌላ ኬሚካሎችን በመጠቀም ውሃውን ከጤና ጠንቅ ተህዋስያን ነፃ ማድረግ ይቻላል።

ምንጭ፣ ውሃና ልማት፣ መስከረም 1990 ዓ.ም. ከቁጥር ሁለት ከገጽ 11-15 የተወሰደ።

ሻባሪ ሁለ

ለጥብቅ ቡድኑ (Control Group) የተዘጋጀ የማስተማሪያ መሣሪያ

1. ውሃን አፍልቶ መጠቀም የሚለው ምንባብ ሲነበብልህ ባዳመጥሕው መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በተሟላ ዓረፍተ ነገር በቃልህ መልስ።
   - ሀ. ውሃን አፍልቶ መጠቀሙ ጥቅሙ ምንድን ነው?
   - ለ. ውሃን ማፍላት ማለት ምን ማለት ነው?
   - ሐ. የሚጣራው ውሃ መልኩ ንፁህ የሆነውና ያልሆነው ከተፈላ በኋላ በመካከላቸው ልዩነት አለ? ከሌለስ ለምን?
   - መ. ውሃ ከተፈላ በኋላ እስኪቀዘቅዝ ድረስ ንፅሕናው እንደተጠበቀ ለማቆየት የምንወስደው እርምጃ ምንድን ነው?
   - ሠ. ተፈልቶ የዘቀዘ ውሃ ጣሙ ለምን ይቀንሣል?
   - ረ. የቀዘቀዘው ውሃ ለመጠጣት ብንፈልግ እንዴት መጠቀም እንዳለብን ግለጽ
   - ሰ. የምንጭ ውሃን ወለድ በሽታዎች ለመከላከል ከማፍላት በተጨማሪ የተጠቀሰው ሌላው ዘዴ ምንድን ነው?
   - ሸ. ውሃን ለማጣራት ሲባል ውሃውን ለማፍላት የምንገለገልባቸውን የቁሣቁስ ዓይነቶችን ዘርዝር
   - ቀ. ውሃን በሚገባ ለማፍላት የሚወስደው ጊዜ ስንት ነው?
   - በ. የምንባቡን አጠቃላይ መልዕክት አጠቃሎ የያዘው ዓረፈተ ነገር የሚገኘው በስንተኛው አንቀጽ ነው? ዓረፍተነገሩን ጥቀስ።

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በተነበበልህ ምንባብ መሠረት እውነት ወይም ውሸት በማለት በቃል መልስ
   - ሀ. ከምንጭ የተቀዳ ውሃ መልኩ ንፁህ ከሆነ ማፍላቱ ትርፉ ድካም ነው።
   - ለ. ከምንጭ የተቀዳ ውሃ መልኩ ንፁህ ይሁንም አይሁንም ከተፈላ በኋላ የሚያሳየው ውጤት ተመሣሣይ ነው።
   - ሐ. ከምንጭ የተቀዳን ውሃ አንድ ጊዜ በማፍላት ብቻ ንፁህ ማድረግ ይቻላል።
   - መ. ለመጠጥ የምንጠቀምበትን ውሃ ካፈላን በኋላ ከአንድ እቃ ወደ ሌላው እቃ የምናገላብጠው ከሆነ ውሃው ከመበከል አይድንም።
   - ሠ. የተፈላ ውሃ ጣዕሙ እንዲቀንስ ምክንያት የሚሆነው ከመጠን በላይ እንዲፈላ ሲደረግ ነው።
   - ረ. ውሃን አፍልተን የምንጠቀመው ለጣዕሙና ለውሃ ወለድ በሽታዎች ለመከላከል ሲባል ነው።
   - ሰ. ከምንባቡ የምንረዳው ነገር ቢኖር ውሃን አፍልተን እንዴት ማቀዝቀዝ እንደምንችል ብቻ ነው።
   - ሸ. እንደ ደራሲው አባባል ከሆነ ተፈልቶ የቀዘቀዘን ውሃ በጣሳ ጠልቆ ለመጠቀም መሞከር ፈጽሞ የተከለከለ ነው።
   - ቀ. ተፈልቶ ጣዕም የሌለው ውሃ ከመጠጣት ከምንጩ የተቀዳው ውሃ መልኩ ንፁህ ከሆነ እንዳለ መጠቀሙ የተሻለ ነው።

3. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ሆሄ እየመረጥህ ክበብ::

ሀ. ውሃን ማፍላት ማለት ምን ማለት ነው?

1. ከ15-20 ደቂቃዎች ብቻ አፍልቶ መጠቀም
2. ውሃውን ለጥቂት ጊዜ ብቻ አፍልቶ ከቀዘቀዘ በኋላ በድጋሚ ከ15-20 ደቂቃ ድረስ አፍልቶ ማቀዝቀዝ
3. ለጥቂት ጊዜ ብቻ ከእሳት ላይ ጥዶ ማፍላትና ማቀዝቀዝ
4. አንድ ጊዜ ብቻ ጥዶ እስኪፈለቀለቅ ድረስ ማፍላት

ለ. ውሃን አፍልቶ መጠቀም ዓላማው ምንድን ነው?

1. ውሃ ወለድ ተህዋስያን ለማጥፋት
2. የውሃውን መልክ ንፁህ ለማድረግ
3. የውሃውን ጣዕም ለመጨመር
4. የውሃውን ጣዕም ለመጨመርና ተህዋስያንን ለማጥፋት

ሐ. ውሃ ከተፈላ በኋላ ጣዕሙ የሚቀንስበት ምክንያት _____ ነው::

1. ንፁህ አየር ከውሃ ውስጥ ወጥቶ ስለሚያልቅ
2. የተለያዩ ጋዞች ወደ ውሃው ውስጥ ስለሚገቡ
3. የተቃጠለው ዓየር ከውሃው ውስጥ ስለሚወጣ
4. የተቃለው ዓየር በውሃ ውስጥ ስለሚበዛ

መ. እንደደራሲው አባባል ውሃ ከተፈላ በኋላ ከእቃ ወደ እቃ የሚገላበጥ ከሆነ ውሃው _____

1. ጣዕሙ ይቀንሣል
2. ጣዕሙ ይበልጥ ይጨምራል
3. እንደገና ይበከላል
4. መልኩ የበለጠ ንፁህ ይሆናል

ሠ. እንደደራሲው አባባል ውሃ ከተፈላ በኋላ እስከ መጨረሻው ንፅህናውን ጠብቆ እንዲቆይ ለማድረግ የተፈላውን ውሃ _____ ነው::

1. በዚያው በተፈላበት እቃ እንዲቀዘቅዝ ማድረግ
2. በተፈላ ውሃ በተቀቀለ ሌላ እቃ ውስጥ ገልብጦ እንዲቀዘቅዝ ማድረግ
3. ከእቃ ወደ እቃ በማገላበጥ እንዲቀዘቅዝ ማድረግ
4. በተፈላበት እቃ እንዳይቀዘቅዝ ማድረግ

ረ. ደራሲው ውሃን ከማፍላት ሌላ ይተኰርበት የሚለው ___ የሚለውን ነው

1. ውሃው የተፈላበት እቃ ለሌላ አገልግሎት እንዳይውል ማድረግ
2. ውሃው በተፈላበት እቃ እንዳይቀዘቅዝ ማድረግ
3. በተፈላ ውሃ ላይ ሌላ ዓይነት ኬሚካል እንዲጨመር ማድረግ
4. ውሃው በተፈላበት እቃ ብቻ እንዲቀዘቅዝ ማድረግ

ሰ. በምንባቡ ውስጥ አምስተኛው አንቀጽ (ሁለተኛ መስመር) የዚኅ ዓይነቱ የሚለው ሐረግ የቆመው ____ ለሚለው ነው::

1. ተፈልቶ የቀዘቀዘን ውሃ በጣሳ ጠልቆ መጠቀም
2. ጣዕሙ የሌለው ውሃ ከመጠጣት የተበከለ ውሃ መጠጣት
3. የተበከለን ውሃ ከመጠጣት ተፈልቶ የቀዘቀዘን ጣዕም የሌለው ውሃ መጠጣት
4. ተፈልቶ የቀዘቀዘን ውሃ በጣሳ ጠልቆ መጠጣት ተገቢ አይደለም

ሰ. ተፈልቶ የቀዘቀዘን ውሃ ለመጠቀም ስንፈልግ ውሃውን ለማንቆርቆር የሚያገለግል ጡት መሰል ቀዳዳ ወይም ሊከፈትና ሊዘጋ የሚችል ቀዳዳ ከሌለው አማራጩ መንገድ ___ ነው::

1. ውሃውን በጣሳ ጠልቆ መጠቀም
2. ውሃውን የተፈላበትን እቃ አስጐንብሶ በጣሳ ቀድቶ መጠቀም
3. በታጠበ ጣሳ ጠልቆ መጠቀም
4. 2 ና 3 መልስ ናቸው

ቀ. ደራሲው በአምስተኛው አንቀጽ (መስመር 24) «ያ» የሚለውን ቃል የተጠቀመበት ____ ለማመልከት ነው::

1. ውሃውን ለማፍላት የባከነው ጊዜ
2. ውሃውን ለማፍላት የባከነው ጋዝ ወይም ማገዶ
3. ውሃውን ለማፍላት የባከነውን ጉልበት
4. ሁሉም መልስ ነው

ሰ. ደራሲው የውሃ ወለድ በሽታን ለማጥፋት ውሃን ከማፍላት ሌላ ተጨማሪ ዘዴ አለ የሚለው ____ ነው::

1. ውሃው መልኩ ንፁህ ከሆነ እንዳለ መጠቀም
2. ማንኛውንም የኬሚካል ዓይነት ከውሃው ውስጥ በመጨመር መጠቀም
3. ለውሃ ወለድ በሽታ ማጥፊያ የሚሆን ኬሚካል በውሃው ውስጥ በመጨመር መጠቀም
4. 1 ና 3 መልስ ናቸው

4. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቃላት ከአገባባቸው አንፃር ተስማሚ የሆነውን ቦታ እየፈለገህ በአንቀጽ ውስጥ በተሰጠው ባዶ ቦታ እያስገባህ ፃፍ

ጣዕም	ተቀቅሎ	ገንቦ
ፍቱን	ጣሳ	ተከበለ
ውሃ ወለድ	ተከድኖ	ጡት

ውሃን አፍልቶ መጠጣት ከ_____ በሽታ ለመከላከል _____ ዘዴ ነው:: ከምንጭ ወይም ከኩሬ የተቀዳ ውሃ በውሃ ወለድ በሽታወች የ_____ ሊሆን ስለሚችል በ_____ እሳት ላይ ጥዶ እስኪፍለቀለቅ ድረስ ማፍላት ያስፈልጋል:: ውሃው ከተፈላ በኋላ ከአንድ እቃ ወደ ሌላ እቃ ማገላበጥ እንደገና ውሃውን የሚበክለው ስለሆነ በዚያው ውሃው የተፈላበትን እቃ _____ ውሃውን ማቀዝቀዝ ነው:: የተፈላ ውሃ _____ ሊቀንስ ይችላል:: ነገር ግን የተፈላውን ውሃ ጣዕም ለመጨመር ካስፈለገ ቀደም ሲል በፈላ ውሃ _____ የተዘጋጀ እቃ ካለ ውሃው ከተፈላበት እቃ ተቀቅሎ በተዘጋጀው እቃ ማገላበጥ ይቻላል:: ተፈልቶ የቀዘቀዘን ውሃ ለመጠቀም ስንፈልግ በ_____ ጠልቀን መጠቀም የለብንም:: የግድ ውሃውን ለማንቆርቆር የሚረዳ _____ ያለው እቃ ያስፈልገናል::

5. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አያያዥ ቃላት እና ሃረጎች በዓረፍተ ነገር ውስጥ በተስማሚ ቦታዎች ውስጥ አስገባ

ይሁን እንጂ መጀመሪያ እንደገና
ስለሆነ ነገር ግን በተለይ
ከዚያም

ሀ. ከምንጭ ወይም ከኩሬ የተቀዳን ውሃ መልኩ ንፁህ ወይም ድፍርስ ሊሆን ይችላል _____ በውሃ ወለድ አምጪ ተህዋስያን ተሸካሚነታቸው ግን የተለያዩ አይደሉም።

ለ. ከምንጭ መይም ከኩሬ የተቀዳ ውሃ ከመጠጣቱ በፊት _____ ለጥቂት ደቂቃዎች በብረት ድስት ማፍላት _____ እንዲቀዘቅዝ ይደረጋል።

ሐ. ውሃን ማፍላት በውሃ ውስጥ ያሉትን ጋዞች ያሚሚል _____ የተቃጠለ አየር ከውሃ ውስጥ ስለሚወጣ የውሃውን ጣዕም ሊቀንስ ይችላል።

መ. ውሃን ማፍላት ውሃ ወለድ በሽታዎችን ያጠፋል _____ ውሃን ማፍላት የውሃውን ጣዕም ይቀንሰዋል።

ሠ. ያልተፈላ ውሃ ከመጠጣት ጣዕም የሌለው የተፈላን ውሃ መጠጣት ተመራጪነት ያለው _____ በተቻለን መጠን ሁላችንም ከኩሬ ወይም ከምንጭ የተቀዳን ውሃ አፍልተን መጠቀም አለብን።

ረ. ውሃን ለጥቂት ደቂቃዎች አፍልቶ ከቀዘቀዘ በኋላ _____ ከ15 - 20 ደቂቃ አስኪፍለቀለቅ ድረስ ማፍላት ያስፈልጋል።

6. ከዚህ በታች የተሰጡትን ጥያቄዎች እንደየአጠያየቃቸው መልስ

ሀ. ውሃን አፍልተን እንዴት መጠቀም እንዳለብን በአጭሩ በንግግር ግለጽ።

ለ. በመጥለቅና በመቅዳት መካከል ያለውን ልዩነት በቃል አብራራ።

ሐ. የተፈላ ውሃ ጣዕሙ እንዲት ሊቀንስ እንደሚችል በንግግር ግለጽ።

መ. የውሃን አፈላልና አጠቃቀም ሂደት በዕፅ መዋቅር በጽሑፍ አሣይ።

ሠ. ውሃን አፍልቶ መጠጣት ያለውን ጥቅም በቃል ግለጽ።

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ከተሟላ ዓረፍተ ነገር በቃልህ መልስ

ሀ. ማህበር ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. ማህበር በኢትዮጵያ የተጀመረው መቼ ነው?

ሐ. ጽዋ፣ ሰንበቴ፣ ዝክረ ቅዱሳን የመሳሰሉት የሃይማኖር ማህበራት መሆናቸውን የምንረዳው በምን ነው?

መ. የየመንደሩ ነዋሪ የሐይማኖትን የጸታ ልዩነት ሳያደርግ ለመረዳዳት ብሎ የሚያቋቁማቸውን የማኅበራት ዓይነቶች ጥቀስ

ሠ. የዘመናዊ ማህበራት ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲስፋፉ ያስቻላቸው ምክንያት ምንድን ነው?

ረ. ፋስት ኢጣሊያ አገራችንን በ1927 ዓመተ ምህረት በወረረችበት ወቅት የተለያዩ የፖለቲካ ማህበራት ተመስርተዋል። እነዚህን ማህበራት ስማቸውን ጥቀስ ማህበራቱ ያደረጉት አስተዋጽኦ ምንድን ነው?

ሰ. እንደ ቀይ መስቀል፣ የዓለም አቀፍ የሴቶች ክበብ ማህበራት ምሣሌነታቸው ለየትኛው የማህበር ዓይነት ነወ?

ሸ. የሃይማኖት ማህበር ጥቅሙ ምንድን ነው?

ቀ. በመንፈሣዊ እና በአለታዊ ኑሮ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

በ. የምንባቡ መልእክት ምንድን ነው?

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት እውነት ወይም ውሸት በማለት በቃልህ መልስ

ሀ. የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖቶች ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ ወዲህ የማኅበር ትምህርት እየተሰጠና ግዴታም እየተገባበት መጥቷል።

ለ. የጽዋ፣ የሰንበቴና የጽጌ የኳናት ማህበራት እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉት ስያሜዎችና ተቋሞች ከሃይማኖት ጋር ወይም የክርስትና ሃይማኖት ከተሰበከ በኋላ የተመሰረቱ መሆናቸውን ከስያሜያቸውና ከተግባራቸው እንረዳለን።

ሐ. ማህበር ከሃይማኖታ ገጽታው ሌላም ማህበራዊ ወይም ሕዝባዊ አቋም አለው ለምሣሌ በወበራ (ደጦ) በሰርግ በሃዘን ሲረዳዳና ሲደጋገፍ እንደቆየ ከታሪኩ መረዳት ይቻላል።

መ. የምዕራባዊያን ሥልጣኔ ወደ ኢትዮጵያ ከገባ ወዲህ በማህበር አማካይነት ወይም ዋልታነት ልዩ ልዩ ሥራዎችን ማቋቋም ተስፋፍቷል

ሠ. ማህበር ከጥንታዊነት ወደ ዘመናዊነት ሲሸጋገር አያሌ ዘመናትን አስቆጥሯል። ጥንታዊ የሚለው ቃል የሚጠቀመው ሃይማኖታዊ ማህበርን ሲሆን ዘመናዊ የሚለው ቃል ደግሞ የሚጠቀመን አለታዊና ፖለቲካዊ ማህበርን ነው።

3. ከዚህ በታች ለተሰጡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ሆሄ እየመረጥህ ከቁጥሩ ፊት ለፊት በተሰጠው ባዶ ቦታ ፊደሉን ብቻ ጻፍ።

____ ሀ. የየመንደሩ ነዋሪ የሃይማኖትና የጸታ ልዩነት ሳያደርግ የሚያቋቁመው የማህበር ዓይነት _____ ነው።

1. አለታዊ (መረዳጃ) ማህበር
2. ሃይማኖታዊ ማህበር
3. ፖለቲካዊ ማህበር
4. የሙያ ማህበር

___ ለ. እንደደራሲው አገላለጽ በኢትዮጵያ ውስጥ ሃይማኖታዊ ማህበር ወደ አለታዊ ማህበር የተሸጋገረበት ምንያት _____ ነው።

1. የአውሮፖ ስልጣኔ ወደ ኢትዮጵያ መግባት
2. የአሜሪካ ስልጣኔ ወደ ኢትዮጵያ መግባት
3. የምሥራቅ አውሮፖ ሥልጣኔ ወደ ኢትዮጵያ መግባት
4. የምዕራብ አውሮፖ ሥልጣኔ ወደ ኢትዮጵያ መግባት

___ ሐ. ፋሽት ኢጣሊያ ሃገራችንን በወረረችበት ወቅት ስንቅና ትጥቅ በማዘጋጀት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉት የፖለቲካ ማህበራት _____ እና _____ ናቸው።

1. የሴቶች በጐ አድራጐትና የጥቁር አንበሳ ማህበራት
2. የህገር ፍቅርና የሴቶች በጐ አድራጐት ማህበራት
3. የጥንታዊ ጀግኖችና የሴቶች በጐ አድራጐት ማህበራት
4. የጥንታዊ ጀግኖችና የጥቁር አንበሳ ማህበራት

___ መ. የቀይ መስቀል የሞስኮ፣ ኦርቶዶክሳዊና የድኩማን ማህበራት በይዘታቸው _____ ናቸው።

1. አካባቢያዊ
2. ብሔራዊ
3. አህጉራዊ
4. ዓለም አቀፋዊ

___ ሠ. በሶስተኛው አንቀጽ የመጀመሪያው መስመር «በእነዚህ« የሚለው ሃረግ የሚወክለው _____ ነው።

1. የክርስትናና የእስልምናን ሃይማኖቶችን
2. የጽዋ፣ የሰንበቴ እና የጽጌ ማህበራትን
3. የደቦ፣ የሠርግ የህዘን ማህበራት
4. የህገር ፍቅር እና የሴቶች በጐ አድራጐት ማህበራት

___ ረ. የጽዋ፣ የሰንበቴ ዝክረ ቅዱሣን የመሳሰሉት ማህበራት ከክርስትና ሃይማኖት ከተሰበከ በኋላ መመሥረታቸውን የምረዳው በ _____ ነው።

1. በተግባራቸው
2. በስያሜያቸው
3. በአገልግሎታቸው
4. በታሪካዊ አመጣጣቸው

___ ሰ. በዚህ ዓለምና በወዲያኛው ዓለም የሚሉት ሃረጋት _____ ናቸው።

1. በይዘታቸው አንድ የሆኑ
2. በትርገማቸው አንድ የሆኑ
3. የተለያዩ ዓለማት የሆኑ
4. አንድ ዓይነት ዓለማት የሆኑ

___ ሸ. የማህበርን ቅደም ተከተላዊ አመጣጥ የሚገልጸው ከሚከተሉት ውስጥ _____ ነው።

1. ሃይማኖታዊ፣ አለታዊ፣ ፖለቲካዊ
2. አለታዊ፣ ፐለቲካዊ፣ ሃይማኖታዊ
3. ፖለቲካዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ አለታዊ

4. ሃይማኖታዊ ፖለቲካዊ አለታዊ

___ ቀ. ምንባቡ የተጻፈበት የአጻጻፍ ስልት _____ ነው።

1. በማወዳደር
2. በምክንያትና ውጤት ተዛምዶ
3. በትረካ
4. በብያኝ

4. ከዚህ በታች ከተሰጡት ቃላትና ሃረጋር በትርጉም ልዩ የሆነውን ቃል ወይም ሃረግ አስምርበት።

ሀ. ተባበረ፣ አንድ ሆነ፣ ተለያየ፣ ህብር ሆነ

ለ. የዚህ ዓለም፣ ወዲያኛው ዓለም፣ ሥጋዊ ዓለም

ሐ. ዓለማዊ፣ ሥጋዊ፣ መንፈሣዊ፣ አለታዊ

መ. ማስታወስ፣ መዝከር፣ ማመስገን

ሠ. ጨካኝ፣ ሩህሩህ፣ አረመኔ፣ ፋሽስት

5. ከዚህ በታች ለተሰጡት ቃላት ትርጉማቸውን የሚያሣዩ ዓረፍተ ነገር ጽፈህ አንብብ

ሀ. ፋሺስት ሐ. ወዲያኛው ዓለም ሠ. ህብር ሰ. መንፈሳዊ

ለ. ህብር መ. ወበራ ረ. ብሔራዊ

6. የሚከተሉትን ውስብስብ ዓረፈተ ነገሮች ከዚህ በታች በተዘረዘሩት አያያዥ ቃላትና ሃረጎች በማያያዝ ዓረፍተ ነገሮች አንድ የተሟላ ሃሣብ እንዲይዙ አድርገህ ፃፍ።

ለምሣሌ ያህል	በተጨማሪ
በተለይ	ከዚህ ቀጥሎ
ወዲህ	በመሆን
በኋላ	የመሳሰሉት
እንደዚሁ	ከዚህ ሌላም

ሀ. የገና በዓል በተለያዩ ክርስትና እመነት ተከታዮች ዘንድ ይከበራል _____ በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዬች ዘንድ ከፍተኛ የሆነው ቦታ ተሰጥቶታል።

ለ. የክርስትና እምነት ተከታዬች በአምላካቸው ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት ማህበር ይዘክራሉ _____ ሰንበቴ የማርያምና የልደታን መጥቀስ ይቻላል።

ሐ. በጠዋት ተነስቼ ፊቴን ታጠብሁ፤ ቁርስ በላሁ _____ የሚቀረኝ ነገር ቢኖር ቦርሳዬን ይገፍ ወደ ትምህርት ቤት መሄድ ነው።

መ. የፈተና ጊዜ እየተቃረበ ነው። ከየካቲት _____ ቤተሰብ ዘንድ መሄድ አልፈልግም።

ሠ. ፈተናው በጣም ከባድ ነው _____ ግልጽም አይደለም።

ረ. አበበ በትምህርቱ ደካማ _____ አሥራ አንደኛ ክፍል ለሁለት ጊዜ ያህል ደገመ።

7. ከዚህ በታች የተሰጡትን ጥያቄዎች እንዳጠያየቃቸው በጽሑፍ መልስ

ሀ. ማህበር የሚለውን ምንባብ ደጋግመህ ካነበብህ በኋላ ታሪኩን በአጭሩ ተናገር::

ለ. ማህበር ለሚለው ምንባብ አስተዋጽኦ ንደፍለት::

ሐ. የሃይማኖታዊ ማህበር ጥቅም ዘርዝር::

መ. የአለታዊ የማህበር ዓይነቶችና ጥቅማቸውን ግለጽ::

ሠ. የፖለቲካ የማህበር ዓይነቶችን ዘርዝር::

ረ. በዓለም አቀፍ ደረጃ ያሉትን የማህበር ዓይነቶች ዘርዝር::

ሰ. የማህበርን አመጣጥ ቅደም ተከተላዊ ሂደት ዘርዝር::

ምንባብ

የቡና ቤት ሥዕሎች

ሥዕል በጣም እወዳለሁ፤ ሠዓሊዎችንም አደንቃለሁ፤ ለሥዕል ከፍ ያለ ሶሜት አለኝ። ለምን ሠዓሊ አልሆንኩም ብዬ የጠየቅሁት አንድ ወዳጄ «በልጅነትህ ጥሩ የሥዕል አስተማሪዎች ስላላጋጠሙህ ይሆናል።» ብሎኝ ነበር እርግጥ የሥዕል አስተማሪዎቻችን ራሳቸው ሥዕል የማይችሉ ነበሩ።

ነበሩ። እፋቸው ላይ የመጣላቸውን ነገር ሳሉ ማለት ይቀናቸው ነበር ቡለይ ሰባተኛ ክፍል ሆኜ በመስኩት ያዩትን ነገር ለምሳሌ ባቡር ሲልፍ ካዩ ባቡር ሳሉ፤ አህያም ካለፌች አህያ ሳሉ የሚሉ አስተማሪ እንደነበሩ ትዝ ይለኛል።

ሥዕል ከማፍቀሬ የተነሳ ትንሽ ልክር ብል ድሮ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተለማመድኩትን ባለእራት እግር ጠረጴዛ ነው ከዚህ ይልቅ የአንድን ሥዕል ውበት መልእክት መገንዘብ በአጠቃላይ አቅሜ በሚፈቅድልኝ መሠረት መተቸት ደስ ይለኛል ከዚህም በመነሳት ስለአንዳንድ የቡና ቤት ሥዕሎች የመሳሰሉትን ነገሮች ለመናገር እሞክራለሁ

ሳስበው በአንዲት የእርሳስ ጨረት ብዙ መናገር ቅርበትን ርቀትንና ጥላና ብርሃንን ከፍታና ዝቅታን ማሳየት ሰማዩን፤ አድማሱን፤ ዝናቡን፤ ጭጋጉን፤ ማሳየት ከሁሉም በላይ ደግሞ እንደ ሃዘን፤ ደስታ፤ ጸጸትና ናፍቆት ያሉትን ረቂቅ ነገሮች ወረቀት ላይ መፍጠር ምንኛ ደስ ይላል።

በእድሜ ጉዳና ሲያዘግም ናሮ ወደ ሞት አፋፍ ብቅ የሚል ፀጋ የተሞላበት ሽምግልና፤ እንደ እምቡጥ አበባ የሚፈነዳ በተስፋና በምኞት አዝመራ ያሸተ ውጣት በረሃብ የተፈታን አካል ስቃይ ካጉደጉደው ዓይንና ከተጨማደደ ፊት ጋር ተባብሮ የሚያሳየው ብሶት የፍቅር ምትሃት የሃዘን ምሬት በአጠቃላይ ተፈጠሮ በሸራ ላይ የምትሸሞነሞንበት ትልቅ ጥበብ ቢኖር ሥዕል ነው።

ታዲያ ይህችው ተፈጥሮ ተሰጥኦና ችሎታ ባላቸው ሰዓሊያን የምትጌጠውንና በአውነታ የምታሸበርቀውን ያህል ሙያውን በወጉ በማያውቁ ሰዎችም ትዋረዳለች። ይህንን ለማረጋገጥ የቡና ቤት ሥዕሎችን መመልከቱ ይበቃል። የቡና ቤት ሥዕሎች ስንል የሥዕል ጥበብ የሌላቸውን ተራ በም ተራ የሆኑትን ማለቴ ነው። ለምሳሌ « ምን ልታዘዝ የምትል እግሯ ክርኗ ሥር ሊሆን ትንሽ የቀረው የመጠጥ ቤት ኮማሪት ወይም ታዲያስ ምን ይምጣ? ከሚል ጽሁፍ ሥር አንዱ አዳምጡኝ እንደሚል አስተማሪ አጹን የዘረጋ የምግብ ቤት አስተናጋጅ ግድግዳ ላይ ተስለው አይታችሁ አታውቁም? ቀንዱ ተጠምዝዞ ጭራው ጋር የደረሰ ዋልያ፤ ጽጌረዳ ሊቀጥፍ የተዘጋጀ እንደ ሰው ጥርስ ችምችም ያለ አንበሳ፤ ማይክሮፎን የሚመስል ቡና ማፍያ መኪና ዝርዝሩ ብዙ ነው።

በአንድ የባህል ምግብ ቤት ያየሁት ሌላ ሥዕል አለ በምን አወቅህ እንዳትሉኝ እንጂ የተሳሉት ባልና ሚስት ሳይሆኑ አይቀሩም። ጉን ለጉን ተቀምጠዋል። ምግብ ቀርቧል በመሶበወርቅ። አንድ ውሻ ተጋድሟል ዓይኖቹን ጨፍኗል። እንቅልፍ የወሰደው ይመስላል። ምግብ እየሸተተው የሚተኛ ውሻ ታውቃላችሁ? ከምጣኔ ስህተት የተነሳ ውሻው አልጠፋ ቦታ አመሶበወርቁ ሥር ነው። ጭራው እንደ ደህና ነገር ባልየው እግር ላይ አርፏል። ሴትየዋ እጆቿን ዘርግታለች ወደ ሰዎቹ «በሉ እስቲ እንደ ነገሩም ቢሆን።» ትላለች ማለት ነው፤ ነገር ግን እጅ አዘረጋግዋ መድረክ ላይ ወጥታ ንግግር የምታደርግ አስመስሏታል። ባልየው እጹን ይታጠባል፤ የሱ እንኳ ደህና ነው። የምታስታጥበው ልጅ ግን በቅጣት ላይ ነው ለች የሚመስላችሁ። ምክንያቱም ጉንበስ በማለት ፋንታ እንደ መንበርከክ ብላለች። የቁሱ ከሁሉ የተለየ ነው። ለመብላት የተዘጋጁ አይመስሉም፤ ብቻ ዝም ብለው መስቀልና ጭራቸውን ለምግብ ቤቱ ደምበኞች ያሳያሉ። የምግብ ቤቱን ባለቤት ማነው ይህን የሳለልዎት ብዬ ጠየቅኳቸው።

« አንድ የተባረከ ልጅ ነወ እንዲህ አንዳንተ ሊመገብ መጥቶ አሉኝ»

« ለመሆኑ ምን ያህል አስከፈለዎት? »

« ዛሬ አታገኘው ምን ያደርግልሃል? »

« እንዲያው ለማወቅ ብዬ ነበር» አልኳቸው።

« ክፍለ ሀገር ከሄደ ዘመን የለውም።»

« የለም ብዬሃለሁ። የለም አዲስ አበባ።»

« ግን ሥዕሉ ጥሩ ነው ወይም እርስዎ ሲያስቡት?»

« ያው ታየዋለህ ምን ትጠይቀኛለህ?»

« ሥለ ሥዕሉ ለዎትን አስተያየት።»

« አንድ አስተያየት የለም የበሉትን በልተው ውልቅ።»

1. የቡና ቤት ሥዕሎች የሚለውን ምንባብ ሲነበብልህ ባዳመጥኸው መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በተሟላ ዓረፍተ ነገር በቃልህ መልስ።

ሀ. በምንባቡ ውስጥ እኔ የሚለው ተራኪ ሠዓሊ ለመሆኑ ያልቻለበት ምክንያት ምንድን ነው?

ለ. በምንባቡ ውስጥ እኔ የሚለው ተራኪ ሠዓሊ ለመሆን ፍላጐት አለው በሚል ተገልጿል። ነገር ግን ተራኪው ምንም እንኳን ሠዓሊ የመሆን ፍላጐት ቢኖረውም ሊስል ቢፈልግ ምን የሚስል ይመስልሃል? ለምን?

ሐ. እኔ የሚለው ተራኪ በምንባቡ ውስጥ ከአገላለጹ እንደምንረዳው ችሎታው ምንድን ነው?

መ. እንደምንባቡ ከሆነ ተፈጥሮ በእውነት የምታሸበርቀውና የምታዜጠው መቸ ነው?

ሠ. የሥዕል ሙያ ተከበረውን ያህል እንደተዋረደ በደራሲው ተገልጿል። የሥዕል ሙያ የተዋረደ መሆኑን ለመግለጽ ደራሲው ለአብነት የጠቀሰው የሥዕል ዓይነት ምንድን ነው?

ረ. አንድ ሰው ሠዓሊ ለመሆን የሚያስፈልገው ምንድን ነው?

ሰ. እኔ የሚለው ተራኪ በአንድ የባሕል ምግብ ቤት ገብቶ ያየውን የሥዕል ዓይነት ዘርዝር

ሸ. ተራኪው የምግብ ቤቱን ባለቤት ምግብ ቤታቸው ስላለው ሥዕል አስተያየታቸውን እንዲሰጡት ጠይቆ የተሰጠው ቁርጠኛ ምላሽ ምንድን ነው?

ቀ. እኔ የሚለው ተራኪ ስለ ሥዕል ሙያ ያለውን ከፍተኛ አድናቆቱን የገለፀባቸውን አንቀጾች ምሣሌ እየሰጠህ ጥቀስ

በ. የምንባቡ መልዕክት ምንድን ነው?

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት እውነት ወይም ውሸት በማለት በቃልህ መልስ።

ሀ. በታሪኩ ውስጥ እኔ እያለ የሚተርከው ተራኪ ለስዕል ያለው ፍላጐት ከፍተኛ ነው።

ለ. እኔ የሚለው ተራኪ ሥዕል ከመሣል ይልቅ ሥዕልን መተቸት ይወዳል።

ሐ. በምንባቡ እንደተገለፀው የሥዕልን ሙያ የተዋረደ መሆኑን ለመግለጽ ለዓብነት የቀረቡት የቲ.ፖትር ቤት ሥዕሎች ናቸው።

መ. በምንባቡ ውስጥ እንደተገለፀው የሥዕልን ሙያ ከሁሉም በላይ ሊያስደንቀው የሚችለው ረቂቅ ነገሮችን ለመግለጽ መቻሉ ነው።

ሠ. የምንባቡ መሠረት ሁሉም የቡና ቤት ሥዕሎች በግድየለሽነት የተሳቡ በመሆናቸው ከተራነት ያስመድባቸዋል።

ረ. በምንባቡ መልዕክት የቡና ቤት ሥሎች ከማንኛውም ቦታ ከተለጠፈ ሥዕሎች ያሚለውን ለማስተላለፍ ነው።

3. በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ የያዙትን ፊደል እየመረጥህ ክበብ

ሀ. ለጉደጉደ ዓይንና ለተጨማደደ ፊት መንስኤው

1. ጉስቁልና 3. እርጅና
2. ረሀብ 4. ሁሉም

ለ. በምንባቡ መሠረት ሰዓሊ ለመሆን የሚያስፈልጉት ___ ና ___ ናቸው።

1. ብዕርና ወረቀት 3. ስሜትና ብዕር ብቻ
2. ተሰጥኦና ችሎታ 4. ተሰጥኦ ብቻ

ሐ. ደራሲው ተራ በጣም ተራ የሚላቸው የሥዕል ዓይነቶች _____ ናቸው።

1. የሥዕልን ጥበብ ያልተከተሉ ስዕሎችን
2. የምጣኔ ጉድለት የሚታይባቸውን ስዕሎች

3. የተለያየ ቀለማት የሌላቸውን ስዕሎች
4. 2 ና 3 መልስ ናቸው

መ. በምንባቡ እንደተጠቀሰው የሥዕልን ሙያ ከሁሉም በላይ ተደናቂ የሚያደርገው _____ ነው::

1. ደስታን፣ እርሃትን፣ ጸጸትንና ናፍቆት ማሳየት መቻሉ
2. የሰማዩን አድማስ፣ ጭጋጉንና ዝናቡን ማሳየት መቻሉ
3. ከፍተታን፣ ዝቅታን፣ ጨለማንና ብርሃንን ማሳየት መቻሉ
4. ሁሉም መልስ ነው

ሠ. በልጅነትህ ጥሩ የሥዕል አስተማሪዎች ስላላጋጠሙህ ይሆናል የሚለው አባባል _____ ነው::

1. የደራሲው
2. የተራኪው
3. የተራኪው ወዳጅ
4. የተራኪው ወንድም

ረ. እኔ የሚለው ተራኪ ስለ ቡና ቤት ሥዕሎች አስተያየት ለመስጠት ያነሳሳው _____ ነው::

1. ስዓሊ በመሆኑ
2. ችሎታው ከስዓሊነት ይልቅ ወደ ተቺነት ስለሚያደላ
3. ስዓሊም ሃያሲም በመሆኑ
4. መተቸት ለማንም ሰው ቀላል በመሆኑ

ሸ. ደራሲው የሥዕልን ሙያ የተዋረደች መሆኗን ለማሳየት ሲል የጠቀሰው ምሣሌ _____ ነው::

1. የቲያትር ቤት ሥዕሎች
2. የጠጅ ቤት ሥዕሎች
3. የቡና ቤት ሥዕሎች
4. የመኖሪያ ቤት ሥዕሎች

ቀ. በምንባቡ ውስጥ ስለተራኪው እውነት የሆነው _____ ነው::

1. ተራኪው ለስዕል ያለው አድናቆት ከፍተኛ ነው የሚለው
2. ተራኪው የአንድን ሥዕል ውበት መገንዘብና መተቸት ይችላል
3. ተራኪው ለሥዕል ያለው አድናቆት ዝቅተኛ ነው የሚለው
4. ተራኪው ከፍተኛ የሆነ የስዕል ችሎታ አለው የሚለው

በ. እንደደራሲው አባባል ተፈጥሮ ተሰጥኦና ችሎታ ባላቸው ሰዓሊያን የምታሸበርቀውንና የምታጊጠውን ያህል በአንፃሩ ደግሞ ተፈጥሮ _____ ትዋረዳለች::

1. የሥዕልን ሙያ በወጉ በሚያውቁም ሆነ በማያውቁ ሰዎች
2. የሥዕልን ሙያ በወጉ በሚያውቁ ሰዎች
3. የሥዕልን ሙያ በወጉ በማያውቁ ሰዎች
4. ለሥዕል ሙያ ስሜት በሌላቸው ሰዎች

4. በ«ሀ» ሥር ለተሰጡት ቃላትና ሃረጎች በምንባቡ ውስጥ ካላቸው አገባብ አንፃር የያዙትን ትርጉም ከ«ለ» ሥር ከቀረቡት አማራጮች በመምረጥ በ«ሀ» ሥር በተሰጡት ባዶ ቦታዎች ፊትለፊት ፊደሎቹን እየመረጥህ ጻፍ

«ሀ»		«ለ»	
___ 1.	አፋፍ	ሀ.	አስተያየት መስጠት
___2.	ጸጸት	ለ.	የጠጅ ቤት አስተናጋጅ
___3.	ትችት	ሐ.	ስስ ደመና
____4.	መሸሞንሞን	መ.	ያልደረሰ ወይም ያልበሰለ
____5.	ኮማሪ	ሠ.	ደረሰ
____6.	እምቡጥ	ረ.	ደምግባት
____7.	እሸት	ሰ.	በፈጸሙት ተግባር ማዘን
____8.	ውበት	ሸ.	ከፍተኛ ቦታ
____9.	ተስፋ	ቀ.	ይሆናል ብሎ በቀና መንፈስ መጠበቅ
___10.	ጭጋግ	በ.	መኪኪል መዋብ

5. ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ቃላት ዓረፍተ ነገር በመሥራት ትርጉማቸውን አሳይ

ሀ. ተሰጥኦ ሐ. መሰቦ ወርቅ ሠ. ደምበኛ ሰ. ተስፋ
ለ. ማሽብረቅ መ. ምጣኔ ረ. ጌጥ

6. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አያያዥ ቃላትና ሃረጎች ከምንባቡ የወጡ ናቸው። እነዚህን አያያዥ ቃላትና ሃረጎች ከዚህ በታች በተሰጡት ዓረፍተ ነገሮች ከአገባብ አንፃር እንዲስማሙ አድርገህ በተሰጠህ ባዶ ቦታ ላይ በማስገባት ጻፍ።

ከሁሉም በላይ ከዚህ ይልቅ ከዚህም በመነሣት በአጠቃላይ
በተለይ ነገር ግን ምክንያቱም

ሀ. ሥዕል ለመሣል ፍላጐቱ የለኝም _____ አጫጭር ልቦለዶችንና ቀልዶችን መጻፍ ደስ ይለኛል።

ለ. በዚህች ዓለም ላይ እኔን _____ የሚያስደስተኝ ነገር ቢኖር ሁሉም ሰው ደስተኛ ሆኖ ማየትን ነው።

ሐ. ሥዕል ለመሣል ያለኝ ችሎታ በጣም ዝቅተኛ ነው _____ የተሳሉትን ሥዕሎች መልዕክት መገንዘብና አስተያየት መስጠት ይቀለኛል።

መ. በአብዛኛው የዱር እንስሳት እራሳቸውን ከጠላት ለመከላከል ሲሉ መተናኮላቸውን አይቀርም _____ ለዚህ ዓይነቱ ተግባር እንበሳና ነብር በምሣሌነት የሚጠቀሱ ናቸው።

ሠ. የሰው ልጅ ሲሠራ፣ ሲቀመጥም ሆነ ሲተኛ ስላከናወናቸውና ወደፊትም ስለሚያከናውናቸው ተግባራት ያስባል። የሰውን ልጅ ከሌሎች እንስሳት ለየት የሚያደርገውም ስላከናወነውና ወደፊትም ስለሚያከናውነው ነገር ከወዲሁ ማሰብ መቻሉ ነው።

ረ. ቀደም ሲል ለክባተኛ ክፍል ጀምሮ የተለያዩ መጽሔቶችን፣ ጋዜጦችን፣ አንዳንድ ወጋዊ ጽሑፎችንና ቀልዶችን አነባለሁ። _____ ዛሬ የተለያዩ መጣጥፎችን በተለያዩ መጽሔቶችና ጋዜጦች ለማቅረብ በቅቻለሁ።

7. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ሥርዓተ ነጥባቸውንና ምልክታቸውን አስተካክለህ ፃፍ።

ሀ. ማነው ይህንን ሥዕል የሳለልዎት አለ ጠያቂው።

ለ. ሳስበው አንዲት የእርሳስ ጭረት ብዙ መናገር ርቀትናንና ጥላና ብርሃንን ከፍታና ዝቅታን ማሳየት ትችላለች።

ሐ. እግር ኳስ ጨዋታ መመልከት በጣም እወዳለሁ። ተጫዋቾችንም አደንቃለሁ።

መ. ስምንተኛ ክፍል ሳለሁ በመስኮት ያዩትን ነገር ለምሣሌ ባቡር ሲያልፍ ባቡር ሳሉ አህያም ስታልፍ ካለፈች አህያ ሣሉ የሚሉ የሥዕል አስተማሪ እንደነበሩ ትዝ ይለኛል።

ሠ. አንድ ውሻ ተጋድሚል ዓይኖቿን ጨፍኗል እንቅልፍ የወሰደው ይመስላል ምግብ እየሸተተው የሚተኛ ውሻ ታውቃላችሁ።

8. መመሪያ፦ የሚከተለውን አንቀጽ ተመልከት

ሃዋ ጉበዝ ተማሪ ናት። በጠዋት ተነስታ ፊታን ታጥባ ቁርሷን ከበላች በኋላ በእግሯ ሁለት ኪሎ ሜትር የሚያህለውን መንገድ አቆራርጣ በሰዓቱ ትምህርት ቤት ትገኛለች። ሃዋ የተሰጣትን ማናቸውም የቤት ሥራ ሰርታ ስለምትገኝ መምህራን ሁሉ በጥሩ ምሣሌነት ያነሷታል። ሃዋ የእለቱን ትምህርት እንዳጠናቀቀች በፍጥነት ወደ ቤቷ ከተመለሰች በኋላ የትምህርት ቤት ልብሷን አውልቃ የሥራ ልብሷን ቀይራ በአንዳንድ ሥራዎች ቤተሰቧን ታግዛለች። በቤተሰቧ በኩል የተሰጣትን ሥራ አጠናቃ እንደጨረሰች ከመኝታ ክፍሏ ገብታ ለትንሽ ደቂቃ ያህል አሸልባ ትነሳለች። ትንሽ ከአረፈች በኋላ የዘወትር ተግባር የሆነውን ጥናቷን ከጥናት ክፍሏ ገብታ ታከናውናለች።

ማብራሪያ ሃዋ ጉብዝ ተማሪ ናት የሚለው ዓረፍተ ነገር መንደርደሪያ ዓረፍተ ነገር ሲሆን ጥቅሙም የአንቀጹን መልእክት አጠቃሎ መያዙ ነው። በጠዋት ተነስታ ፊቷን ታጥባ ቁርሷን ከበላች በኋላ _____ የሚለው ዓረፍተ ነገር ዝርዝር ዓረፍተ ነገር ነው። ጥቅሙም በጥቅል የተቀመጠውን የአንቀጹን መንደርደሪያ ዓረፍተ ነገር ዘርዘር ባለ ሁኔታ መግለጽ ነው። በመንደርደሪያ ዓረፍተ ነገርና በዝርዝር ባለ ሁኔታ መግለጽ ነው። በመንደርደሪያ ዓረፍተ ነገርና በዝርዝር ዓረፍተ ነገር መካከል ያለው ልዩነት የጥቅል ነትና። የዝርዝርነት ነው በሁለቱ መካከል ያለው ዝምድና ደግሞ የተገላጪና። የገላጪ ነው። ጥቅልና ተገላጪነት የመንደርደሪያ ዓረፍተ ነገር ባሕሪ ሲሆን የዝርዝርነትና የገላጭነት ባሕሪ ደግሞ የዝርዝር ዓረፍተ ነገር ባሕሪ ነው።

በዚህ ማብራሪያ መሠረት የቡና ቤት ሥዕሎች የሚለውን ምንባብ የተለያዩ አንቀጾችን መንደርደሪያ ዓረፍተ ነገር እየለየህ ተናገር።

ሀ. የአንቀጽ አንድ መንደርደሪያ ዓረፍተ ነገር _____

ለ. የአንቀጽ ሁለት መንደርደሪያ ዓረፍተ ነገር _____

ሐ. የአንቀጽ ሶስት መንደርደሪያ ዓረፍተ ነገር _____

መ. የአንቀጽ አራት መንደርደሪያ ዓረፍተ ነገር _____

ሠ. የአንቀጽ አምስት መንደርደሪያ ዓረፍተ ነገር _____

9. የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንደ አጠያየቃቸው መልስ

ሀ. መንደርደሪያ ዓረፍተ ነገሮች ከአንቀጽ መጀመሪያ መካከል መጨረሻ መጀመሪያና መጨረሻ እንደሚመጡ ታውቃለህ የቡና ቤት ሥዕሎች የሚለው ምንባብ የተለያዩ አንቀጾች መንደርደሪያ ዓረፍተ ነገር በአብዛኛው የተገኙት በየት ነው?

ለ. ተራኪው የሥዕል ፍላጐት እያለው ሰዓሊ ለመሆን ያልቻለው በምን ምክንያት ነው? በቃልህ አስረዳ።

ሐ. ተራኪ የሥዕልን ሁኔታ የሚያደንቅበትን አንቀጽ የትኛው እንደሆነ ጠቁመህ ጥቀስ።

መ. ተራኪው በአንድ የባህል ምግብ ቤት ገብቶ የተመለከታቸውን የሥዕል አይነቶች በጽሑፍ ዘርዝር።

አባሪ «ለ»

ለአዳባ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የ11ኛ ክፍል ተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረጃዎች ክሂላቸውን ለመለካት የተዘጋጀ ቅድመ ተፈና (Pre Test)

ጾታ _____ እድሜ ____ ኮድ ___ ቀን _____ ተ.ቁ _____

ምንባብ _____ የተፈቀደው ጊዜ _____

ጠላት ድል አድርጎ ሲገባ የሚያወጣውን ሕግ የሚያደርገውን ጥፋት ለማወቅ አንችልም። ጣሊያኖች ኢትዮጵያን ሲወሩ የተመሩበት ሃሣብ በበቀልና በዘር ጥላቻ ብቻ ሣይሆን የፖለቲካቸው መሠረት ኢትዮጵያን ጦር ሕዝቧን በተሻለ በመቀነስና የራሳቸውን ጦር አደራጅቶ ለማርካት ነው። ሙሶሎኒ ኢጣሊያ።

አገሪ ለመጥበብ ያላትን ችግርና ቀድሞ የነበረውን የቁሣር መንግሥት እንደገና ለመፍጠር ያለውን ትእቢተኛ ምኞች ለመፈጸም ሲፈለግ የመጀመሪያ እርምጃውን ኢትዮጵያ ላይ አሳርፏል። ስለዚህ እኛ ኢትዮጵያውያን በመሣሪያ ጉልበት ጦራችን ቢሸነፍም አገራችን በመላ ብትወረርም ቅሉ እስከመጨረሻው መታገልና መከራከር በያለንበት ጠላትን ማስጨነቅ፣ ሥር እንዳይሰድ ማወክ። ሥራውን

ማበላሸት መንገዱን ማጠር ያስፈልጋል።

ከእንግዲህ ወዲህ የምንዋጋው ለክብራችን፣ ለሀገራችን ብቻ ሣይሆን ለሕይወታችንና ለመጪው ትውልድ ሕይወት ነው። የሕይወት ትግል የሚባለው ምሕረት የሌለው ጦርነት ሲሆን ነው። እኔ ሠላማዊ ነኝ፤ እነሱ የሚያወጡትን ደንብ ከተከተልኩና ሰርቼ በእምነት ከኖርኩ፣ ታዛኝ።

ከሆንኩላቸው አያስቸግሩኝም፣ ወይም እኔን ድህውን፣ እኔን ሠርቶ አዳሪውን ምን ብለው ያስቸግሩኛል? እነ· የሚከታተሉት ታላላቆችን የሕዝብ መሪዎች የነበሩትን ብቻ ነው። የሚል ከንቱ ስህተት ባንጎላችሁ እንዳይገባ፤ እውነት ነው ጣሊያን ለጊዜው ብዙ ችግር እንዳያገኘው የማባባያ ፖለቲካውን እና የማታለያ ፕሮፖጋንዳውን መንዛቱ አያጠራጥርም፤ ነገር ግን እንዳትታለሉ።

እሱ የሚፈልገው አገሪቷን፣ መሬቷን፣ ነው እንጂ እኛን አይፈልግም አገሪቷን በእጅ አስገብቶ ለመረጋገጥ ስጋቱን ሁሉ ለማስቀረት ተወላጆቹን አውድሞ እሱ መርካት አለበት፤ ይህም ፖለቲካ በጣሊያን የተጀመረ አዲስ ነገር አይምሰላችሁ በአውስትራሊያ፣ በመላው አሜሪካ፣ በኒውዝላንድ ሁሉ የታየ አይደለምን? ስለዚህ።

ሌላ ምርጫ የለንም፣ ታግሎ መዳን ወይም ለዘላለም ጠፍቶ መቅረት ነው። እኔ ራሴ ብሆን ወንድሞቼ የቆረጥኩትን ሃሣቤን ልንገራችሁ፣ ብዙ መጽሐፍ አንብቤያለሁ/ ብዙዎች ቆራጥ ሕዝቦች ለጊዜው ቢወረሩም ትግላቸውን ባለማቋረጥ በእግዚአብሔር ፍርድ እምነትን በማደርግ ከትውልድ እስከ ትውልድ ትግላቸውን በመቀጠል ማንኛውንም ፈታኝ ፈተና በመቀበል።

ነፃነታቸውን መልሰው ለማግኘትና ሕይወታቸውን መልሰው ለመመሥረት ችለዋል።

ሕይወት እኮ የምትገኘው በትግልና በፈተና ነው። የሟይንቀሳቀስና የማይጣጣር ሕይወት ያለው ሊሆን አይችልም፣ በድን ነው፣ ስለዚህ እኔ እንደሆንሁ ከእንግዲህ ወዲህ እስከሞቴ ድረስ ጠላትን ለመታገል ቆርጫለሁ። ዓይኔ እያየ ራሴን ለመደለል በውጥመድ አልገባም አባቶቼ አገር ባሌ ገብቼ።

ገደል ለገደል፣ ደን ለደን እየተዘዋወርኩ እስከ ሞቴ ቀን ድረስ መዋጋቴን አላቋርጥም፤ ይህ የቆረጠ ሃሣቤ ነው። ይህን ሃሣቤን ምንም የሚለውጠው ነገር ሊኖር አይችል። እናንተ ወንድሞቼ አሁን

የዘረዘርኩላችሁን ተገንዝባችሁ እንደሆነ ተከተሉኝ፤ ላገራችን እንሙትላት፤ እንደ ወንዶች፤ እንደ ጀግኖች እንሙት::

40. አገራችን ሰፊና ምቹ ናት፤ ብዙ ዓመት ሸፍተን ለመሞት እንችላለን::

ምንጭ፤ አፈወርቅ ገ/የሱስ፤ የቄሣር መንግሥት መልዕክተኛ፤ ቁጥር ስድስት፤ ሁለተኛ እትም፤ አዲስ አበባ::

መመሪያ 1:- የሚከተሉት ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው:: እነዚህን ቃላት ከምንባቡ ውስጥ የተኩትን ቃላት፤ ሀገሳች ወይም ዓረፍተ ነገሮች እየፈለግህ በተሰጠህ ባዶ ቦታ ላይ ጻፍ/ፊ/

1. «እኛ» መስመር /7/ የሚወክለው _____
2. «እኔ» መስመር /13/ የሚወክለው _____
3. «እኔን» መስመር /15/ የሚወክለው _____
4. «እነነሱ» መስመር /16/ የሚወክለው _____
5. «እሱ» መስመር /20/ የሚወክለው _____
6. «እኔን» መስመር 15/ የሚወክለው _____
7. «እኛን» መስመር /20/ የሚወክለው _____
8. «እነናንተ» መስመር /38/ የሚወክለው _____
9. «ይህ» መስመር /36/ የሚወክለው _____
10. «እሱ» መስመር /22/ የሚወክለው _____

መመሪያ 2:- የሚከተሉት ቃላትና ሃረጎች ከምንባቡ ውስጥ የወጡ ናቸው:: እነዚህን ቃላትና ሃረጎች ከአገባባቸው አንፃር የያዙትን ፍቺ ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን ፍቺ የያዘውን ፊደል መርጠህ /ሺ/ ከቁጥሩ ጀርባ በተሰጠው ባዶ ቦታ ጻፍ/ፊ/::

___ 11. መስመር /6/ «ያለውን <u>ትዕቢተኛ</u> ምኞት ለመፈጸም» ሲል የተሰመረበት ቃል የያዘው ፍቺ _____ ነው::

ሀ. ኩራተኛ
ለ. ጉረኛ
ሐ. እልኸኛ
መ. ግልፍተኛ

___ 12. መስመር /16-17/ «እነሱ የሚፈልጉት ታላላቆቹን የሕዝብ መሪዎች ብቻ ነው፤ የሚል <u>ከንቱ</u> ስህተት በአእምሮአቸሁ ውስጥ እንዳይገባ» ሲል የተሰመረበት ቃል የያዘው ፍቺ _____ ነው::

ሀ. ባዶ
ለ. የማይሆን
ሐ. እንቶፈንቶ
መ. የማይረባ

___ 13. መስመር /23/ «ተወላጆችን <u>አውድሞ</u> እሱ መርባት አለበት» ሲል የተሠመረበት ቃል ፍቺ _____ ነው::

ሀ. አጥፍቶ
ለ. ደብድቦ
ሐ. አስማምቶ
መ. ረድቶ

___ 14. መስመር /31/ «<u>የማይንቀሳቀስና የማይጣጣር</u> ሕይወት ሕይወት ሲሆን አይችልም ሲል» የተሰመረበት ሃረግ ፍቺ _____ ነው።

ሀ. የሚነሣና የሚወድቅ ሐ. ግዑዝ ያልሆነ

ለ. የማይፍጨረጨር መ. የማይሯሯጥ

___ 15. መስመር /34/ «አራሴን በመደለል <u>በውጥመድ</u> አልገባም» ሲል የተሰመረበት ሀረግ ፍቺ _____ ነው።

ሀ. በተጠመደው አደገኛ መሰናክል ሐ. እንዲጠልፍ በተዘጋጀው ገመድ

ለ. በተጠመደው አደገኛ ሴራ መ. በተዘጋጀው እሥር ቤት

___ 16. መስመር /10/ «መንገዱን ማጠር ያስፈልጋል።» ሲል _____ ማለቱ ነው።

ሀ. ዙሪያውን በግንብ መከለል ሐ. መውጫ ቀዳዳ ማሳጣት

ለ. መንገዱን በውጥመድ መዝጋት መ. መንገዱን በአሾክ ማጠር

___ 17. መስመር /9/ «ሥር እንዳይሰድ <u>ማወክ</u>» ሲል የተሠመረበት ቃል ፍቺ _____ ነው።

ሀ. ማረጋጋት ሐ. መረበሽ

ለ. ማስማማት መ. የማሻሻያ

___ 19. መስመር /25/ «ለዘለዓለም ጠፍቶ መቅረት ነው»። ሲል የተሰመረበት ሃረግ ፍቺ _____ ነው።

ሀ. ከአገር መልቀቅ ሐ. መክዳት

ለ. መሸሸግ መ. ሕይወትን ማጣት

መመሪያ 3:- ከዚህ በታች የቀረቡት የምርጫ ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት አድርገው የወጡ ናቸው። ምንባቡን በጥንቃቄ ካነበብህ በኋላ ከተሰጡት አራት አማራጮች መካከል ለጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል እየመረጥህ /ሽ/ ከቁጥሩ ፊት ለፊት በተሰጠው ባዶ ቦታ ጻፍ/ፊ/

___ 20. የኢጣሊያን መንግሥት ሙሶሎኒ የመጀመሪያውን የወረራ ተግባር የፈጸመበት ምክንያት _____ ነው።

ሀ. የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመረዳት ባለው ጽኑ ፍላጎት

ለ. ትቢተኛ በመሆኑ ያለውን ፍላጎትና ምኞት ለመፈጸም ነው

ሐ. ለኢትዮጵያ ሕዝብ ባለው ፍቅር

መ. ኢትዮጵያን ከሌላ ወራሪ ኃይል ለመጠበቅ

___ 21. ጣሊያኖች በወቅቱ ኢትዮጵያን ሲወሩ የተነሳሱት ምክንያት ____ነው።

ሀ. በዘርና በበቀል ብቻ ሐ. በጥላቻ ብቻ

ለ. በዘር፣ በበቀልና በፖለቲካ መ. በበቀልና በፖለቲካ ብቻ

___ 22. እንደ ደራሲው /ተናጋሪው/ አባባል «የሕይወት ትግል» የሚባለው _____ ነው።

ሀ. ምህረት የሌለው ጦርነት የሚካሄድበት

ለ. ለሃይማኖት ሲባል የሚደረግ ትግል

ሐ. የተወሰኑ ኢትዮጵያውያን ብቻ የሚሳተፉበት

መ. ሰላማዊ ሰዎች የማይሳተፉበት

___ 23. እንደ ደራሲው አባባል የኢጣሊያን ወራሪ ኃይል ከኢትዮጵያ ይፈልግ የነበረው _____ ነው።

ሀ. መሬትን ብቻ ሐ. ሕዝቦቿን ብቻ

ለ. ልጆቷንና መሬቷን መ. ከርሰ ማዕድን ብቻ

___ 24. እንደ ደራሲው አባባል ኢትዮጵያውያን ከኢጣሊያን ጋር ማድረግ ያለባቸው ውጊያ _____ በመሆን አለበት::

ሀ. ለክብር ብቻ የሚደረግ

ለ. ለመጪው ትውልድ ሲባል የሚካሄድ

ሐ. ለክብር፣ ለመጪው ትውልድና ለኢትዮጵያውያን ሕይወት ሲባል የሚካሄዱ

መ. ለክብር፣ ለድንበር፣ ለመጪው ትውልድና ለኢትዮጵያውያን ሕይወት የሚደረግ

___ 25. የኢጣሊያንን መሰል ፖለቲካ አቋም አላቸው በማለት ደራሲው በምሣሌነት የጠቀሳቸው አገሮች _____ ናቸው::

ሀ. አውስትራሊያና ኒውዝላንድ

ለ. አሜሪካ፣ አውስትራሊያና ኒውዝላንድ

ሐ. አሜሪካ፣ አውስትራሊያና ኒውዝላንድ

መ. አውስትራሊያ፣ አሜሪካና እንግሊዝ

___ 26. ደራሲው በምንባቡ ውስጥ «ከንቱ ስህተት» የሚለው _____ ነው::

ሀ. ጣሊያን ኢትዮጵያን መውረሩን

ለ. የጣሊያንን ወረራ ኢትዮጵያን እንደ መጥፎ መመልከታቸውን

ሐ. ጣሊያን መንግሥት በኢትዮጵያ ውስጥ ገብታ ርምጃ የሚወስደው በታላቅ መሪዎች ብቻ ነው የሚለውን

መ. እኔ ሁሉም ኢትዮጵያውያን በወራሪው ጣሊያን ላይ መነሣሣት አለበት የሚለውን

___ 27. የቀስቃሹ ቁርጠኛ አቋም የተገለጸበት ዓረፍተ ነገር የሚገኘው _____ አንቀጽ ውስጥ ነው::

ሀ. በአንደኛው ሐ. በሶትኛው

ለ. በሁለተኛው መ. በአራተኛው

___ 28. የጽሑፉ ዓላማ _____ ነው::

ሀ. ስለ ወራሪው ጣሊያን ጦር ማስረዳት

ለ. ስለ ኢጣሊያን መልክአምድር አቀማመጥ መግለጽ

ሐ. ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ በወራሪው ጣሊያንን እንዲዋጋ መቀስቀስ

መ. ስለ ኢጣሊያን መንግሥት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የነበረውን ቀና አመለካከት ማሳወቅ::

___ 28. ደራሲው ለነገሩ ያለው ከፍተኛ ስሜት የተገለጸው _____ አንቀጽ ውስጥ ነው::

ሀ. በአንደኛው ሐ. በሶስተኛው

ለ. በሁለተኛው መ. በአራተኛው

መመሪያ 4:- ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ዓረፍተ ነገሮች ከምንባቡ ውስጥ የወጡ ናቸው በ«ሀ» ሥር የተደረደሩትን ዓረፍተ ነገሮች ፀሐፊው መልዕክቱን ለማስተላለፍ የተጠቀመባቸው ዓረፍተ ነገሮች ሲሆኑ በ«ለ» ሥር ያሉት ደግሞ የአጠቃቀም ዓይነቶች ናቸው በ«ሀ» ሥር ለተደረደሩት ከ«ለ» ሥር ተስማሚ የሆነውን እየፈለግና/ሽ/ በቁጥሩ ጀርባ በተሰጠው ባዶ ቦታ ፊደሉን ብቻ ጻፍ/ፊ/

«ሀ»	«ለ»
___ 30. እኔን ደሃውን፣ እኔን ሠርቶ አዳሪውን ምን ብለው ያስቸግሩኛል?	ሀ. ማብራሪያ መስጠት
___ 31. እኔ ራሴ ብሆን ወንድሞቼን የቆረጥኩት ሃሣብ ልንገራችሁ፣ ብዙ መጽሐፍ አንብቤያለሁ	ለ. መጠይቅ ማቅረብ
___ 32. ከእንግዲህ ወዲያ የምንወያየው ለክብራችን	ሐ. ተጨማሪ
___ 33. በተግባራችን ብቻ ሣይሆን ለሕይወታቺንና ለመጪው ትውልድ ነው።	መ. መቀስቀስ
___ 34. ሙሶሎኒ ያለውን ትዕቢተኛ ምኞት ለመፈጸም ሲፈልግ የመጀመሪያውን ርምጃ ኢትዮጵያ ላይ አሳርፏል። ስለዚህ እኛ ኢትዮጵያውያን በመሣሪያ ጉልበት ብንሸነፍም እስከመጨረሻው እንታገላለን።	ሠ. ቁርጠኛ ውሣኔ መስጠት

መመሪያ 5:- የሚከተሉት ጥያቄዎች ከምንባቡ ውስጥ የወጡ ናቸው ለእነዚህን ጥያቄዎች ከምንባቡ ውስጥ እየፈለግህ ካገኘህ በኋላ በተሰጠህ ክፍት ቦታ ላይ ጻፍ/ፊ/

36. ጣሊያን ኢትዮጵያን ለመውረር ያነሳሱት ምክንያቶች ምንድን ናቸው? _____

37. ደራሲው /ቀስቃሹ/ ጽሑፉን የጻፈው ጣሊያን ኢትዮጵያን ከወረረ በኋላ ቢሆንም ማድረግ አለብን የሚለው ነገር ምንድን ነው? _____

38. ቀስቃሹ የሕይወት ትግል የሚለው ምንድን ነው? _____

39. ቀስቃሹ የጣሊያን መንግሥት በወቅቱ ከኢትዮጵያ የሚፈልገው ምነድን ነው ብሎ ያምናል? _____

40. የቀስቃሹ ቁርጠኛ ዓላማ ምንድን ነው? _____

41. ቀስቃሹ እንዲ ቆርጥ ያደረገውን ነገር በማስረጃነት የጠቀሳቸው ነገሮች ግለጽ/ጭ/ _____

42. ደሐፊው ይህን ጽሑፍ ሲጽፈው ለምን ዓላማ አስቦ ይመስልሀል/ሻል/? _____

43. «የመጀመሪያውን አንቀጽ መንደርደሪያ ዓረፍተ ነገር አውጥተና ጻፍ/ፊ/ _____

44. የሁለተኛውን አንቀጽ መንደርደሪያ ዓረፍተ ነገር አውጥተህ ጻፍ/ፊ/ _____

45 የቀስቃሹን ያለውን ከፍተኛ ስሜት የሚገልጽ ሁለት ቃላትን ወይም ሃረጋትን አውጥተህ ጻፍ/ፊ/ _____

አባሪ «መ»

ለጥብቅ ቡድኑና ለተጠኚ ቡድኑ የተዘጋጀ ጽሁፍ ፈተና (post-test)

ኮድ _____

ቀን_____

ጾታ ___ ዕድሜ ___ ተ.ቁ ___ ክፍል ____ የተፈቀደው ጊዜ _____

ምንባብ

1. የአውቀት ምንጭ ጠቅላላ ቁሳዃዊና ሰው ሠራሽ አካባቢያችን እንደሆነ ሊቃውንት ይናገራሉ የሰው ልጅ አውቀቱን የሚያገኘውና የሚያዳብረው ቀስ በቀስ ደረጃ በደረጃ ሲሆን ይህም የሚከሰተው ሰዎች ከተፈጥሮ ወይም ከአካባቢ ጋር በሚያደርጉት የእለት በእለት ፍጭት ወይም ፍትጊያ ነው።

ነው። ይህ ትግል የተለያየ መልክና ይዘት ቢኖረው በአካባቢ ኃይሎች ተውጠው እንዳይጠፉ ኑሮን

5. ለማሸነፍ ሲባል የሚያደርጉት መፍጨርጨር ነው ከጥንት ቅድመ ታሪክ ወቅትና ከዚያም ወዲህ ከጥንታዊ የጋርዩሽ ሥርዓተ ማህበር ጀምሮ እስካለንበት ዘመን ድረስ የሰው ልጆች የእድገት ጉዞ ታሪክ በተጨባጭ የሚያሳየን ይህንኑ ነው። የሰው ልጆች የአውቀት ክምችት በዓይነትም ሆነ በጥራት በእያንዳንዱ ተከታታይ ትውልድ አማካይነት እየተሻሻለና እየዳበረ እንደሚሄድ ይኸው የሰው ልጆች የታሪክ ማህደር ጉልህ ማስረጃ ነው።

10. የሰው ልጅ አውቀት ለመዳበር ከአካባቢና ከተፈጥሮ ጋር የሚያደርገው ትግል የሚከሰተው በሚከተለው ዓይነት ነው። ትግሉም የሚካሄድበት አካባቢ በሁለት ዘርፍ ሊታይ ይችላል። አንደኛው ጠቅላላ የቁስአካላዊ አካባቢ ሲሆን ይህም

ማንኛውም በመሬት ላይና ውስጥ የሚገኙትን ሕይወት ያላቸውንና የሌላቸውን /ሕይወት አልባ/ ነገሮችን ሁሉ ከማካተቱም በላይ ልዩ ልዩ ክስተቶችንና እንዲሁም ከመሬት ሌላ በጠፈር ውስጥ

15. የሚገኙትን ክዋክብትንና ሌሎች አካላትን ሁሉ ይጨምራል። ሁለተኛው ደግሞ ሕብረሰብአዊ ወይም ሰው ሠራሽ ባሕላዊ አካባቢ ነው። ይህ ሰው ሠራሽ የሆኑ ቁሳዊ ባሕሎችን ሁሉ ያካትታል። ለምሣሌ ከተሞችና መንደሮች ከነባሕላዊ ቅርሶቻቸው ማለትም የሰዎችን አስተሳሰቦች ልምዶች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶች፣ ፈልስፍናዎች፣ ወዘተ. ባጠቃላይ የሰው ልጅ እስተዋጽኦ ያላቸውን የኑሮ መገልገያዎችንና ዘይቤዎችን ሁሉ ያጠቃልላል።

20. አንድ ሰብዓዊ ግለሰብ የሚወለደውና የሚያድገው በነዚሁ አካባቢዎች መካከል ነው። የእድገቱ ታሪክ በነዚሁ አካባቢዎች ውስጥ ለመኖር የሚያደርገው የትግል ታሪክ ነው። ትምህርትም በዚህ የትግል ታሪክ ውስጥ የሰው ልጅ ከአባባቢው ጋር በሚያደርገው ግብግብ በአሸናፊነት ለመወጣት ሲል ቀስ በቀስ የፈጠረውና ያዳበረው ዓይነተኛመማሪያ ነው። ስለዚህ ግለሰቡ የሚያካሂደው ትግል፣ ግጭትና ፍትጊያ

25. ተግባራዊ እንዲሆን ግለሰቡ ከተፀነሰበት ጊዜ ጀምሮ ለነዚህ አባቢያዊ ክስተቶች መጋለጥ አለበት። ይህም ማለት ፊት ለፊት መጋለጥና መፋተግ ይኖርበታል ማለት ነው።

ግለሰቡ በአካባቢ የመጋለጥ ሁኔታ ስፋቱና ጥልቀቱን የቱን ያህል ነው? ከተጋለጠስ በኋላ ግለሰቡ በሚያደርገው ትግል በአሸናፊነት ለመወጣት

የቱን ያህል ምላሽ ይሰጣል? ለምሣሌ በልዩ ልዩ አደጋዎች ለበሽታ ለድንቁርና ለረሃብ ወዘተ.

30. ሲጋለጥ ከችግሩ በአሸናፊነት ለመወጣት ምን ያደርጋል? ይህም ማለት በጠቅላላው በግለሰቡ የሕይወት ዘመን ውስጥ የተለያዩ ሁኔታዎች የሚያጋጥመው የመጋለጥ ሁኔታ መጠን እንዲሁም በሚጋለጥበት ወቅት ግለሰቡ የሚፈጽመው የትግል ስፋት ጥልቀትና ዓይነት መጠን በመጨረሻ የሚያገኘውንና የሚያዳብረውን የእውቀት፣ የችሎታ የክህሎትና የልምድ ስፋት ጥልቀትና ጥራት እንዲሁም ጠቅላላ የንቃተ ሕሊናውን ደረጃ ይወስናል ማለት ነው።

ምንጭ፣ መጽሔተ ትምህርት ቅጽ 1 ቁጥር 1 ፖ1987፣ 81ዓ የተወሰደ።

መመሪያ 1:- የሚከተሉትን ቃላትና ሃረጎች ከምንባቡ ውስጥ የወጡ ናቸው። እነዚህ ቃላትና ሃረጎች ከምንባቡ ውስጥ ሊተኩት የሚችለውን ቃል ሀረግ ወይም ዓረፍተ ነገር እየፈለግህ በተሰጠህ ባዶ ቦታ ላይ ጻፍ።

1. «ይህም» /መስመር 2/ የሚወክለው _____
2. «ይህንኑ» /መስመር 20/ የሚወክለው _____
3. «ይህ» /መስመር 4/ የሚወክለው _____
4. «ይህው» /መስመር 8/ የሚወክለው _____
5. «ይህ» /መስመር 16/ የሚወክለው _____
6. «በነዚሁ» /መስመር 20/ የሚወክለው _____
7. «ይህም» /መስመር 12/ የሚወክለው _____
8. «በነዚሁ» /መስመር 21/ የሚወክለው _____
9. «ለነዚህ» /መስመር 25/ የሚወክለው _____
10. «ይህም» /መስመር 26/ የሚወክለው _____

መመሪያ 2:- የሚከተሉትን ቃላትና ሃረጎች ከምንባቡ ውስጥ የወጡ ናቸው። ቃላትና ሀገሳቹ ከአገባባቸው አንፃር ሊይዙት የሚችሉትን ትርጉም ከተሰጡት አራት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል እየመረጥህ/ሽ/ የተሰጠው ባዶ ቦታ ላይ ጻፍ/ፊ/

___11. መስመር /6/ «ከጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓት ማህበር ጀምሮ እስከ አለንበት ዘመን ድረስ የሰው ልጆች <u>የእድገት ጉዞ</u> የሚያሳየን ይህንኑ ተጨባጭ ነው» ሲል የተሰመረበት ሃረግ ትርጉም _____ ነው።

1. የሚጓዝበት አስቸጋሪ መንገድ
2. የሚጓዝበት ጠመዝማዛ መንገድ
3. የእድገት አቅጣጫ
4. የእድገት መወጣጫ

___12. መስመር /7-8/ «የሰው ልጆች የእውቀት ክምችት በዓይነትም ሆነ በጥራት በእያንዳንዱ ተከታታይ ትውልድ እየተሻሻለና እየዳበረ እንደሚሄድ ይኸው የሰው ልጆች <u>የታሪክ ማህደር</u> ጉልህ ማስረጃ ነው» ሲል የተሰመረበት ሃረግ ትርጉም _____ ነው።

1. የታሪክ ጉዞ
2. የታሪክ እድገት
3. የታሪክ ማስረጃ
4. የታሪክ አመጣጥ

___13. መስመር /11/ «ትግሉ የሚካሄድበት አካባቢ በሁለት <u>ዘርፍ</u> ሲታይ» ሲል የተሠመረበት ቃል ትርጉም _____ ነው።

1. በተመሣሣይ አቅጣጫዎች
2. በሁለት የተለያዩ አቅጣጫዎች
3. በአንድ ዓይነት አቅጣጫዎች
4. ከሁለት በላይ ባሉ አቅጣጫዎች

__14. መስመር /12/ «አንደኛው ጠቅላላ ቁስአካላዊ የተፈጥሮ አካባቢ ሲሆን» ሲል የተመሠመረበት ቃል የሚወክለው _____ ነው።

1. ማንኛውም ተፈጥሮአዊ አካባቢ
2. ማንኛውም ሰው ሠራሽ አካባቢ
3. ማንኛውም ሰው ሠራሽ ተፈጥሮአዊ አካባቢ
4. ማንኛውም ማህበራዊ አካባቢ

__15. መስመር /15/ «ሁለተኛው ደግሞ ሕብረተሰባአዊ ወይም ሰው ሠራሽ አካባቢ ነው» ሲል የተሠመረበት ቃል የሚወክለው _____ የሚለውን ነው።

1. ማንኛውም ተፈጥሮአዊ አካባቢ
2. ማንኛውም ሰው ሠራሽ አካባቢ
3. ማንኛውም ሰው ሠራሽና ተፈጥሮአዊ አካባቢ
4. የተወሰኑ ቁስአካላዊ አካባቢ ብቻ

__16. መስመር /16/ «ይህ ሰው ሠራሽ የሆነ ቁሣዊና ሃሣባዊ ባሕሪዎችን ሁሉ ያካትታል» ሲል የተሰመረባቸው ቃላት በአጻጻፋቸው ቅደም ተከተል የያዙት ባሕሪ _____ እና _____ ናቸው።

1. የሚጨበጡና የማይጨበጡ
2. በዓይነት የማይታዩና የሚታዩ
3. የማይጨበጡና የሚጨበጡ
4. የማይዳሰሱና የሚዳሰሱ

__17. መስመር /13-14/ «ማንኛውም በመሬት ላይና ውስጥ የሚገኙትን ሕይወት ያላቸውንና ሕይወት አልባ የሆኑት ነገሮች ሁሉ ከማካተቱም በላይ» ሲል የተሠመረበት ቃል ትርጉም _____ ነው።

1. ሕይወት አያላቸው ማሰብ የማይችሉ
2. ለኑሮ ግድ የሌላቸውን ሰዎች
3. በቡድን የሆኑ ነገሮች
4. ለመኖር ውሃ፣ አየርና ምግብ የሚያስፈልጋቸው ፍጡሮች

___18. መስመር /18-19/ «ባጠቃላይ የሰው ልጅ አስተዋጽኦ ያላቸውን የኑሮ መገልገያዎችንና ዘይቤዎችን ሁሉ ያጠቃልላል» ሲል የተሰመረበት ቃል ትርጉም _____ ነው።

1. የማምረቻ መሣሪያዎን
2. የኑሮ ፍልስፍናዎችን
3. ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን
4. የአነጋገር ፈሊጦችን

__19. መስመር /19/ «አንድ ሰብዓዊ ግለ.ብ የሚወለደውና የሚያድገው በነዚሁ አካባቢዎች መካከል ነው?» ሲል የተሰመረበት ቃል ትርጉም _____ ነው።

1. ማንኛውም ሕይወት ያለው ፍጡር
2. ማንኛውም ሰው የሆነ ፍጡር
3. አመለካከቱ ደህና የሆነ ነው
4. የሰውነት ባሕሪ የሌለው ፍጡር

___20. መስመር /22/ «የሰው ልጅ ከአካባቢው ጋር በሚያደርገው ግብግብ ሰአሸናፊነት ለመወጣት» ሲል የፈጠረውና ያዳበረው ነው ሲል የተሰመረበት ቃል ፍቺ _____ ነው።

1. ንትርክ
2. ትንቅንቅ
3. ንዝንዝ
4. አሰጥ አገባ

መመሪያ 3:- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ የወጡ ናቸው። ምንባቡን በጥንቃቄ ካነበብህ በኋላ ለጥያቄው የሚስማማውን መልስ ከተሰጡት አራት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል መርጠህ ከቁጥሩ በስተጀርባ በተሰጠው ባዶ ቦታ ጻፍ/ፊ/

___21. እንደደራሲው ስምምነት ከሆነ የአውቀት ምንጭ ሊሆን የሚችለው _____ ነው።

1. ሰው ሠራሽ አካባቢ ብቻ
2. ተፈጥሯዊ አካባቢ ብቻ
3. ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ አካባቢ
4. ሰው ሠራሽ የሆነ ቁሣዊና ሃሣባዊ ብቻ

___22. እንደደራሲው አባባል እውቀት ሊዳብር የሚችለው _____ ነው::

1. በአጋጣሚ
2. በአንድ ጊዜ
3. ደረጃ በደረጃ
4. ቅጽበታዊ በሆነ አጋጣሚ

___23. እንደደራሲው አባባል የሰው ልጅ እውቀትን ለማግኘት ሲል መታገል ያለበት ከ_____ ነው::

1. ከተፈጥሯዊ አካባቢ
2. ከተፈጥሯዊና ከሰው ሠራሽ አካባቢ
3. ከማህበራዊ አካባቢ
4. ሰማያዊ ዓለም

___24. እንደ ደራሲው አባባል የሰው ልጅ ከተፈጥሮ ጋር ግጭትና ፍትጊያ የሚያደርገው _____ ሲል ነው::

1. ለመታወቅ
2. የተለያዩ ሰው ሠራሽና ተፈጥሮአዊ ችግሮችን ለመቅደም
3. ለመዝናናት
4. ጊዜውን ለማሳለፍ

___25. አንድ ግለሰብ ለአካባቢ የመጋለጥ ሁኔታው ስፋቱና ጥልቀቱ የሚወሰነው በ _____ ነው::

1. ተፈጥሮን ለመለወጥ በሚያደርገው ትግል ስፋትና ጥልቀት
2. ተፈጥሮን ለመለወጥ በሚያደርገው ቅድመ ዝግጅት
3. ተፈጥሮን ለመለወጥ በአለው መልካም ምኞት
4. ተፈጥሮን ለመለወጥ በአለው የወደፊት እቅድ

_____26. የዚህ ምንባብ ዓቢይ ትኩረት_____ላይ ነው::

1. የተለያዩ የእውቀት ዓይነቶችን መግለጽ
2. ስለዘመኑ የእውቀት ሁኔታ
3. የእውቀት ምንጭና የእድገት ሁኔታ
4. ስለ ዘመኑ ሰው የእውቀት ደረጃ

___27. ከጥንት ቅድመ ታሪክ ወቅትና ከዚያም ወዲህ ከጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓተ ማህበር ጀምሮ እስካለንበት ዘመን ድረስ በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ ደራሲው የተሠመረበትን ሀረግ የተጠቀመው _____ለማመለከት ነው::

1. ከጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓተ ማህበር ጀምሮ እስካለንበት ዘመን ድረስ ለውን
2. ከጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓተ ማህበር በፊት ያለውን
3. ከጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓተ ማህበር እስከ ባሪያ አሳዳሪ ሥርዓተ ማህበር ድረስ ያለውን
4. የጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓተ ማህበርን

___28. ቀስ በቀስ፣ ደረጃ በደረጃ የሚሉት አገላለጾች የሚያመለክቱ _____ ነው::

1. የነገሮችን ታሪካዊ አመጣጥን
2. በጊዜ ተከታታየነት የሚከሰተውን እድገት
3. የድርጊቶች ቅደም ተከተላዊ ሂደትን
4. የሁኔታዎችንና የድርጊቶችን ቅደም ተከተላዊ ሂደትን

___29. በምንባቡ እንደተገለጸው አንድ ግለሰብ ከተፈጥሮና ከሰው ሠራሽ አካባቢ ጋር መታገል መጀመር ያለበት ከ_____ ነው::

1. እንደተወለደ
2. እንደተፀነሰ
3. በቋንቋ መግባባት እንደጀመረ
4. በወጣትነት የአድሜ ዘመኑ

___30. የምንባቡ ርዕስ ከሚከተሉት ውስጥ የቱ ሊሆን ይችላል?

1. የእውቀት ዓይነቶች
2. የእውቀት ምንጮች
3. የእውቀት ዘርፎች
4. የእውቀት አመጣጥና ታሪካዊ እድገት

መመሪያ 4:- የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ከምንባቡ ውስጥ የወጡ ናቸው:: በ«ሀ» ሥር የተደረደሩት ዓረፍተ ነገሮች ደራሲው መልእክቱን ለማስተላለፍ የተጠቀመባቸው ሲሆን በ «ለ» ሥር ደግሞ ደራሲው ምን ዓይነት መልእክት ለማስተላለፍ እንደፈለገ የሚገለጹ ናቸው በ«ሀ» ሥር ለተደረደሩት ዓረፍተ ነገሮች በ«ለ» ሥር ተስማሚ የሆነውን የአገላለጽ ዓይነት እየፈለግህ ከቁጥሩ ጀርባ በተሰጠው ባዶ ቦታ ፊደሉን ብቻ ጻፍ/ፊ/

«ሀ» «ለ»

___31. የሰው ልጅ እውቀት ለማዳበር ከአካባቢና ከተፈጥሮ ጋር የሚያደርገው ትግል የሚከሰተው በሚከተለው ዓይነት ነው:: አንደኛው ተፈጥሮአዊ አካባቢ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በሰው ሠራሽ አካባቢ ነው::

ሀ. የጊዜን ተከታታይነት ይመለከታል::

___32. ሕብረተሰባዊ አካባቢ ሰው ሠራሽ አካባቢን ያካተተ ለምሳሌ ከተሞችና መንደሮችን ከነ ባህላዊ ቅርሳቸው ማለትም የሰዎችን አስተሳሰቦች ልምዶች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶች፣ ፍልፍፍናዎች ወዘተ. ባጠቃላይ የሰው ለጅ አስተዋጽኦ ያላቸውን የኑሮ መገልገያዎችንና ዘይቤዎችን ሁሉ ያጠቃልላል::

ለ. የድርጊቶችን ቅደም ተከተላዊ ሂደት ይጠቁማል::

___33. የሰው ለጅ እውቀቱን የሚገኘውና የሚያዳብረው ቀስ በቀስ፣ ደረጃ በደረጃ ሲሆን ይህም የሚከሰተው ሰዎች ከተፈጥሮ ወይም ከአካባቢ ጋር የእለት በእለት ትግል ግጭት ወይም ፍትጊያ ነው::

ሐ. ጥያቄ ማቅረብን

___34. ከጥንት ቅድመ ታሪክ ወቅትና ከዚያም ወዲህ ከጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓት ጀምሮ እስከአለንበት ዘመን ድረስ የሰው ልጆች የእድገት ታሪክ በተጨባጭ የሚያሳየን ይህንኑ ነው::

መ. ዝርዝር ማስረጃ ማቅረብን ያሳያል

35. ግለሰቡ ለአካባቢው የመጋለጥ ሁኔታ ስፋቱና ጥለቀቱ የቱን ያህል ነው?

ሠ. ማብራሪያ መስጠትን ያመለክታል::

መመሪያ 5:- የሚከተሉት ጥያቄዎች ከምንባቡ ውስጥ የወጡ ናቸው:: ምንባቡን ካነበብህ በኋላ ለጥያቄዎች መልስ ከምንባቡ እየፈለግህ በተሰጠህ ባዶ ቦታ ላይ ጻፍ/ፊ/

36. የእውቀት ምንጮች ምንድን ናቸው ?_____

37. የሰው ልጅ እውቀቱን ሊያዳብር የሚችለው በምን ሁኔታ ነው ?_____

38. ሰው ሠራሽ አካባቢ የሚባለው በውስጡ የሚያጠቃልላቸውን የአካባቢ ዓይነቶች ግለጽ? _____

_____

39. የሰው ልጅ ከተፈጥሮ ጋር ግብግብ ለመግጠምና ለማሸነፍ ይረዳው ዘንድ መጠቀም የአለበት ዓይነተኛ መሣሪያ ምንድን ነው:: _____

40. የሰው ልጅ ለመኖር ሲል የሚያደርገው ትግል በሁለት ዓይነት መለኩ እንደሆነ በምንባቡ ተገልጿል እነዚህ ሁለት መንገዶች ጥቀስ:: _____

41. የአንድን ሰው የንቃት ህሊና ደረጃ የሚወስነው ምንድን ነው ?_____

42. የመጀመሪያውን አንቀጽ መንደርደሪያ ዓረፍተ ነገር አውጥተህ ጻፍ:: _____

43. የምንባቡ መልእክት ምንድን ነው? _____

44. የሁለተኛውን አንቀጽ መንደርደሪያ ዓረፍተ ነገር አውጥተህ ጻፍ _____

45. የጠፈር ውስጥ ከዋክብት የሚመደቡት ከየትኛው የአካባቢ ዓይነት ነው? _____

ሐ

የፖይለት ፕሮጀክት ስታትስቲካዊ ሥሌቶች ውጤት መግለጫ

አባሪ «ሐ-1»

በፓይለት ፕሮጀክት ናሙናዎች የምንባቦችን ተነባቢነት ለመለካት የግንዛቤ ፈተና (Cloze Test) የተገኘውን ውጤት የሚያሣይ ሠንጠረዥ

ተ.ቁ	ውሃን አፍልቶ መጠቀም		ማህበር		የቡና ቤት ሥዕሎች		ጥንታዊ ጉዞ	
	35	100%	37	100%	64	100%	54	100%
1	18	51.41	29	78.37	37	57.81	12	22.22
2	22	62.85	26	70.27	42	65.62	29	53.70
3	12	34.28	17	45.94	36	56.25	26	48.14
4	13	65.71	23	62.16	29	45.31	23	42.59
5	16	45.71	20	54.05	45	70.31	31	57.40
6	25	71.42	25	67.56	38	59.37	22	40.74
7	27	77.14	33	89.18	48	75.00	16	29.62
8	28	80.00	18	48.64	55	85.93	25	46.29
9	14	40.ዐ0	31	83.78	39	60.93	17	31.48
10	19	54.28	17	45.94	27	42.18	20	37.03

አባሪ ሐ-2

የቅድመ-ፈተና Reliability Cofficient (አስተማማኝነት ውጤት)

EVEN	ODD	E^2	0^2	EO
40	45	1600	2025	1800
64	59	4096	3481	3776
70	60	4900	3600	4200
30	40	900	1600	1200
80	75	6400	5625	6000
50	45	2500	2025	2250
60	65	3600	4225	3900
70	65	4900	4225	4550
55	45	3025	2025	2475
60	70	3600	4900	4200
579	569	35521	33731	34351

E = 579

0 = 569

ΣE^2 = 35521

$\Sigma 0^2$ = 33731

EO = 34351

$(\Sigma E)^2$ = 335241

$(\Sigma o)^2$ = 323761

$$r_{oe} = \frac{N\Sigma Eo - \Sigma e\Sigma o}{\sqrt{N\Sigma E^2 - (\Sigma E)^2 - (N\Sigma o^2 - (\Sigma o)^2}}$$

$$r_{oe} = \frac{10(34351 - (579 X 569)}{\sqrt{10(35521 - 335241 - 10(33731 - 323761}}$$

$$r_{oe} = \frac{343510 - 329451}{\sqrt{355210 - 335241 - (337310 - 323761)}}$$

$$r_{oe} = \frac{14059}{\sqrt{(19969)(13549)}}$$

$$r_{oe} = \frac{14059}{\sqrt{270559981}}$$

$$r_{oe} = \frac{14059}{\sqrt{16448.70758}}$$

$$r_{oe} = 0.8547$$

አባሪ «ሐ-3»

የድህረ-ፈተና አስተማማኝነት ውጤት

EVEN	ODD	E^2	0^2	EV
40	44	1600	1936	1760
53	55	2809	3025	2915
63	64	3969	4096	4032
65	63	4225	3969	4095
75	70	5625	4900	5250
60	55	3600	3025	3300
74	78	5476	6084	5772
43	45	1849	2075	1935
58	60	3364	3600	3480
65	60	4225	3600	3900

ΣE (Sum of Even) = 596

Σo (sum of odd) = 594

$(\Sigma E)^2$ (sum of even the hole square) = 355216

$(\Sigma O)^2$ (sum of odd the hole square = 352836

ΣO^2 (sum of even square = 36742

$(\Sigma E)^2$ (sum of odd square = 36260

ΣEo (the sum of even X odd) = 36439

r_{oe} ⇒ reliability coefficient

$$r_{oe} = \frac{N\Sigma Eo - \Sigma E\Sigma o}{\sqrt{N\Sigma E - (\Sigma E)^2 - N\Sigma o^2(\Sigma O)^2}}$$

$$r_{oe} = \frac{10(36439 - (596X594)}{\sqrt{10(36742) - 355216 - 10(36260 - 352836}}$$

$$r_{oe} = \frac{364390 - 354024}{\sqrt{367420 - 354024 - (362600 - 3528361)}}$$

$$r_{oe} = \frac{10366}{\sqrt{(12204)(9764)}}$$

$$r_{oe} = \frac{10366}{\sqrt{119159856}}$$

$$r_{oe} = \frac{10366}{10916}$$

r_{oe} = 09496

r_{oe} = 0.95

"00"

ﾚﾍﾄﾗｸﾃﾞ：ｵｰﾙ7：ﾒｼﾞｬﾒﾄｸﾘｸﾞ：ｵﾚﾋﾞ

"00-1"

ﾚｸﾁｽｵｰﾑﾄﾗ：ﾒｼﾞｬﾒﾄｸﾘｸﾞ：ﾊﾞﾘｱﾌﾞﾙｵﾌﾞｼﾞｪｸﾄ

28 Apr 98 SPSS for MS WINDOWS Release 6.1 Page 4

t-tests for Independent Samples of GROUP

Variable	Number of Cases	Mean	SD	SE of Mean
Pretest				
Control Pre	25	56.6400	13.564	2.713
Exp Pre	25	56.6000	9.916	1.983

Mean Difference = .0400

Levene's Test for Equality of Variances: F= 2.061 P= .158

t-test for Equality of Means

Variances	t-value	df	2-Tail Sig	SE of Diff	95% CI for Diff
Equal	.01	48	.991	3.360	(-6.717, 6.797)
Unequal	.01	43.95	.991	3.360	(-6.733, 6.813)

"CD-2"

30 Apr 98 SPSS for MS WINDOWS Release 6.1 Page 1

t-tests for Paired Samples

Variable	Number of pairs	2-tail Corr	Sig	Mean	SD	SE of Mean
CONPOST				53.7826	11.261	2.348
	23	.067	.762			
EXPOSTTE				66.7826	11.029	2.300

Paired Differences Mean	SD	SE of Mean	t-value	df	2-tail Sig
-13.0000	15.226	3.175	-4.09	23	.000
95% CI (-19.584, -6.416)					

አስቤ፡- "ሰ

በሳምሪሳሩ፡ መሹት፡ ዲተጠኝ፡ ቡድኑ፡ ሲጥጠቅ፡ ቡድኑ፡ የክፍል፡ ውስጥ፡

ልሳሳኦድ፡ የሚያሰይ፡ ፎቶግራፍ

"ሰ-1"

ተጠኝ፡ ቡድኑ፡ በክፍል፡ ውስጥ፡ አንብቦ፡ የመጨዳት፡ ክሊሉን፡ ለማዳበር፡

የሚያረገው፡ ልሳሳኦድ፡ የሚያሰይ፡ ፎቶግራፍ







"ሸ-ረ"

ጭብጭቅ፡ ቡድን፡ አንብቦ፡ የመረዳት፡ ክሊኒክ፡ ለማዳበር፡ ሲባል፡

የክፍል፡ ውስጥ፡ የመማር፡ ማስተማር፡ ሂደት፡ የሚያሳይ፡ ሞዴል፡







ክላሪ "ሀ"
የማንበብ ፈተና

ስያሜው እንደሚያመለክተው ማህበራት ማለት እንደሆነ ተባበረ ህብር ሆነ_____ ነው። በኢትዮጵያም የአያሌ ዘመናት ታሪክና ምክንያት ያለው ነው። የክርስትና እና _____ ሃይማኖት ወደ ሀገሪቱ ከገቡ ወዲህ የማህበር ትምህርት እየተሰጠበትና ግዴታም እየተገባበት መጥቷል። _____ በክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ ጠበቅ ያለ እምነት እና አቋም ይዞ_____

ለምሣሌ ያህል የጽዋ፣ የሰንበቴ፣ የጽጌ የኳናትና ማህበራት ዝክረ ቅዱሳን የልደታ _____ እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉት ስያሜዎችና ተቋሞች ከሃይማኖት ጋር የተያያዙ _____ የክርስትና ሃይማኖት ከተሰበከ በኋላ የተመሠረቱ መሆናቸውን ከስያሜዎችና ከተግባራቸው ላይ ____

በእነዚህ ማህበራት አስተባባሪነት ሕዝቡ እየተሰበሰበ ከእለት ምግቡ እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ ድረስ ያለውን ጉዳዩን ሲወያዩበትና ሲረዳዳበት እንደሆረ ከዚህ ዓለም_____ በወዲያኛው ዓለም የሚጠበቀውን ምህረትም ሆነ ቅጣት ለመለየት የሚችልበትን መንገድ_____እንደሚፈለግበት እንገነዘባለን።

ማህበር ከሃይማኖታዊ ገጽታው ሌላም ማህበራዊ ወይም ሕዝባዊ ተቋም አለው።_____ ነዋሪ የጸታና የሃይማኖት ልዩነት ሳያደርግ የሚረዳዳበት ታላቁ ገጽታው አያሌ_____ ያስቆጠረ ነው።

ለምሳሌ በወበራ ወይም በደቦ፣ በሀዘን፣ ሕዝቡ እርስ በርስ ሲረዳዳና _____ እንደኖረ ከታሪኩ ላይ መረዳት ይቻላል። ማህበር ከጥንቃዊነት ወደ ዘመናዊነት የተሸጋገረበት ምክንያትና _____ እንደዚሁ አያሌ ዓመታት ያስቆጠረ ገጽታ አለው። ነምዕራባውያን ሥልጣኔ ወደ ሀገሪቱ _____ ከጀመረ ወዲህ በማህበር አማካይነት ወይም ዋልታነት ልዩ ልዩ ሥፍራዎችን _____ እየተስፋፋ መጥቷል። ገንዘብ አዋጥቶ ሃሳብንና ጉልበትን አስተባብሮ የንግድ ሥራ ማካሄድና _____ ___ መስጠት የተለመደ ሆኗል።

ማህበር ከመንፈሳዊ እና ከእለት ኑሮ ዋልታም ወጥቶ ወደ ፖለቲካ ምዕራፍም ተሸጋግሯል።_____ኢጣሊያ በ1927 ዓ.ም. አገራችንን ለመውረር ግፊትዋነ በሶሜንና በምሥራቅ በጀመረችበት _____ የኢትዮጵያ ሴቶች በጐ አድራጐት እና የሀገር ፍቅር ማህበራት ተመሥርተው ሕዝቡ ለነፃነቱ_____ ክብርና አንድነት እንዲነሳሳ ገንዘብም እያዋጣ ትጥቅና ስንቅ እንዲያዘጋጅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ_____ ከዚህ ቀጥሎ ማህበር ወደ ብሔራዊ ስሜትና ኃላፊነትም ተሸጋግሮ በ1928 ዓ.ም. የጥቁር _____ በ1931 ዓ.ም. የጥንታዊ ጀግኖች ማህበራት ተቋቁመው የተዋጊነቱንና የፖለቲካውን ተጋድሎ ቀጥለው_____ድራጊነቱ በቅተዋል።

ማህበር ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ ባህርይ ይዞ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ_____ የታየባቸው ጊዜያትና ምክንያቶች ሰፋ ያለ ምዕራፍ ያለው ለመሆኑ ዝርዝር ጉዳዩን_____ እንደ ቀይ መስቀል እንደ ሠራተኛ፣ የድኩማን፣ ረድዔት የዓለም አቀፍ የሴቶች ክበብ የሞስኮ ኦርቶዶክሳዊ_____ እና የመሳሰሉትን ጠቅሰን ብናልፍ በቂ_____።

ከዚህ በታች የተሰጠውን መመሪያ በጥንቃቄ ካነበባችሁ በኋላ ከራሳችሁ ስሜትና አቅም በላይ ነጻነትን ከማይደግፍ በመሆን ለየተወያያችሁ ጠቃሚ የሆነውን ድጋፍ ወይም ሀረግ በተሰጠህ ባዶ ቦታ ላይ ፃፍ።

ውላንን አፍፊተ መጠቀም በውላ ውስጥ የሚገኙ ..... በሽታ ለማጥፋት ቀጥታ ዘዴ ነው።የሚጠራው ውላ ..... የመሠሉት ነፃነት ፍቃድ ወይም በሽፊፊ የተበከለ ወይም በጣም የተበከለ ..... ይችላል ።ይሁን እንጂ ሁሉንም ዓይነት ውላ በማፍላት ..... ውጤት ተመሳሳይ ነው።

ለንፃህራ የሚፈለገው ውላ በማንኖር ፆሪያ፣ሙከራት ፍስት ወይ በገንበ ..... የቸ ለፊ።ውላን ማፍላት ማለት ለጥ ሂት ጊዜ .....ለይ ጥደ ከዚያም አሻዘቅዘ መጠቀም ማለት አይደለም።.....ጠንቅ የሆነ ተህዋስያንን ለማጥፋት መጀመሪያ ውላው .....ደቂቃያ ች ይፈላል። ከዚያም እንዲቀዘቅዝ ይደረግና እንቢገና ከ.....ደቂቃያች አየተፍለቀ ቀለቀ እንዲፈላ ከተደረገ በኋላ አቀዝቅቀ መጠቀም.....

ሱሳው ሉተከርበት የሚገቧው ጉጓይ ውላው የተፈለበት .....ሉሉ አገልግሎት እንጓይውና ማድረግ ነው ።ውላው ..... በተፈለበት ለታ ውስጥ እንዲቀዘቅዝና በደንብ ተከድኖ ..... ለንጂኖይ ቢደረግ የውላው ንፅህና እንደተጠበቀ ይቆያል ።.....ማድረግ ካለ ተቻለ በ ፈለ ውላ ተቀቅሎ በታጠበ ..... ውስጥ ውላው ከተገለበጠ በኋላ በሚገባ ተከድኖ ..... አገልግሎት ለይ መሳል ይኖርቦታል።

ውላን ማፍላት በውላ ውስጥ የሚያሙ ጋዘችን .....ይ ተቃጠለን አየር ከውላ ውስጥ ስለሚያውጣቸው የተፈለ ..... ጣዕሙ ይለውጣል የውላውን ጣዕም ለማሻሻል ሲባል ከ..... ወደ ለታ የጣገለበጡ ተግባር ውላውን እንደገና ለንጂበክል ..... ስለሆነ ከዚህ ዓይነቱ ድርጊት መቆጠብ ያስፈልጋል ..... ውላን ከመጫጫት ጣዕም የሉለው ንፁህ ውላ መጠጣቱ .....

ተፈልጎ ከቀዘቀዘው የውላ ለታ ውስጥ ውላው በጥቀሳበት ..... ጊዜ በጣሰ ለየተጠለቀ መሆን የለበትም የዚህ .....አቀፃፅ በተከበለ ጣሰ ጽዘንያት ውላው ወጂያውን ..... ያ የተደከመበት ተግባር ሁሉ ከንቱ ሆነናል።

የፎኒክስ ፡ ምንጣፍ ፡ በፕላቃቂ ፡ ግንባታ ፡ ለኋላ ፡ አራተኛ ፡ ማንሳፈ
በመነሳት ፡ እምንገቡ ፡ ጋር ፡ ተሳመሚ ፡ የሆኑትን ፡ ቃላት ፡ በባዶ ፡ ቦታ
ሳይ ፡ ሞሉ ፡

ሥዕል በጣም እወዳለሁ። ሠዓሊዎችንም እደንቃለሁ። ለሥዕል_____ ያለ ስሜት እያለኝ ለምን ሠዓሊ አልሆንኩም _____የጠየቅሁት አንድ ወዳጄ በልጅነትህ ጥሩ የሥዕል_____ ስላላጋጠሙህ ይሆናል ብሎኝ ነበር እርግጥ የሥዕል_____ ራሳቸን ሥዕል የማይችሉ ነበሩ። አፋቸው ላይ_____ ነገር ሳሉ ማለት ይቀናቸው ነበር በተለይ _____ ክፍል ሆኜ በመስኮት ያዩትን ነገር ለመሳል_____ ሲያልፍ ካዩ ባቡር ሳሉ አህያ ሲልፍ _____ አህያ ሳሉ የሚሉ አስተማሪ እንደነበሩ ትዝ_____

ሥዕል ከማፍቀሬ የተነሳ ትንሽ ልሞክር ብል_____ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተለማመድኩትን ባለአራት እግር _____ነው።

ከዚህ ይልቅ የአንድን ሥዕል ውበት _____ መገንዘብ ባጠቃላይ አቅሜ በሚፈቅድልኝ መሠረት መተቸት_____ ይለኛል። ከዚህ በመነሳት ስለአንዳንድ የቡና ቤት ሥዕሎች _____የመሳሰሉትን ነገሮች ለመናገር እክራለሁ።

ሳስበው በአንዲት የአርሳስ ጭረት ብዙ መናገር _____ ርቀትን ጥላንና ብርሃንን፣ ከፍታና ዝቅታን፣ ማሳየት _____አድማሱን፣ ዝናቡን፣ ጭጋጉን ማሳየት ከሁሉም በላይ ደግሞ እንደ _____እንደ ደስታ፣ ጸጸት፣ ናፍቆት፣ ያሉትን ረቂቅ ነገሮች _____ ላይ መፍጠር ምንኛ ደስ ይላል።

በእድሜ ጐዳና ሲያዘግም ኖሮ ወደ ሞት አፋፍ_____ የሚል ፀጋ የተሞላበት ሽምግልና፣ እንደ እምቡጥ አበባ _____በተስፋና በምኞት አዝመራ ያሸተ ወጣት በረሃብ _____ አካል ስቃይ ከተጎዳው ዓይንና ከተጨማደደ ፊት_____ተባብሮ የሚያሳየው ብሶት፣ የፍቅር ምትሃት፣ የሐዘን_____በአጠቃላይ ተፈጥሮ በሸራ ላይ የምትሸሞነሞንበት ትልቅ_____ቢኖር ስዕል ነው።

ታዲያ ይህችው ተፈጠሮ፣ ተሰጥኦና ችሎታ ባላቸው_____የምትሰጠውንና በእውነታ የምታሸበርቀውን ያህል ሙያውን በወጉ_____ሰዎችም ትዋረዳለች ይህን ለማረጋገጥ የቡና ቤት ሥዕሎችን _____ይበቃል። የቡና ቤት ሥዕሎችን ስንል የሥዕል ጥበብ የሌላቸውን_____ በጣም ተራ የሆኑትን ማለቴ ነው። ለምሳሌ ምን_____ የምትል እግሯ ክርኗ ሥር ሊሆን ትንሽ _____ የመጠጥ ቤት ኮማሪት ወይም ታዲያስ ምን _____ከሚል ጽሁፍ ሥር አንዱ አዳምጡኝ እንደሚል _____ እጁን የዘረጋ የምግብ ቤት አስተናጋጅ ግድግዳ ላይ_____ አይታችሁ አታውቁም ቀንዱ ተጠምዝዞ ጭራው ጋር የደረሰ_____ጽጌረዳ ሊቀጥፍ የተዘጋጀ አንድ ሰው ጥርስ_____ ያለ አንበሳ፣ ማይክሮፎን የሚመስል ቡና ማፍያ _____ ዝርዝሩ ብዙ ነው።

በአንድ የባህል ምግብ ቤት ያየሁት ሌላ ሥዕል_____። በምን አወቅህ እንዳትሉኝ እንጂ የተሳሉት ባልና_____ሳይሆኑ አይቀሩም። ጐን ለጐን ተቀምጠዋል።_____ቀርቧል። በመሶበወርቅ አንድ ውሻ ተጋድሟል።_____ ጨፍኗል፣ እንቅልፍ የወሰደው ይመስላል ምግብ አየሸተተው_____ውሻ አይታችሁ ታውቃላችሁ? ከምጣኔ ስህተት የተነሳ ውው_____ ቦታ እመሶበወርቁ ሥር ነው። ጭራው እንደደህና ነገር_____አግር ላይ አርፏል። ሴትየዋ እጆቿን ዘርግታለች_____በሉ እስቲ እንደነገሩም ቢሆን ትላለች ለማለት_____ ነገር ግን እጅ አዘረጋግዋ መድረክ ላይ ሆና_____ ንግግር የምታደርግ_____ባልየው እጁን ይታጠባል፣ የሱ እንኳን ደህና_____የምታስታጥበው ልጅ ግን በቅጣት ላይ ያለች_____ ምክንያቱም ጐንበስ በማለት ፊንታ እንደመንበርከክ ብላለች_____ ከሁሉም የተለየ ነው ለመብላት የተዘጋጀ አይመስሉም። _____ ዝም ብለው መስቀልና ጭራቸውን ለምግብ ቤቱ ደምበኞች_____የምግብ ባለቤት ማነው ይህን ሥዕል የሳለልዎት _____ ጠየቅኳቸው።

« አንድ የተባረከ ልጅ ነው እንዲሁ እንዳንተ_____ መጥቶ አሉኝ» ፡ ፡

ማረጋገጫ

እኔ ከታች ስሜ የተገለጸው በኢትዮጵ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል ተማሪ የሆንሁት ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የእኔ ሥራ መሆኑንና በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸው የተዛማጅ ጽሑፎችንና ሌሎች መረጃዎች ምንጮች የጠቀስኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ::

ስም:- የኔሰው ደሴ

ፊርማ:- _____

ቦታ :- የቋንቋዎች ጥናት ተቋም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ቀን :- ግንቦት 14 ቀን 1990 ዓ.ም.